# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# የአሥር ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

# (ከ2013-2022 በጀት ዓመት)

ጥራዝ 1፡ ዋና ዶክመንት

ፕላንና ልማት ቢሮ

ጥቅምት /2015

**ባህር ዳር**

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 3

2. የክልሉ የልማት አቅሞች ........ 4

3. የክልሉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ........ 8

3.1. ከማክሮ ኢኮኖሚ አንፃር ........ 8

3.2. የክፍላተ ኢኮኖሚ ዘርፎች አፈፃፀም ........ 14

3.2.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች ........ 14

3.2.2. መሠረተ ልማት የማስፋፋት አፈፃፀም ........ 22

3.2.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም ግምገማ ........ 24

3.2.4. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈፃፀም ግምገማ ........ 33

3.2.5. የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ አፈጻጸም ግምገማ ........ 42

4. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች ........ 50

4.1. አገራዊ የረጅም ጊዜ ርዕይ ........ 50

4.2. አገራዊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች ........ 50

4.4. የሕዝባችን አዳዲስ ፍላጐቶች እና ጥያቄዎች ........ 51

4.5. የፌደራል የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ........ 51

4.6. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እና አጀንዳ አፍሪካ 2063 ........ 51

5. ክልላዊ ርዕይ ........ 52

6. የልማት መሪ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 52

6.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ ........ 52

6.2. የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ብቁ የልማት መሪ ኃይል እንዲሆን ማድረግ ........ 53

6.3. የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና ብቃት ማሳደግ ........ 54

6.5. የክልሉን የሀብት አቅም መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ ኢኮኖሚ መገንባት ........ 54

6.6. ፍትሐዊ ልማትን በሁሉም አካባቢዎች ማረጋገጥ ........ 55

6.7. የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት፣ የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ........ 55

7. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች ........ 56

7.1. ብዝሀ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር ........ 56

7.1.1 የዘመናዊ ግብርና ልማት ..... 56
7.1.2 የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ..... 56
7.1.3 የማዕድን ሀብት ልማት ..... 57
7.1.4 የቱሪዝም ልማት ..... 58
7.1.5 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ..... 58
7.2. ዘላቂ የከተማ ልማት ..... 59
7.3. መሠረተ ልማት ..... 59
7.4. የሰው ኃብት ልማት እና የሥነ-ህዝብ ትሩፋት ..... 60
7.5. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ ..... 61
7.6. ተቋማዊ አቅም መገንባት ..... 62
8. የ10 ዓመቱ የልማት መሪ ዕቅድ ልዩ ባህሪያት ..... 62
9. የዘላቂ ልማት ግቦችና የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ትስስር ..... 64
10. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ ..... 71
11. የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦች ..... 87
12. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ..... 93
12.1. ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ ..... 93
12.2. መሠረተ ልማት ዘርፍ ..... 121
12.3. ማህበራዊ ልማት ዘርፍ ..... 132
12.4 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ..... 146
12.5 የፍትህና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ..... 156
12.6. የልማት ፋይናንስ ..... 165
13. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ..... 166

# 1. መግቢያ

በክልሉ ያለውን ዕምቅ አቅም መሠረት በማድረግ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመቅረፍ ወደሚፈለገው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እና የዕድገት ከፍታ ለመድረስ የሚያስችል ከ2013-2022 በጀት ዓመት የሚዘልቅ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ረቂቅ ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ዕቅዱ በወቅቱ ሳይጸድቅ ቆይቷል። ረቂቅ ዕቅዱ ከተዘጋጀ በኋላ በነበሩት ሁለት ዓመታት የኮቪድ ወረርሽኝ እና በተለይም በ2014 በጀት ዓመት በክልላችን በሚገኙ 7 ዞኖች በነበረው ጦርነት ማለትም ሰሜን ጎንደር በከፊል፣ ደቡብ ጎንደር በከፊል፣ ዋግ ኽምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ ዞኖች ላይ ከፍተኛ የሰብዓዊ፣ ቁሳዊና ስነልቦናዊ ቀውስ አስከትሏል። ይህን ተከትሎ በተደረገው ጥናት መሠረት ወደ ብር 289 ቢሊየን የሚደርስ ውድመት ደርሷል። በጥናት ውጤቱም መሠረት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳ እንደሚችልና ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢኮኖሚው የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅሙም ዝቅ እንደሚል ይታሰባል።

በሌላ በኩል በተለይ ከጦርነቱ በኋላ በህዝቡና በአመራሩ ከፍተኛ ቁጭትና መነሳሳት መፈጠሩ፣ የፌደራል መንግስቱም ክልሉን በተለያየ መንገድ ድጋፍ የማድረግ እንቅስቃሴ የሚጠናከር መሆኑ እንዲሁም ዲያስፖራው ለክልሉ የሚያደርገውን ድጋፍ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያሳድግ መሆኑ ታሳቢ ከተደረገ የወደሙ ተቋማት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ከማድረግግና ወደኋላ የቀረውን የልማት እንቅስቃሴ ከማካካስ ባሻገር በመሪ ዕቅዱ ከተቀመጡ ግቦች በላይ ስኬት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው።

በአጠቃላይ በአለፉት 2 ዓመታት የነበሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመተንተንና የአጠቃላይ ዕቅዱ የግምገማ አካል በማድረግ እና ያላሳካናቸውን እና ወደኋላ ያስቀሩን ጉዳዮችን በመለየት በቀጣይ 8 ዓመታት ለማካካስና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገብን ታሳቢ ያደረገ የዕቅድ ክለሳ ተደርጓል። ዕቅዱም በ2015 በጀት ዓመት መጀመሪያ /ጳጉሜን 5 ቀን/ ለክልሉ ካቢኔ ቀርቦ የጸደቀ ሲሆን ካቢኔው በወቅቱ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረትም ጥቅምት መጨረሻ የክልል መሥሪያ ቤቶች የዕቅድ ዝግጅትና በጀት ዳይሬክተሮች በተገኙበት በእንጅባራ ከተማ በተዘጋጀ መድረክ የጋራ ተደርጎና የተገኘው አስተያየት በግብዓትነት ተወስዶ ዶክመንቱ የመጨረሻ ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

በአጠቃላይ ይህ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ሠነድ በውስጡ የክልሉን የልማት ዕምቅ አቅሞች ትንተና፣ ከማክሮ ኢኮኖሚው እና ከክፍላተ ኢኮኖሚ አኳያ የክልሉን ያለፉት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም፣ የአገር አቀፉን እና የክልሉን ርዕይ፣ የዕቅዱን መነሻዎች፣ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የትኩረት መስኮች እና የዕቅዱን ልዩ ባህሪያት እንዲያካትት ተደርጎ ጠቅለል ባለ መልኩ ተዘጋጅቷል።

## 2. የክልሉ የልማት አቅሞች

ክልሉ ለሁሉም ዓይነት የኢኮኖሚ ዘርፎች ልማት ምቹ የሆኑና ከሞላ ጎደል ሁሉም ዓይነት መሠረታዊ የተፈጥሮ ሀብት አቅሞች ያሉት ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ ያሉትን ዕምቅ የልማት አቅሞች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ በመለየትና በማልማት እና የክልሉን ሀብት በስፋት ተጠቅሞ ኢኮኖሚውን ማሳደግ ያስችላል፡፡ ከዚህ አኳያ የአማራ ክልል በብዙ ዕምቅ ሀብቶች ተነፃ ጻሪ ጠቀሜታ /Comparative Advantage/ ያለው በመሆኑ ያሉትን ፀጋዎች በአግባቡ በመለየትና ለልማት በማዋል ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እና የህዝቡን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በክልሉ የሚገኙ ዕምቅ አቅሞች በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**የመሬት ሀብት፡-** የክልሉ የመሬት አቀማመጥ ሲታይ 27.6 በመቶ ሜዳማ፣ 27.79 በመቶ ተራራማ፣ 11.4 በመቶ ሸለቋማ፣ 21.67 በመቶ ወጣ ገባ እና 1.54 በመቶ ረግረጋማ እንደሆነ የግብርና ቢሮ መረጃ /የግብርና ቢሮ የ2011 ዓመታዊ መጽሄት/ ያመለክታል፡፡ ከፍታው በምሥራቅ ከ500 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ ጀምሮ 4,620 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ እስከሚገኘው የራስ ዳሽን ተራራ የሚደርስ ቦታን ይሸፍናል፡፡ ስለሆነም በተለያየ የመሬት አቀማመጥ ያሉ ሀብቶችን እንደ የአግባቡ በመጠቀም ማልማት እንደሚቻል ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ተራራማ አካባቢዎችን ደን በማልማት የሥራ ዕድል ከመፍጠር፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከማግኘትና የክልሉን የአየር ንብረት ከመጠበቅ ባለፈ ከተራራው በታች የሚገኙ አካባቢዎችን ከአፈር መሸርሸር ለመጠበቅ እና የውኃ መገኛ ዕድሎችን ለማስፋት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ሜዳማ አካባቢዎችን ለእርሻ አገልግሎት ለማዋል ዕድል ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ሰንሰለታማ ተራሮች የብዝሀ ሀብታቸውን በመጠበቅ የቱሪስት መስህብ ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉበት ሰፊ ዕድል ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ክልሉ ለግብርና ልማት ተስማሚ የሆነ ሰፊ መሬት ባለቤት ነው፡፡ በመኸር በመልማት ላይ የሚገኝ ነገር ግን የማምረት አቅሙ ላይ ያልደረሰ 4.8 ሚሊየን ሄ/ር መሬት ያለ ሲሆን ለምግብ፣ ለኢንዱስትሪና ለውጭ ገበያ ማምረት የሚችል ነው፡፡ የሰብል ልማቱም ተወስዶ ሲታይ በአገር ደረጃ ከሚመረተው እስከ 33 በመቶ ድርሻ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ገብስና ስንዴ ያሉ ብርዕ ሰብሎችን፣ እንደ በቆሎና ማሽላ ያሉ የአገዳ ሰብሎችን፣ እንደ ባቄላ፣ አተር፣ ምስር እና ሽንብራ ያሉ ጥራጥሬዎችን እንዲሁም እንደ ሰሊጥ፣ ማሾ ያሉትን የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ ሰብሎችን ጨምሮ እንደ ኑግ ያሉ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የቅባት ሰብሎችን በስፋት የማምረት አቅም አለው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታም ሆነ ለኤክስፖርት ሊውሉ የሚችሉ የአትክልትና ፍራፍሬ እና የአበባ ምርት የማምረት ሰፊ አቅም አለው፡፡ እነዚህን የግብርና ምርቶች በዝናብ ብቻ ሳይሆን በመስኖም ታግዞ የማምረት ሰፊ አቅም አላቸው፡፡ ይኸውም የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውኃን ጨምሮ 1.2 ሚሊየን ሄክታር መሬት በመስኖ መልማት የሚችል አቅም ያለው ክልል ቢሆንም እስከ አሁን የለማው ዝቅተኛ ነው፡፡

ስለሆነም እያንዳንዱ አካባቢ ሊሰጠው የሚችለውን የላቀ ጠቀሜታ ይበልጥ በጥናት በመለየት በተገቢው ጥቅም ላይ የማዋል ሁኔታን ይበልጥ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ግን እስከ አሁን የተሠራው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራ በቂ ባለመሆኑ ይልቁንም በደን መመንጠርና ያልተገባ የመሬት አያያዝ ምክንያት ሰፊ የአፈር መሸርሸር በክልሉ እየታየ ነው፡፡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሄክታር እስከ 100 ቶን አፈር በዓመት እየታጣ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በሚቀንስ ምርታማነት እንደ አገርም ሆነ እንደ ክልል ከሚገኘው ጥቅል ምርት ቀላል የማይባል ድርሻ በየዓመቱ እየታጣ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በአርሶ አደር ደረጃም የመሬት ምርታማነት መቀነስ ለገቢ ዝቅ ማለትና ለምግብ ዋስትና መታጣት ችግር የሚዳርግ ሆኗል፡፡ ከዚህም አልፎ ለብዝሀ ህይዎት መመናመን፣ በውኃ ሚዛን መዛባት ምክንያት የከርሰ ምድር ውኃ መቀነስና በዚህም ለመጠጥና ለመስኖ የሚሆን ውኃ እጥረት መከሰት፣ በደለል ምክንያት የግድቦች የአገልግሎት ጊዜ ማጠር፣ እንደ ጣና ያሉ ሀይቆች እንደ እንቦጭ ባሉ አደገኛ አረሞች መወረር እና የመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚያስከትል ስለሆነ ተራሮችን አረንጓዴ በማልበስ እና

በመሰሰሉት የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ዘዴዎች መሬትን ዘላቂ ጥቅም ሊሰጥ በሚያስችል መልኩ መጠበቅና ማልማት የግድ ይላል፡፡

**የውኃ ሀብት፡-** እንደሚታወቀው ውኃ ለመጠጥ፣ ለመስኖ ልማት፣ ለእንስሳት ሀብት ልማት፣ ለዓሳ እርባታ፣ ለብዝሀ ህይዎት ጥበቃ፣ ለመዝናኛ፣ ለቱሪስት መስህብነትና ለመሳሰሉት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያገለግላል፡፡ ስለሆነም ወደፊት የሚታሰበውን ዘላቂ ልማት ከማረጋገጥ አንፃር ያለንን የውኃ ሀብት ዕምቅ አቅም መለየትና በዘላቂነት መጠቀም የሚቻልበትን ሥልት መቀየስ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የክልሉ ዕምቅ የውኃ አቅምን በተመለከተ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከአገሪቱ የውኃ ሀብት የአማራ ክልል ከፍተኛውን /60 በመቶ/ ድርሻ ይይዛል፡፡ ክልሉ በአባይ፣ ተከዜ፣ ተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ነው፡፡ በዓለም በርዝመቱ የሚታወቀውን አባይን ጨምሮ ተከዜ፣ በለስ፣ አንገረብ፣ ሚሌ፣ ከሰም እና ጀማ የመሳሰሉ ትላልቅ ወንዞች በክልሉ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ወደ 1,677 የሚደርሱ ዓመቱን በሙሉ የሚፈሱ እና 297 በክረምት ብቻ የሚፈሱ ወንዞች በክልሉ የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም በዓመት ወደ 35 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውኃ እንደሚገኝ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪ እርጥበት አዘል ቦታዎችን ጨምሮ ወደ 335,282 ሄክታር ስፋት ያላቸው በአገሪቱ ትልቅ የሆነውን ጣና ኃይቅን ጨምሮ እንደ አርዲቦ የመሳሰሉ 12 ሀይቆች ያሉ እንደሆነና የእነዚህ ሀይቆች ብዝሀ ህይዎትን በመጠበቅ ለዓሳ ሀብት ልማት፣ ለመዝናኛ፣ ለቱሪስት መስህብነት ማዋል ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በወንዞችና ሀይቆች ሰፊ በመስኖ የማልማት አቅም እንዳለ ግርድፍ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በክልሉ ውስጥ ባሉ ትላልቅ ወንዞች መጋቢ ወንዞችና ሀይቆች ከመስኖ ልማት በተጨማሪ የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ የዓሳ ሀብት ልማት ለማስፋፋት እና ለትራንስፖርት አገለግሎት የሚውል ከፍተኛ የውኃ ሀብት ክምችት እንዳለ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን በጥቅም ላይ የዋለው የውኃ ሀብት በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የዓሳ ሀብት ልማትን አስመልክቶ በክልሉ በሚገኙ ወንዞችና ሀይቆች በየዓመቱ ከ30 እስከ 50 ሺህ ቶን ዓሳ ማምረት እንደሚቻል ያሉት ጥናቶች ቢያመላክቱም እስከ አሁን እየተመረተ ያለው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ስለሆነም እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ይህን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ረገድ ሰፊ የሆነ ውስንነት ያለ በመሆኑ በቀጣይ ሀብቱን እንደ እንቦጭ ካሉ ወራሪ አረሞች ከመከላከል ጀምሮ ለዘላቂ ልማት የሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**የአየር ንብረት፡-** በክልል ደረጃ መረጃው እንደሚያሳየው የክልሉ ምዕራባዊ፣ ሰሜናዊ፣ ደቡባዊ እና ምሥራቃዊ እንዲሁም ደቡባዊ ምሥራቅ አካባቢዎች የመኸር ዝናብ ብቻ ተጠቃሚ ሲሆኑ ቀሪው አብዛኛው የምሥራቃዊ ክፍል የመኸርና በልግ ዝናብ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ዝቅተኛው የሙቀት መጠን 12.4 ዲግሪ ሴሊሺየስ ሲሆን ከፍተኛው ደግሞ 27.8 ዲግሪ ሴሊሺየስ ነው፡፡ ክልሉ በአራት ዓይነት የአየር ንብረት ቀጣናዎች የተከፋፈለ ሲሆን እነሱም ውርጭ (3 በመቶ)፣ ደጋ (31 በመቶ)፣ ወይና ደጋ (60 በመቶ) ቆላ (6 በመቶ) ናቸው፡፡ በመሆኑም ክልሉ ከበርሃ የአየር ንብረት በስተቀር ሁሉንም የአየር ንብረቶች የያዘ መሆኑ በግብርና ምርት እና በእንስሳት ሀብት ልማት ዕድገት ብልጫ ማምጣት የሚችል እንደሆነ ያመላክታል፡፡

**የእንስሳት ሀብት፡-** የክልሉ የእንስሳት ሀብትን ስንመለከት በአገር አቀፍ ደረጃ ከአጠቃላይ አገራዊ የእንስሳት ሀብት 28.6 በመቶውን የሚሸፍን ክልል ነው፡፡ በ2010 ዓ.ም ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተገኘ መረጃ መሠረት 16.14 ሚሊየን የዳልጋ ከብቶች አገራዊ ድርሻ 26.7 በመቶ፣ 11.1 ሚሊየን በጎች 35.4 በመቶ ድርሻ፣ 7.7 ሚሊየን ፍየሎች 23.7 በመቶ ድርሻ፣ 3.99 ሚሊየን የጋማ ከብቶች 35.3 በመቶ ድርሻ፣ 0.15 ሚሊየን ግመሎች 10.7 በመቶ ድርሻ፣ 19.8 ሚሊየን ዶሮዎች 33 በመቶ ድርሻ፣ 1.15 ሚሊየን ህበረ ንብ 17.7 በመቶ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ በእንስሳት ሀብት የበለፀገ ብቻ ሳይሆን በወተት ምርታማነታቸው የታወቁ የፎገራ የዳልጋ ከብቶች፣ በፀጉር ምርታቸው የታወቁ የመንዝ በጎች፣ በሥጋ ምርታቸው የታወቁ የዋሸራ በጎች፣ የአበርገሌ ፍየል እና የቲሊሊ ዶሮ ዝርያዎች የሚገኙበት ክልል ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት በቁጥር ደረጃ ከአፍሪካ አህጉር በቀዳሚነት የምትጠቀስ አገር ስትሆን ክልሉም ከዚህ ሀብት ሲሶ የሚሆነውን ድርሻ የሚያበረክት መሆኑ ሲታይ ለኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ አቅምና የወደፊት አለኝታ ሊሆን የሚችል ከፍተኛ ሀብት እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል የተከዜ ተፋሰስን ጨምሮ በብዙ አካባቢዎች ከደን ልማት ጋር በማጣመር ለንብ እርባታ ምቹ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በሀገሪቱ ትልቁን ኃይቅ ጣናን ጨምሮ የተለያዩ ሀይቆችና ወንዞች ያሉ በመሆኑ ለዓሳ ማምረት ሥራ ምቹነት አላቸው፡፡ ለአብነት ያህል በጣና ኃይቅ ብቻ በዓመት 15 ሺህ ቶን ዓሳ ማምረት እንደሚቻል ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡

በአጠቃላይ ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ቁጥር፣ ለእርሻና ለእንስሳት እርባታ ተስማሚ የሆነ መሬትና የአየር ንብረት እንዲሁም የውኃ ሀብቶች ያሉት ሲሆን በተለይም ለሰብል እና ለእንስሳት ሀብት ልማት ሊውል የሚችል አቅም እንዳለው ከመረጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በዝናብም ሆነ የመስኖ ልማት በማስፋፋት የክልሉን ፍጆታ ከማሟላት በላይ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚውሉ የተለያዩ የብርዕ፣ የአገዳ እና የቅባት ሰብሎችን እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬዎችን ማምረት ይቻላል፡፡

**የማዕድን ሀብት፡-** የማዕድን ሀብትን በተመለከተ በክልሉ አሲዳማ አፈርን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውለውን ላይምስቶን ጨምሮ እንደ ጂፕሰም፣ ሲልካ ሳንድ፣ ፑሚስ፣ ካኦሊን፣ ክሌይ፣ ካልሣይትና የመሣሠሉት ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ማዕድናት በሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ጎንደርና ምሥራቅ ጎጃም አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል እንደ ኦፓል፣ አምበር እና ጃስፐር የሚባሉ የከበሩ ማዕድናት በሰሜን ሸዋ፣ በደቡብ ወሎ፣ በደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን ጎንደር እና ሰሜን ወሎ በሚገኙ በርካታ ወረዳዎች ይገኛሉ፡፡ ብረት ነክ ማዕድናትን በተመለከተ አስተማማኝ ክምችት መኖሩ ተጨማሪ ሥራ የሚያስፈልገው ቢሆንም በመስኩ እስከ አሁን የተደረጉ ጥናቶች በዋግኽምራ፣ በምሥራቅ ጐጃም እና በአዊ መስተዳድር ዞኖች እንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በተጨማሪም በዋግኽምራ ዞን አበርገሌ እና በአዊ ዞን ቅላጅ አካባቢ በተካሄደ የመስክ ጥናት የወርቅ አዘል አለት መኖሩ ታውቋል፡፡ በክልሉ ከሚገኙ የኢነርጂ ማዕድናት ውስጥ የድንጋይ ከሠል በጭልጋ 19.9 ሚሊየን ቶን፣ በውጫሌ 3.3 ሚሊየን ቶን እና በሙሽ ሸለቆ ከ0.3 ሚሊየን ቶን በላይ የክምችት መጠን እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም ኦይል ሼል /ነዳጅ አዘል አለት/ በመርሳ አካባቢ እንዳለ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የማዕድን ውኃ የሚገኝ ሲሆን በደቡብ ጎንደር እና በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞኖች ደግሞ ለመዝናኛነትና ለህክምና የሚያገለግሉ እንዲሁም ለኃይል ምንጭ አገልግሎት የሚውሉ የሙቅ ውኃ እና የጅኦተርማል ኃይል ምንጮች ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪ ለግንባታ የሚያገለግሉ እንደ እምነበረድ፣ ግራናይት፣ ሳንድስቶን፣ ነጭ ድንጋይ፣ ጥቁር ድንጋይ፣ አሸዋ፣ ቀይ ገረጋንቲ (Scoria) እና ለዘመናዊ ህንፃ ማስዋቢያ በጣም ተፈላጊ የሆነው የጥርብ ድንጋይ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ እስከ አሁን የማዕድን ሀብትን በተገቢው መንገድ ከመጠቀም አንፃር ክፍተት ያለ ቢሆንም ዘርፉ ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትና የህዝብ ተጠቃሚነት አኳያ ፋይዳው የጎላ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የተሰጠው ነው፡፡ በመሆኑም የማዕድን ሀብቱን በአግባቡ በጥናት በመለየትና የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት በጣም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

**የቱሪዝም ሀብት፡-** የአማራ ክልል ሰፊ የቆዳ ስፋት ያለው እና የተለያዩ የአየር ንብረቶች፣ የመልክዓ ምድር አቀማመጥና የተለያዩ ባህሎች ባለቤት ነው፡፡ በክልሉ ከማይንቀሳቀሱ ቅርሶች መካከል አገሪቱ በዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት ካስመዘገበቻቸው ቅርሶች መካከል የላል-ይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር ቤተመንግስታት፣ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ እንዲሁም በዙሪያው እና በውስጡ በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ቅርሶችን /አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት/ እና ብዝሀ-ህይወቶችን ያቀፈው የጣና ኃይቅና አካባቢው ይገኛል፡፡ ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል የጥምቀት በዓል በሁሉም የክልሉ አካባቢዎችና በተለይም በጎንደር በስፋት የሚከበር፣ የመስቀል በዓል እንዲሁም የልደት በዓል በተለይም በላል-ይበላ የሚከበሩ የክልሉ መስህቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪ ወደ 9 የሚደርሱ

ጥብቅ ቦታዎች እና የብዝሀ ህይዎት ሀብት እንዲሁም በአገሪቱ በከፍታው 1ኛ የሆነውና አስደናቂ የመሬት ገጽታ ያለውን የራስ ደጀን ተራራ ጨምሮ እንደነ አቡነ ዮሴፍ ያሉ ለህዋ ሳይንስ ምርምር ተመራጮ የሆኑ ተራሮችና በርካታ ሠንሰለታማ ተራሮች በክልሉ ይገኛሉ፡፡

በተጨማሪም ልዩ ልዩ ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንዲሁም መስጊዶች በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ክልሉ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ በመሆኑ ለዘመናት የተካበቱ የሥዕልና የቅርፃ ቅርጽ ሥራዎች እና እንደ ሙዚቃ እና ሥነጽሁፍ ያሉ የኪነ ጥበብ ሀብቶች ያሉት ሲሆን እነዚህ ቅርሶች ለአገር ገጽታ ግንባታ ጭምር ያላቸው ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊም ሆነ ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸውን መጠነ ሰፊ ልማቶች ለማረጋገጥ የተቸረው ክልል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ቱሪዝም አንዱ የክልሉ የወደፊት አለኝታና የኢኮኖሚ ምንጭ እንደሚሆን ተስፋ ተጥሎበታል፡፡ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ሀብቱን በተገቢው በማልማትና በማስተዋወቅ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ የሚጠበቅበትን አስተዋጽዖ ከማበርከት አንፃር ውስንነት ያለበት በመሆኑ በዚህ ረገድ ወደፊት የተጠናከረ ሥራ የሚከናወን ይሆናል፡፡

**አምራች ሰብዓዊ ሀብት፡-** የክልሉ የህዝብ ቁጥር ሲታይ እጅግ በጣም ግዙፍና ትልቅ የልማት አቅም ሊሆን የሚችል ኃይል ነው፡፡ ክልሉ ወጣት የሚበዛበት የዕድሜ ስብጥር ያለው ሲሆን ከአጠቃላይ በሥራ ኃይልነት ከተያዘው ህዝብ አንፃር 53 በመቶ የሚሆነውን ይይዛል፡፡ ይህ ኃይል ትኩስ ኃይልና የልማት አለኝታ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ክልሉ የቀጣይ የሥነ-ህዝብ ትሩፋት ተጋሪ በመሆኑ እንደ አንድ የዕድገት አቅም ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሰብዓዊ ሀብት ልማት በአንድ በኩል የልማት ጥረት ውጤት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለልማት ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡

በትምህርትና በጤና ዙሪያ እስከ አሁን የተገነቡ አቅሞች ለተሻለ የሰብዓዊ ካፒታል ትልቅ አቅሞች ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የህዝብ ቁጥር ብቻውን ለዕድገት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ይልቁንም የህዝቡን ዕውቀት እና ክህሎቱን በማሳደግ እንዲሁም አመለካከቱን በማስተካከል የማምረት አቅሙን በማሳደግ ለልማት መረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ በኩል በአምራች የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ከአጠቃላዩ ህዝብ ጋር ሲነፃ ፀር ሰፊ ስለሆነ ይህን ዕድል ወይም ትሩፋት በአግባቡ መጠቀምና ልማትን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ በአጠቃላይ በትምህርትና በጤና ሴክተር የተጀመሩትን ሥራዎች አጠናክሮ በማስቀጠል ተወዳዳሪና የማምረት አቅሙ ያደገ ሰብዓዊ ሀብት የመገንባት ሥራውን በቀጣይ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

**ቁሳዊ የካፒታል አቅሞች፡-** አብዛኛቹ የተገነቡ የቁሳዊ ካፒታል አቅሞች በመሠረተ ልማትና የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማትን ለማካሄድ የተገነቡ ህንፃዎች እንዲሁም የመስኖ መሠረተ ልማቶች፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችና የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የኢነርጂ መሠረተ ልማት የመሳሰሉት ለዕድገት መነሻ አቅሞች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

# 3. የክልሉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም

## 3.1. ከማክሮ ኢኮኖሚ አንፃር

### የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ

ክልሉ በ2012 በጀት ዓመት የ3.6 በመቶ የክልል ውስጥ ጥቅል ምርት ዕድገት አስመዝግቧል።በተጠቀሰው ዓመት በክልሉ የተመዘገበው ዕድገት ከዘርፎች አንፃር ሲታይ የግብርናው ዘርፍ የ2.5 በመቶ፣ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የ2.0 በመቶ እና በተለይ ደግሞ የአምራች እንዱስትሪ ንዑስ ዘርፉ የ14.0 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ የ6.6 በመቶ ዕድገት አስመዝግበዋል። ከዚህም እንደ ክልል የግብርናው ዘርፍ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ድርሻ ትልቅ ቢሆንም የዕድገት ምጣኔው ግን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ያሳያል። የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን በሚመለከት በ2012 በጀት ዓመት የግብርናው ዘርፍ 53.7 በመቶ ኢንዱስትሪው የ15.7 በመቶ እና የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ድርሻ 6.58 በመቶ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፉ የ31.7 በመቶ ድርሻ ነበራቸው። ይህም የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ከክልሉ ጥቅል ምርት ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ በአንጻሩ ግን የኢንዱስትሪውና በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው ድርሻ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ የክልሉ ኢኮኖሚ አሁንም በግብርናው ላይ ጥገኛ እንደሆነና የሚታሰበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እንዳልመጣ ያመለክታል።

ይህ አፈፃፀም የሚያሳየን ክልሉ በኢንዱስትሪ በኩል በተለይ የአምራች ኢንዱስትሪው ድርሻ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ነው። ይኸውም ኢኮኖሚው አመርቂ የሚባል የምርታማነት ዕድገት ባለማምጣቱና አምራች ዘርፎች የማምረት አቅማቸው ላይ አለመድረሳቸው እንዲሁም በዘርፎች መካከል ትስስር አለመኖርና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግሮች እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህም በክልሉ የአሥር ዓመቱ የልማት መሪ ዕቅድ ዘመን የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪውን በማስፋፋት ዕድገቱን በተቻለ መጠን በማፋጠን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው መዋቅራዊ ለውጥ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ያመለክታል።

### ኢንቨስትመንት

በክልሉ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ መሠረት የክልሉ አጠቃላይ ኢንቨስትመንት በ2008 በጀት ዓመት ብር 70.7 ቢሊዮን በጊዜው የገበያ ዋጋ የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ ብር 144.17 ቢሊዮን ደርሷል። ይህም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን 4 ዓመታት በአማካይ የ7 በመቶ ዕድገት ነበረው። በየዓመቱ የክልሉ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የያዘው ድርሻ ሲታይ በ2011 በጀት ዓመት የ30.3 በመቶ ድርሻ ያስመዘገበ ሲሆን በአገር ደረጃ ከተመዘገበው የ34.1 በመቶ ድርሻ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ አፈፃፀም አሳይቷል። በ2012 በጀት ዓመት ደግሞ ወደ 28.3 በመቶ ወርዷል። በመሆኑም የክልሉ ኢንቨስትመንት ድርሻ ከሚፈለገው አንፃር ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ኢንቨስትመንት (Gross capital formation) ለኢኮኖሚ ዕድገት እንደ መነሻ የሚወሰድና ለአጠቃላይ ክልላዊ ልማት አስቻይ ሁኔታ ተደርጎ የሚታይ ነው። ስለሆነም የሚፈለገውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የኢንቨስትመንት መጠኑ በእጅጉ ማደግ ይኖርበታል። በቂ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ካስፈለገ ደግሞ የቁጠባ መጠን ማደግ ይገባዋል።

### የልማት ፋይናንስ አፈፃፀም


**የመንግስት ፋይናንስን በሚመለከት** የክልሉ ጠቅላላ ወጪ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ የዕቅድ መነሻ ዓመት (2007 በጀት ዓመት) ብር 22.8 ቢሊዮን ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት በክልሉ ለልማት ጥቅም ላይ የዋለው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ወደ ብር 46.6 ቢሊዮን አድጓል። የዕድገት ምጣኔው ተወስዶ ሲታይ ከፍተኛ የወጪ ዕድገት የተመዘገበው በ2009 በጀት ዓመት ሲሆን ይህም የመደበኛ በጀት በ6.5 ቢሊዮን ብር በማደጉ የተከሰተ እንደሆነ ከመረጃው ማየት ይቻላል። በተቃራኒው የ2010 በጀት ዓመት የወጪ አፈፃፀምን ስንመለከት

የ3.3 ቢሊዮን ብር ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም የዕድገት ምጣኔው ግን ከ2009 በጀት ዓመት አንፃር በመቀነስ 13.8 በመቶ ሆኗል፡፡ ለወጪ አፈፃፀም የዕድገት ምጣኔ መቀነስ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የመደበኛ በጀት ወጪ የ3.3 ቢሊዮን ጭማሪ ብቻ ሲያሳይ የካፒታል በጀቱ በ210.6 ሚሊየን ብር ወጪው ቀንሶ ይታያል፡፡

የአጠቃላይ የበጀቱን እንቅስቃሴ የ2ኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታትን ብቻ ተወስዶ ሲታይ የመደበኛ በጀት በ2008 በጀት ዓመት ብር 17.72 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ ብር 36.67 ቢሊዮን አድጓል፡፡ በተመሳሳይ የካፒታል በጀት አፈፃፀም በ2008 በጀት ዓመት ብር 8.24 ቢሊዮን የነበረው በ2012 በጀት ዓመት ወደ ብር 9.93 ቢሊዮን አድጓል፡፡ የመደበኛና የካፒታል በጀት ድርሻ ከአጠቃላይ በጀቱ አንፃር ተወስዶ ሲታይ በ2012 በጀት ዓመት የመደበኛ በጀት 78.7 በመቶ ሲሸፍን የካፒታል በጀት ወጪ 21.3 በመቶ ሆኗል፡፡

ይህም የሚያሳየው አብዛኛው በጀት ለመደበኛ ወጪ የሚውል በመሆኑ ይህ ሁኔታ በዚህ መልኩ ከቀጠለ በአጠቃላይ በክልሉ የኢንቨስትመንት ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም በክልሉ በካፒታል በጀት የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ከአጠቃላይ የክልሉ ልማት ፍላጎት አንፃር ሲታይ ክልሉ ወደኋላ የቀረበት ሁኔታ እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በጥናት ላይ የተመሠረተ የክልሉን ልማት ሊያግዝ የሚያስችል የበጀት ሥምሪት እንዲኖር መሠራት ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር የወጪ ድርሻ ሁኔታ እንደሚከተለው በግራፍ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡


**ግራፍ 1፡ የመደበኛና የካፒታል በጀት አፈፃፀም ድርሻ በመቶኛ**




| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| መደበኛ በጀት (በመቶኛ) | 68.25 | 73.35 | 76.24 | 75.52 | 78.7 |
| ካፒታል በጀት (በመቶኛ) | 31.75 | 26.65 | 23.76 | 24.48 | 21.3 |

የድህነት ተኮር ሴክተሮችን የበጀት አጠቃቀም በተመለከተ በ2008 በጀት ዓመት ከአጠቃላይ በጀት ውስጥ 16.3 ቢሊዮን ወጪ የተደረገ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 28.3 ቢሊዮን አድጓል፡፡ ይሁን እንጂ የወጪ በጀቱ ድርሻ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን 3 ዓመታት እያደገ የመጣ ሲሆን በ2012 ግን ቀንሶ ይታያል፡፡ ይህም ማለት በ2010 በጀት ዓመት 63.1 በመቶ የነበረው ድርሻ በ2012 ወደ 60.8 በመቶ ቀንሷል፡፡

**ግራፍ 2፡ የድህነት ተኮር ሴክተሮች ከአጠቃላይ በጀት የወጪ በጀት ድርሻ በመቶኛ**





| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| ድርሻ ከአጠቃላይ የወጪ በጀት በመቶኛ | 62.76 | 62.86 | 63.1 | 61.84 | 60.8 |
| የዕድገት ምጣኔ በመቶኛ | 10.32 | 27.13 | 9.93 | 11.75 | 11.47 |

ከላይ በግራፉ እንደሚታየው ድህነትን በዘላቂነት ከመፍታት አንፃር ለድህነት ተኮር ሴክተሮች በበጀት ምደባ እና አፈፃፀም በየዓመቱ መሻሻሎች እየታዩ የመጡ ቢሆንም በክልሉ ያለውን ሥር የሰደደ ድህነት ለማጥፋት የሚደረገው ርብርብ የሚቀረው በመሆኑ በቀጣይ በጀት ዓመታት የድህነት ተኮር ሴክተሮች የበጀት ምደባው ዋነኛ ማዕከል ሆኖ ሊታይ እንደሚገባው ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩልም ለድህነት ቅነሳው ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ ሌሎች ዘርፎችንም በጥናት በመለየት የበጀት ሥርዓቱን መቃኘት ተገቢ ይሆናል፡፡

ሌላው ከልማት ፋይናንስ አኳያ የሚታየው የክልሉ የገቢ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የክልሉን ገቢ ለማሳደግ በተደረገው ጥረት ጠቅላላ የክልል ውስጥ ገቢ በ2008 በጀት ዓመት ከነበረው ብር 7.32 ቢሊዮን በ2012 በጀት ዓመት ወደ ብር 11.063 ቢሊዮን ለማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህም በአማካይ 16.4 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ሲኖረው በ2008 በጀት ዓመት የገቢ ዕድገቱ 22.8 በመቶ የነበረው በ2012 በጀት ዓመት ወደ 14 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በሌላ በኩል ጠቅላላ ገቢው ከአጠቃላይ የክልል ውስጥ ምርት ጋር ያለው ጥምርታ በ2008 በጀት ዓመት 3.14 በመቶ የነበረው በ2012 ወደ 2.18 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን ምንም እንኳን በየዓመቱ የገቢ ጭማሪ ቢኖርም የዕድገት መጠኑ አሳሳቢ ነው፡፡

**ግራፍ 3፡ የክልሉ ገቢ ክልላዊ ወጪን የመሸፈን ድርሻ በመቶኛ**




ከላይ በግራፉ እንደተመላከተው ክልሉ የልማት ወጪውን በገቢው የመሸፈን አቅሙን በተመለከተ የመጨመርና የመቀነስ አዝማሚያ ሲያሳይ ይኸውም በ2008 በጀት ዓመት 28.2 በመቶ የነበረው በ2012 በጀት ዓመት ግን ወደ 23.7 በመቶ ቀንሶ ይታያል፡፡ ምንም እንኳን በ2010 በጀት ዓመት ወጪን በገቢ የመሸፈን አቅም ወደ 27.6 በመቶ ከፍ ያለ ቢሆንም በየዓመቱ እየተመዘገበ ያለው አማካይ የዕድገት ምጣኔ ከ2 በመቶ አይበልጥም፡፡ ይህም

የሚያሳየው ክልሉ ለልማት የሚያስፈልገውን ወጪ በገቢው ከመሸፈን አንፃር በጣም ከፍተኛ ክፍተት የሚታይበት በመሆኑ የክልል ወጪን በፌደራል ድጎማ መደገፍ ግዴታ ሆኗል፡፡

ሌላው የግል የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚመለከት ሲሆን የባንኮችና አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማትን ተደራሽነት እና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በልዩ ልዩ መንገድ እንዲያድግ የሚያስችሉ ሥራዎች በማከናወን በ2012 በጀት ዓመት በክልሉ በሁሉም የፋይናንስ ተቋማት የተሰበሰበ ተቀማጭ መጠን በድምሩ ብር 113.11 ቢሊዮን ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የንግድ ባንኮች ተቀማጭ ድርሻ 86.16 በመቶ ወይም ብር 97.46 ቢሊዮን እንዲሁም የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት 14.59 በመቶ ወይም ብር 16.51 ቢሊዮን ነው። በተጨማሪ በብድርና ቁጠባ የህብረት ሥራ ማህበራት የተሰበሰበ ተቀማጭ ቁጠባን ተወስዶ ሲታይ ደግሞ በ2012 በጀት ዓመት ብር 2.57 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

በክልሉ አብዛኛው ህብረተሰብ የሚገኝበት በገጠር መሆኑና የክልሉ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ በመመስረቱ የፋይናንስ ተቋማትን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር በአነስተኛ የገንዘብ ተቋማትና በገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት እየተሰበሰበ ያለው ተቀማጭ የቁጠባ ገንዘብ ከዓመት ዓመት መጨመር አሳይቷል፡፡ ይህም የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገ ያለና አርሶ አደሩ በገጠር ኢንቨስትመንት ለሚከናወኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ገንዘቡን በመጠቀም የግብርናውን ዘርፍ ለመቀየር የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በገጠር የፋይናንስ ተቋማትን የማበራከትና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በማጎልበት የተቀማጭ ቁጠባን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኛውን የክልሉ ተቀማጭ ቁጠባ ወደ ክልል ኢንቨስትመንት ከመቀየር አኳያ ከፍተኛ ችግር ያለበት በመሆኑ የክልሉ ነዋሪ በቆጠበው መጠን ልክ ከብድር ተጠቃሚ እየሆነ አይደለም፡፡ የተቀማጭ ቁጠባው በብድር መልክ እየተሰጠ ያለው እነደ አገር ቢሆንም በክልሉ በብድር የተወሰደው ከተቆጠበው አንፃር ሲታይ በ2011 በጀት ዓመት 44.8 በመቶ ሲሆን እንደ ክልል ቆጣቢ ህብረተሰብ (Net saver) መሆኑን ያሳያል፡፡

## የድህነት ቅነሳ

ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢን በተመለከተ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን 5 የዕቅድ ዓመታት (ከ2003-2007 በጀት ዓመት) በአማካይ በዓመት ብር 7,414 ወይም 403 የአሜሪካ ዶላር የነበረ ሲሆን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት (ከ2008 እስከ 2011 በጀት ዓመት) ተወስዶ ሲታይ በአማካይ ብር 14,230 ወይም 561 የአሜሪካ ዶላር እንዲሁም በ2012 በጀት ዓመት ብር 23,119 ወይም 739 የአሜሪካ ዶላር ደርሷል፡፡ የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ ግምት ዝቅተኛ ሲሆን በተመሳሳይ ዓመት ከአገር አቀፉ የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር በቀጥታ ማነፃፀር ባይቻልም እንኳን በግርድፉ ሲታይ ዝቅ እንደሚል ከመረጃው ማየት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት የክልሉ ኢኮኖሚ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ በመሆኑ፣ ምርታማነታቸው ዝቅተኛ በሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች እየተመራ በመሆኑ እንዲሁም ኢኮኖሚው ዕሴት በሚጨምሩ ዘርፎች ላይ አለመመስረቱ በድህነት ቅነሳው ላይ ያመጣው ለውጥ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚ ከዓመት ዓመት ባስመዘገበው ዕድገት የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአንፃራዊ መልኩ ዕድገት አሳይቷል፡፡

በሌላ በኩል ክልላዊ የድህነት ሁኔታን ስንመለከት በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ መነሻ ዓመት (2003 በጀት ዓመት) ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው የክልሉ ህዝብ 30.5 በመቶ ያህል የነበረ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባወጣው መረጃ መሠረት በክልሉ ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው ህዝብ ብዛት ወደ 26.1 በመቶ ዝቅ ማለቱን ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው በክልሉ እየተሠራ ባለው የልማት ሥራ ወደ 4.4 በመቶ የሚሆነው የክልሉ ህዝብ ከድህነት ወለል በላይ ማምጣት የተቻለ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል በ2003 በጀት ዓመት በምግብ ድህነት ውስጥ የነበረው የክልሉ ህዝብ 42.5 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህም በ2008 በጀት ዓመት ወደ 31.3 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ የምግብ ድህነቱ በከፋ ሁኔታ በገጠር የሚታይ ሲሆን በዚሁ በተመሳሳይ ዓመት 34.9

በመቶ የሚሆነው የገጠሩ ህዝብ በምግብ ድህነት ውስጥ እንደነበረ ያሳያል፡፡ በከተማም 11.9 በመቶ ይሆናል፡፡ ይህም የሚያሳየው ከአገር አቀፉ ሁኔታ ይልቅ በክልላችን ያለው ገጽታ አስከፊ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በአሥሩ ዓመት የመሪ ዕቅዱ የመነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ የክልሉ የድህነት ምጣኔ 21 በመቶ እንደሆነ ተገምቷል፡፡

ከግብርና ሥነ-ምህዳር /Agro Ecology/ አንፃር ሲታይ ደጋ አካባቢዎች በይበልጥ ለድህነት የተጋለጡ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል አጠቃላይ ድህነት /Incidence of Poverty/ ትርጉም ባለው ሁኔታ እየቀነሰ የመምጣቱን ያህል አስከፊ የድህነት ሁኔታ /Severity of Poverty/ ብዙ ለውጥ እንዳላመጣ በተለያዩ ጥናቶች ታይቷል፡፡ ይህም ማለት የድሀ ድሀ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል እየተሰራ ያለው ሥራ በቂ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡ ህብረተሰቡ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ፈጣን፣ ዘላቂ፣ ፍትሐዊ እና ህዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ለማድረግ የክልሉን ኢኮኖሚ በማሳደግ ድህነትን በሂደት ለማስወገድ በመሪ ዕቅዱ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ህጻናትን አስመልክቶ ዘርፈ ብዙ የህጻናት ድህነት አመላካች /Multi-dimensional Child Deprivation/ ጥናት በ2010 በጀት ዓመት የተጠና ሲሆን በዚህ ጥናትም በአገር ደረጃ 88 በመቶ የሚሆኑ ህጻናት በችግር ውስጥ እንዳሉ የሚያሳይ ሲሆን በአማራ ክልልም 91 በመቶ የሚሆኑት ህጻናት በችግር ውስጥ እንዳሉ ያሳያል፡፡ ይህም ጥናት በአገር ደረጃ ሰፊ የድህነት ሁኔታ ያለ መሆኑንና በአማራ ክልል ደግሞ በከፋ ሁኔታ ችግሩ እንዳለ ያሳያል፡፡ ስለሆነም የድህነት መነሻዎች ዘርፈ ብዙ እንደሆኑ ሁሉ ድህነትን ለማስወገድ የሚሠራው ሥራም ዘርፈ ብዙ መሆን ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም የህጻናት መቀንጨርን አስመልክቶ በተጠናው የሥነ-ህዝብና ጤና ጥናት መሠረት በአገር ደረጃ በ1992 ዓ/ም የነበረው 56.6 በመቶ በ2011 ዓ.ም ወደ 37 በመቶ ቀንሷል፡፡ በተመሳሳይ በክልል ደረጃ 64.5 በመቶ የነበረው ወደ 41.3 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ እንደ ክልል ያለው አኃዝ በጣም ከፍተኛ እና አስከፊ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ ክልሉ የሀገሪቱን የሰብል ምርትና የእንስሳት ሀብት ከ1/3ኛ በላይ የሚሸፍን ሆኖ ተቃርኖ /Paradox/ በሚመስል መልኩ የመቀንጨር መጠን ከሀገሪቱ አማካይም ሆነ ከአብዛኛዎች ክልሎች ከፍ ያለ ነው፡፡ በክልል ደረጃ በአሁኑ ወቅት ከሞላ ጎደል ከ5 ህጻናት 2 የሚሆኑት የመቀንጨር ችግር እንዳለባቸው ይገመታል፡፡ በአሁኑ ወቅት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከከተማ ይልቅ በገጠር አካባቢዎች ችግሩ ይበልጥ አሳሳቢ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ችግሩ ያለባቸው ህጻናት አድገው ወደ ሥራ በሚሰማሩበት ወቅት ምርታማነታቸው ዝቅ እንደሚል ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በክልላችን ጉዳቱ ምን ያህል አሳሳቢ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

በአጠቃላይ የህጻናት መቀንጨር ችግር የሰብዓዊ ሀብት ልማትን በእጅጉ የሚጎዳና የመልማት አቅምን የሚፈታተን ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የልማት መሪ ዕቅዱ ለዚህ አሳሳቢ ችግር የበለጠ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ያመላክታል፡፡

## የሥራ ሥምሪት ሁኔታ

የክልሉ የሥራ ሥምሪት ሁኔታን በተመለከተ በሥራ ላይ የተሰማራውን የሰው ኃይል በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ተከፋፍሎ ሲታይ አብዛኛው በሥራ ላይ የተሠማራው የሰው ኃይል በግብርና ዘርፍ ላይ ሲሆን በዕቅዱ መነሻ ዓመት (በ2008 በጀት ዓመት) ከነበረው 9.2 ሚሊየን ሠራተኛ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 7.34 ሚሊየን ወርዷል፡፡ ይህም 66.6 በመቶ የሚሆነውን የሰው ኃይል ሥምሪት ድርሻ ይዟል፡፡ ከግብርናው በመቀጠል ሰፋ ያለው የሰው ኃይል ሥምሪት የታየበት ዘርፍ የአገልግሎት ዘርፍ ሲሆን ከሰው ኃይል ሥምሪት አንፃር በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 2.3 ሚሊየን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 3.019 ሚሊየን ያደገ የሰው ኃይል በዘርፉ ተቀጥሮ እንዲሠራ አስችሏል፡፡ ይህም ከአጠቃላይ የሰው ኃይል ሥምሪቱ 27.3 በመቶ ድርሻ ይዟል፡፡ ከሶስቱ ዘርፎች በሰው ኃይል ሥምሪት ዝቅተኛ አስተዋጽዖ ያለው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ሲሆን በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ አምስት ዓመታት በአማካይ 7.9 በመቶ የሚሆነውን የሰው ኃይል በመቅጠር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 700 ሺህ በማድረስ ከአጠቃላይ የሰው ኃይሉ

6.4 በመቶ የሚሆነው እንዲሰማራ በማድረግ በሥራ አጥ ቅነሳው ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ አበርክቷል። ከኢንዱስትሪ ዘርፉ በተለይም የአምራች ንዑስ ዘርፉ በ2012 በጀት ዓመት 363 ሺህ የሰው ኃይል በማሠማራት ከአጠቃላይ የሰው ሀይል ሥምሪት 3.28 በመቶ ድርሻ ይዟል። በከተሞች ያለው የሥራ ሥምሪት ሁኔታ ተለይቶ ሲታይ በ2012 በጀት ዓመት የኢንዱስትሪ ዘርፉ አጠቃላይ ከተሠማራው የሰው ኃይል 15.7 በመቶውን ሲሸፍን አብዛኛው የከተማ ነዋሪ ማለትም ወደ 71.4 በመቶ የሚሆነው በአገልግሎት ዘርፉ የተሠማራ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ከከተሞች መስፋፋት ጋር በተጣጣመ መልኩ ኢንዱስትሪው ተስፋፍቶ ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ዘርፍ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ያለው ክፍተት ሰፊ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በአጠቃላይ ምንም እንኳን የሰው ኃይል ሥምሪቱ ከግብርናው ዘርፍ እየወጣ ወደ አገልግሎቱና ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደሚሠማራ የሚጠበቅ ቢሆንም ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው በክልሉ ባለመስፋፋቱ የሠራተኛ ሥምሪቱን ከፍ በማድረግና የሥራ አጥ መጠኑን በመቀነስ ረገድ ሰፊ ችግሮች ይስተዋላሉ።

ሌላው ተከማችቶ የቆየው የሥራ አጥ ዜጋ ብዛት እና ወደ ሥራ ሥምሪት ገበያ የሚቀላቀለው አዲስ የሰው ኃይል ከፍተኛ መጠን ያለው በመሆኑ የሥራ አጥነት ችግሩ አሁንም በከተማ ከፍተኛ ነው። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ተወስዶ ሲታይ በከተማ በ2006 በጀት ዓመት የነበረው የ17.6 በመቶ የሥራ አጥ የዕድገት ምጣኔ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 17.9 በመቶ ከፍ ሲል እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወደ 19.7 በመቶ ማደጉን ያሳያል። በ2012 በጀት ዓመት ወደ 20.4 በመቶ ከፍ ብሎ የተመዘገበ ሲሆን ይህም በአገር አቀፍ ከነበረው 18.7 በመቶ ምጣኔ አንፃር ሲታይ በጣም ከፍተኛ ነው። የወጣቶች /ከ18-29 ዕድሜ ያሉ/ ሥራ አጥነት ተለይቶ ሲታይ 28.5 በመቶ የደረሰ መሆኑን መረጃው ያሳያል። ስለሆነም የሥራ አጥነት ምጣኔው ለሥራ ሥምሪት ከተዘጋጀው ኃይል አንፃር ተወስዶ ሲታይ በክልሉ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በከተማ እያደገ የመጣው ሥራ አጥነት እንዲሁም በተለይ የሴቶች እና የወጣቶች የሥራ አጥነት ሁኔታ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው መሆን ይገባዋል። ከዚህም በላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ የተሻለ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እንዲሆን በልማት መሪ ዕቅዱ ዘመን ለዚህ ጉዳይ የበለጠ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

## የዋጋ ግሽበት

ከግንቦት 2011 በጀት ዓመት እስከ ግንቦት 2012 በጀት ዓመት ድረስ በተንከባላይ አማካይ ስሌት መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ በ2012 ዓ.ም ባወጣው መረጃ እንደ አገር አጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ 19.8 በመቶ መድረሱን ያሳያል። ይህም ምግብ እና ምግብ ነክ የሆኑ የዋጋ ግሽበት 20.3 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ የ19.1 በመቶ እንደሆነ በመረጃው ተመላክቷል። እንደ አማራ ክልልም በተመሳሳይ ወቅት አጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ 17.4 በመቶ የደረሰ ሲሆን ምግብ እና ምግብ ነክ የሆኑ የዋጋ ግሽበት 22.8 በመቶ እንዲሁም ምግብ ነክ ያልሆኑ የ11.4 በመቶ ሆኖ ተመዝግቧል። በዚህም ክልሉ ለሀገሪቱ የዋጋ ግሽበት የነበረውን አስተዋጽዖ በተለይ ምግብና ምግብ ነክ በሆኑ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ከፍተኛ እንደሆነ ማየት ይቻላል። ስለሆነም በቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ዓመታት የአምራች ዘርፎችን ምርትና ምርታማነት በላቀ ደረጃ ለማሳደግ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር የነፃ ገበያ ሥርዓቱን የሚጎዱ አሠራሮችን መከላከልና የህግ ማዕቀፎችን በሙሉ አቅም ተጠቅሞ የገበያውን ህጋዊነት በማረጋገጥ የዋጋ ግሽበቱን የመቀነስ ሥራ መሰራት ይኖርበታል።

## 3.2. የክፍላተ ኢኮኖሚ ዘርፎች አፈፃፀም

### 3.2.1. የኢኮኖሚ ልማት ዘርፎች

#### ግብርና ልማት

በግብርና ልማት ዘርፍ ክልሉ የሚገኝበት ሁኔታን በሚመለከት በአነስተኛ የመሬታ ይዞታ በመኸር በዋና ዋና ሰብሎች የሚመረተው ምርት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 67 ሚሊየን ኩንታል በ2012 በጀት ዓመት ወደ 177 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ቢታቀድም ወደ 108 ሚሊየን ኩንታል አድጓል። በተመሳሳይ የብርዕና አገዳ ሰብሎች ምርት ከነበረበት 57 ሚሊየን ኩንታል ወደ 93 ሚሊየን ኩንታል፣ የጥራጥሬ ሰብሎች ምርት ከ7.6 ሚሊየን ኩንታል ወደ 12.9 ሚሊየን ኩንታል እንዲሁም የቅባት ሰብሎች ምርት ከ2.3 ሚሊየን ኩንታል ወደ 2.8 ሚሊየን ኩንታል ከፍ ብሏል። ይህ የምርት ጭማሪ የመጣው አማካይ የሰብል ምርታማነት ከነበረበት 16.34 ኩንታል በሄክታር ወደ 24.14 ከፍ በማለቱ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ የብርዕና አገዳ ሰብሎች ምርታማነት ከ17.43 ኩንታል ወደ 26.68 ኩንታል፣ የጥራጥሬ ሰብሎች ምርታማነት ከ13.79 ኩንታል ወደ 18.43 ኩንታል እንዲሁም የቅባት ሰብሎች ምርታማት ከ7.36 ኩንታል ወደ 8.70 ኩንታል በሄክታር ዕድገት አሳይቷል። ይህም ትልቅ የምርት ጭማሪ የመጣው ከብርዕና አገዳ ሰብሎች እንደሆነና በአንጻሩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የጥራጥሬና የቅባት ሰብሎችን ምርታማነት ለማሳደግ የተደረገው ጥረት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ በአለፉት 10 ዓመታት የሰብል ምርትን ለማሳደግ የተከናወነው ሥራ እና የተገኘው ውጤት የሚያበረታታ ነበር። ለምርት መጨመር ክላስተርን መሠረት ያደረገ የማሳ ኩታ ገጠም አደረጃጀትን ተግባራዊ በማድረግ የኮሞዲቲ ሰብሎችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በአለፉት ዓመታት አበረታች እንቅስቃሴ መደረጉ አሰተዋጽዖ አድርጓል። በ2012 በጀት ዓመት በክልሉ የተገኘው ምርት በአገሪቱ የተገኘውን ምርት 1/3ኛ ወይም 32.45 በመቶ የሚሸፍን መሆኑ ክልሉ ትልቅ ዕምቅ አቅም ያለው መሆኑን ያሳያል። ይሁንና ክልሉ በሰብሎች ምርታማነት ሲታይ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመላክታል። በተለይ በክልሉ የአግሮ ፕሮሰሲንግ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት መሠረታዊ የሆኑት የቅባት ሰብሎች፣ የጥራጥሬ ሰብሎች ምርታማነታቸው በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑ ችግሩን አሳሳቢ ያደርገዋል። የእነዚህን ሰብሎች ምርታማነት በተወሰነ ደረጃ በማሳደግ ብቻ የክልሉን የግብርና ምርት በፍጥነት ለመጨመር ሰፊ ዕድል መኖሩን ከዚህ ከተጠቀሰው መረጃ ለመረዳት ይቻላል። በመሆኑም ይህ ጉዳይ በመሪ ዕቅዱ ዘመን የግብርናው ዘርፍ ዕቅድ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያመለክታል።

በየዓመቱ ያለውን የሰብል ምርት የዕድገት ምጣኔ ተወስዶ ሲታይ በ2007/08 የምርት ዘመን የምርት ዕድገቱ ከ2007 በጀት ዓመት አንፃር በ0.2 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን በ2009 በጀት ዓመት በ8.9 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ይሁን እንጂ በቀጣይ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ የዕቅድ ዓመታት ይህንኑ ዕድገት ማስቀጠል አልተቻለም። እንዲሁም በ2010 በጀት ዓመት ወደ 5.5 በመቶ እና በ2011 በጀት ዓመት ወደ 2.4 በመቶ እየቀነሰ መጥቷል። ሆኖም ግን በ2012 በጀት ዓመት ወደ 5.49 በመቶ ከፍ ብሏል። በመሆኑም የሰብል ልማት ሥራችን እንደ ክልል ከአየር ንብረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ችግር በሌለበት ወቅትም ቢሆን እያስመዘገብን ያለው የምርት ዕድገት ክልሉ በሰብል ልማት ሥራዎቹ ቆም ብሎ ሊያስብ እንደሚገባ ያመላክታል።

ከላይ በግብርናው ዘርፍ ለመግለጽ እንደተሞከረው የሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድ መሠረት በማድረግ በግብርናው ዘርፍ ለአርሶ አደሩ እርሻ ትኩረት በመስጠት የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል። በዚህም መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም አርሶ አደሩን ሙሉ በሙሉ የዘመናዊ የግብርና ልማት ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በማድረግ የግብርና ምርታማነትን በሚፈለገው ደረጃ ለማሳደግ አልተቻለም። በተወሰኑ አርሶ አደሮች ተሞክሮ ውጤታማ የሆነውን ቴክኖሎጂና የግብርና ዘዴ ወደ ሁሉም አርሶ አደሮች ለማዳረስ አለመቻልና

በዚህም በአርሶ አደሮች መካከል ሰፊ የምርታማነት ልዩነት መኖር፣ የመስኖ ልማትን በማጎልበት የግብርና ልማቱን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ ጥረት ቢደረግም ከተፈጥሮ ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ዓላማን ማሳካት አለመቻል፣ የማዳበሪያና የምርጥ ዘር እንዲሁም የአነስተኛ የእርሻ መሣሪያዎች በጥራትና በብዛት በተፈለገው ጊዜና ቦታ ማቅረብ አለመቻል እንዲሁም የግብርና ሜካናይዜሽን በሚፈለገው ደረጃ አለመስፋፋት ለአብነትም በ2011/12 ምርት ዘመን በክልሉ በትራክተር የታረሰው መሬት ጠቅላላ ከታረሰ መሬትሽፋን ውስጥ 6.59 በመቶ ብቻ የነበረ መሆኑ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ከኬሚካል ማዳበሪያ ባሻገር የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀም ማስፋፋት አለመቻሉ፣ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ ሲሠራ የቆየ ቢሆንም ከዘላቂነት አንፃር ውስንነት በመኖሩ ምክንያት የአፈር ለምነት መቀነስ፣ በደጋማው አካባቢ አሲዳማነት ሰፊ ችግር እየሆነ መምጣት፣ በተባይና በአያያዝ ጉድለት ምክንያት የቅድመ እና ድህረ ምርት ብክነት ከፍተኛ መሆን ለሰብል ምርት ዕድገት ተግዳሮቶች ናቸው።

የእንስሳት ምርትና ምርታማነት የሚገኝበትን ሁኔታ በተመለከተ የተወሰኑ ማሳያዎችን ለማመላከት የወተት ምርትን በ2003 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 336,397 ሊትር በ2012 በጀት ዓመት 1,217,381 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 1,196,749 ቶን (98 በመቶ) ማድረስ ተችሏል። ከአንድ ላም የሚታለብ በቀን አማካይ የወተት ምርት ከአካባቢ ላም ከ1.5 ወደ 2.0 ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች ከ9 ሊትር ወደ 14 ሊትር ለማድረስ ታቅዶ ከአካባቢ ላም 2.0 ሊትር እና ከተሻሻሉ ዝርያዎች 11.8 ሊትር ማድረስ ተችሏል። የሥጋ ምርታማነትን በሚመለከት በ2003 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 209,500 ቶን የሥጋ ምርት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ 450,000 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 438,534 ቶን (የዕቅዱ 98 በመቶ) ተመርቷል። የአንድ እንስሳት አማካይ የሥጋ ምርታማነት የዳልጋ ከብት ከ110 ኪሎ ግራም ወደ 157 ኪሎ ግራም፣ የበግ ከ10 ኪሎ ግራም ወደ 14 ኪሎ ግራም፣ የፍየል ከ9 ኪሎ ግራም ወደ 12 ኪሎ ግራም፣ የዶሮ ከ1 ኪሎ ግራም ወደ 1.8 ኪሎ ግራም ለማሳደግ ታቅዶ የዳልጋ ከብት 148.5 ኪሎ ግራም፣ የበግ 13.2 ኪሎ ግራም፣ የፍየል 11.3 ኪሎ ግራም እና የዶሮ 1.73 ኪሎ ግራም እንዲደርስ ተደርጓል። በ2003 በጀት ዓመት የነበረውን 25 ሚሊየን የዕንቁላል ምርት በ2012 በጀት ዓመት 535 ሚሊየን ለማድረስ ታቅዶ 523 ሚሊየን (የዕቅዱ 96 በመቶ) እንዲደርስ ተደርጓል። ዓመታዊ የዕንቁላል ምርታማነት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረው የአካባቢ ዶሮ 48 ዕንቁላል፣ ከተሻሻሉ ዶሮዎች 148 ዕንቁላል በ2012 በጀት ዓመት ወደ 61 (94 በመቶ) እና 190 (86 በመቶ) በቅደምተከተል ማድረስ ተችሏል።

የማር ምርትን በ2003 ከተደረሰበት 10,456 ቶን በ2012 በጀት ዓመት 23,255 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 20,930 (90 በመቶ) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የሰም ምርት በ2003 በጀት ዓመት ከነበረው 94 ቶን በ2012 በጀት ዓመት 180 ቶን ለማድረስ ታቅዶ 176 (97 በመቶ) ማድረስ ተችሏል። የማር ምርታማነትን በአንድ ቆረጣ በባህላዊ ቀፎ ከ8 ወደ 9 ኪሎ ግራም፣ በሽግግር ቀፎ ከ17.5 ወደ 19 ኪሎ ግራም እና በዘመናዊ ቀፎ ከ25 ወደ 29 ኪሎ ግራም ለማድረስ ታቅዶ በቅደምተከተል 8.53፣ 18.56 እና 26.5 ኪሎ ግራም ለማድረስ ተችሏል። አብዛኛው ማለትም ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው ምርት የተገኘው ከባህላዊ ቀፎ እንደሆነም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ምንም እንኳን ክልሉ በእንስሳት ሀበት በኩል ሰፊ ዕምቅ አቅም ያለው ቢሆንም በእንስሳት ምርታማነት ክልሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዳለ ያመለክታል። የእንስሳት ሀብት ልማት ሥራን በማስፋፋት ረገድ በመኖ አቅርቦት፣ በዝርያ ማሻሻል እና በእንስሳት ህክምና አገልግሎት እየተተገበረ ያለው ሥራ ውጤታማ አለመሆን ይህም እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖን በበቂ ሁኔታ ለአምራች ኢንዱስትሪዎችም ሆነ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ወደ ገበያ ማቅረብ አላስቻለም። በሌላ በኩል የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማቱ በሰፊው ተሰማርቶ በእርሻ ምርቶች አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለውን ክፍተት ለመሸፈን ማገዝ አለመቻሉ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በቡና ልማት እንዲሁም በሆርቲካልቸር ልማት አበረታች ሥራዎች እየተከናወኑ ቢሆንም በውጤት ደረጃ ሲለካ ብዙ የሚቀረው መሆኑ እንዲሁም የግል ባለሀብቱ በዘርፉ ያለው ተሳትፎ አነስተኛ መሆን እንዲሁም ዘርፉ እንደ አዋጭ ቢዝነስ ሳይሆን እንደ ኑሮ ዘይቤ የሚታይ በመሆኑ ብዙ አምርቶ ትርፍ የማግኘት ዓላማ ሳይሆን ያለው ሲቸግረው ወይም ጨው

የሚገዛበት ገንዘብ ሲያጣ ገበያ የሚወጣ መሆኑ፣ የግብይት ሥርዓቱ የዘመነ እና አርሶ አደሩን ቀጥተኛ ተጠቃሚና ተሳታፊ የሚያደርግ አለመሆኑ እና የመሳሰሉት በዘርፉ እየታዩ ያሉ እጥረቶች ናቸው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን የፋይናንስ ተደራሽነት ችግር ማለትም የፋይናንስ ተቋማት ለግብርና ግብዓት እና ምርት ግብይት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ በበቂ ሁኔታ እያቀረቡ ባለመሆኑ አርሶ አደሩ ለብድሩ የሚውል ማስያዣ የማቅረብ አቅም ውስን መሆን ምክንያት በሚፈለገው መጠን ከብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም። በዚህም ምክንያት አነስተኛ ትራክተሮችና የመውቂያ መሣሪያዎችን እንዲሁም የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎችን በበቂ መጠን በብድር ለማግኘት አላስቻለም፡፡ እንዲሁም አበዳሪ ተቋማት ያስቀመጡትን የብድር መሥፈርት አርሶ አደሩ የማያሟላ መሆኑና የብድር መጠኑም የተገደበ በመሆኑ ብድሩን ለፈለጉት ሥራ መጠቀም እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። በተመሳሳይ በዘርፉ ለተሰማሩ ሰፋፊ አልሚዎች፣ ለዕሴት ጨማሪዎች እና ለአግልግሎት ሰጪዎች የልማት እንቅስቃሴ የሚገድብ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ሁኔታ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ዘርፉን ለማሳደግ እንቅፋት ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም ደካማ መሆንም ለዘርፉ አለማደግ አንዱ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም እነዚህና ሌሎች ድክመቶችና ፈታኝ ሁኔታዎችን በቀጣይ መሪ የዕቅድ ዓመታት በማስወገድና ሁኔታዎችን በመቀየር አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የአመራረት ሂደት ተላቆ በዘመናዊ ግብርና አመራረት ታግዞ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ፣ የህብረተሰቡን የምግብ ፍጆታ የሚያሟሉና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ምርቶችን በጥራትና በብዛት ለማምረት እንዲችል ለዘርፉ በመሪ ዕቅዱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

ሌላው የግብርና ልማቱ በምርምር ሊደገፍ እንደሚገባ ታቅዶ ወደ ሥራ የተገባ ቢሆንም ከታቀደው አንፃር ውጤታማነቱ ላይ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ስለሆነም የግብርና ምርምር ሥራዎች እየጨመረ የሚሄደውን የህዝብ ዕድገት መሠረት በማድረግ የህብረተሰቡን የምግብ ፍጆታ ከማሟላት ባሻገር የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግርን በዘላቂነት በመፍታት ላይ ያተኮሩ እንዲሆኑ ርብርብር ማድረግ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግብርናው ከልማዳዊ የኢክስቴንሽን ሥርዓት ወጥቶ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘና በግብርና ሜካናይዜሽን ሰፊው የክልሉ አርሶ አደር የሚጠቀምበት ሥርዓት በመፍጠር አርሶ አደሩን ወደ ዘመናዊ የግብርና ሥርዓት ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡

በሌላም በኩል የደን ሽፋንን ሁኔታ ስንመለከት ከ1997 እስከ 2010 ባሉት 14 የበጀት ዓመታት ውስጥ 2.3 ሚሊየን ሄክታር መሬት ላይ ወደ 18.4 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል እና በተሰሩ የጥበቃና አያያዝ ሥራወች የክልሉን የደን ሽፋን በወቅቱ ከነበረበት 6.5 በመቶ ወደ 14.6 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህም በአገሪቱ በደን ከተሸፈነው ከ15.5 በመቶ በላይ የደን ሽፋን አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ በክልሉ በመሪ ዕቅዱ ዘመን ብዙ መሥራት ይጠበቃል፡፡ ይህ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በሚደረገው አገራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ለመጫወት እንዲሁም በደን ልማት ዙሪያ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ህዝብ የማንቀሳቀስ አቅም ላለው ክልል ከባድ ተግዳሮት ሊሆን ስለማይችል በመሪ ዕቅዱ ዘመን ለዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ የሚያሳይ ነው፡፡

## ኢንዱስትሪ ልማት

የክልሉን አምራች ኢንዱስትሪ በ2012 በጀት ዓመት ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የነበረው ድርሻ 6.6 በመቶ ሲሆን ከኢንዱስትሪ ዘርፍ ጠቅላላ ምርት አኳያ የ41.9 በመቶ ዕድገት ለዘርፉ አስተዋጽዖ ነበረው፡፡ በአምራች ኢንዱስትሪው ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ ለጠቅላላ ክልላዊ ምርት የነበራቸው አስተዋጽዖ 2.93 በመቶ እንደሆነና በኢንዱስትሪ ዘርፉ ውስጥ ደግሞ 18.6 በመቶ ድርሻ አላቸው፡፡ የመካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በ3ኛ ደረጃ ያሉ ሲሆን ለዘርፉ ዕድገት 18.41 በመቶ አስተዋጽዖ ሲያበረክቱ ለጠቅላላ ክልላዊ ምርት ዕድገት የነበራቸው ድርሻ 2.8 በመቶ ብቻ ነው፡፡ በጎጆ ኢንዱስትሪነት ወይም

በጥቃቅን አምራችነት የሚመደበው በዘርፉ ውስጥ የ4.8 በመቶ ድርሻ ሲይዝ ለጠቅላላ ክልላዊ ምርት ዕድገቱ የ0.8 በመቶ አስተዋጽዖ ነበረው፡፡

በሌላ በኩል በኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ በአምራች ዘርፍነት የሚጠቀሰው የማዕድን ልማት ሲሆን ይህም ንዑስ ዘርፍ ከክልሉ ጠቅላላ ምርት የ0.1 በመቶ ድርሻ ሲኖረው ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ግን የ0.8 በመቶ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

ከአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ አምራች ዘርፎችን በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪና የማዕድን ዘርፎች ሲታዩ የአምራች ዘርፎችን በክልሉ የማስፋፋትና ለክልሉ የሚኖራቸውን የኢኮኖሚ አስተዋጽዖ ከማሳደግ አንፃር በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት በክልሉ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ፈታኝ ጉዳይ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ ኢኮኖሚ ከግብርና ጥገኝነት ያልተላቀቀ መሆኑ እንዲሁም የግብርና ዘርፍ በከፍተኛ ፍጥነት አድጎ የኢንዱስትሪውን ድርሻ በማሳደግ በኩል ሊጫወት የሚገባውን ሚና ገና ብዙ የሚቀረው በመሆኑ የኢንዱስትሪ ዘርፉ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በዚህ በኩል ያለው ችግር በግብርና ምርት ዕድገት የተገኘውን ትርፍ ምርት ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት ሊሆን በሚያስችል መልኩ የማዘጋጀት ሥርዓት ባለመኖሩ በክልሉ እየተፈጠሩ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ጥሬ ዕቃ በበቂ መጠን ማግኘት አላስቻላቸውም፡፡ ይህም በአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ በመሆኑም በክልላችን ለሚቋቋሙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የሚውሉ ግብዓቶችን ግብርናው የማምረት አቅም ያለው ስለሆነ ይህንን መነሻ በማድረግ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ይገባል፡፡ ለዚህም አምራች ኢንዱስትሪዎች በተለይ አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን መሠረት ያደረጉ ምርቶች በልዩ ሁኔታ ታቅደው መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም ለኢንዱስትሪዎች በጥሬ ዕቃነት የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በመጠን፣ በጥራት እና በጊዜው ለማቅረብ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

ሌላው ደግሞ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ዓመታት በአምራች ዘርፍ የሚሳተፈው የግል ባለሀብት ቁጥር እያደገ የመጣ ቢሆንም ከተቀመጠው ግብ አንፃር ግን ዕድገቱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የግል ኢንቨስትመንትን በክልሉ የማስፋፋት ሥራው በሚፈለገው መጠንና ጥራት እንዲረጋገጥ ለማድረግ የአመራር ድጋፍና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱ ከፍተኛ መሻሻል ማሳየት አለበት፡፡ እንዲሁም በክልሉ እየተፈጠረ ያለውን የካፒታል እና የተቀማጭ ቁጠባ ዕድገት በክልሉ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለሚሳተፉ ባለሀብቶች የማቅረብ ሥራዎች የማከናወን ጅምር ሥራዎች ያሉ ቢሆንም በክልሉ ያለውን የአምራች ዘርፍ በማሳደግ ረገድ ብዙ ሥራዎች እንደሚቀሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንዲሁም በክልሉ የኢንቨስትመንት ፍሰትን በብቃትና በፍጥነት ለማስተናገድ የኢንዱስትሪ መንደሮች ግንባታና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አማራጭ የሌለው ተግባር በመሆኑ ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት እየተሠራ ይገኛል፡፡ በክልሉ የኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ የሚበረታታ ሲሆን የክልሉ መንግስት እየወሰደ በሚገኘው ባለሀብትን ወደ ክልሉ የማምጣት ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ለዚህም በክልሉ እየተተገበረ የሚገኘው የኢንዱስትሪ መንደር ግንባታና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት በቀጣይ በልማት መሪ ዕቅድ ዓመታት በክልሉ ተጨማሪ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሠማሩ ባለሀብቶችን በመፍጠር ረገድ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ተግባሩን ከማጠናከር ሥራ ጎን ለጎን የባለሀብቶች ምልመላ ላይ አተኩሮ የመሥራትና ለአምራች ኢንዱስትሪ የሚሆኑትን ጥሬ ዕቃዎች ከወዲሁ በክልሉ አልሞ በስፋት እንዲመረቱ የማድረግ ሥራ ከመሥራት ውጭ የኢንዱስትሪ ልማት የሚታሰብ አይደለም፡፡

ሌላው የክልሉን ኢንዱስትሪ ልማት ለማፋጠን የማዕድን ዘርፍ ልማት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ክልሉ በማዕድን ሀብት ዙሪያ ያልተነካ ዕምቅ ሀብት ያለው ሲሆን እንደ ወርቅ፣ ብረት፣ የድንጋይ ከሰል፣ ኦፓል እና ሌሎች ማዕድናት

የሚገኙበት ነው፡፡ ይሁንና ያሉትን ሀብቶች አውቆ ለኢንዱስትሪ ልማት ለማዋል እየተደረገ ያለ ጥረት ቢኖርም ነገር ግን በዘርፉ ብዙ ሥራ ተሠርቷል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ ልዩ ትኩረት በመስጠት በክልሉ ያለውን የማዕድን ሀብት በዝርዝር በማጥናት ማወቅና ለኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ ግብዓት አድርጎ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በከተማና በገጠር ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና የሥራ አጥ ምጣኔን ለመቀነስ እንዲሁም የህብረተሰቡን ገቢ በማሳደግ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ በክልሉ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ የግድ ይላል፡፡ ለዚህም በተለይም በገጠር ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስና ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት በማስወገድ በከተሞች ሊኖር የሚችለውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለመፍታት ግብርናን ማዕከል በማድረግ የገጠር ጥቃቅንና አነስተኛ አግሮ ኢንዱስትሪን ማስፋፋት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የማስፋፋት፣ ቀጣይነታቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም በምርት እና ጥራት ተወዳዳሪ ሆነው ለመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ማደግ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ የአመራርና የድጋፍ ሥራዎች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ክልላዊ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው ዘርፎች ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ወደ አላቸው ዘርፎች የሚደረግ ለውጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የአምራች ኢንዱስትሪና የማዕድን ዘርፎችን ማስፋፋትና ማሳደግ የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም በመሪ ዕቅዱ ዓመታት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማጠናከርና የማቋቋም እንዲሁም የአገር ውስጥና የግል ባለሀብቶችን ወደ ዘርፉ እንዲገቡ የመሳብና የማበረታቻ ሥርዓቶችን በማጠናከር ዘርፎቹን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ከዝቅተኛ ምርታማነት ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ለመሸጋገር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

ለዘርፉ ከአቅም በታች የማምረት ችግር በዋናነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል የክልል ውስጥ ኩባንያዎች ዘመናዊ የሥራ አመራርና የጥራት ሥርዓት የተጠናከረ አለመሆኑ፣ ኢንዱስትሪዎች ከዩኒቨርስቲ፣ ከምርምር እና ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ያላቸው ትስስር ደካማ መሆኑ፣ ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ቴክኖሎጂን የማሸጋገር ሥራ በሚፈለገው ደረጃ አለመሠራቱ፣ ለጥናትና ምርምር በቂ ፋይናንስ አለመመደቡ፣ ጥራት ያለው መሠረተ ልማት አለመስፋፋቱ እና የመሬት አቅርቦት እጥረት፣ የግብዓት እና የኃይል አቅርቦት እጥረት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በአጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ንዑስ ዘርፍ ዝቅተኛ ምርታማነት የሚስተዋልበት በመሆኑ ተወዳዳሪነቱም ደካማ መሆኑን የአፈጻጸም መረጃው ያሳያል። በተጨማሪም የትግራይ ወራሪ ኃይል በከፈተው ጦርነት በተለይም እንደ ኮምቦልቻ ባሉ የክልሉ የኢንዱስትሪ ማዕከላት ጉዳት በመድረሱ በርካታ ኢንዱስትሪዎች እንዲወድሙ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም በጦርነቱ የወደሙ ኢንዱስትሪዎች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ከማድረግና ይህን የሚያካክስ ሥራ በቀጣይ ከመሥራት ባሻገር በቀጣይ መሠረታዊ የብረታ ብረት ምርቶችን በክልል ውስጥ ግብዓት በማምረት፣ የነባር ኢንዱስትሪዎችን የአቅም አጠቃቀም በማሻሻል፣ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ እና ጥራት ያለው ኢንቨስትመንትን በመሳብ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውጤት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ አትኩሮ መሥራት እንደሚገባ አፈጻጸሙ ያመላክታል። ስለሆነም እነዚህን ማነቆዎች መቅረፍ በቀጣይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

## ንግድና ገበያ ልማት

በንግድ ዘርፉ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሠጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ለዚህም የንግድ አሠራሩን ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ ከምዝገባ፣ ከዕድሳትና ከንግድ ሥም ማጣራት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማስፋት አገልግሎቱን ፈጣንና ቀልጣፋ ሊያደርጉ የሚያስችሉ ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሥራዎችን በማከናወን በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ይከሰቱ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ እና

ደንቦች በማሻሻል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በመስጠት፣ ከምዝገባና ማጣራት ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ቅድመ መስፈርቶችን በመቀነስ በምዘገባና በዕድሳት ዙሪያ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በዚህም መሠረት በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥርዓትን የማጠናከር፣ ከጥራት ደረጃቸው በታች የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች በገበያ ላይ እንዳይውሉ ጠንካራ የኢንስፔክሽን ሥራ የማከናወን እና የገበያ አድማስን ለማሳደግ የሚያስችሉ የገበያ ፕሮሞሽን ሥርዓትን የማጠናከር አቅጣጫ በማስቀመጥ በንግድ ዘርፍ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዘርፉ ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ ማድረግ፣ ምርትን በመገደብና በመደበቅ እንዲሁም በተፈቀደው የግብይት መስመር አለመነገድ፣ ፀረ-ውድድር ተግባራት መፈጸም፣ የምርት ጥራት ማጓደል በተለይም በሸማቹ ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የሚጥሉ ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ለሸማቹ ማቅረብ…ወዘተ አሁንም ጎልተው የሚታዩና ያልተፈቱ የገበያ ችግሮች በመሆናቸው እነዚህን ችግሮች በመፍታት ህጋዊ የግብይት ሥርዓት መፍጠር የግድ ይላል፡፡

## ሥራና ሥልጠና

የሥራ ዕድል ፈጠራ በ10 ዓመቱ ውስጥ በከተማና በገጠር ለ4,151,959 ሥራ አጥ ዜጎች በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ5,784,780 ሥራ ፈላጊዎች ቋሚ (ወንድ 2,382,853፣ ሴት 1,038,058፣ ድምር 3,420,911) ጊዜያዊ (ወንድ 1,579,847፣ ሴት783,995 በድምሩ 2,363,842) ዜጎች የሥራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን አፈፃፀሙ 139.3 በመቶ ተከናውኗል፡፡

በአጠቃላይ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 65 በመቶ ቋሚ እና 35 በመቶ ጊዜያዊ ሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 60.86 በመቶ ቋሚ እንዲሁም 39.14 በመቶ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ 80 በመቶ ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 69.52 በመቶ የሚሆኑ ወጣቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሥራ ዕድል ፈጠራ 50 በመቶ ሴቶችን ተጠቃሚ ለማደረግ ታቅዶ 31.11 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በሥራ ፈላጊነት የተመዘገቡትን ለሁሉም የአካል ጉዳተኞች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ወንድ 2,047፣ ሴት 1,911፣ በድምሩ 2,470 አካል ጉዳተኞች በሥራ ፈላጊነት ተመዝግበው ከእነዚህ ውስጥ ወንድ 1,945፣ ሴት 1,418፣ በድምሩ 3,363 አካል ጉዳተኞች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን አፈፃፀሙ 85 በመቶ ነው፡፡

የሥራ ዕድል ፈጠራው ከዕቅድ በላይ የተከናወነው የክልሉ መንግስት፣ በየደረጃው የሚገኝ የዘርፉ አመራርና ፈፃሚ፣ አጋር አካላት ለሥራ ዕድል ፈጠራው ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው በመንቀሳቀሳቸው እና የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ሀብቶችን በተሻለ ሁኔታ በመጠቀማቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ምሩቃንን፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችንና አካል ጉዳተኞችን በሥራ ዕድል ፈጠራው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተከናወነው ሥራ እንዲሁም የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውን ዜጎች በቋሚ የሥራ ዕድል ለማሰማራት የተደረገው ጥረት አበረታች ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የቋሚ ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የተቀመጠውን ግብ በማሳካት፣ የወጣቶችን፣ የሴቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን በሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ፣ በሥራ ፈላጊነት ተመዝግበው ሥራ ያልያዙ እያሉ ሣይመዘገቡ ሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው መኖሩ፣ ምሩቃንን ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ በማስገባት፣ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ፀጋዎችን አሟጦ በመጠቀም እና በገጠር ለሚገኙ ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንደ ከተማው ግልፅ የሆነ ስትራቴጂ አለመኖር በአሠራር ላይ ችግር መፍጠሩ በእጥረት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የአካባቢ ፀጋዎችን በመጠቀም ለሥራ አጥ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል በመፍጠር በተለይም ምሩቃንን፣ የወጣቶችን፣ የሴቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

**ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣**- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በገበያ ተወዳደሪ ሆነው እንዲገኙና በትክክል የኢንዱስትሪ ልማት መሠረት መሆናቸውን ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም መሠረት በተሰጠው ኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የአዋጭ ቴክኖሎጂ ሽግግርን አስመልክቶ በ10 ዓመቱ 2,415 አዲስና የተከለሱ የዕሴት ሰንሰለት ትንተና ለመሥራት ታቅዶ 3,602 የዕሴት ሰንሰለት ትንተና የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙም 149 በመቶ ሆኗል። የኢንተርፕራይዞችን ምርት፣ የአገልግሎት ጥራትና ምርታማነት የሚያሻሽሉ 170,212 ቴክኖሎጂ አብዢ ኢንተርፕራይዞችን ለማሠልጠን ታቅዶ 20,624 (12.1 በመቶ) ተከናውኗል። 1,931 ፕሮቶታይፕ ለማዘጋጀት ታቅዶ 3,697 (191.5 በመቶ) ተዘጋጅቷል። እንዲሁም የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነት የሚያሻሽሉ 3,032 የተዘጋጁ ቴክኖሎጂዎችን በዓይነት ለአብዥዎች ለማሸጋገር ታቅዶ 5,564 ቴክኖሎጂ የተሸጋገረ ሲሆን አፈፃፀሙ 183.6 በመቶ ነው። በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ብር 200 ሚሊየን ሀብት ለማፍራት ታቅዶ ብር 50.42 ሚሊየን (30 በመቶ) ሀብት ማፍራት ተችሏል። ለጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች ለ3,745,605 የሥራ አመራርና ለ1,650,793 የቴክኒክ ክህሎት ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ እንደ ቅደምተከተላቸው ለ2,656,976 እና 1,650,793 አንቀሳቃሾች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙም በሥራ አመራር 70 በመቶ በቴክኒክ ክህሎት 60 በመቶ ሆኗል።

አንቀሳቃሾችን ማስመዘን፣ ማብቃት፣ መሪ መዘኞችን እና የምዘና ማዕከል ማፍራትን በተመለከተ በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ታቅዶ የተሰራ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑም 233,374 አንቀሳቃሾችን ለማስመዘን፣ 118,914 አንቀሳቃሾችን እንዲበቁ፣ 11,520 መሪ መዘኞችን ለማፍራት እና 3,985 የምዘና ማዕከል ለማፍራት ታቅዶ፣ 7,997 (33.9 በመቶ) አንቀሳቃሾችን በማስመዘን 41,029 (34.5 በመቶ) አንቀሳቃሾችን በማብቃት 8,730 (75.8 በመቶ) መሪ መዘኞች እና 2,565 (64.4 በመቶ) ኢንተርፕራይዞች የምዘና ማዕከል ማፍራት ተችሏል። የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት የኢንተርፕራይዞችን ምርት/አገልግሎት ጥራት እና አቅም ለማሳደግ አንቀሳቃሾችን ማስመዘን፣ማብቃት፣ መሪ መዘኛ ማፍራት እና ኢንርፕራይዞችን የምዘና ማዕከል ለማድረግ የተሰራው ሥራ የሚጠበቀውን ያህል አልተፈጸመም ምክንያቱም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ጥራት ላይ ያለማተኮር፣ በኢንተርፕራይዞችና አንቀሳቃሹ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን የድጋፍ ሰጪ አሠልጣኙን አመለካከት የሚቀይር የጋራ ዕቅድ ተይዞ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በተፈለገው መልኩ አለመተግበሩ፣ የትኩረት ዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ዋና ደጋፊ ተቋም ሆነው አለመገኘት ለአብነት ይጠቀሳሉ። የኢንተርፕራይዞችን ምርት/አገልግሎት ጥራት ለማስጠበቅና በነፃ ገበያ ሥርዓት ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሁነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ አንቀሳቃሾችን ማስመዘን፣ ማብቃትና መሪ መዘኛ ማፍራት፣ ኢንተርፕራይዞችን የምዘና ማዕከል ለማድረግ እና በዕውቀትና በበቂ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የማቀድ ሥራ በቀጣይ የዕቅድ ዘመን በትኩረት መሰራት ይኖርበታል።

ለነባርና አዲስ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመረጃና ምክር አገልግሎት መስጠት በመጀመሪያ ዕትዕ ዘመን ታቅዶ የተሰራ ሲሆን በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለ288,841 ኢንተርፕራይዞች (ለ1,157,924 አንቀሳቃሾች) የመረጃና ምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 372,235 ኢንተርፕራይዞች (906,729 አንቀሳቃሾች) የመረጃና የምክር አገልግሎት የተሰጠ ሲሆን አፈፃፀሙ በኢንተርፕራይዞች 128.8 በመቶ በአንቀሳቃሽ 78.3 በመቶ ማከናወን ተችሏል።

የቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የተፈጠሩ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመለየትና ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች ማስፋት የሚያስችል አሠራር መዘርጋት ወሳኝ ተግባር ነው። ስለሆነም በተመሳሳይ መንገድ በመጀመሪያ ዕትዕ ዘመን ታቅዶ ያልተሰራ ሲሆን በ2ኛው ዕትዕ ዘመን 5,324 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር እና የ2,662 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ ቀምሮ ለማስፋት ታቅዶ 4,565 (123.3 በመቶ) ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር የ2,808 (105.2 በመቶ) ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመር

ለ26,996 ኢንተርፕራይዞች ማስፋት ተችሏል። ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስተላለፍ በኩል የተከናወነው ሥራ አፈጻጸሙ ሲታይ የተሻለ እንደሆነ ቢያሣይም ለውጡ በሚፈልገው ልክ ያልመጣ በመሆኑ በቀጣይ ዕቅድ ዘመን በተሻለ ሁኔታ ሊሰራ ይገባዋል።

## የቱሪዝም ልማት

በአለፉት ዓመታት ነባርና አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን፣ ቅርሶችንና ምርቶችን በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን ለማልማት በተደረገ ጥረት አዳዲስ መዳረሻዎችን መለየት ተችሏል። በቋሚ ቅርሶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የጥገና ሥራ ተሰርቷል። በዘርፉ የግል ባለሀብቶችን ለማበረታታት በተደረገው ጥረት ወደ ዘርፉ ለሚገቡ በርካታ ባለሀብቶች የምክርና የሙያ ድጋፍ ተሰጥቷል። የክልሉን የቱሪስት ሀብት ለማስተዋወቅ የሚያስችሉ ሥራዎችም ተከናውነዋል። በዚህ እና በሌሎች ሥራዎች የተነሳ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ቱሪስት ፍሰት ከዓመት ዓመት እያደገ መጥቷል። በዚህም ህብረተሰቡ በተለያየ መንገድ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን ችሏል። ይሁን እንጂ በመስኩ ክልሉ ያለውን ትልቅ አቅም ለመጠቀም በሚያስችል ደረጃ ከማሰብና ከመሥራት ይልቅ የተለመደውን የቁጥ ቁጥ መንገድ ተከትሎ የመሄድ ሁኔታ በስፋት ይታያል። በሌላ በኩል ከ2012 በጀት ዓመት በኋላ በተከሰተው የኮረና በሽታ /COVID-19/ እንዲሁም በጦርነቱ ምክንያት በተለያዩ ቅርሶችና ቱሪስት መስህቦች ጉዳት በመድረሱ በአጠቃላይ የጎብኝዎች ቁጥር በተለይም የውጭ አገር ቱሪስት ጎብኝዎች ቁጥር በእጅጉ እየቀነሰ በመምጣቱ ዘርፉ ከፍተኛ የሆነ ተግዳሮት አጋጥሞታል። ስለዚህም የወደሙ የቱሪስት መስህቦችና ቅርሶችን በመጠገን እንዲሁም በቀጣይ የቱሪስት መቆያ ጊዜን ማራዘም የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የአገልግሎት አቅርቦትና ኩነቶችን በስፋት በመሥራትና በማሻሻል የቱሪስቶችን ፕሮፋይል መሠረት ያደረገ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገትና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ሊያበረክት በሚያስችል መልኩ ማልማት የግድ ይላል።

ክልሉ ከመስህብ ሀብቶች የሚያገኘውን ጥቅም ለማሳደግ የቱሪዝም ገበያን ከማልማትና ተወዳዳሪነትን ከማሳደግ አኳያ በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን የቱሪዝም ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት የቱሪስት አገልግሎቶችን በዓይነትና በመጠን ከማሳደግና የአገልግሎት ጥራትን ከማጎልበት አንፃር ፋይዳ ያላቸው በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። እየጨመረ የመጣውን የቱሪስት ፍሰት ለማስተናገድ እና የአገልግሎት ጥራትን ለማጎልበት ያስቻሉ ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው የሆቴሎች ደረጃ ምደባ ሥርዓት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በዚሁ መሠረት በክልሉ ደረጃቸውን የጠበቁ 32 ባለ ኮከብ ሆቴሎች እና በደረጃ ያልታቀፉ ብዛት ያላቸው ሆቴሎች፣ ሎጆች፣ ሬስቶራንቶች እና የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተፈጥረዋል። በተጨማሪም ሕጋዊ ዕውቅና የተሰጣቸው አስጎብኝ ድርጅቶች ቁጥር ጨምሯል።

የውጭ ቱሪስት ፍሰትን ለማሳደግ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይቷል። በሌላ በኩል እንደ አገር በቱሪዝም ዘርፍ ከተሰማራው ጠቅላላ የሰው ኃይል ውስጥ 23 በመቶ ብቻ የሚሆነው በዘርፉ የሠለጠነ መሆኑን በጥናት ማረጋገጥ ተችሏል። በክልላችንም ከዚህ ያልበለጠ እንደሆነ ይታመናል። በሆቴልና ቱሪዝም ትምህርት ዘርፍ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጡ ከፍተኛ ተቋማት ቁጥር በክልሉ ያላደገ በመሆኑ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ክፍተት የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ ጊዜያት በትኩረት ሊሠራበት ይገባል። በአጠቃላይ በቱሪዝም ልማት እንቅስቃሴዎች የህብረተሰቡ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በተደረገው ጥረት ለበርካታ ዜጎች ቀጥተኛ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ተደርጓል።

ከዚህም በተጨማሪም የቱሪዝም ዘርፉ ካለው ሰፊ ዕምቅ አቅም አኳያ በክልሉ ልማት ውስጥ ተገቢ ሚና እንዲጫወት ማድረግ የሚጠበቅ በመሆኑ በክልሉ የቱሪዝም ፕሮሞሽን እና የገበያ ሥርዓትን ለማሳደግ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመኑ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። ይሁን እንጅ ከሚጠበቀው ውጤት አኳያ ገና ብዙ

እንደሚቀር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ የበጀት ዓመታት የአገር ውስጥና የውጭ አገራት ቱሪስት ፍሰትን ለማሳደግ በዘርፉ የቱሪስት መዳረሻዎችን በማጠናከር ፍሰቱ እንዲጨምር ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠርና ተከታታይ የሆኑ የፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን የክልሉን ገጽታ መገንባት ተጠናክሮ የሚሠራ ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ ካለው ሰፊ ዕምቅ አቅም አንፃር በክልሉ ልማት ውስጥ ተገቢ ሚና እንዲጫወት ማድረግ በአሥር ዓመቱ ዕቅድ ዘመን በትኩረት የሚከናወን ሥራ ይሆናል፡፡

## 3.2.2. መሠረተ ልማት የማስፋፋት አፈፃፀም

በክልሉ የመሠረተ ልማት አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ይኸውም የተጀመሩ የዋና ዋና መንገዶች ግንባታ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንሽፎርሜሽን ዘመን ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ አብዛኛውን የክልሉ ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገዶች ጋር ለማገናኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር አጋዥ የሚሆኑ ደረጃቸው DS6 የሆኑ መንገዶች በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ተደርሶበት ከነበረው 7,617 ኪሎ ሜትር እስከ 2012 በጀት ዓመት መጨረሻ በመደበኛ እና በተቋራጭ ኘሮጀክቶች 5,796.18 ኪሎ ሜትር ማድረስ የሚል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በ2012 በጀት ዓመት በራስ ኃይልና በተቋራጭ የተሠራውን 348 ኪ.ሜ ጨምሮ በአለፉት 10 ዓመታት በድምሩ 3,793.693 ኪሎ ሜትር መንገድ መገንባት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የዚህ አፈጻጸም ቀደም ብሎ ከተያዘው በመጀመሪያው እና በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን 65.45 በመቶ የሚሆነውን ማከናወን የተቻለ ቢሆንም በአለፉት 10 ዓመታት ከታቀዱት አንፃር የተገኙት ውጤቶች የአፈጻጸም ክፍተት እንዳለባቸው ለመረዳት ተሞክሯል። የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች ከፍተኛ ካፒታል እና ክህሎት የሚጠይቁ በመሆኑ በተፈለገው ፍጥነት መንቀሳቀስ አለመቻል፣ የግንባታ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የአቅም ውስንነት ግንባታዎችን በወቅቱና በጥራት ያለማጠናቀቅ፣ የተገነቡትን መሠረተ ልማቶች በብቃት የማስተዳደር ተቋማዊ አቅም አነስተኛ መሆን፣ የመንገድ ወሰን ማስከበር፣ በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር ያለመኖር፣የእግረኛ መንገድ ግንባታው በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ የመንገድ ሀብት ደህንነትና መብት እንክብካቤ ችግር በዘርፉ የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ በነበረው ጦርነት በመንገድ መሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ፈጣንና አስተማማኝ ለውጥ በማምጣት ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ ይገባል፡፡የትራንስፖርት አገልግሎቱ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ ተወዳዳሪ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ከማድረግ አንፃርም ጥረቶች ሲደረጉ የቆዩ ቢሆንም ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡ የትራንስፖርትና የትራፊክ ህጎችን ለማስከበርም ሆነ አደጋን ለመቀነስ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም አደጋን በተጨባጭ መቀነስ አልተቻለም፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት መሠረተ ልማትን የማስፋፋት ጉዳይ ወሳኝ ነው፡፡ መሠረተ ልማቱ ከግብርና ዝመና፣ ከአምራች ኢንዱስትሪ፣ ከማዕድን እና ከቱሪዝም ልማት እንዲሁም የእነዚህን ዘርፎች ልማት ለማፋጠን እና ትስስራቸውን ለማጎልበት ታስቦ በቀጣይ የክልሉ ልማት መሪ ፕላን ትኩረት ተሰጥቶት ሊታይ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ክልሉ ሰፊ የገፀ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት ባለቤት በመሆኑ ይህንን ሀብት በአግባቡና ውጤታማ በሆነ መንገድ በመጠቀም የክልሉን ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንዲቻል በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ሰፊ ጥረት ተደርጓል፡፡ ይኸውም የንፁህ መጠጥ ውኃ በገጠርና በከተማ ለማዳረስ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ይህም አሁንም አገልግሎቱን በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በገጠርም ሆነ በከተማ ሙሉ በሙሉ በማዳረስ በኩል የሚቀር ሥራ እንዳለ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የውኃ ግንባታ ሥራዎች በጥራት እና በተቀመጠው

የጊዜ ገደብ አለማጠናቀቅ እንዲሁም የሚቆፈሩ የውኃ ጉድጓዶች መምከን እና መበላሸት በአገልግሎቱ የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡

ከዚህም ሌላ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ለዘላቂ የግብርና ልማት ያለው ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ በክልሉ ያለውን የውኃ ሀብት በስፋት ለመጠቀም አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ የመስኖ ግንባታዎችን ለማከናወን ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የሥራ ተቋራጮች፣ የአማካሪዎችና የአቅራቢዎች እጥረት እንዲሁም የጉድጓድ ቁፋሮ ድርጅቶች የአቅም ማነስ፣ የፈፃሚ አካላት አቅም ውስንነት፣ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለው ቅንጅታዊ ትስስር በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያለመሆን አበይት ችግሮች ናቸው፡፡ በቀጣይም የችግሮቹን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ በማበጀት የክልሉን የመስኖ አውታሮችን ማሳደግ ይገባል፡፡

ከተሞች በፕላን የሚመሩ፣ ጽዱ፣ ውብና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎቻቸውና ለጎብኝዎቻቸው የሚመቹ የምርትና የግብይት ማዕከላት ሁነው እንዲያድጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ከፕላን ዝግጅት አኳያ ለ415 (81.35 በመቶ) አነስተኛ ከተሞች የመሠረታዊ ካርታና ፕላን፣ ለ32 (72.73 በመቶ) ከተሞች መዋቅራዊ ካርታና ፕላን፣ ለ71 (78.89 በመቶ) የከተሞች የመሠረታዊ ካርታና ፕላን ክለሳ፣ ለ217 ከተሞች የማስተካከያ ፕላን፣ ለ2,860 (66.27 በመቶ) የገጠር ማዕከላት ስኬች ፕላን፣ እንዲሁም 145 (49.32በመቶ) የአካባቢ ልማት ፕላን የተዘጋጀ ሲሆን የ244 (94.21 በመቶ) ከተሞችን መሠረታዊ መረጃዎች (Urban Profile) የማሰባሰብና የመተንተን ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

የከተማ መሬት ሀብትን ከንጥቂያ እና ከወረራ በመከላከል በቁጠባ ለላቀ ልማት ማዋል እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነበት ዘመን ላይ ስለምንገኝ የጠራ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ማስተዳደር ይገባል፡፡ በክልሉ ከሚገኙ 650 ከተሞች ውስጥ 447 ከተሞች የአስተዳደር ወሰናቸውን ያካለሉ ሲሆን 382 ከተሞች በመሬት ላይ ቋሚ የወሰን ምልክቶችን ያስቀመጡ እና በካርታ ላይ ያመላከቱ ናቸው፡፡ በ354 ከተሞች 19,266.8 (105.86 በመቶ) ሄክታር ክፍት ቦታ እና 2,817.51 (80.50 በመቶ) ሄክታር በጊዜያዊነት የተሰጠ ቦታ መቁጠርና መመዝገብ ተችሏል፡፡ በከተሞች ማስፋፊያ እና በመሃል ከተማ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚሆን 33,744.66 ሄክታር መሬት (3,649.31 ሄክታር ለጨረታ እና 30,095.35 ሄክታር ለምደባ) የተዘጋጀ ሲሆን 13,769.23 (69.29 በመቶ) ሄክታር መሬት (664.39 ሄክታር በጨረታ እና 13,104.84 ሄክታር በምደባ) ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

የከተሞች ይዞታ ወደ ሊዝ ስሪት እንዲገቡ ከማድረግ አኳያ በክልሉ ካሉ 650 ከተሞች መካከል 293ቱ በአለፉት 10 ዓመታት ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ የተደረገ ሲሆን በእነዚህ ከተሞች ከ2005-2012 ባለው ጊዜ ውስጥ ከሊዝ ይዞታዎች 1,911,687,661.14 ብር እና ከኪራይ ይዞታዎች 366,594,113.55 ብር በድምሩ 2,278,281,774.69 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በከተሞች ቆሻሻን ከምንጩ በመለየት እና በመቀነስ መልሶ መጠቀም እንዲሁም አረንጓዴ፣ ፅዱ፣ ውብና ማራኪ በማድረግ ለኑሮ ተስማሚ እና ለጎብኝዎቻቸው የሚመቹ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ለ417,723 (ወንድ 208,604፣ ሴት 209,119) የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ በመፍጠር 416,619 (ወንድ 208,192፣ ሴት 208,427) ወይም 83.32 በመቶ የህብረተሰብ ክፍል በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥራ ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በሁሉም ከተሞች በፕላን የተመላከቱ 3,480 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለመስጠት ታቅዶ በ354 ከተሞች በፕላን የተመላከቱ 3,422 (98.33 በመቶ) የአረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት ለ2,970 (86.79 በመቶ) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መስጠት ተችሏል፡፡የከተሞች ፋይናንስ አቅርቦትን ከማሳደግ አንፃር ስትራቴጂክ ሠነድ በማዘጋጀት እና የአደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ከ312 መሪ ማዘጋጃ ቤቶች፣ ንዑስ ማዘጋጃ ቤቶች እና ታዳጊ ከተሞች 2.034 (96.79 በመቶ) ቢሊዮን ብር እና ከ47 ከተማ አስተዳደሮች 5.597 (83.44 በመቶ) ቢሊዮን ብር

በድምሩ 7.631 (86.62 በመቶ) ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 57 የገቢ አርዕስቶች በአማካይ ከ22-35 በሚሆኑት ብቻ ገቢ እየተሰበሰበ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡

የከተሞችን መስፋፋትና የህብረተሰቡን ወደ ከተሞች መሰባሰብ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ልማቱን ተከትሎ የመጣው ተግዳሮት የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ጉዳይ ነው፡፡ በመንግስት አስተባባሪነት ተገንብተው ለተጠቃሚ ከተላለፉት የጋራ መኖሪያ (ኮንዶሚኒየም) ቤቶች በተጨማሪ በተለያዩ አማራጮች ማለትም (በመኖሪያ ቤቶች የኅብረት ሥራ ማኅበራት 149,263፣ በግለሰቦች 12,273፣ በሪል-ስቴት 721፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 6,341 (የቁጠባ ቤቶች ለመገንባት) በጠቅላላው 168,685 (79.35 በመቶ) ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

በከተሞች የሚገነቡ የመሠረተ-ልማት አውታሮች ለከተሞች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር እንደ መፍቻ የሚወሰዱ የልማት ማዕከል ናቸው፡፡ ከተሞች የልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል በአለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት የክልሉ መንግስት ከፍተኛ በጀት መድቦ ዘርፈ ብዙ የመሠረተ ልማት አውታሮችን የማስፋፋት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በአለፉት 10 ዓመታት የULGDP ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ እና ከፕሮግራሙ ውጭ ያሉ ከተሞች በራሳቸው አቅም የገነቧቸው መሠረተ ልማቶች ከተቀመጡ ግቦች አንፃር ሲታይ የማህበራዊና አካባቢ ደህንነትን መሠረት ያደረገና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የጌጠኛ ድንጋይ (Cobble Stone) ንጣፍ መንገድ 818.28 (49.88 በመቶ) ኪሎ ሜትር፣ ጠጠር መንገድ 4,482.74 (92.96 በመቶ) ኪሎ ሜትር፣ አስፓልት መንገድ 98.69 (74.06 በመቶ) ኪሎ ሜትር፣ ጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ 269.27 (68.4 በመቶ) ኪ.ሜ የተገነባ ሲሆን መለስተኛና ከፍተኛ ድልድይ ለመገንባት ታቅዶ በቁጥር 602 (86.37 በመቶ) ድልድይ ግንባታ ለማከናወን ተችሏል፡፡ እንዲሁም የከተማ ውስጥ ለውስጥ መንገድ መብራት 2,458.85 (76.91 በመቶ) ኪ/ሜ፣ የውኃ መስመር 4,202.78 (99.81 በመቶ) ኪ/ሜ፣ የውኃ ቦኖ 946 (98.03 በመቶ) በመገንባት ለማከናወን ተችሏል፡፡ በዘርፉ የተከናወኑ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎችን በተመለከተ በከተማ ፕላን ዝግጅት፣ በአረንጓዴ ልማትና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በመሠረተ-ልማት ግንባታ እና በኮንስትራክሽን በዘርፍ ለ753,266 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ624,265 (82.87 በመቶ) ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

### 3.2.3. የማህበራዊ ልማት ዘርፍ አፈፃፀም ግምገማ

## የትምህርት ልማት

በክልሉ የመልካም አስተዳደርን በማስፈን እና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት በማረጋገጥ ወደ ብልፅግና ለሚደረገው ጉዞ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ይኸንን ዓላማ ከማሳካት አንፃር የትምህርት ልማት ዘርፍ በክልሉ በየደረጃው በሚገኙ ክፍላተ ኢኮኖሚዎች ተፈላጊ የሆነ የሠለጠነ የሰው ኃይል በበቂ እና በጥራት በማፍራት ረገድ ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት መሆኑ ታምኖበት በአለፉት ዓመታት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በትምህርት ልማት ዘርፍ በግብ ተይዘው ከነበሩት መካከል የትምህርት ተሳትፎ እና ፍትሐዊነትን ከማሳደግ አንፃር እንዲሁም የትምህርትን ጥራትና ተገቢነትን ከማሻሻል አኳያ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

የትምህርትን ተሳትፎ ከማሳደግ አኳያ በተከናወነው ተግባር የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2007 ከነበረበት 51.5 በመቶ በ2012 ወደ 37.2 በመቶ ዝቅ ያለ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም ከመሻሻል ይልቅ ከነበረበት ያሽቆለቆለ መሆኑ ታይቷል፡፡ ለአፈፃፀሙ ማነስ ተጠቃሽ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው የህፃን ለህፃን የትምህርት ፕሮግራም (ከ20.7 በመቶ በላይ ህፃናትን ተደራሽ ያደረገው) የውጤታማነት ችግር የታየበት መሆኑ ተገምግሞ ሙሉ በሙሉ እንዲቋረጥ በመደረጉ ነው፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎው ሲታይ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 92.2 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 81.3 በመቶ ደርሷል፡፡ንጥር የትምህርት ተሣትፎም በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት 84 በመቶ በ2012 ወደ 74.7 በመቶ በመውረድ ዝቅ ያለ አፈፃጸም አስመዝግቧል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች ተሳትፎ (1-8) በየእርከኑ ተሸንሽኖ ሲታይ የ1ኛው እርከን (1-4) ጥቅል ተሣትፎ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 113.9 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 82.3 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን የ2ኛው እርከን (5-8) ከ67.1 በመቶ ወደ 81.8 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በ1ኛ እና በ2ኛ የትምህርት እርከን መካከል የነበረው የተሳትፎ ልዩነት እየጠበበ መምጣቱን ሲሆን ነገር ግን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ጥቅል እና ንጥር የትምህርት ተሣትፎ በየዓመቱ እያሽቆለቆለ መሄዱ በችግር የሚጠቀስ ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ የ1ኛ እርከን (9-10) ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ በተመለከተ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 36.0 በመቶ (ወንድ 33.1 በመቶ፣ ሴት 39.5 በመቶ) በ2012 ዓ.ም ወደ 49.8 በመቶ (ወንድ 46.4 በመቶ፣ ሴት 53.4 በመቶ) ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም በ2011 ዓ.ም ከተመዘገበው 48.5 በመቶ አገራዊ አማካይ አንፃር አፈፃፀሙ ከፍ ያለ ቢሆንም እ.ኤ.አ. በ2030 ሁሉም ዕድሚያቸው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የደረሱ ወንዶች እና ልጃገረዶች ጥራቱንና ፍትሐዊነቱን የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቅቃሉ የሚለውን የዘላቂ ልማት ግብ ለማሣካት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡ በተመሳሳይ በዓለም ባንክ ጥናት መሠረት የመካከለኛ ገቢ የኢኮኖሚ እርከን ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚያቸውን መሸከም የሚችል የሰው ሀብት ከማፍራት አንፃር ሊያሳኩት ይገባል ተብሎ ከተቀመጠው 72 በመቶ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ አኳያም ያለንበት ሁኔታ አበረታች አለመሆኑን ያሳያል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት 11.14 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 23.3 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡

ከልዩ ፍላጎት ትምህርት አንፃር በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2007 ዓ.ም 1.55 በመቶ (ወንድ 1.72 በመቶ፣ ሴት 1.37 በመቶ) የነበረው ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በ2012 ዓ/ም 2.39 በመቶ የደረሰ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 0.82 በመቶ ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ ወደ 0.33 በመቶ ላይ ይገኛል፡ ፡

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በተመለከተ እንደ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የ2009 ዓ.ም ሪፖርት መሠረት በክልሉ ከሚኖረው ጎልማሣ መካከልው ማንበብና መፃፍ የማይችሉት 5,772,470 (ወንድ 2,158,512፣ ሴት 3,613,958) ወይም 52.7 በመቶ (ወንድ 41.2 በመቶ፣ ሴት 63.2 በመቶ) ይሆናሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል አብዛኛው በገጠር አካባቢ የሚኖረው ህዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ከ2010 እስከ 2012 ዓ/ም በተደረገው እንቅስቃሴ የ2 ዓመቱን የጎልማሶች የመሠረታዊ ትምህርት ማጠናቀቅ የቻሉት 1,143,968 (ወንድ 686,957፣ ሴት 457,011) እንደሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም 47.3 በመቶ ሲሆን ከአገር አቀፍ አማካይ 53.7 በመቶ ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም ባሻገር መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ከደረሱበት የ76.4 በመቶ ምጣኔ አንፃር ሲታይ በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቃል፡፡

### የትምህርት ፍትሐዊነት አፈፃፀም

ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት በተመለከተ በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት በቅድመ መደበኛ 0.98፣ በመጀመሪያ ደረጃ 0.99፣ በአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ 1.20 እና በከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ 0.94 ሲሆን በ2012 ዓ/ም እንደ ቅደምተከተላቸው 0.99፣ 0.97፣ 1.15 እና 0.97 ሆኗል፡፡ይህም በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የሴቶችን የትምህርት ተሣትፎ ከወንዶች ጋር በማመጣጠን ረገድ የተከናወኑ ተግባራት እና የተገኘው ተጨባጭ ውጤት አበረታች መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ የገጠር ከተማ ክፍተት በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት 0.84 በ2012 ዓ/ም ወደ 0.79 ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ይህ የሚያመላክተው ክፍተቱ ከመጥበብ ይልቅ እየሰፋ በመሄድ ላይ መሆኑን ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የማቋረጥ መጠን እና ክፍል የመድገም አፈፃፀም በ2007 ዓ.ም ከነበረበት 11.4 በመቶ እና 8.1 በመቶ በ2012 ዓ.ም የማቋረጥ ምጣኔ ወደ 2.44 በመቶ እና የመድገም ምጣኔ ወደ 9.76 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው የደረሰ መሆኑ ታይቷል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ የመቀነስ አዝማሚያ ያሳየ ቢሆንም ክፍል የመድገም ምጣኔ ግን ጭማሬ አሳይቷል፡፡ በተለይ ከፍተኛ የሆነ የተማሪዎች መድገም የተመዘገበው በአንደኛው እርከን (1-4) ላይ መሆኑ ታይቷል፡፡

በ2ኛ ደረጃ የ1ኛ እርከን (9-10) የትምህርት ኘሮግራም የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 5.3 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 5.9 በመቶ ያደገ ሲሆን የ9ኛ ክፍል የመድገም ምጣኔ ከ13.5 በመቶ ወደ 10.9 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡ በሌላ በኩል በከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም የተማሪዎች የትምህርት የማቋረጥ ምጣኔ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 3.6 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 4.44 በመቶ እንዲሁም የ11ኛ ክፍል የመድገም ምጣኔ ከ2.34 በመቶ ወደ 3.15 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑ ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ የተማሪዎች ማቋረጥ በሁለቱም የትምህርት እርከኖች ጭማሪ ያሳየ ቢሆንም በከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ የተማሪዎች የመድገም ምጣኔ ጭማሪ የታየበት ነበር፡፡

### የትምህርት ጥራትና ተገቢነት አፈፃጸም

የትምህርትን ጥራት እና ተገቢነት ማሻሻያ በትምህርት አመራር፣ በመምህራን ልማት፣ በሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ፣ በትምህርት ቤት ማሻሻያ፣ በሥነ-ዜጋ እና በሥነምግባር ትምህርት እና በአይሲቲ ማስፋፊያ መርሀ ግብሮች ትኩረት በማድረግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶች ለደረጃው በሠለጠኑ የትምህርት ቤት አመራሮች እንዲመሩ ከማድረግ አኳያ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ርዕሰ መምህራን እና የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች በ2007 ዓ/ም ከነበረበት 20.7 በመቶ እና 61.1 በመቶ በ2012 ዓ/ም እንደ ቅደምተከተላቸው 66.3 በመቶ እና 92.8 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም በ2007 ዓ/ም ከነበሩበት 20.4 በመቶ እና 44.3 በመቶ በ2012 ዓ/ም ወደ 53.4 በመቶ እና 92 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡

ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በተመለከተ በ2007 ዓ/ም ከነበረበት በቅድመ መደበኛ ተቋማት 0፣ በልዩ ፍላጎት 10 በመቶ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት 86.2 በመቶ፣ በአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 96.13 በመቶ እና በከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 7.36 በመቶ በተከናወነው በርካታ ተግባራት በ2012 ወደ 29.3 በመቶ፣ 94.3 በመቶ፣ 96.1 በመቶ፣ 99.2 በመቶ እና 25.6 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው ማድረስ ተችሏል፡፡

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በስታንዳርዱ መሠረት ወደ ደረጃ 3 እና ወደ ደረጃ 4 ማሻሻልን በተመለከተ የቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2012 ወደ 4 እና 0 በመቶ፣ 14.1 እና 0 በመቶ እንዲሁም 17.1 እና 0 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው የደረሰ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚህ በኩል የተመዘገበው አፈፃፀም 85 በመቶ ትምህርት ቤቶችን ወደ ደረጃ 3 እንዲሁም 75 በመቶ የሚሆኑትን ወደ ደረጃ 4 ለማድረስ ተብሎ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ስለሆነም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ተግባር በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

የተማሪ ሴክሽን ጥምርታ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት 1፡45 በ2012 ወደ 1፡41 ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2007 ዓ/ም ከተደረሰበት 1፡49 በ2012 ወደ 1፡59 ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ይህ መረጃ ተማሪዎች በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተጨናነቀ ሁኔታ በመማር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ በቀጣይ አዲስ ትምህርት ቤቶችን ከመክፈት ጎን ለጎን በነባር ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ክፍሎችን ማስፋፋት እና የተማሪ ሴክሽን ጥምርታን ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡ የመምህር ተማሪ ጥምርታ በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2007 ከተደረሰበት 1፡38 በ2012 ወደ

1:29 ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2007 ከተደረሰበት 1:24 በ2012 ወደ 1:25 ደርሷል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህር ተማሪ ጥምርታ ሊቀንስ የቻለው የክፍል ውስጥ አደረጃጀቱ ከአሃዳዊ ወደ ዲፖርትመንት መቀየሩ በአንድ ክፍል ውስጥ ከአንድ በላይ መምህራን እንዲያስተምሩ ለማድረግ የተጨማሪ መምህራን ቅጥር እና ሥምሪት እንዲፈፀም መደረጉ ነው፡፡

**ዋና ዋና ማነቆዎች**

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከሚስተዋሉት ተግዳሮቶች መካከል የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ ዋነኛው ነው፡፡ በዚህ በኩል የክልላችን አፈፃፀም በአገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበው አማካይ ጥቅል ተሣትፎ አንፃር ሲመዘን የተሻለ ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ በስታንዳርድ ከተቀመጠው ቢያንስ 80 በመቶ አፈጻጸም ላይ በማድረስ በኩል በአገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ተሳትፎውን ለማሳደግ በቀጣይ የተጠናከሩ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቃል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም ከሚታዩ ተግዳሮቶች መካከል የጥቅል እና የንጥር የትምህርት ተሣትፎ በየዓመቱ እያሽቆለቆለ መሄዱ፣ በ1ኛ (1-4) እና በ2ኛ (5-8) እርከኖች መካከል በጥቅል እና በንጥር ተሳትፎ ተመጣጣኝነት የጎደለው መሆኑ እና በተለይም በ2ኛ እርከን (5-8) ትምህርት ላይ ከፍተኛ የሆነ መጠነ ማቋረጥ እና ከትምህርት ውጭ መሆን የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ብክነት በከፍተኛ ደረጃ ይስተዋላል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በ2030 እ.ኤ.አ ሁሉም ወንዶች እና ልጃገረዶች ጥራቱን እና ፍትሐዊነቱን የጠበቀ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያጠናቅቃሉ የሚለውን የዘላቂ ልማት ግብ ከማሣካት አኳያ አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ይታመናል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ ክፍል) ጥቅል ተሳትፎ የተደረሰበት የአፈፃፀም ደረጃ ሲታይ አገራችን ከምትፈልገው በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል አንፃር በጣም ዝቅተኛ እና አሣሣቢ ጉዳይ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ከመካከለኛ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች በተነፃፃሪነት ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን/ተደራሽነት ማሳደግ በቀጣይ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

ጥቅል የትምህርት ተሣትፎን ከማሳደግ አኳያ ከሚጠቀሱ ተግዳሮቶች መካከል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በበቂ ሁኔታ አለመስፋፋት፣ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወደ 2ኛ ደረጃ የሚደረገው የተማሪዎች ሽግግር በሚጠበቀው መጠን አለመሆን እና ከፍተኛ የሆነ የተማሪዎች መጠነ ማቋረጥ መታየቱ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር የተማሪዎች የደረጃ ሽግግር ዝቅተኛ በመሆኑ በርካታ ህፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን አያጠናቅቁም፡፡ ለአብነት ያህል የ2010 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል የተማሪዎች የማጠናቀቂያ ምጣኔ 66.1 በመቶ ነበር፡፡ ስለሆነም ትምህርት ቤቶችን ከማስፋፋት በተጨማሪ በየደረጃው የንጥር ተማሪዎች ተሣትፎ ምጣኔን ማሣደግ አስፈላጊ ነው፡፡

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት ከመሠረታዊ የማንበብና መጻፍ ክህሎት እስከ የሕይወት ክህሎት እንዲሁም ጎልማሶች በአጫጭር የሙያ ክህሎት ትምህርት እና ሥልጠና በመሳተፍ በገቢ ማስገኛ ተግባራት በብቃት መሳተፍ እንዲችሉ የሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የሰው ሀብት ልማትን ከማሳደግ አኳያ ጉልህ ሚና ያለው መሆኑ የሚታመን ቢሆንም በዚህ በኩል እስከ አሁን የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሣ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ክልላችን ያለበት የተሳትፎ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጋር ሲወዳደር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ የሚጠበቀውን ልማት ከማስፈን አኳያ ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ በኩል ከፍተኛ ርብርብ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የትምህርት ፍትሐዊነትን ከማስፈን አንፃር ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል የገጠር ከተማ ክፍተቱ በቅድመ መደበኛ፣ በመጀመሪያ እና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ዙሪያ እየጠበበ ከመሄድ ይልቅ እየሠፋ መምጣቱ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት በተማሪዎች ተሳትፎ እንዲሁም ለትምህርቱ አጋዥ የሆኑ የመሠረተ ልማትን ከማስፋፋት አኳያ በሚፈለገው ደረጃ

አለመሟላቱ፣ በተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ ከፍተኛ ክፍተት ያለበት እና ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የትምህርት ውስጣዊ ብቃት ዙሪያ ከሚታዩ ተግዳሮቶች መካከል የተማሪዎች አዘውትሮ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት፣ የመማር ፍላጎት ማጣት እና አማራጭ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሠማራት፣ የትምህርት ማቋረጥ እና ክፍል መድገም /የትምህርት ብክነት/ ገና ያልተሻገርነው ችግር ነው፡፡ በተጨማሪም በመጀመሪያ ደረጃ 2ኛ እርከን (5-8) የተማሪዎች ትምህርት የማጠናቀቅ ምጣኔ በተፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ የሚሉ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በትምህርት ጥራትና ተገቢነት ዙሪያ ከሚታዩ ተግዳሮቶች መካከል በትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲው ከተቀመጠው አንፃር የሁሉም ተማሪዎች የመማር ውጤት እና ሥነምግባር ሙሉ በሙሉ አለመሣካቱ፣ የመምህራን ሙያዊ ብቃት በሚጠበቀው ደረጃ አለመሻሻል እንዲሁም በትምህርት አመራሩም ሆነ በባለሙያው በኩል የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የአደረጃጀት እና የአሠራር ችግር መኖር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የክልሉ መንግስት ለትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ለትምህርት ጥራት መጓደል ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዘርፉን ከዕድገት አቅጣጫ ወደኋላ ከጎተቱትና ጥራቱን እና ብቃቱን ከተፈታተኑት መካከል በዘርፉ የሠለጠኑ በቂ መምህራን አለመኖር፣ ጥራት ያለው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች እጥረት፣ የክትትል፣ ቁጥጥር እና የግምገማ ሥርዓት በበቂ ሁኔታ አለመዘርጋት፣ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ ለመሆን የሚያስችል ደረጃ ባለመያዛቸው የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ አሉታዊ ጫና ማሣረፉ፣ ወዘተ…ተጠቃሽ ናቸው። ትምህርት በጥራት ካልተሰጠ ደግሞ ከትምህርት የሚጠበቁትን ጥቅሞች ማግኘት አዳጋች ይሆናል። በመሆኑም በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት ብቁ፣ ተወዳዳሪ ዕውቀትና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል በትምህርት ተሳትፎ ረገድ በቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ንጥር ቅበላ የተሻለ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ የመቀነስ አዝማሚያ መኖሩ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ተሣትፎ ዝቅተኛ መሆን የዘርፉ ሌላው ችግር ነው፡፡ ለዚህም የትምህርት ተሣትፎን ለማሣደግ የትምህርት አቅርቦቱን (supply) እና የትምህርት ፍላጎቱን (Demand) ማጣጣም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በክሉ በነበረው ጦርነት ምክንያት በርካታ የትምህርት ተቋማት ወድመዋል፣ ብዙ በትምህርት ገበታ ላይ የነበሩ ተማሪዎችም ከትምህርት ውጪ እንዲሆኑ ተገደዋል፡፡ ስለሆነም የወደሙ ተቋማትን በመጠገን ሥራ እንዲጀምሩ የማድረግ እንዲሁም ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ እንዲኖር መሥራት ያሰፈልጋል፡፡

## የጤናው ዘርፍ

የጤናው ዘርፍ ዋነኛው ተልዕኮ ያልተማከለ የጤና ሥርዓት በመዘርጋት፣ የህብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ፣ በሽታን በመከላከል እንዲሁም የፈውስ እና የማገገሚያ የሕክምና አቅርቦቶችን በማሳደግ እና ቁጥጥር በማድረግ ሁሉን አቀፍ የጤና ፓኬጆች እንዲተገበሩ በማድረግ የዜጎችን የጤንነት ሁኔታ ማሻሻል ላይ አተኩሮ ይሠራል ፡፡ ዜጎች ጤንነታቸው የተጠበቀ፣ ብቁ እና አምራች እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር በአገር ደረጃ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ልማት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በአለፉት የዕቅድ ዓመታት በጤናው ዘርፍ መከላከልን መሠረት ያደረገ ስትራቴጂ በመከተል አበረታች አፈፃፀም ተመዝግቧል፡፡ ጤና ለሁሉም ከማዳረስ አኳያ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ለማሳደግ እና ጥራት ያለው አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም በጤናው ዘርፍ እ.ኤ.አ በ2030 ይደረስበታል ተብሎ ከተያዘው የዘላቂ ልማት ግቦች አፈፃፀም አንፃር አዎንታዊ ለውጦች የተመዘገቡ መሆኑ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በአለፉት ዓመታት በዕቅድ አፈፃፀም ዙሪያ የተመዘገቡ ውጤቶችን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የእናቶች፣ የጨቅላ ህፃናት እና የህፃናት ጤና ለማሻሻል በተከናወኑ ሥራዎች የእናቶች ሞት ምጣኔ በ2003 ዓ.ም ከነበረበት 676/100,000 እናቶች በ2009 ዓ.ም ወደ 401/100,000 እናቶች ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ ዕድሜያቸው

ከአምስት ዓመት እና ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔ በ2008 ከነበረበት ከ85/1,000 እና ከ67/1,000 እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 59 እና 58 ዝቅ ማድረግ ተችሏል፡፡ የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ በተመለከተ በህይዎት ከተወለዱ ህፃናት መካከል በ2008 ዓ.ም 47/1000 የሞት ምጣኔ የተመዘገበ ሲሆን በ2012 ወደ 46/1000 መቀነስ ተችሏል፡፡

የመቀንጨር እና የመቀጨጭ ምጣኔን በተመለከተ በ2008 ከተደረሰበት 46 እና 10 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 41 እና 8 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ከዚህ በተጓዳኝ በቲቢ በሽታ ምክንያት የሚከሰት የሞት ምጣኔ በ2008 ከተደረሰበት 32/100,000 ህዝብ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 22/100,000 መቀነስ ተችሏል። ምንም እንኳን የወባ በሽታ ከዓመት ዓመት መቀነስ ይታይበት የነበረ ቢሆንም በ2012 በጀት ዓመት እንደገና የማገርሸት ሁኔታ በማሳየት በወባ ምክንያት የተመዘገበው የሞት መጠን በስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመኑ የመጀመርያ ዓመት ከተደረሰበት ጋር ሲነፃፀር ብዙም መሻሻል ሣያሳይ ተከናውኗል።

በአጠቃላይ በአለፉት የዕቅድ ትግበራ ዓመታት በጤናው ዘርፍ በተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራት የዜጎች አማካይ በህይዎት የመኖር የዕድሜ ጣሪያ በ2005 ከነበረበት 56 ዓመት በ2008 ወደ 65.5 ዓመት አድጓል፡፡

**ማነቆዎች**

ከእርግዝና እና ወሊድ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የእናቶች ሞት ለመቀነስ ጥረት ተደረገ ቢሆንም አጥጋቢ ለውጥ ያልታየበት ነው፡፡ በመሆኑም የእናቶችን ሞት ከመቀነስ አኳያ የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ጥራትን የበለጠ ማሻሻል እና የእናቶችን ጤና ማረጋገጥ በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት ይሻል። ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት የሞት ምጣኔ አበረታች በሆነ መልኩ የቀነሰ ቢሆንም ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ሕፃናት መከላከል በሚቻሉ የጤና ችግሮች በየዓመቱ እንደሚሞቱ ጥናቶች ያሳያሉ። ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው የህጻናት እና ጨቅላ ህጻናት ሞት መከላከል እና መታከም በሚችሉ ችግሮች ምክንያት የሚከሰት ነው። ከእነዚህ በተጨማሪ ለሕፃናት ሞት መንስዔ ከሆኑት መካከል የድንገተኛ አደጋዎች፣ ኩፍኝ እና ወባ በ7.1 በመቶ፣ 4.6 በመቶ እና ለ0.8 በመቶ ሞት እንደ ቅደምተከተላቸው ይገኛሉ። የተመጣጠነ ምግብ እጥረት 50 በመቶ ለሚሆኑ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ሞት መንስዔ መሆኑ ታይቷል፡፡

ለጨቅላ ህፃናት ሞት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ከሚያደርጉ ተግዳሮቶች መካከል ፍትሐዊ ያልሆነ የጤና ሀብት ሥርጭት፣ ጥራቱ የተጓደለ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ በህብረተሰቡ የሚታየው የህፃናት ጤና ክብካቤ ልማድ አነስተኛ መሆን፣ የካንጋሮ ማዘር ኬር (KMC) አገልግሎቶች ሽፋን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት እና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ አስፈላጊ የሆኑ የጤና ግብዓቶች እና መሣሪያዎች እጥረት ተጠቃሽ ናቸው።

በጤና ዘርፍ በብዙ መልኩ እየተሻሻሉ ያሉ የፕሮግራም እና የአገልግሎት አሰጣጥ ቢኖሩም በንፁህ ውኃ እና በግል እና በአካባቢ ንፅህና ጉድለት፣ የአልኮል መጠጥ፣ የስኳር እና ከአመጋገብ ሥርዓት ጋር ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች መንስዔ የሚከሰት በሽታ እና ሞት አሁንም ችግር እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሥራ ላይ የሚያጋጥም አደጋ እና ከፍተኛ የሆነ የደም ግፊት ካለፉት አሥር ዓመታት ወዲህ ጭማሪ እያሳየ መጥቷል፡፡ ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገራት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነ አጣዳፊ እና ሥር የሰደደ የተመጣጠነ ምግብ እና ጠቃሚ የሆኑ ንጥረ ነገሮች እጥረት ካለባቸው አገራት ውስጥ በቀዳሚነት ተጠቃሽ ናት፡፡

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቀድሞ ያለ ዕድሜ ጣሪያ ለሚከሰት ሞት የሚያደርጉት አስተዋጽዖ እየጨመረ መምጣት እና በጤና ዕክል ምክንያት ለሚከሰት የአካል ጉዳት ዋና መንስዔዎች እየሆኑ ይገኛሉ። እንደ እ.ኤ.አ በ2016 በተጠናው ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰቱ የአካል ጉዳቶች 43.5 በመቶ እና

ሞት 8.5 በመቶ ነው። ይህ መረጃ የሚያሳየው ከጠቅላላው በአካል ጉዳት ምክንያት በህይዎት ዘመን የመኖር ዕድል መቀነስ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የሚከሰቱት 46.1 በመቶ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። በአገራችን ከ60 በመቶ በላይ በአካል ጉዳት ምክንያት በህይዎት የመኖር ዕድል መቀነስ የሚከሰተው ዕድሜያቸው ከ40 ዓመት በታች በሆኑት አምራች የህብረተሰብ ክፍል ነው። በመሆኑም በቀጣይ ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተግባራዊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የጤና አገልግሎት ሽፋን በተለይም የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት፣ የቤተሰብ ጤና፣ የእናቶች ጤና እና የክትባት አገልግሎቶች እና ሌሎች የፕሮግራም ሽፋን ላይ ተመሳሳይ ለውጦች ተስተውለዋል። ሁሉን አቀፍ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋን ለማምጣት በርካታ ለውጦች እና መሻሻሎች የታዩ ቢሆኑም የመሠረታዊ ጤና ክብካቤ ተቋማት በተመለከተ እንደ ውኃ፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴክኖሎጂ ተደራሽነት፣ የተግባቦት መሣሪያዎች እና የሳኒቴሽን መጠቀሚያዎች የመሳሰሉት ከመሠረታዊ መገልገያዎች (amenities) እንዲሁም የጤና ሴክተር መዋቅር አዳዲስ አሠራሮችን መሸከም የማይችል መሆኑ ከሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ውስጥ ይገኛሉ።

የዘላቂ የልማት ግቦችን ከማሳካት አንፃር የዓለም የጤና ድርጅት ካስቀመጠው የባለሙያ ከህዝብ ጋር ያለው ጥምርታ 4.5/1000 ነው። ይህ ጥምርታ ከክልላችን አንፃር ሲታይ 0.96/1000 በመሆኑ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል። ይህንን ከፍተኛ የሆነ ክፍተት ማጥበብ የሚቻለው የጤና ባለሙያዎችን ቁጥር በማሳደግ፣ አቅማቸውን የማጎልበት ሥራ በማከናወን እና የባለሙያ ሥምሪቱን በማሻሻል በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

ማህበረሰቡ መሠረታዊ የጤና ፍላጎቱን ማሟላት እንዳይችል ከሚገድቡት ተግዳሮቾች መካከል በገንዘብ እጥረት ምክንያት የጤና ውጪን መሸፈን አለመቻል ዋነኛው ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 36 በመቶ የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት እያስፈለጋቸው የጤና አገልግሎት ያላገኙት በገንዘብ እጥረት መሆኑን ተጠቅሷል። የድሀ ድሀዎችም በአንጻራዊነት በከፍተኛ ሁኔታ ለችግር እንደተጋለጡ ያሳያል። በመሆኑም የጤና ውጪ መሸፈንና ህክምና ማግኘት ላልቻሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር በትኩረት የሚከናወን ይሆናል።

የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም አሁንም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። በወረዳ ደረጃ ያለው የሰው ኃይል ውስንነት፣ የዘርፈ ብዙ ትብብር ደካማነት በተለይም በWASH intervention እንዲሁም የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ሽፋን በሚፈለገው መልኩ ተደራሽ አለመሆን እና የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ ለወረዳ ትራንስፎርሜሽን አለመሳካት ዋነኞቹ ተግዳሮቶች ናቸው። በመሆኑም ሁሉም ወረዳዎች አገልግሎቱን እንዲጀምሩ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ርብርብ እና የአመራር ትኩረት የሚሻ ነው።

በአጠቃላይ በጤናው ዘርፍ የክልሉን ህዝብ የጤንነት ደረጃ ለማሻሻል መንግስት ጤና ለሁለንተናዊ የልማት ዕድገት ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ መከላከልን መሠረት አድርጎ የተቀረፀውን የጤና ፖሊሲ ለተግባራዊነቱ በመረባረብ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ተደርጓል። ሆኖም ግን ክልሉ በወሊድና ከወሊድ ጋር በተያያዙ የጤና ችግሮች የእናቶችና የህፃናት ሞት በሚፈለገው ደረጃ ያልቀነሰበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም የጤና ተቋማት ተደራሽነት በክልሉ እያደገ የመጣ ቢሆንም የሚቀር ሥራ ያለው መሆኑን ነባራዊ ሁኔታዎች ያሣያሉ። በዚህም መሠረት የክልሉ መንግስት በገጠሩ ህብረተሰብ ዘንድ የመሠረተ ጤና ክብካቤ ማስፋፋት አስፈላጊነትን በመገንዘብ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተዘርግቶ እየተተገበረ ቢገኝም ሁሉም ፓኬጆች በተሟላ መልኩ ተግባራዊ አለማድረግና አፈፃፀሙም ከዓመት ዓመት ወደኋላ እየተመለሰ መሆኑ በጤና ልማት ሥራዎች ላይ አሉታዊ ውጤቶች እንዲመዘገቡ እያደረገ ይገኛል። በአጠቃላይ ሲታይ የክልሉ የጤና አገልግሎት ሽፋን ያለበት ደረጃ ዝቅተኛ ከሚባሉት

ክልሎች የሚያስመድበው እንደሆነና ከአገልግሎት ጥራትም አኳያ የህክምና መሣሪያዎች እንዲሁም የግብዓት ወይም መድኃኒት አለመሟላት መሠረታዊ ማነቆዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን ውጤታማ የማድረግና የወረዳ ጤና ትራንስፎርሜሽን አጀንዳዎችን ሙሉ በሙሉ በመተግበር ክልሉ በጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት ደረጃውን ከፍ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## ስፖርት ልማት

ስፖርቱ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው የማህብረሰቡን እንቅስቃሴዎች በማጠናከር እና በማስተሳሰር፣ የህዝባዊ አደረጃጀቱን በመጠቀም፣ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን በመተግበር የስፖርቱን ልማት በማጠናከርና አገርን የሚወክሉ ኤሊት አትሌቶችን በማፍራት ረገድ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በስፖርቱ ዘርፍ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ ለስፖርት ልማት የሀብት ማሰባሰብ ውስንነት፣ የፋሲሊቲዎች በየደረጃው አለማሟላት፣ ስፖርታዊ ውድድሮችን እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን በሚጠበቀውና በሚፈለገው ደረጃ በመተግበር ረገድ ውስንነቶች መኖር እንዲሁም ኤሊት ስፖርተኞችን በማፍራት በኩል ጉድለቶች የነበሩ በመሆኑ እነዚህን ጉድለቶች ለመሙላትና ስፖርቱ ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ለማድረግ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ህዝባዊ አደረጃጀቶችንና የማህብረሰቡን አቅም አሟጦ በመጠቀም የስፖርቱን ልማት በማስፋፋት የአገር ኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነቶችን ማሳደግ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጣቸው ሥራዎች ይሆናሉ፡፡

በስፖርት ፖሊሲው የተቀመጠውን አቅጣጫ መነሻ በማድረግ በአለፉት 10 ዓመታት የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በዘርፉ ውስን የነበረውን የባለሀብት ቁጥር በማሳደግ በአሁኑ ወቅት 409 ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደው በዘርፉ ብር 467.21 ሚሊየን የካፒታል መጠን ኢንቨስት በማድረግ ለዘርፉ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች ስታንዳርድ እና የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅቶላቸው በአገር ውስጥ እንዲመረቱ እንዲሁም ከውጪ እንዲገቡ በተፈጠሩት ምቹ ሁኔታዎች በአለፉት ዓመታት 804 ባለሀብቶች የስፖርት ትጥቅና መሣሪያዎችን በማቅረብ የስፖርቱን ልማት በማጠናከር ተሳትፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአፈፃፀም ግምገማዎች እንደታየው በዘርፉ የግል ባለሀብቱን ለመሳብ የሚያስችሉ ግንዛቤ ፈጠራ እና የማበረታቻ ሥርዓቶች ባለመኖራቸው ስፖርቱን ወደ ንግድ ሥራ ቀይሮ አትራፊ ለማደረግ የተከናወነው ሥራ ዝቅተኛ ነበር፡፡ ስለሆነም በቀጣይ 10 ዓመታት ለባለሀብቶች በስፖርቱ ዘርፍ የሚሰማሩባቸውን የሥራ መስኮች በመለየትና ደረጃ በመስጠት፣ የስፖርት ኢንቨስትመንቱ የሚጠይቀውን ማበረታቻዎች በማመቻቸት እና እንደ ሌሎች ልማቶች ሁሉ የብድር አቅርቦት የሚያገኙበትን ሥርዓት በመዘርጋት ባለሀብቶች በስፖርት ኢንቪስትመንት እንዲሳተፉ በማድረግ ስፖርቱ ለክልሉ ብሎም ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና ማሠልጠኛ ማዕከላትን በሚመለከት የተከናወነው ሥራ አበረታች ቢሆንም በየስፖርት ዓይነቱ በመኖሪያ አካባቢዎች፣ በፋብሪካዎችና በትምህርት ቤቶች የሚገኙ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ከክልሉ የህዝብ ቁጥር አንፃር ቁጥራቸው አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር በበቂ ሁኔታ ለህብረተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ተደራሽ መሆን እንዳልቻሉ ታይቷል፡፡ የሚገነቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና ማሠልጠኛ ማዕከላት አካል ጉዳተኞችን እና ዕድሜን ታሳቢ ያላደረጉ እና ስታንዳርዶችን ጠብቀው ከመገንባት አንፃር ክፍተቶች የተስተዋሉባቸው ናቸው፡፡ ከዚህም ባሻገር ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ትጥቅ እና ቁሳቁሶች በሚፈለገው መጠን እና ዓይነት ያለመኖር እንዲሁም በዘርፉ የሚሳተፉ የግል ባለሀብቶች ቁጥር ዝቅተኛ መሆን በስፖርቱ ዘርፍ የተስተዋሉ ክፍተቶች ሆነዋል፡፡ በቀጣይ እነዚህን ዘርፈ ብዙ ክፍተቶችን እና ማነቆዎችን ለማስወገድ ሁሉን አቀፍ ቅንጅታዊ አሠራሮችን መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ በአለፉት ዓመታት በስፖርቱ ዘርፍ በርካታ የልማት

ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ በማጠናከር የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማስወገድ ስፖርቱ ለማህበራዊ ልማት፣ ለክልል እና ለአገር ብልፅግና ካለው ጉልህ ሚና በመነሳት የስፖርት ሪፎርም ፕሮግራሞችን ተግባር ላይ በማዋል የሴክተሩን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችንና ሥልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

### በዘርፉ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ለወጣቶች በቂና ተደራሽ ያለመሆን እና ያሉትም ቢሆኑ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ለወጣቶች አገልግሎት በመሰጠት በኩል ሰፊ ውስንነት ያለባቸው መሆኑ፣ ስፖርቱን ህዝባዊ መሠረት ለማስያዝ የሀብት ምንጮችን አሟጦ በመጠቀም እና በተለይ ከከተሞች፣ ከነጋዴዎችና ከመንግስት ሠራተኞች ሀብት መሰብሰብ አለመቻሉ (በአርሶ አደር ብቻ መሰብሰብ መቻሉ)፣ የታዳጊ ወጣቶች የሥልጠና ፕሮጀክት በሚፈለገው ደረጃ እየተፈጸመ አለመሆኑ፣ ክልሉን የሚወክሉ ብሎም በአገር ደረጃ አትሌት ማስመረጥ የሚችሉ ክለቦችን ከማደራጀት እና ከማጠናከር ይልቅ የልማት ድርጅቶች ይዘዋቸው የነበሩ ክለቦችን የማፍረስ፣ ከባህርዳር ዓለም አቀፍ ስታዲየም ባሻገር በዞኖችና በወረዳዎች ደረጃቸውን የጠበቁ የማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማስፋፋት ውስንነቶች መኖር፣ በስፖርት ኢንቨስትመንት ባለሀብቱን በማሳተፍ ረገድ ሰፊ ክፍተት መኖሩ፣ የሰው ሀብቱን በማልማት ረገድ በተለይ በታችኛው እርከን በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ ቅንጅታዊ አሠራር እና የአጋርነት መንፈስ በሚፈለገው ደረጃ የጎለበቱ አለመሆን እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ያለመኖር በዘርፉ የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱ ተግዳሮቶችን ሙሉ በሙሉ በመቅረፍ በዘርፉ የተቀመጠውን ዕቅድ ማሳካት ተገቢ ይሆናል፡፡

### የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ

በአለፉት ዓመታት የመንግስትን ዘርፍ የማስፈጸም አቅም ለማጎልበት የተለያዩ የለውጥ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ለአብነት ያህል በዕቅድ ዘመኑ ቀልጣፋና ውጤታማ የመንግስት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በተለያዩ ጊዜያት የአደረጃጀት ለውጦች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን የዜጎችን ያደገ ፍላጎት ለማስተናገድ የሚችሉና ከወቅታዊ ተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ ነባር አደረጃጀቶችን በማሻሻልና በአዲስ መልኩ እንዲቋቋሙ የተፈቀዱ አደረጃጀቶችን በመገምገም የማጽደቅ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በተጨማሪም ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ መርህን ተግባራዊ ለማድረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ሲጠናቀቅ የሠራተኛ ድልድል ተካሂዷል፡፡ በተለይ ቀደም ሲል በክልላችን የነበረው የሥራ ደረጃ ዝቅ ያለ በመሆኑ ከሌሎች ክልሎች ጋር በማነፃፀር የደረጃ ማሻሻያ በማድረግ በጠቅላላ 56,589 (ወንድ 28,612፣ ሴት 27,977) ሠራተኞች የሚያስፈልግ በጀት በክልሉ መንግስት ተፈቅዶ የአሥር ወራት የኋላ ክፍያ ብር 464,787,169 እንዲከፈል በመደረጉ የሥራ መደቦች ከአገራዊው የሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት አኳያ ወጥ እንዲሆኑ ዕድል ፈጥሯል፡፡ የህግ ማዕቀፎች ማለትም የሰው ሀብት አስተዳደሩን የሚመለከቱ አዋጅ፣ ደንብና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ወጥተው እንዲተገበሩ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ በህዝብ አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ደረጃውን የጠበቀ ሙያዊ አገልግሎት በመስጠት ዙሪያ ሰፊ ክፍተቶች ይታዩባቸዋል፡፡

በተመሳሳይ በህዝብ አገልግሎት ዘርፉ ዜጎችን ለማገልገል የተመደበውን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ያለማዋልና ሀብትን የማባከን ችግሮች ተከስተዋል፡፡ በዘርፉ የሰው ሀብት ልማትን ከውጤት ጋር አስተሳስሮ ለመምራት የሚያስችል የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲ አለመኖሩ ችግሩን የባሰ ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የመንግስት ዘርፍም በተሟላ ሁኔታ በአገልጋይነት መንፈስ የተሞላ ቀልጣፋ አገልግሎት ለህብረተሰቡ ማቅረብ ባለመቻሉ ክልላዊ የመልካም አስተዳደር ችግር ፈጥሯል፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ያለው ሠራተኛ በከፊል የብቃት ክፍተት ያለበትና በቂ ክፍያና ማበረታቻ የሌለው በመሆኑ የመፈጸም አቅሙ ክፍተት ሥር የሰደደ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በተጨማሪም የልማት ዕቅዶችን ከማሳካት አንፃር የተሟላ የአገልጋይነት ስሜት ለመያዝና የለውጥ ሥራዎችን ለመተግበር በቁርጠኝነት እንዳይንቀሳቀስ አድርጎታል። በአጠቃላይ የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር ፖሊሲ ባለመኖሩ በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከመፍጠሩ በተጨማሪ የሰው ኃይል ዕቅድ፣ ምልመላና መረጣ፣ የሰው ኃይል ልማት፣ የጥቅማ ጥቅምና ማበረታቻ ሥርዓት፣ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት፣ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓት፣ የሰው ኃይል መረጃ ሥርዓት፣ ጥናትና ምርምር እና ሌሎች ተግባራት ከመሠረታዊ የኢኮኖሚ አቅም በመነሳት በተቀናጀ አግባብ የመከታተል፣ የመደገፍ፣ የመያዝ (Retention) እና አልምቶ የመጠቀም (Utilization) ልምዱ አለመዳበር በቀጣይ ትኩረት የሚያሻቸው ተግዳሮቶች ናቸው።

**የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስናን** በተመለከተ በአለፉት ዓመታት ያለድካም የራስ ያልሆነውን የህዝብና የክልል ሀብት በመዝረፍ በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚደረጉ ሩጫዎች ከመቀነስ ይልቅ የዝርፊያ ዘዴዎችን በመንደፍ ጭምር እየተበራከቱ ይገኛሉ። ሚዲያዎች በህዝብ አገልግሎት ላይ እንግልት የሚያደርሱ እንዲሁም በአቋራጭ ለመበልፀግ የህዝብና የክልል ሀብትና ንብረት የሚዘርፉ አመራር እና ሠራተኞችን አነፍንፎ የማጋለጥ እንዲሁም ዜጋው ከሌብነት ይልቅ በሥራ ለመበልፀግ ጥረት እንዲያደርግ ሥነምግባርን በማስተማር ረገድ የጎላ ሚና እንዲኖረው ይጠበቃል። በዚህ ዙሪያ ያሉ አደረጃጀቶች በተቋማት ውስጥ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርቶችን ሰጥተዋል፣ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ተከላክለዋል። ሆኖም በሁሉም ተቋማት የተሟላ አደረጃጀት በመፍጠር የሥራ ክፍሉ ለፀረ ሙስና ትግል ሊሰጥ የሚገባውን አስተዋጽዖ አቅምን አሟጦ የመጠቀም ሥራ በአግባቡ አለማከናዎን የሚታዩ ክፍተቶች ናቸው። እነዚህ በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት ትኩረት ተሰጥቷቸው በተለየ አመራር ሊፈቱ ይገባል።

### 3.2.4. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈፃፀም ግምገማ

**ሴቶች እና ህፃናትን በሚመለከት** በክልላችን ሴቶች በአማካይ በቀን ከ14 እስከ 17 ሠዓት በሥራ ላይ እንደሚያሳልፉ መረጃዎች ቢያመላክቱም በነበረው ጐታችና ኋላቀር አመለካከት የተነሳ ሴቶች በቤተሰብ ደረጃም ሆነ በህብረተሰብ ውስጥ የጐላ ሚና እንደሌላቸው ተደርጐ ሲታሰብ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በሥርዓተ ፆታ ፅንስ ሀሳብ መሠረት ሴቶች በአገራችን ብሎም በክልላችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ሰፊ አስተዋጽዖ እንዳላቸው የሚያሳይ ሲሆን እነዚህም የማምረት ሥራ፣ ትውልድ እንዲቀጥል የማድረግ ሚና እና በማህበራዊ ግንኙነቶች የመሳተፍ ሚና ናቸው። ስለሆነም ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ሆነው በተለያዩ የማምረት ሥራዎች በመሳተፍ፣ ወልዶ በማሳደግ እና በመንከባከብ ትውልድን እንዲቀጥል በማስቻል እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግባትራን በማከናወን ለልማቱ እያደረጉት ያለው አስተዋጽዖ ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባ ነው።

የመሬት ተጠቃሚነት መብትን ከማረጋገጥ አንፃር በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ለ1,067,493 ሴቶች (384,461 እማዎራ እና 683,032 ባለትዳር) የመጀመሪያ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸው ሲሆን 1,258,386 (395,540 እማዎራ እና 862,846 ባለትዳር) ሴቶች ደግሞ የመሬት ባለቤት እና ተጠቃሚ ለማድረግ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ተደርጓል። ይህም ከጠቅላላ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ካገኙት የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የሴቶች ድርሻ 23 በመቶ ነበር። በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና በፓኬጅ ዙሪያ ግንዛቤ ካገኙት ውስጥ 8,364,834 (2,445,276 እማዎራ፣ 5,919,558 ባለትዳር) ሴቶች የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ የሆኑ ሲሆን 912,829 እማዎራ ሴቶች ደግሞ በሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ 2,608,299 (660,275 እማዎራ፣ 1,948,024 ባለትዳር ሴቶች) በመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት እንዲሁም 4,149,837 (1,490,801 እማዎራ፣ 2,659,036 ባለትዳር ሴቶች) በተለያዩ የእንስሳት ሀብት ልማት ፓኬጆች በማሳተፍ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በአጠቃላይ የሴቶች የመሬት ባለቤትነት እያደገ የመጣ ቢሆንም የመሬትን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ተግባራት አፈጻጸም ግን ዝቅተኛ ነው፡፡ በግብርና ከሴቶች ተጠቃሚነት አንፃር መታየት ያለበት ሌላው ችግር እማዎራ ሴቶች መሬታቸውን በአነስተኛ ዋጋ በማከራየት ከመሬታቸው ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም አለማግኘት፣ በቂ የኤክስቴንሽን ድጋፍ አገልግሎት በተለይ ለባለትዳር ሴቶች ያለመስጠት ችግሮች ሲሆኑ በቀጣይ መፈታት ያለባቸው ናቸው፡፡

የሴቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከሚረጋገጥባቸው ዘርፎች አንዱ ጥቃቅንና አነስተኛ በመሆኑ የመሥሪያና መሸጫ በታዎች አቅርቦት፣ የገበያ ትስስር፣ የሥልጠና፣ የብድር፣ የግብዓትና የቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ የንግድ አዋጭነት ጥናትና የልምድ ልውውጥ ድጋፎች በማድረግ በአለፉት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዓመታት 2,541,452 ሴቶች በጥቃቅን እና አነስተኛ ዘርፎች ተሰማርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ግንዛቤ በመፍጠር 1,822,053 ሴቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አፈፃፀሙም 31.11 በመቶ ሆኗል፡፡ ይህ አፈፃጸም ከዕቅዱ አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር በ2002 ከነበረው 36 በመቶ አፈጻጸም የወረደ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ በየደረጃው ከሚገኝ የሚመለከተው አካላት ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ በዘርፉ ለተሰማሩ 166,038 /27.8 በመቶ አንቀሳቃሾች የመሥሪያና መሸጫ ቦታ የተሰጠ ሲሆን ለ444,347 /52 በመቶ/ ሴቶች ደግሞ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ እየተሰራ ያለው ሥራም ቢሆን ገና ብዙ የሚቀረው በመሆኑ በቀጣይ ዓመታት በልዩ ትኩረት ሊታይ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ-19 ቫይረስ በሀገራችንም ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው የተዳከመ በመሆኑ እንደ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ሁሉ በጥቃቅንና አነስተኛ የሥራ ዘርፎች ለተሰማሩ ሴቶች የራሱን ተጽዕኖ ያሳደረ ከመሆኑም ባሻገር በክልሉ በነበረው የትግራይ ወረራ እና ጦርነት የጥቃት በትሩን ካሳረፈባቸው ተቋማት መካከል የአነስተኛና ጥቃቅን የማምረቻና የመሸጫ ሼዶች በመሆናቸው በርካታ ሴቶች ሥራቸውን እንዲያቆሙ የተገደዱ ሲሆን በአንፃራዊነት ወረራው ባልተፈጸመባቸው አካባቢዎችም ቢሆን ክልሉ በህልውና ዘመቻ ውስጥ የነበረ በመሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው የተዳከመ መሆኑ ታይቷል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሴቶች በህብረት ሥራ ማህበራት መደራጀታቸው የገቢ አቅማቸውን ለማሳደግ የሚኖረው አስተዋጽዖ ከፍተኛ በመሆኑ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ በአለፉት ዓመታት የተሰራ ሲሆን የሴቶች የአባልነት ድርሻ በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት 19.2 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 26 በመቶ ደርሷል፡፡ በሌላ በኩል የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት 8.1 ሚሊየን ሴቶች ብር 11.2 ቢሊየን እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ የሴቶች የቁጠባ ተጠቃሚነት ድርሻም 72 በመቶ ሆኗል፡፡ ከብድር አኳያም 5.9 ሚሊየን ሴቶች የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በአለፉት ዓመታት በተከናወኑ ሥራዎች የሴቶች የቁጠባ ባህል፣ የብድር ተጠቃሚነታቸው እና የወሰዱትን ብድር በአግባቡ ተጠቅመው በወቅቱ የመመለስ ልምዳቸው እያደገ በመምጣቱ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ አበረታች እና ተስፋ ሰጪ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በሴቶች የብድር ተጠቃሚነት ዙሪያ የሚታዩ ዋና ዋና ችግሮች መካከል ሴቶች በቆጠቡት ልክ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸው፣ የወሰዱትን ብድር በትክክል ወጤታማ በሆነ መልኩ ስለመጠቀማቸው የተጠናከረ ክትትል እና ድጋፍ አለማድረግ፣ አበረታች የሆነ የወለድ ሥርዓት እና አማራጭ የብድር አገልግሎት ሥርዓት አለመኖር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በቀጣይ ይህን ለማስተካከል ሰፊ ጥረት ማድረግ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥም የሴቶችን የሥራ ዕድል ለማስፋት በሚደረገው ጥረት በ2002 በጀት ዓመት ከነበረበት አጠቃላይ 36.8 በመቶ የሴቶች ተሳትፎ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ወደ 41.3 በመቶ

ለማሳደግ ተችሏል። በዚህ ዘርፍ ያለው የተሳትፎ ምጣኔ ዕድገት ያሳየ ቢሆንም አሁንም አብዛኛው ሴቶች በዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ መደቦች ላይ ተመድበው የሚሰሩ ናቸው። ይህን ችግር ለመፍታት የሴቶችን የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል የረጅምና የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎች መስጠት እንዲሁም የቅጥር፣ የዝውውር፣ የደረጃ ዕድገትና የልዩ ድጋፍ ርምጃ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። ይሁን እንጅ አሁንም በአስፈጻሚ አካላት በኩል ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ የአመለካከትና የተግባር ችግሮች ያሉ ሲሆን ራሳቸው ሴቶችም ቢሆኑ ችግሩን ታግለው መብቶቻቸውን በማረጋገጥ በኩል ሰፋ ያሉ ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል። በመሆኑም በቀጣይ ዓመታት ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እና የኃይል ጥቃቶችን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በድግግሞሽ ለ13 ሚሊየን የህበረተሰብ ክፍሎች በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና የኃይል ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል። በሌላ በኩል በEDHS 2016 ጥናት መሠረት የልጅነት ጋብቻ 42.9 በመቶ እና የሴት ልጅ ግርዛት /ከ0-14 የዕድሜ ክልል/ 34.8 በመቶ መሆኑን ያሳያል። በሌላ በኩል የኮረና ቫይረስ መከሰቱን ተከትሎ የትምህርት ተቋማት ዝግ በመደረጋቸውና በሌሎች ምክንያቶች ያለዕድሜ የልጅነት ጋብቻ፣ አስገድዶ መድፈር፣ የኃይል ጥቃት በሴቶች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ሲሆኑ አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ክልሉን በኃይል ወሮ በቆየባቸው ወቅቶች ቢያንስ በ1,797 ሴቶች ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽሟል። የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከተፈፀመባቸው ሴቶች መካከል 16 የሚሆኑት የኤች.አይ.ቪ ኤድስ ምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ፣ 40 ሴቶች እርግዝና አጋጥሟቸው የጽንስ ማቋረጥ ያደረጉ እንዲሁም 25 ሴቶች ለአባለዘር በሽታ እንደተጋለጡ መረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ በተጨማሪም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከተፈጸመባቸው ሴቶች መካከል 1,328 የሚሆኑት የሥነልቦና፣ 969 የህክምና፣ 90 የህግ አገልግሎት እና 920 ሴቶች ብር 7,955,900 ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል።

የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በተወሰዱ ርምጃዎች እጅግ በጣም ዝቅተኛ የነበረው የምክር ቤት አባልነት ተሳትፎ ከፍተኛ የሆነ ዕድገት በማሳየት በክልል ምክር ቤት 47.27 በመቶ፣ በተወካዮች ምክር ቤት 41 በመቶ፣ በብሔረሰብ አስተዳደር ምክር ቤቶች 40.63 በመቶ፣ በወረዳ ምክር ቤቶች 47.5 በመቶ እና በቀበሌ ምክር ቤት 41.34 በመቶ ደርሷል። ይህም በቀጣይ ዓመታትም በተሻለ ሁኔታ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

በአስፈጻሚው አካል የአመራር ሰጭነት ቦታ ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። በተለይም በትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓቱ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳድግ የልዩ ድጋፍ ርምጃዎችን በመውሰድ፣ በተለያዩ የአመራር እርከኖች በመመደብ የመሪነት ልምድ በተግባር እንዲያዳብሩ በማድረግ የተሳትፎ መጠኑ በወረዳ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 20.2 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 22.9 በመቶ፣ በዞን በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 11 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 20 በመቶ እና በክልል በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 10.8 በመቶ በ2012 በጀት ዓመት ወደ 21.3 በመቶ ደርሷል። በዚህ ረገድ ተሳትፎውን ለማሳደግ የተደረገው ጥረት ያመጣው ውጤት መሻሻሎች ቢያሳይም ገና ወደፊት ብዙ መሥራት የሚጠይቅ ነው። በሜሪት ከሚያዙ የአመራር ቦታዎች ላይ ያሉ የሴቶች ቁጥርም በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,309 በ2012 በጀት ዓመት ወደ 4,327 የደረሰ ሲሆን የሴቶች ድርሻ 23.4 በመቶ ነው። በተመሳሳይ በ2012 በጀት ዓመት በክልችን ሴቶች በህግ ተርጓሚነት ያላቸው ተሳትፎ በዳኛነት ሲታይ በወረዳ 25.9 በመቶ፣ በዞን 25.9 በመቶ እንዲሁም በክልል 22.8 በመቶ ደርሷል። በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ ሴቶች በአስፈፃሚ፣ በህግ አውጭና ተርጓሚ ደረጃ ያላቸው የአመራርነት ድርሻ እንዲያድግ በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የሚያሻው ጉዳይ ነው።

ከህጻናት አኳያ በአብክመ ሴቶች ህፃናት እና ወጣቶች ቢሮ በ2010 በጀት ዓመት በተጠናው ጥናት መሠረት ማህበረሰቡ ስለ ህፃናት ጉልበት በዝብዛ ያለው ግንዛቤ 66.9 በመቶ፣ በህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ያለው የአመለካከት

ደረጃ 51.7 በመቶ እንዲሁም ድርጊቱን የመፈፀም ደረጃ 55.7 በመቶ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ስለሆነም በህፃናት ላይ የሚፈፀመው የጉልበት ብዝበዛ እንዲቀንስ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል፡፡

ህጻናት እንደ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጉዳዮቻቸውን እና ሀሳቦቻቸውን በነፃ ነት የመግለጽ፣ በማህበር የመደራጀት፣ የመሰብሰብና በማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ምንም ዓይነት ልዩነት እና መድልዎ ሳይፈጸምባቸው የመብቶቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በህገ መንግስቱ በማረጋገጥ እና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን፣ አህጉራዊ የህጻናት መብቶችን እና የደህንነት ቻርተሮችን ተግባራዊ በማድረግ የህጻናትን መብት እና ደህንነት ለመጠበቅ እና ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ ህጻናት የዴሞክራሲ ሥርዓት ሂደትን እንዲለማመዱና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ተቀርጸው እንዲያድጉ ለማድረግ የህጻናት ፓርላማ ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ በአለፉት ሁለት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በክልል 1፣ በብሔረሰብ አስተዳደር ዞን 3፣ በ183 ወረዳዎች እና በ2,920 ቀበሌዎች የህጻናት ፓርላማ በማቋቋማና 1,172 ፓርላማዎችን በገንዘብ እንዲሁም 1,356 ፓርላማዎችን በቁሳቁስ በመደገፍና በማጠናከር ወደ ተግባር ገብተዋል፡፡ በዚህም በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች 9,612 የህፃናት ፓርላማ አመራሮች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ የህፃናት ተሳትፎ አሁን ያለበት ደረጃ በሁሉም አካባቢዎች ማለትም በገጠርና በከተማ፣ በፆታ፣ በዕድሜ እና ልዩ ፍላጎት ሲታይ ተመጣጣኝ አለመሆኑ፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለህፃናት አደረጃጀቶች መጠናከር የሚያደርጉት ድጋፍ እንዲሁም ህብረተሰቡ ስለ ህፃናት ተሳትፎ ጠቀሜታ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ የህፃናት ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ ላለመድረሱ በክፍተት የሚታዩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ለህፃናት ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ የተዘረጉ የአደረጃጀት፣ የህግና ፖሊሲ ማዕቀፎችን እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ተጋላጭ እና በችግር ውስጥ የሚገኙ ህፃናትን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ፣ ህብረተሰቡ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህጻናትን የመደገፍና የመንከባከብ ባህሉ እያደገ በመምጣቱ የመጨረሻ አማራጭ የሚባለውን ማሳደጊያ የሚገቡ ህጻናት ቁጥርን በመቀነስ እና የውጭ አገር ጉዲፈቻን በማስቀረት ህጻናት በአካባቢያቸው ወግና ባህል ከህብረተሰባቸው ሳይርቁ እንዲያድጉ ዕድል መፍጠሩ የተገኙ ውጤቶች ሲሆኑ ለህፃናት የሚደረገው ድጋፍና እንክብካቤ በስታንዳርዱ መሠረት ደረጃውን የጠበቀ አለመሆን፣ ለህጻናት የሚሰጡ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎቶች አሁንም ሁሉም ድጋፍ ለሚፈልጉ ህጻናት ተደራሽ አለመሆን፣ ሌሎች የድጋፍና እንክብካቤ አማራጮችን አሟጦ ሳይጠቀሙ ህጻናትን ወደ ህጻናት ማሳደጊያ እና ማቆያዎች ለማስገባት አዝማሚያዎች መኖር፣ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ የተሀድሶ አገልግሎት ማዕከላት አለመኖር፣ በጎዳና ላይ ያሉ ህፃናትን ወደ ቤተሰባቸው የማዋሀድና የማቀላቀል ሂደት መሠረታዊ ችግሩን ለመቅረፍ በሚያስችል ሁኔታ አለመከናወኑ፣ የቅንጅትና ትብብር አሠራር በሚፈለገው ልክ አለመጎልበቱ እንዲሁም የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ የሚሉ ዋና ዋና ችግሮች በመሆናቸው በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡

ከአረጋዊያን አኳያ እንደ ማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል መብታቸውን ለማስጠበቅ አረጋዊያን በተናጥል ሳይሆን በተለያዩ አደረጃጀቶች መደራጀት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ በአለፉት ሁለት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት 52,637 (ወንድ 27,347፣ ሴት 25,290) አባላት ያሏቸው 417 ማህበራት በማቋቋም እና ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ በየደረጃው የሚገኙ የአረጋውያን ማህበራትን ውጤታማ እንዲሆኑ የማስቻል ሥራ የተቆራረጠ እና በሚፈለገው ደረጃ በማህበራቱ ላይ ውጤት ማምጣት ያላስቻለ በመሆኑ ማህበራቱ ለአባላቶቻቸው መብት መከበር በሚፈለገው ልክ ሚናቸውን አልተወጡም፡፡ የአረጋዊያን የመብት

ጥሰትን ከመከላከል አኳያ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት በመስጠት በኩል ሰፊ ክፍተት በመኖሩ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማዳበር ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን እና ተሳትፊነትን ማረጋገጥ በቀጣይ በትኩረት የሚተግበር ይሆናል፡፡

የአካል ጉዳተኞች እንደየ ችግሮቻቸው ዓይነት በነፃ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸውና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው እንዲሳተፉና ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በተለያዩ አደረጃጀቶች መደራጀት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ በአለፉት ሁለት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት 32,935 (ወንድ 18,445፣ ሴት 14,490) አባላት ያሏቸው 400 ማህበራት ለማደራጀት ጥረት ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ በዕቅድ ዘመኑ 109 ፌደሬሽኖች እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ማህበራቱም ሆኑ ፌደሬሽኖች የአባሎቻቸውን መብት እና ጥቅም ከማስከበር አንፃር የአቅም ውስንነት ያለባቸው መሆኑ እና ችግሮቻቸው በሌላ አካል እንዲፈታላቸው የመፈለግ አዝማሚያ የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ለመቀበል የፈቃደኝነት ማነስ፣ ህብረተሰቡ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ ያለው ግንዛቤ የዳበረ ባለመሆኑ የተነሣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት አለመላክ፣ መምህራኑ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች እንደ ፍላጎታቸው ለማስተማር የክህሎት ማነስ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት በተጀመረባቸው ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሙን ከሌላው መደበኛ ፕሮግራም ጋር በእኩልነት አለማየት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ግብዓቶች (ስሌት፣ ስታይለስ፣ የብሬል ወረቀት፣ ቴፕ ወዘተ) እጥረት፣ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች አስተርጓሚ አለመኖር እና ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ አለመኖር፣ በየትምህርት ቤቱ የድጋፍ መስጫ ማዕከላት በሚፈለገው መጠን አለመቋቋም፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን እጥረት፣ ትምህርት ቤቶቹ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ታሳቢ አድርገው አለመገንባታቸው እና የትምህርት አመራሩ አቅዶ ባለመሥራቱ አፈጻጸሙ የሚጠበቀውን ያህል ውጤት አለማምጣቱ የሚሉት ናቸው፡፡ ስለሆነም ችግሩን ለማቃለል የተጠናከረ ሥራ በቀጣይ ማከናወን ተገቢ ይሆናል፡፡

የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያ መንግስት በህብረተሰቡ ውስጥ የቆየውን የጠበቀ እርስ በእርስ የመደጋገፍ ባህል መልካም አጋጣሚን በመጠቀም በህዝቡ አቅም ድጋፍ የሚፈልጉ ለኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመንከባከብ እንዲቻል የማህበረሰብ ድጋፍ እና እንክብካቤ ጥምረት በህግ የተደገፈ የህብረተሰብ ተቋም ሆኖ በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ቀበሌዎች ለማቋቋም ጥረት ተደርጓል፡፡ የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረትን በህብረተሰቡ መልካም ዕሴቶች ላይ ተመስርቶ ማቋቋም ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በራሱ በህብረተሰቡ የሚመራ በመሆኑ አበረታች ውጤት እየተመዘገበበት የመጣ ሲሆን በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ መነሳሳት ፈጥሯል፡፡ ይሁን እንጂ በየደረጃው የሚገኙ የጥምረቱ ኮሚቴዎች ሥራውን በወቅቱ እየገመገሙ የመምራት ውስንነት መኖር፣ የሚሰበሰበው ሀብት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተገቢው መንገድ ተጠቃሚ አለማድረግ፣ የዕድሳት ጊዜያቸውን ጠብቀው ዕድሳት የማያደርጉ ጥምረቶች መኖራቸው፣ የሀብት ብክነት እንዳይኖር በወቅቱ ኦዲት የማያደርጉ ጥምረቶች መኖራቸው፣ በማህበረሰብ አቀፍ ጥምረቱ ላይ የምልመላ እና መረጣ ችግር መኖር እንዲሁም በየደረጃው ያለው የመንግስት አመራር ጥምረቱ ትልቅ የልማት አቅም መሆኑን በመገንዘብ ትኩረት ሰጥቶ ተገቢውን ድጋፍ እና እገዛ አለማድረግ የታዩ ዋና ዋና ችግሮች ሲሆኑ በጦርነቱ ምክንያት አብዛኛው የጥምረቶች ሥራዎች የተቀዛቀዙ በመሆናቸው በቀጣይ ለተግባሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠይቃል፡፡

የቀጥታ ድጋፍ ሴፍቲኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን በመለየት እና አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች በተቀመጠው ሥርዓት መሠረት ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ የማድረግ ችግር የተስተዋለበትና ሽፋኑ ዝቅተኛ መሆኑ ዜጎችን

ከድህነት ለማላቀቅ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣ በጎዳና ላይ የሚተዳደሩ ዜጎችን ወደ ጤናማ ማህበራዊ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ እንዲያገኙ አለማድረግ እና የትብብርና ቅንጅት አሠራሩ ያልተጠናከረ መሆኑ፣ ለአካል ጉዳተኞች የአካል ድጋፍ የሚያመርቱ የአካል ተሃድሶ ማዕከላት የእንቅስቃሴ ጉዳት ላይ ያተኩሩ መሆናቸው፣ በሙያው የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረት እንዲሁም የጥሬ ዕቃ አቅርቦት እጥረት በአጠቃላይ ማህበራዊ ችግሮችን በሚፈለገው ደረጃ መቅረፍ ያለመቻል ሁኔታዎች ታይቷል። ስለሆነም ችግሩን በዘለቄነት ለመፈታት በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ጉዳይን ከማካተት አኳያ ጉዳዩ በሁሉም ሴክተሮችና የልማት ዘርፎች ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ እንዲሰራ የተለያዩ የአሠራር ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደ ተግባር ተገብቷል። በመሆኑም የሥርዓተ-ፆታን፣ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን ጉዳይ አካቶ የመሥራት ተግባር ለተወሰነ ሰው ወይም ቡድን ብቻ የሚተው ባለመሆኑ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ተግባሩ ከፎካል ፐርሰን አሠራር ወጥቶ የአመራሩ ኃላፊነት እንዲሆን መደረጉ ለሴክተሮች የመፈጸም አቅም ማደግ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በዚህ የአካትቶ ትግበራ ጉዳይ ተቋማት በፕሮግራሞች፣ በፕሮጀክቶች እና በዕቅዶች የማካተት ልምድ እንዲሁም በሪፖርቶች ለይቶ መረጃ የመያዝ እና የማቅረብ አሠራሮች እያደጉ መጥተዋል።

በተጨማሪም የተወሰኑ ተቋማት የሥርዓተ ፆታ ኦዲት እና ትንተና ማድረግ ጀምረዋል። ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን ተቋማቱ አካቶ ለመሥራት የትኩረት ማነስና የአመለካከት ችግር መኖር፣ አንዳንድ ተቋማት አካቶ ለመሥራት ግፊት/ጉትጎታ መፈለግ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ፣ ተቋማት በምክር ቤት የሚሰጣቸውን አቅጣጫ በግብዓትነት ወስደው ተግባራዊ አለማድረግ፣ በተዋረድ የተቋማትን ክፍተት ለይቶ አቅማቸውን አለመገንባት፣ ተከታታይ እና ወቅታዊ ሥልጠና አለመስጠት፣ ለተቋማት ችግር ፈች የሆነ ድጋፍና ክትትል አለማድረግ፣ የምክክር መድረኮችን በተቀመጠው አሠራር መሠረት በመፍጠር በኩል ችግር መኖር፣ የተቋሙ አመራር የማካተት ሥራ ተቋማዊ ሆኖ እንዲሰራ በማደረግ በኩል ትኩረት ሰጥቶ እየገመገመ አለመምራት እንዲሁም ተቋማት በሥርዓተ ፆታ ኦዲት የተገኙ ግኝቶችን ተግባራዊ አለማደረግ ዋና ዋና ተጠቃሽ ችግሮች በመሆናቸው በቀጣይ ችግሮቹን ፈትቶ ለስኬት መንቀሳቀስ የሚጠበቅ ይሆናል።

### በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮች

በአለፉት ሁለት የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በዘርፉ የታዩ ተግዳሮቶች ሲዳሰሱ በህብረተሰቡ ዘንድ በሴቶች፣ በህጻናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያን እና በድህ እና ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት፣ ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በቂና ዘላቂ አለመሆናቸው፣ የሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ድሀ እና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ውክልና በዋና ዋና የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች ማነስ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና የኃይል ጥቃቶች መበራከት፣ የሴቶች የቁጠባ ባህል አለመዳበር፣ ነፃ እና ጠንካራ አደረጃጀቶች አለመፈጠራቸው፣ የህግ አፈጻጸም ክፍተት ወጥነት የሌለው እና ተደራሽ ያልሆነ መዋቅራዊ አደረጃጃት፣ ሴቶችን የመደገፍና ወደ አመራርና ወደ ውሳኔ ሰጪነት የማምጣት ችግር እና የመንግስት ተቋማት የሴቶች ህጻናት አካል ጉዳተኞች አረጋውያን እና ድሀ እና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ የዋና ሥራቸው አካል አድርገው አለመመልከት እንዲሁም የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓት በሚፈለገው ደረጃ ያልተቀናጀ እና ያላደገ መሆኑ፣ በአገራችን የሚገኙ በርካታ አካል ጉዳተኞች የሲቪል፣ የፖለቲካ፣ የባህል መብቶቻቸው በሚፈለገው ደረጃ እየተከበሩ አለመሆኑ እና በተለይም አካል ጉዳተኞች ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለመረጃ እና ለቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት እና ለሌሎች ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ዝቅተኛ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም የሚመለከታቸው ተቋማት በተሰጣቸው ተግባር እና ኃላፊነት ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ዜጎችን በተለይም አካል ጉዳተኞችንና የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ ችግር ተጋላጮችን ጉዳይ አካተው እና ለውጥ በሚያመጣ ሁኔታ ትኩረት ሰጥተው ያለመሥራታቸው፣ አገልግሎቶችን በሚፈለገው ደረጃ እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት አለመሰጠታቸው፣ በሀገራችን የማህበራዊ ዕሴቶች እየቀነሱ ማህበራዊ ችግሮች እየተባባሱ የጎዳና ተዳዳሪነት እና የወጣት ሱሰኝነት እየከፋ መምጣት፣ የሥራ ባህል በሚፈለገው ደረጃ ያልዳበረ እና በየጊዜው እየተሸረሸረ እና እየተዳከመ በመሄዱ በመንግስት የተጀመረው ድህን ማዕከል ያደረገ ፈጣን ዕድገት ዘላቂ እና አስተማማኝ ሆኖ እንዳይቀጥል የራሱን ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ እና ቤተሰብ በድህነትና ተጋላጭነት ቅነሳ ላይ እንዲሁም የማህበራዊ ችግሮች እንዳይበራከቱ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ የቤተሰብን ጉዳይ የሚከታተል እና ቤተሰባዊ ግንኙነትን የሚጎለብትበት ሁኔታ የሚመለከተው አካል ባለመኖሩ ዜጎች ለማህበራዊ ችግሮች የሚጋለጡበት ዕድል የሰፋ መሆኑ ሌሎች ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

**ከወጣቶች አኳያ** የዕምቅ አቅም ባለቤት የሆኑትን ወጣቶች በልማት፣ በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ሂደት ያላቸውን ሚና በመረዳት የክልሉ መንግስት ሰፊውን ወጣት ወደ ልማት ለማስገባት፣ የተጀመረውን አበረታች የልማት ጉዞ ዳር ለማድረስ እንዲሁም ብቁ ዜጎች ሆነው የአገር ተረካቢነት ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማድረግ እና የኢኮኖሚ ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ የተለያየ ዓለም አቀፍ የድርጊት መርሃ ግብር እና የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተርን በመቀበል እንዲሁም ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ እና የወጣቶች የዕድገትና ልማት ፓኬጅ በመቅረጽ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ወጣቶች ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል በተለየ መልኩ ባላቸው የፈጠራ አቅምና አዳዲስ ሃሳቦችንና ለውጦችን የመቀበል ችሎታ ለአንድ አገር ፖለቲካዊ መረጋጋት፣ ማህበራዊ አንድነትና የኢኮኖሚ ብልፅግና የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የአገራችን የልማት ሂደት፣ ጥልቀት እና ወሰን የሚወሰነው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶችን ዕምቅ አቅም ለመጠቀም በሚደረገው የእንክብካቤ፣ የሥምሪትና የመጠቀም ችሎታ ላይ ነው። በአለፉት 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በዘርፉ በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ለወጣቱ በቂ የሥራ ዕድል አለመፈጠሩ፣ ብቁ የሆኑ የማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም የመዝናኛ ማዕከላትና የተሣትፎ መድረኮች በበቂ ሁኔታ አለመመቻቸት፣ ሥራን የማማረጥ፣ የመንግስትን ሥራ የመጠበቅ፣ በአገር ሰርቶ ለመለወጥ ያለው ፍላጎት አናሳ መሆን በወጣቶቹ በኩል የሚስተዋሉ የአመለካከት ችግሮች ናቸው። በሌላ በኩል ወጣቶች አቅም ናቸው ብሎ መመልከት እና መጠቀም አለመቻል እንዲሁም ወጣቶችን ቀድሞ መፈረጅና ተቀራርቦ አለመሥራት ሌሎች የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው። በአጠቃላይ ለወጣቶች በሚፈለገው ሁኔታ የሥራ ዕድል መፍጠር ካልተቻለ በአገርና በክልል ደረጃ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን እያስከተለ በመሆኑ በቀጣይ ጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባዋል።

ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በመሳተፋቸው የወጣቶች አመለካከት፣ የባለቤትነት ስሜትና ተነሳሽነት እያደገ የመጣ ሲሆን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የክልሉ ባህል እየሆነ በመምጣቱ የወጣቶች ተሳትፎ ከዓመት ዓመት አድጓል። በመካሄድ ላይ ባለው የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ወጣቶች የበኩላቸውን ሚና በመጫወታቸው በመንግስት የማይሸፈኑ የልማት ክፍተቶችን በመሙላት አስተዋጽዖ አድርገዋል። ይሆን እንጂ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን እና አጠቃላይ የትምህርት ጥራት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ ላልተማሩ እና በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ላቋረጡ ወጣቶች የሚሰጠው አጫጭር ሥልጠና በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን፣ ልዩ ተሰጥዖና ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች የልዩ ትምህርት መርሃ ግብር አለመዘጋጀት፣ የጤና ተቋማት ወጣት ተኮር አገልግሎት አለመስጠት (በሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ)፣ የወጣት ማዕከላት ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን፣ የማዕከላት ጥራት /ስታንዳርድ/ ችግር እና ማዕከላትን በመገንባትና በማስፋፋት በኩል ያለው ትኩረት ማነስ፣ በወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ጠቀሜታውን ተገንዝበው ትኩረት ሰጥቶ አለመሥራት፣ ከችግሩ ስፋት አንፃር ህገወጥ የሰዎች ዝውውርንና አደንዛዥ ዕፅን

ለመግታት የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሰጥተው በተደራጀ አግባብ አለመንቀሳቀስ እንዲሁም የወሲብ ፊልሞች መስፋፋት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ለመቅረፍ በቀጣይ በየደረጃው የሚመለከተው አካል ሁሉ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የሚጠበቅበት ይሆናል፡፡

የወጣቶችን ጉዳይ አካቶ የመሥራት ተግባር ለተወሰነ ሰው ወይም ቡድን የሚተው ባለመሆኑ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ተግባሩ ከፎካል ፐርሰን አሠራር ወጥቶ የአመራሩ ኃላፊነት እንዲሆን መደረጉ ለሴክተሮች የመፈጸም አቅም ማደግ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ በዚህም የወጣቶችን ጉዳይ ተቋማት በፕሮግራሞች፣ በፕሮጀክቶችና በዕቅዶች የማካተት ልምድ መሻሻል  እንዲሁም የወጣቶችን ጉዳይ በሪፖርቶች ለይቶ መረጃ የመያዝና የማቅረብ አሠራሮች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እያደጉ መጥተዋል፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም ቢሆን ተቋማት በሚጠበቀው ደረጃ የወጣቶችን ጉዳይ በዕቅዶቻቸው፣ በፕሮግራሞቻቸውና በፕሮጀክቶቻቸው ላይ አካቶ ለመሥራት የትኩረት ማነስና የአመላካከት ችግር መኖር፣ አንዳንድ ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ አካቶ ለመሥራት ግፊት /ጉትጎታ የመፈለግ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ፣ ተቋማት በምክር ቤት የሚሰጣቸውን አቅጣጫ በግብዓትነት ወስዶ ተግባራዊ አለማድረግ፣ በተዋረድ የተቋማትን ክፍተት ለይቶ አቅማቸውን አለመገንባት፣ ተከታታይ እና ወቅታዊ ሥልጠና አለመስጠት፣ የተቋሙ አመራር የማካተት ሥራ ተቋማዊ ሆኖ እንዲሰራ በማደረግ ትኩረት ሰጥቶ እየገመገሙ አለመምራት የሚሉት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የወጡ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ የልማት ዕቅዶችን፣ ጋይድ ላይንና መመሪያዎችን የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም ዙሪያ ውስንነት የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ ሁሉንም ችግሮች ቀርፎ መንቀሳቀስ በየደረጃው ከሚገኝ ሁሉም የሚመለከተው አካል የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**ተግዳሮቶች**

ከወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያ ወጣቶችን ወደ ሥራ የማስገባት ጉዳይ ከራሱ ከወጣቱ እና ከቤተሰቦች ጋር መሰራት ያለበት የአመለካከት ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ አመራሩና ባለሙያው ምቹ ሁኔታዎችን አለመፍጠር፣ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ከሚፈልጉት ወጣቶች ቁጥር እና በየዓመቱ ከሚፈጠረው አዲስ ሥራ ፈላጊ ወጣት አንፃር ሲታይ ገና ብዙ የሚቀር መሆኑ፣ ለወጣቶች የሚፈጠረው የሥራ ዕድል በቋሚ ከመሆን ይልቅ በጊዜያዊ የሥራ ዘርፎች ላይ ማተኮር፣ የወጣቶችን የሥነተዋልዶ ጤና ለማስጠበቅ በየጤና ተቋማቱ ወጣቶች ሳያፍሩ እና ሳይሸማቀቁ አገልግሎቱን የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ በሚፈለገው ደረጃ አለመፈጠር፣ ለህገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ለአደንዛዥ ዕፅ እና ለመጤ ባህል ወጣቶች በስፋት ተጋላጭ መሆን፣ የወጣት አደረጃጀቶች በሚፈለገው ደረጃ ተቋማዊነታቸው የጎለበተ ባለመሆኑ የመላውን ወጣት ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አለመቻል፣ በገጠር የወጣቶች የልማት ቡድን አደረጃጀት ውጤታማ አለመሆን፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በብሄረሰብ ዞኖች እና በክልል ምክር ቤቶች ላይ ወጣቶች በበቂ ሁኔታ አለመሳተፍ፣ ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ አካትተው በመፈፀም በኩል ውስንነት መኖር እንዲሁም የወጣት ማዕከላት ለወጣቶች በቂና ተደራሽ ያለመሆን እና ያሉትም ቢሆኑ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ለወጣቶች አገልግሎት በመስጠት በኩል ሰፊ ውስንነት ያለባቸው መሆኑ በዘርፉ የታዩ ተግዳሮቶች በመሆናቸው በቀጣይ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ የተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ በየደረጃው ከሚገኘው የሚመለከተው አካል ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

**ከአረንጓዴ ልማት አኳያ** በክልሉ የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችሉ አሠራሮችን በመንደፍ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተገብቶ የነበረ ሲሆን በዚህም በደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ህብረተሰቡን በስፋት በማሳተፍ የልማት ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ ሁሉም የልማት እንቅስቃሴዎች ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ ለማድረግ በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ በመገንዘብ የማስተሰርያ እና የማጣጣሚያ ርምጃዎች ለመውሰድ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስትራቴጂን

ለህብረተሰቡ በማስገንዘብ እና በየደረጃው የሚገኙ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ ተግባሪ አካላትን በማስተባበር ወደ ተጨባጭ እንቅስቃሴ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራ በሁሉም ዘንድ የጠራ ግንዛቤ ተይዞ ተግባሩ በተሟላ ሁኔታ አለመፈፀሙ፣ ተቋማዊ የቅንጅት ሥራዎች አለመኖራቸው፣ ለአካባቢ ጥበቃ ሥራ በየደረጃው ያለው አመራር የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፣ በጥብቅ ሥፍራዎች የልቅ ግጦሽ እና የደን ጭፍጨፋ መበራከት፣ ተስፋፊና መጤ አረም የመከላከል እና የመቆጣጠር አቅም አለመኖር፣ አንዳንድ ፕሮጄክቶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሥርዓትን ሳያልፉ ተግባራዊ መደረጋቸው፣ የሙቀት አማቂ ጋዞችን የልቀት መጠን የመለካት፣ የመመዝገብና የማረጋገጥ ሥርዓት አለመዘርጋት የሚሉ በዘርፉ የሚጠቀሱ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ በደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ ተስፋፊና መጤ አረሞችን የመከላከልና የመቆጣጠር አቅም የመገንባት እና የአካባቢን ብክለት ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል፡፡

የክልሉ ህዝብ በአካል፣ በዕውቀት፣ በአመለካከት እና በክህሎት አቅሙ የጎለበተ እንዲሁም አምራችና የገቢ አቅሙ ያደገ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ባሳለፍናቸው ዓመታት በርካታ ተግባራት ሲከናወኑ የቆዩ ቢሆንም በሥነ-ህዝብ ዙሪያ የሚፈለገውን ግንዛቤ በመፍጠርም ሆነ በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ አካቶ በመሥራት ረገድ ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ ጥቅል የወሊድ ምጣኔ (TFR) አንዲት በመውለጃ ዕድሜ ክልል ውስጥ (ከ15-49 ዓመት) የምትገኝ ሴት በአማካይ የምትወልዳቸውን ልጆች መጠን የሚያሳይ አመልካች ሲሆን በክልል ደረጃ ፖሊሲው ሲወጣ እ.ኤ.አ. በ1985 ዓ.ም ከነበረበት 7.7 ልጆች በ2003 ዓ.ም ወደ 4.2 ልጆች በ2008 ዓ.ም ደግሞ ወደ 3.7 መቀነሱን የሥነ-ህዝብ እና ጤና ዳሰሳ ጥናቶች ያመላክታሉ። በዚህ መረጃ መሠረት ጥቅል የወሊድ ምጣኔ(TFR) በክልሉ እየቀነሰ እንደሆነ የሚያመላክት ቢሆንም ከአደጉት አገራት አንፃር ከፍተኛ ሲሆን እንዲሁም ክልሉ በቀጣይ ከሥነ ህዝብ መልካም አጋጣሚ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ጥቅል የውልደት ምጣኔ ከ 3 ልጆች በታች መሆን ስለሚገባው አሁንም የበለጠ መሥራት እንደሚገባ ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ1993 የሥነ-ህዝብ ፖሊሲው ሲወጣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ከነበረበት 4 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 47.3 በመቶ እና በ2011 ወደ 49.5 በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን ያልተሟላ የቤተሰብ ምጣኔ ፍላጎት ግን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 22.1 በመቶ በ2008 በጀት ዓመት ወደ 17.4 ቀንሷል፡፡ ስለሆነም አሁንም በክልሉ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም እየፈለጉ በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎቱን የማያገኙ ሴቶች እንዳሉ ያመላክታል፡፡

የህዝብ ብዛት ፈተናዎችንም ሆነ ዕድሎችን ይዞ የሚመጣ ጉዳይ ነው። በአንድ በኩል እያደገ ያለ ህዝብ በወጣቶች የተሞላና በበቂ ሁኔታ የሚገኝ ሠራተኛ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የሚያደርግ ሲሆን በተጨማሪም በአገር ውስጥ የተመረቱ ምርቶችን ሊገዛ የሚችል ሰፊ የአገር ውስጥ የገበያ ዕድሎችን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ደካማ አቅም ላለው አገር እንደ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ ትራንስፖርት፣ መኖሪያ ቤት የመሳሰሉት በቂ መሠረተ ልማቶች በሌሉበት ሁኔታ በህዝብ አገልግሎት ተቋማት ላይ ጫናን ያሳድራል፡፡ በመሆኑም ከሥነ-ህዝብና ልማት ጋር ተያይዘው የሚሰሩ ተግባራት መልካም ዕድሎችን አሟጦ በመጠቀም ፈተናዎችን የሚቀርፉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም የሚመለከተው አካል ሁሉ በጉዳዩ ላይ አልሞ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

### 3.2.5. የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ዘርፍ አፈጻጸም ግምገማ

#### የፍትህ ዘርፍ

በአለፉት 10 ዓመታት በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ረገድ የመጀመርያው ተግባር የሆነው የወንጀል ድርጊት ከመፈጸሙ በፊት በወንጀል መከላከል ረገድ የንቃተ-ህግ ትምህርት በመስጠት ወንጀልና የወንጀል ሥጋቶችን በመቀነስ የህብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት የመጠበቅ ሥራ ተከናውኗል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ወንጀል ፈጻሚዎችን በህግ ፊት አቅርቦ ራሳቸውንና ሌሎችን ሊያስተምር የሚችል ተመጣጣኝ ቅጣት የማስቀጣት ሥራ ሲከናወን በመቆየቱ ምክንያት የክልሉ ህብረተሰብ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ሊኖረው የሚገባውን አመኔታ በየጊዜው እንዲጨምር ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

አቃቤ ህግ የወንጀል መዛግብትን መርምሮ ውሳኔ ከመስጠት አንፃር የማጥራት ምጣኔን 98.95 በመቶ መፈፀም ተችሏል፡፡ የማስቀጣት ምጣኔም በቀጥታ ክስ 94.46 በመቶ፣ በዐቃቤ ህግ ይግባኝ 79.34 በመቶ፣ በፍርደኛ ይግባኝ 89.9 በመቶ፣ በዐቃቤ ህግ ሰበር አቤቱታ 72 በመቶ እና በፍርደኛ ሰበር አቤቱታ 89.32 በመቶ መፈፀም ተችሏል፡፡ የማቋረጥ ምጣኔም 5.56 በመቶ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደሩ ረገድ የመጀመሪያው ተግባር የሆነው የመንግስት፣ የህዝብ እና ነፃ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅም እንዲከበር ሰፊ የቅድመ መከላከል ሥራ መሥራት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የአሠራር ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ በማቅረብና የተጠናከረ የህግ ምክርና ድጋፍ በመስጠት የመንግስትና የህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ሥልቶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመሥራት ተቋማቱ ተግባራቸውን በህግ አግባብ ለመፈጸም እንዲችሉ የሚጠበቀው ድጋፍና እገዛ ተደርጓል፡፡

ድርድር በክርክር የሚወጣውን ጊዜ እና ወጪ በመቀነስ ጉዳዮችን በአጭር ጊዜ ለመጨረስ የሚያስችል አማራጭ ሆኖ እየተሰራበት የሚገኝ ሲሆን በዚህ አግባብ በድርድር እልባት ያገኙ ጉዳዮችን በመዝገብ 15.02 በመቶ እንዲሁም በገንዘብ 3.67 በመቶ መፈፀም ተችሏል፡፡ በ2ቱ የዕቅድ ዘመናት 48 አዋጆች፣ 109 ደንቦች፣ 136 መመሪያዎችና 9 ማንዋሎች የተረቀቁ ሲሆን 66 የምክር አገልግሎቶች ለጠያቂ የመንግሥት ተቋማት ተሰጥተዋል። የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በሚመለከት በ25 ርዕሶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተከናውነዋል።

#### በዘርፉ የታዩ ችግሮች

የለውጥ የመልካም አስተዳደር ተግባራትን በተመለከተ የፀረ ኪራይ ሰብሣቢነት ትግሉ በተደራጀ የህዝብ ንቅናቄ የተመራ ባለመሆኑ መሠረታዊ ለውጥ መጥቷል ማለት አይቻልም፡፡ በህብረተሰቡም ዘንድ ዘርፉን ከብልሹ አሠራር ያልተላቀቀ አድርጎ የማየት አመለካከት ሰፊ እንደሆነ ታይቷል፡፡ በሁለቱም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመናት የተቀመጡትን ግቦች ከማሣካትና የለውጡን ቀጣይነት በማረጋገጥ ረገድ በሚፈለገው መንገድ የተገልጋዮችን እርካታ ያመጣ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ ኃይል በአመለካከት፣ በክህሎት፣ በአሠራር እና በአደረጃጀት የሚታዩ ክፍተቶችን በአግባቡ ለይቶ ይህንን ሊፈታ የሚችል ዕቅድ በማዘጋጀት እና በመተግበር የአቅም ውስንነት ያለበት እንደነበር ታይቷል፡፡

በዘርፉ የተዘረጋው ቅንጅታዊ የአሠራር እና የአደረጃጀት ሥርዓት የዘርፉን ተቋማዊና ክልላዊ ራዕይ ለማሣካት ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ እና ጠቀሜታ በዕምነትና በባለቤትነት ያለመያዝ እና የዝግጁነት ማነስ ችግሮች የነበሩበት ነው፡፡ እንዲሁም የጋራ መድረኮች አሠራር እና አደረጃጀትም የዘርፉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማስተግበር የሚያስችል የጋራ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ያልተዘረጋበት ከመሆኑም ሌላ መድረኮች መሠረታዊ

ለውጥ በሚያመጡ ክልላዊ አጀንዳዎች ላይ የህዝብ ንቅናቄን በመፍጠር የለውጥ ሥራን ቀጣይነት የሚያረጋግጡ በመሆን በኩል ጉድለት የነበረባቸው ነበሩ። በዚህም ምክንያት የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራሙን በጋራ በመገምገም ወቅታዊ ችግሮችን በመፍታት ውጤታማ የማሻሻያ ሥራዎች ያለመሥራት፣ የለውጥ መሣሪያዎችን ወጥና ተናባቢ ሆነው እንዲፈፀሙ ያለማድረግ፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በጋራ ያለማከናወን እና በለውጥ ንቅናቄ የሚገኙ የአመለካከት፣ የዕውቀት እና የሥነምግባር ችግሮችን በጋራ ለይቶ ያለመፍታት ችግሮች በስፋት ተስተውለዋል።

ከወንጀል ፍትህ አስተዳደር ተግባራት አኳያ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ አፋጣኝ ውሳኔ አለመስጠቱ፣ የመዛግብት መብዛትና የዐቃቤያነ ህግ ቁጥር ማነስ ችግር የነበረ ሲሆን የተፋጠነ ክስ እና ፍርድ አሰጣጥ በሁሉም አካባቢ ወጥነት የጎደለው ነበር። የዚህም ምክንያት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የተወሰኑ ዳኞች፣ አቃቤ ህጐች እና ፖሊሶች ለጉዳዩ ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ እንዲሁም በተፋጠነ የፍርድ ሥነ ሥርዓት የሚታዩ ጉዳዮችን የሚመለከት ዝርዝር የህግ ማዕቀፍ አለመዘጋጀቱ ነው። ከማስቀጣት ምጣኔ አኳያ አፈፃፀሙ ጥሩ የሚባል ቢሆንም በየዓመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር ግን መድረስ አልተቻለም። ከታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ ያልተቻለው የተለያዩ የውስጥና የውጭ ችግሮች በመኖራቸው መሆኑ ተስተውሏል። ከውስጥ ችግሮች መካከል ዓቃቤ-ህግ የወንጀል ሥነሥርዓት ህጉን መሠረት ያደረገና ጥራት ያላቸው ክሶች፣ መልሶችና ክርክሮችን ካለማድረግ አንፃር የሚታይ ሲሆን ከውጫዊ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፖሊስ የሚያሰባስባቸው የሰው እና የሠነድ ማስረጃዎች ምስክሮች በአካል ቀርበው በፍርድ ቤት ከሚሰጡት ቃል ጋር የማይገናኝበት ሁኔታ መኖር እና የሀሰተኛ ምስክርነት መበራከት፣ ፍርድ ቤቶች ክርክሮችን በአግባቡ ያለማስኬድና ውሳኔዎችንና ትዕዛዛትን በአግባቡ ካለመስጠት ጋር የሚያያዙ ችግሮች መኖራቸው ነው። የንቃተ-ህግ ሠነድ ዝግጅት እና የትምህርት አሰጣጥ ጥራትን ለማጠናከር የሚያስችሉ አሠራሮች እና ዘዴዎች እየተመቻቹ ቢሆንም ውጤቱ ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሰ በመሆኑ ተጨማሪ ሥራዎችን የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል።

ከፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ጉዳዮች አኳያ ለመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚሰጠው ድጋፍ ተከታታይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ የሚሰጠው ድጋፍ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ብክነት እና ምዝበራ የሚፈፀምባቸው ተቋማት ቁጥር ቀላል አልነበረም። ከዚህ ጋር ተያይዞ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የውል ግዴታ ከገቡ በኋላ ግዴታቸውን አለመፈፀም እንዲሁም ከውሉ የሚጠበቀውን መብትና ጥቅም አለማስፈፀም፣ ውሉን በዘፈቀደ ማቋረጥና ለውል መፍረስ ምክንያት በመሆን መሥሪያ ቤቱን ለከፍተኛ ወጪ መዳረግ፣ የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም ለተዋዋይ ወገኖች አሳልፎ መስጠት፣ ህገወጥ ተግባር ከፈፀሙ በኋላ ዐቃቤ ህግ በመንግስት ሥም ሽፋን እንዲሰጣቸው የመፈልግ ዝንባሌ ነበር። የውል ረቂቅ ምርመራና ዝግጅት አገልግሎት አሰጣጥም ቢሆን ወጥነት የጎደለውና አልፎ አልፎ በውሉ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ውዝግቦችን መፍታት የማያስችል ክፍተቶች ያሉበት ነበር።

ድርድርን አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ አድርጎ በመጠቀም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮች ሲታዩ የመንግስት መሥሪያ ቤት ተወካዮች ለድርድር ሲጠሩ ፈቃደኛ ያለመሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመንግስትን ጥቅም ለተደራዳሪዎች አሳልፎ ለመስጠት የመፈለግ፣ ድርድሩን የሚመሩ ዓቃቤ ህጎች ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠት እና በቂ ዝግጅት አለማድረግ፣ ድርድሩ የሚመራበት የአሠራር ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ባለመኖሩ ኃላፊነት ወስዶ ለመደራደር አለመቻል ዋና ዋና ችግሮች እንደነበሩ ታይቷል። ከመዛግብት ማጥራት አንፃርም በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በተወሰኑ መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ አፋጣኝ ውሳኔ አለመስጠቱ፣ የመዛግብት ፍሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር፣ የዐቃቤያነ ህግ ቁጥር ማነስ እንዲሁም ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በቀላሉ የማይገኙ መሆን የሚሉ ተጠቃሽ ችግሮች ነበሩ።

የክርክር ውጤታማነትን በሚመለከት የታዩ ችግሮች በአንዳንድ ጉዳዮች ዓቃቤ ህግ ጥራት ያላቸው ክሶችንና መልሶችን ካለማቅረብ፣ ክርክሮችን በአግባቡ ካለመምራት፣ የችሎት ዝግጅት ካለማድረግ እና ጉዳዮችን በጥልቀት ከህግና ከማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ በውል ካለመለየት ጋር የተያያዙ ሲሆን በተለይ በነፃ የህግ ድጋፍ ጠያቂዎች እና በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ተገፋፍቶ ጉዳዩ እንደማያዋጣው እየታወቀ ፍርድ ቤት ይወስነው በሚል ክስና መልሶችን የማቅረብ አሠራር ተስተውሏል፡፡ ከውጫዊ ችግሮች መካከል ደግሞ ዋና ዋናዎቹ ከመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚላኩ የሰውና የሠነድ ማስረጃና ምስክሮች በቂ አለመሆን፣ ማስረጃዎችን አለመስጠት፣ ውሉን ያለበቂ ምክንያት ማቋረጥ፣ በተጋነነ ዋጋ ውል መስጠት፣ የግንባታ አማካሪ ድርጅቶች የሚሰጡትን ውሳኔ አለመቀበል፣ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በሚከሰሱበት ጊዜ በፍርድ ቤት የተያዘው ቀጠሮ እስኪደርስ መጥሪያውን በእጃቸው አቆይተው በቀጠሮው ቀን ለዓቃቤ ህግ ማቅረብ አልፎ አልፎ በራሳቸው መልስ ከሰጡ በኋላ ድጋፍ መጠየቅ፣ ፍርድ ቤቶች ክርክሮችን በአግባቡ ያለማስኬድና አንዳንድ ውሰኔዎች እና ትዕዛዞች የህግ መሠረትና ተገማችነት የሌላቸው መሆን ሌሎች ችግሮች ነበሩ፡፡

ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትን በሚመለከት የተሠጠው የአገልግሎት ሽፋን አነስተኛ ከመሆኑም በላይ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች የት፣ እንዴት፣ ለማን፣ መቼ ማቅረብ እንዳለባቸው ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ እጥረት ያለባቸው መሆኑ እና ራሰቸው በግል ፍርድ ቤት ካቀረቡ በኋላ ሲሸነፉ ድጋፍ የሚጠይቁ በመሆኑ ጉዳያቸውን ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል፡፡ ንብረት ፈልጎ ማሳገድን በሚመለከት ክስ ከቀረበበት መዛግብት ውስጥ መታገድ የነበረበት ንብረት ሙሉ በሙሉ ከማይታገድበት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው ለጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ በወቅቱ ንብረት አለመፈለግ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የትብብር ማነስ፣ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ተቋማት ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተፈጠረ በኋላ ለብዙ ዓመት አቆይተው የሚልኩት በመሆኑ ተከሳሾች ንብረታቸውን ለማሸሽና ወደ 3ኛ ወገን ለማዛር ምቹ ሁኔታን የፈጠረላቸው መሆኑ ተስተውሏል፡፡ በድርድር እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን በተመለከተም ዐቃቤያነ ህግ ትዕዛዝ በሰጡባቸው አቤቱታዎች እስከመጨረሻው አፈጻጸማቸውን በመከታተል ረገድ ውስንነቶች ታይተዋል፡፡

ከሠነዶች ማረጋገጥ እና ከጠበቆች ጉዳይ ተግባራት አፈጻጸም አኳያም ከፍተኛ ገንዘብ በገቢነት እየተሰበሰበ ያለ ቢሆንም ይህንን ገንዘብ በኃላፊነት ሰብስቦ ገቢ ሊያደርግ የሚችል የገንዘብ ሰብሳቢ ሠራተኛ በሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች በቋሚነት ባለመመደቡ ለሥራው እንቅፋት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የጠበቆችን 50 ሠዓት ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ደግሞ ጠበቆቹ በያዙት ነፃ አገልግሎት መዝገብ ላይ ያስመዘገቡት ውጤትና የተገልጋዩን እርካታ በተመለከተ ክትትል በማድረግ ረገድ ውስንነት የታየበትና ጠበቆች ጥሩ ሥነምግባር በመያዝ የፍትሕ ሥርዓቱ አጋዥ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ትኩረት ሰጥቶ የመሥራት ውስንነት የታየበት ነበር፡፡ ጠበቆች በተሰጣቸው ፈቃድ ህግን መሠረት አድርጎ ከመሥራት ይልቅ ሀሰተኛ ሠነድ ከማህበራዊ ፍርድ ቤቶች እና ከአንዳንድ መንግሥታዊ ተቋማት አሠርቶ ለፍርድ ቤት ማቅረብ፣ የዓቃቤ ህግ ምስክሮችን እንዳይመሰክሩ ማባበል እና መደለል፣ የደንበኞቻቸውን ሚስጢር ለተቃራኒ ደንበኛ መግለጽ፣ በነፃ አገልግሎት ላይ ክፍያ መጠየቅ፣ ከፍትህ አካላት ጋር አላስፈላጊ ግንኙነት መፍጠር፣ ከደንበኞቻቸው ጋር ውል አለመያዝ፣ የሚያዋጣና የማያዋጣውን ጉዳይ ሳይለዩ ክፍያ ለማግኘት ብቻ አዋጭ ያልሆኑ ጉዳዩችንም ጭምር መያዝ እና የመሳሰሉት የሥነምግባር ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምዝገባ እና ክትትልን በተመለከተም ከክልል እስከ ወረዳ ሥራው በተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀት ያልተጀመረ በመሆኑ የምዝገባ፣ የፈቃድ ዕድሳቱ እና የቁጥጥር ሥራው ውስንነት ያለበት እንደነበር ተገምግሟል፡፡

ከህግ ምክር ማርቀቅ እና ማጠቃለል ተግባራት አንፃር ደግሞ በሥራው ላይ የተሰማሩት ባለሙያዎች የሚሠሩት የህግ ረቂቅ ሥራ በበቂ ሥልጠና ላይ ያልተደገፈ በመሆኑ የጥራት ጉድለት የሚታይ መሆኑ፣ የባለሙያ እጥረት፣ የተቋማት ኃላፊዎች ባለባቸው የግንዛቤ እጥረትና በየጊዜው የሚለዋወጡ በመሆናቸው ምክንያት

የሚያመነጯቸው ረቂቅ ህጎች ወደ መሥሪያ ቤቱ ሳይልኩ ማጽደቅ ወይንም በራሳቸው ማጽደቅ፣ በመሥሪያ ቤቱ ያልታዩ ረቂቅ ህግጋት እንዳይጸድቁ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ያለመኖር፣ የህግ አጽዳቂ አካላት የጸደቁ ህግጋትን ለማጠቃለል ለመሥሪያ ቤቱ የማይልኩ መሆኑ እንዲሁም ሥልጠናዎችን ለመስጠት እያጋጠመ ያለ የበጀት እጥረት ሌሎች ተጠቃሽ ችግሮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን በተመለከተም የሁለተኛው ብሔራዊ የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር አፈጻጸም አስመልክቶ በፈጻሚ ተቋማት የሚታቀዱ ዕቅዶች እና ሪፖርቶች በተቀመጠው የድርጊት መርሃ-ግብር መሠረት እየተፈጸሙ አለመሆኑ፣ የአንድ ማዕከል የተቀናጀ የእንክብካቤ እና የፍትህ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ተደራሽ ማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣ የህፃናት ጋብቻን በመከላከል ረገድ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የተሰራው ሥራ በቂ አለመሆን፣ ጋብቻን በሚመለከት ከህክምና ተቋማት የሚሰጡ የተወሰኑ የዕድሜ ምርመራ ማስረጃዎች ትክክለኛነታቸው አሻሚ መሆን፣ የኃይል ጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ህፃናት ተገቢ የሆነ አገልግሎት በፍትህ እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲያገኙ የሚጠበቅ ቢሆንም የተወሰኑ የባለድርሻ አካላት ባለሙያዎች ተነሳሽነት አናሳ በመሆኑ አገልግሎቱን በተፈለገው ልክ እንዲያገኙ እየተደረገ ባለመሆኑ ለድጋሚ ጉዳት እየተዳረጉ መሆኑ፣ አሁን ላይ ያለው ቅንጅታዊ አሠራር የሚጠበቀውን ያህል አለመሆኑ እንዲሁም ከክልል እስከ ወረዳ የተቋቋሙት የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል መከላከል ምክር ቤት፣ ግብረ ኃይል እና ንዑስ የሥራ ቡድኖች በበላይ አመራሩ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተሰሩ አለመሆናቸው ዋና ዋና ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡

## የሠላም ግንባታ ዘርፍ

የማህበረሰብ አቀፍ የፖሊስ አገልግሎት ስትራቴጂ በክልሉ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ተግባራዊ እየተደረገ የቆየ ሲሆን ይህን መሠረት በማድረግ የማህበረሰብ አቀፍ የወንጀል መከላከል ሥራ በየደረጃው ሲከናወን ቆይቷል፡፡ በሁለቱም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዓመታት በነበረው ሂደት ህብረተሰቡ ለፀጥታ ሥራው የሚያደርገውን አስተዋጽዖ በማሳደግና ወንጀልን ከመቀነስ አንፃር ተሳትፎውን በቁሳቁስና በገንዘብ በማሳደግ እንዲሁም ለፀጥታ ሥራው ተሳታፊ በመሆን ከፍተኛ ሚናውን ሲወጣ ቆይቷል፡፡ ይህንን ተግባር ቀጣይና ውጤታማ ለማድረግ የቀበሌ ኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋንን ማሳደግ፣ አዳዲስ የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰሮችን በማሠልጠን ወደ ሥራ ማስገባት፣ የቀበሌዎችን ኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ የአፈፃፀም ደረጃ ለማሻሻል በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመፍጠር የህብረተሰቡን ሠላም ለማስፈን ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይሁን እንጅ በሁለቱ የዕድገትና ትሬንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመናት የቀበሌዎችን ሽፋን ለማሳደግ የሰው ኃይሉን ቁጥር ወደ 7,863 ለማድረስ ቢታቀድም የሰው ኃይሉ ቁጥር በቀበሌ ደረጃ ወደ 2,282 ዝቅ ብሏል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

ከአጠቃላይና ዋና ዋና ወንጀል አኳያ በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ አጠቃላይ ወንጀል 48,086 ዋና ዋና ወንጀል ደግሞ 21,015 የነበረ ሲሆን ከላይ እስከታች በተደረገው ክትትልና ቁጥጥር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ አጠቃላይ ወንጀልን ወደ 35,699 ዋና ዋና ወንጀልን ደግሞ ወደ 13,717 ዝቅ ለማድረግ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ ወንጀል በአንድ ሺህ ሰዎች መካከል በገጠር 1.6 እንዲሁም በከተማ 5.45 ላይ የሚገኝ ሲሆን በተመሳሳይ ዋና ዋና ወንጀል በአንድ ሺህ ሰዎች መካከል በገጠር 0.6 በከተማ ደግሞ 1.95 ላይ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በአለፉት ሁለት የዕድገትና ትሬንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመናት የክልሉን ሠላምና ፀጥታ የሚፈታተኑ አደጋዎችን በመከላከል ረገድ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ህዝቦች መካከል የሠላም ዕሴት ለመገንባትና በዘላቂነት መልካም ግንኙነት ለመመስረት የሠላም ክበባትን እና ኮሚቴዎችን የማደራጀትና የማጠናከር፣ የህዝብ ለህዝብ ኮንፈረንሶችን የማካሄድ፣ በጋራ ዕቅድ እየተመራ የአመራር ለአመራር ግንኙነትን የማጠናከር ሥራ በትኩረት ተሰርቷል፡፡ በሌላ በኩልም በ2ኛው ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን በክልሉ ህዝብ ውስጥ

የሚፈጠሩ ግጭቶችንና አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በአማካይ 48,044 አባላትን ያቀፈ 3,623 የሠላም ኮሚቴ በማቋቋምና በሥልጠና በማጠናከር ወደ ሥራ ለማስገባት ጥረት ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ በአደረጃጀቱም በህብረተሰቡ መካከል ሰላማዊ ግንኙነት እንዲዳብርና አለመግባባቶችና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ በአካባቢው ባህል መሠረት እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ለውጡን ተከትሎ ለአደረጃጀቶች የሚደረገው ክትትልና ድጋፍ አናሳ መሆንና ችግር ፈቺ የሆነ ሥልጠና ባለመሰጠቱ እየተዳከሙና ለሥራው ያላቸው ፍላጎት እየቀዘቀዘ በመምጣቱ አሁን ላይ አሉ ለማለት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ አይገኙም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ መታየት ያለበት ጉዳይ ይሆናል፡፡

በማህበረሰቡና በየአካባቢያቸው የሚታዩ የግጭት አመላካቾችን፣ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን ቀድሞ በመለየት ተገቢ ምላሾችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ተግባር ላይ በማዋል፣ በግጭት የሚደርስ ጉዳትን ቀድሞ መከላከል ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በክልሉ በርካታ የጦር መሣሪያ በመንግስትና በግል ታጣቂዎች እጅ የሚገኝ ሲሆን የጦር መሣሪያ አያያዝ እና ሥርጭቱን ለመከታተል እንዲያመች በየዓመቱ በመንግስትና በግል ታጣቂዎች እጅ የሚገኝ የጦር መሣሪያ ከ88 በመቶ በላይ የፈቃድ ዕድሳትና የአካል ቆጠራ ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም በአማካይ 86 በመቶ ለሚሆኑ የሚሊሻ ጽህፈት ቤቶች የጦር መሣሪያ ኦዲት በማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ ህገወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን ለመቆጣጠርና ለመግታት ህገወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር የሚፈፀምባቸውን አካባቢዎችና ህገወጥ አዘዋዋሪዎችን በጥናት በመለየት ህገወጥ ትጥቅን የማስወረድና አጥፊዎችን ደግሞ ለህግ የማቅረብ ሥራ በስፋት ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም በቀጣይ የአፈጻጸም ድክመት በታየባቸው ላይ በመረባረብ ማስተካከል እና የነበሩ ጥንካሬዎችን የበለጠ አጠናክሮ ማስቀጠል በየደረጃው ከሚገኝ የሚመለከተው አካል ሁሉ የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

የትራፊክ ቁጥጥር ሥራን በሚመለከት በሰው ኃይል እጥረት ምክንያት በሁሉም ወረዳዎች ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች አለመሸፈናቸው፣ ለዘርፉ አሁንም በቂ ትኩረት ያለመስጠትና ለክትትልና ቁጥጥር የሚያግዙ የተለያዩ ግብዓቶች ያለመሟላት፣ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራውን ችግር ፈች በሆነ አግባብ አለማከናወን፣ አጋዥ የተማሪ ትራፊኮችን በበቂ ሁኔታ ማሠልጠንና መጠቀም አለመቻል፣ የትራፊክ ፖሊስ አባላትን አቅም እና ሥነምግባር የሚያሻሽል ሥልጠና አለመሰጠቱ፣ የአሽከርካሪዎች ብቃት ማነስ፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ችግር፣ የአሽከርካሪ ማሠልጠኛ ተቋማት ብቃት ማነስ እንዲሁም የመንጃ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በመኖራቸው በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዩች ይሆናሉ፡፡

በአለፉት ዓመታት 164,797 አዲስ የሚሊሻ አባላትን በህብረተሰቡ ተሳትፎ በመመልመልና በማሠልጠን ወደ ሥራ እንዲገቡ ሲደረግ አሁን ላይ 218,172 የሚሊሻ አባላትን በፀጥታ ሥራ እንዲሰማሩ በማድረግና ለጥበቃ ሥራ በማደራጀት የህገ መንግስቱን መርሆዎችና ሌሎች ህጐችን በመጠበቅ የሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይጣሱ እና መልካም አስተዳደር ዕውን እንዲሆን በክልሉ ውስጥ ካሉ የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀትና በመተባበር የጥበቃ በሮችንና የመሠረተ ልማት አውታሮችን በመጠበቅ ሠላምን በማስፈን ረገድ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ህግን ለማስከበር ሲባልም ከህግ የራቁ ፀረ ሠላም ኃይሎችን በህግ ቁጥጥር ሥር ለማዋል በተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ የአካል ጉዳትና የህይዎት መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ ይሁን እንጅ ህብረተሰቡን በሚፈለገው ደረጃ ያለማሳተፍ፣ ትኩረት ሰጥቶ ያለመሥራት፣ አዲስ የሚሊሻ አባላትን በመመልመል የህዝቡንና የሚሊሻውን ጥምርታ በተቀመጠው ዕቅድ መሠረት ያለማከናወን፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በጥራት ያለመሥራት ችግሮች ታይተዋል፡፡ ሰለሆነም ችግሩን ለማስወገድ የሚሊሻ አባላቱ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ በቀጣይ የተሻለ ሥራ መሥራት ተገቢ ይሆናል፡፡

ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የቀለም ትምህርትና የልዩ ልዩ ሙያዎች ባለቤት ሆነው እንዲወጡና እንደ አገር የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለማስቻል መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርትን ጨምሮ የተለያዩ የሙያ ብቃት ሥልጠናዎች በአለፉት 10 ዓመታት ተሰጥተዋል፡፡ የምክር አገልግሎትን በተመለከተም የታራሚዎችን የተዛባ አመለካከትና ባህሪ በመቀየር የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡና ወንጀል ጠል ዜጋ ሆነው እንዲወጡ ለማስቻል በግልና በቡድን የምክር አገልግሎት በትኩረት ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም የማረምና ማነፅ ሥራዎች ውጤታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በአንዳንድ ማረሚያ ቤቶች ከማሠልጠኛ ግብዓት አለመሟላትና ከአሠልጣኝ እጥረትና ብቃት ጋር በተያያዘ አሁንም የጥራት ጉድለቶች የሚታዩባቸው ማረሚያ ቤቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ በምክር አገልግሎት በኩልም የታራሚ ባህሪ በመቅረጽ በኩል እጥረቶች በመኖራቸው በአንዳንድ ማረሚያ ቤቶች የሠላምና ያለመረጋጋት እንዲሁም የማረሚያ ቤቶች የቃጠሎ አደጋዎች የተከሰቱበት ሂደት እንደነበር የሚታወቅ ስለሆነ በቀጣይ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ የሚያስችል የአፈፃጸም መመሪያ በማዘጋጀት በተገቢው መሥራት የሚያስፈልግ ይሆናል፡፡

## በዘርፉ ያጋጠሙ ችግሮች

**የሰው ኃይል ልማትና አቅም በተሟላ ቁመና ላይ አለመድረስ፡-** ከዚህ አኳያ የቁርጠኝነትና የተነሳሽነት መጓደል፣ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሥራን በትግል አቀናጅቶ የመምራት ችግር፣ የተለወጠ ተቋም ለመገንባት የአመለካከት፣ የክህሎት እና የአቅም ውስንነት መኖር፣ የሰው ኃይል እጥረት፣ የሕዝቡን ተሳትፎ በተደራጀ መንገድ ተጠቅሞ ውጤታማ የፀጥታ ሥራ በመሥራት ረገድ ዋና ዋና የማስፈፀም አቅም ፈተናዎች መሆናቸው፣ በሁሉም የፀጥታ ተቋማት ተጨማሪ የሰው ኃይል በማሠልጠን በቂ የፀጥታ ኃይል ወደ ሥራ ባለመግባቱ በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው የክልሉ የህዝብ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ አገልግሎት መስጠት ያለመቻሉ፣ የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋን እያሽቆለቆለ መምጣቱና የሠላም ችግሮች መከሰታቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች የተለቀቁ ክፍት የሥራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት ባለመቻሉ በአሠራር ሂደት ክፍተቶች መኖራቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሥራ ዘመናቸውን ሳይጨርሱ የሚለቁ የፖሊስ አባላት ቁጥር ከፍተኛ መሆኑና በሚለቁ አባላት ላይ የሰው ኃይል ለመተካት ደግሞ የተጨማሪ በጀት ጥያቄ ማስከተሉ እና በአፈፃጸም ላይ ችግር ማስከተሉ፣ የሚሰጡ አጫጫር የሰው ኃይል ሥልጠናዎች የጥራት መጓደልና ችግር ፈቺ ያለመሆናቸው እንዲሁም በቂ ዝግጅት ያልተደረገባቸው በመሆኑ ለውጥ ማምጣት ያለመቻሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከግብዓትና ከሎጅስቲክ አቅርቦትና ሥርጭት አኳያ ጊዜው የደረሰበትን ለፀጥታ ሥራ የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በግብዓትነት ተሟልተው በሥራ ላይ አለመዋል፣ ለሁሉም የፀጥታ ተቋማት ለፀጥታ ሥራው የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የነፍስ ወከፍ እና የቡድን መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለመሟላትና በአስተማማኝ ደረጃ ለተልዕኮ ሙሉ ያለመሆን፣ በሁለም የፀጥታ ተቋማት በየደረጃው የቢሮ ችግሮች ፈተና እየሆኑ መምጣት፣ የተሽከርካሪ እጥረት በመኖሩ ምክንያት የፀጥታ ኃይሉ በሚከሰቱ ችግሮች ላይ ፈጥኖ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ መሆኑ የሚሉት ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

**የፀረ-ለውጥ ኃይሎች እንቅስቃሴ፣ ያልተረጋጋው የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ እና የቅድመ መከላከል ተግባራት፡-** ሽብርተኝነትና አክራሪነት በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋትነቱ እየጨመረ መምጣቱ፣ በፀረ-ለውጥ ኃይሉ ቀስቃሽነት በአለፉት ሁለት ዓመታት በክልሉ ውስጥ ሲነሱ የቆዩ የማንነት ጥያቄዎች ብዙ ጥፋትና የሰዎች መፈናቀል ማድረሳቸው፣ የኃይማኖት አክራሪነትና ፅንፈኝነት በአመለካከትም ይሁን በተግባር በክልላችን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ያልተሸነፈ ስጋት መሆኑ የሚሉት ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡

**ከክልሉ ውጭ በሚኖሩ የአማራ ብሔር ተወላጆች ግድያና መፈናቀል መበራከት፡-** ከክልሉ ውጭ ለረዥም ጊዜ በሚኖሩ የአማራ ማህበረሰብ ላይ በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄደው ማንነትን መሠረት ያደረገ ግድያና

የማፈናቀል ዘመቻ በክልሉ ውስጥ ወደ ፖለቲካ አለመረጋጋት እና ቀውስ ሊያመራ የሚችል መሆኑ፣ ያልተፈቱ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች አድማሳቸውን እያሰፉ መሄዳቸውና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ባለማግኘታቸው ለፀጥታው የስጋት ምንጭ እንደሆኑ መቀጠላቸው ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

**የግጭት አመላካች መረጃዎችና የቅድመ መከላከል ሂደት፡-** በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ከመሬት ይገባኛል፣ ከዕምነት በታዎች ፍላጎት ጋር፣ በከተሞች አካባቢ ህገወጥ የመሬት ወረራ እንዲሁም በግጦሽ መሬት አጠቃቀምና ከወል መሬቶች ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች በአለፉት ዓመታት ችግር ሆነው ቆይተዋል፡፡ ከሁሉም አጎራባች ክልሎች በአለፉት ዓመታት አልፎ አልፎ ግጭቶች እየተፈጠሩ በሰው ህይዎትና ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ፣ ከአንዳንድ ክልሎችም ሰዎች ተፈናቅለው ወደ ክልሉ እንዲመጡ የተደረገበት ሁኔታ መኖሩ የሚሉት ተጠቃሽ ችግሮች ነበሩ፡፡

**የቅድመ ወንጀል መከላከል አፈፃፀም ውስንነት፡-** የህብረተሰብ አቀፍ የወንጀል መከላከል ሽፋን እና የአፈፃፀም ጥራት በአለፉት ዓመታት ይደረሳል ተብሎ ከተያዘው ግብ አንፃር በተፈለገው ፍጥነት አለመሄዱና ካለፉት 10 ዓመታት መጀመሪያ ላይ ከነበረው በአስጊ ሁኔታ እየቀነሰ የመምጣቱ ምክንያት በጥናት ተደግፎ ምላሽ የሚሻ ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩልም የተቀመጡትን የወንጀል መከላከያ መንገዶችን ተከትለው በተሰሩ ሥራዎች የወንጀል ፍሰቱ ከዓመት ወደ ዓመት የቀነሰ ቢመስልም፣ የተለያዩ አሰቃቂ ወንጀሎች ከመፈጸማቸውም በተጨማሪ ነፍስ ግድያ፣ የመሠረተ ልማት ስርቆት፣ ህገወጥ የጦር መሣሪያና የሰዎች ዝውውር፣ ኮንትሮባንድና የመሳሰሉ ከባድ ወንጀሎችን ሙሉ በሙሉ መከላከል አለመቻል፣ በተለይ ከለውጥ ወዲህ የሚስተዋሉ ወንጀሎች በዋና ዋና ከተሞች ሳይቀር የቀን ዝርፊዎች እየተበራከቱ መምጣት፣ የወንጀል ምርመራ ሂደቱ ባለው የሰው ኃይል አቅም እየተሰራ ቢሆንም ከሚፈጸመው ወንጀል ብዛት እና ሥርጭት አንፃር የምርመራ ፍጥነቱ ለውጤት ለማብቃት የሚኬድበት ርቀት ሙሉ አለመሆኑ የተስተዋሉ ችግሮች ነበሩ፡፡

**የትራፊክ አደጋ ሥርጭት መባባስ፣ የጦር መሣሪያ ሥርጭትና ህገ-ወጥ ዝውውር መጨመሩ፡-** የትራፊክ አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴዎች በአለፉት ዓመታት ቢካሄዱም በህይዎትና በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመረ ከመሄድ ውጭ የቀነሰበት ሂደት አለመታየቱ ሌላኛው ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከጦር መሣሪያ ሥርጭቱ ጋር በተያያዘም የሚስተዋለው የጥይት ተኩስ በየአካባቢው መቆም ባለመቻሉ በሠርግና በለቅሶ በታዎች በሚተኮስ ጥይት የሰው ህይዎት እየጠፋ መሆኑ ሌላው ተጠቃሽ ችግር ነው፡፡

**የማረሚያ ቤቶች አያያዝና የክትትል ተግባራት በሚፈለገው ልክ ያለማደጉ፡-** ወንጀለኝነትን በአግባቡ መቀነስ ባለመቻሉ ወደ ማረሚያ ቤቶች የሚገቡት ታራሚዎች ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ በመምጣቱ ለቁጥጥርና ለክትትል አስቸጋሪ ከመሆኑም ባሻገር ለተጨማሪ ወጪ እየዳረገ መሆኑ አንዱ ተጠቃሽ ችግር ሲሆን በማረሚያ ቤቶች የሚሰጡ የሙያ ሥልጠናዎች ቁጥሩ ከዓመት ወደ ዓመት ዕድገት ቢያሳይም የባህሪ ለውጥ የሚያመጡት ታራሚዎች ግን የተጣጣመ ያለመሆን ችግር ይታይበታል፡፡

## የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች

ዘርፉ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ሲታይ የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች በዋናነት ለሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በተለይም በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባትን በመፍጠር የሠላም፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት በላቀ የአስተሳሰብ ከፍታ እንዲመሩ ያስችላል፡፡ እንዲሁም በክልል ብሎም በአገር አቀፍ ደረጃ ሁለንተናዊ የገጽታ ግንባታ ወሳኝ ሚና በመጫወት ረገድ ኮሚኒኬሽን ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስለሆነም የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች የመረጃ ፍሰትን ትክክለኛ፣ ወቅታዊ እና ፈጣን ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ ኢኮኖሚውን ከማሳለጥም ሆነ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አኳያ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

### የዘርፉ ዋና ዋና ተግዳሮቶች/ማነቆዎች

ዓለም አቀፋዊ ሁነቶች ፈጣንና ተለዋዋጭ መሆን ዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በፍጥነት እያደገ መምጣቱ መልካም ቢሆንም ከሀገራችንም ሆነ ከክልላችን አሁናዊ እና ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ አይደለም ወይም አብሮ መራመድ አልተቻለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በክልሉ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እምብዛም ያልተዘረጋ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃን በፍጥነት ለሚፈለገው ዓላማ ማዋል አዳጋች ነው፡፡ የቴክኖሎጂው ዕድገት ፈጣን በመሆኑ ከዚሁ አጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል የአቅም እና የአስተሳሰብ ደረጃ መድረስ አልተቻለም፡፡ ይህም በመሆኑ ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የዕውቀት እና የንቃት ደረጃ ማቅረብ አለመቻል ሌላው ማነቆ ነው፡፡ የማህበራዊ ሚዲያ በፍጥነት በመስፋፋቱ ሀሰተኛ መረጃዎች እየጨመሩ መጥተዋል፡፡ እነዚህን ሀሰተኛ መረጃዎችን መግታት አለመቻል በገጽታ ግንባታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡ የክልሉን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ የገጽታ ግንባታ በሚፈለገው ልክ አለመሠራቱ የዘርፉ ዋና ዋና ማነቆዎች/ተግዳሮቶች ይሆናሉ፡፡

## ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ ከቀረበው የአፈፃፀም ግምገማ መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስቀጠል ጐን ለጐን በተለይም (1ኛ) የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ከማምጣት አንፃር የኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ ዕድገት ስለሚፋጠንበት፣ (2ኛ) የግብርናው ዘርፍ ሰለሚዘመንበት፣ (3ኛ) የማዕድንና ቱሪዝም ዘርፎች ስለሚያድጉበት፣ (4ኛ) የታክስ ገቢ የክልሉን ኢኮኖሚ ዕድገት በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ፈጥኖ ስለሚያድግበት፣ (5ኛ) በግብርናው ዘርፍ በተለይም የብርዕ ሰብሎችን ምርታማነት ለማሳደግ ስለሚቻልበት፣ (6ኛ) የመሠረተ ልማት አቅርቦቶች በክልሉ ውስጥ ስለሚዳረሱበት ወይም ክልላዊ ሽፋኑ ስለሚሻሻልበት እና በሥርጭቱ ሂደት የሚባክነው የምርት መጠንም ስለሚቀንስበት፣ (7ኛ) በትምህርት ዘርፍ በተለይም የትምህርት ተሳትፎ ስለሚሻሻልበትና የትምህርት ጥራት ስለሚረጋገጥበት እንዲሁም (8ኛ) በጤና አገልግሎት ዘርፍ በወሊድ የሚሞቱ እናቶች እና የሀፃናት ሞት ምጣኔ ስለሚቀንስበት ሁኔታ በመሪ ዕቅዱ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠት ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ የልማት አፈፃፀሙን በጥንካሬና በድክመት ስንመለከት በግብርናው ዘርፍ ለአርሶ አደሩ እርሻ ትኩረት መሰጠቱ፣ አንዳንድ ቴክኖሎጂዎች በተወሰኑ አርሶ አደሮች ተሞክሮ ውጤታማ መሆናቸው፣ በደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ የህብረተሰቡ ተሳትፎ የጎላ መሆኑ፣ ምንም እንኳን ከተቀመጠው ግብ አንፃር ዕድገቱ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በአምራች ዘርፍ የተሳተፈው የግል ባለሀበት ቁጥር እያደገ መምጣቱ፣ የካፒታል እና የተቀማጭ ቁጠባ ዕድገት መኖሩ፣ በክልሉ የኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ የሚያበረታታ መሆኑ፣ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን መለየት መቻሉ፣ በቋሚ ቅርሶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የጥገና ሥራ መሠራቱ፣ አብዛኛውን የክልሉ ቀበሌዎች ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና ዋና መንገዶች ጋር ለማገናኘት ጥረት መደረጉ፣ የንፁህ መጠጥ ውኃ በገጠርና በከተማ ለማዳረስ እና የመስኖ አገልግሎትን ለማስፋፋት የተደረገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑ፣ በርካታ ችግሮች ቢኖሩም ለትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የተሰራ መሆኑ፣ መከላከልን መሠረት አድርጎ የተቀረፀውን የጤና ፖሊሲ ለተግባራዊነቱ በመረባረብ ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት መደረጉ፣ ወጣቶች በክረምትና በበጋ የነበራቸው ተሳትፎ የጎላ መሆኑ የሚሉት በአለፉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዓመታት የታዩ ጥንካሬዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት አለመረጋገጡ፣ በአምራች ዘርፎች የምርታማነት ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ብቁ የልማት መሪ ኃይል እንዲሆን ለማድረግ የተሰራው ሥራ ብዙ የሚቀረው መሆኑ፣ የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና ብቃት ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት የሚያስፈልግ መሆኑ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት ተግባር በርካታ ተደማሪ ሥራዎችን የሚጠይቅ መሆኑ፣ የክልሉን የሀብት አቅም መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ ኢኮኖሚ በመገንባት፣ ፍትሐዊ

ልማትን በሁሉም አካባቢዎች የማረጋገጥ ሥራ ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑ፣ የመንግስትን የማስፈፀም አቅም በማሳደግ እና የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት እንዲሁም የፍትህና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በማጠናከር እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን በኩል በርካታ ሥራዎችን ማከናወን የሚጠይቅ መሆኑ የሚሉት በድክመት ወይም በክፍተት የሚታዩ በመሆናቸው በቀጣዩ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊተገበሩ የሚገባቸው አንኳር ጉዳዮች ናቸው፡፡

# 4. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መነሻዎች

የ10 ዓመቱን መሪ ዕቅድ ይዘት እና ዋና ዋና ግቦች በአግባቡ ለመወሰን በርካታ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል፡፡ መነሻ ታሳቢዎችን ከወዲሁ በግልጽ ማስቀመጥ ካልተቻለ ለጥራት ያለው ግብ ለማስቀመጥ እንዲሁም የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ተገቢነት ያላቸውን ተግባራት በትክክል መወሰንና መፈፀም አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በዚህ ደረጃ መተሳሰር ያለባቸውን ጉዳዮች ከወዲሁ በአግባቡ ለይቶ ወደ ሥራ መግባት ከተቻለ ግን ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ዕቅዱን ለማሳካት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል፡፡ ስለዚህም የዕቅድ ዝግጅት መነሻዎች በተሟላ መንገድ ተተንትነው መቀመጥ ያለባቸው በመሆኑ ዋና ዋና መነሻዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. አገራዊ የረጅም ጊዜ ርዕይ

በኢኮኖሚው መስክ በ2017 በጀት ዓመት ኢትዮጵያን የመካከለኛ ገቢ ደረጃ ካላቸው አገሮች ተርታ የማሠለፉ ርእይ ተቀርጾ ሰፊ መግባባት ከተደረሰበት በኋላ ለተግባራዊነቱ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ የመካከለኛ ገቢ የመድረስ ርዕይ የበለፀገ ህብረተሰብ የመገንባት የረጅም ጊዜ ርዕይ መንደርደሪያ ተደርጐ የሚታይ ነው፡፡ ለዚህ ርዕይ መሳካት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተነድፎ ሲተገበር የቆየ ሲሆን በተለይ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም በርካታ ተግዳሮቶች ገጥመውት ነበር፡፡ በዕቅዱ መገባደጃ ዘመን ከአለፉት መልካም ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ትምህርት በመውሰድ አገራችንን እና ክልላችንን ወደ ተሻለ ብልፅግና የሚያሸጋግር አዲስ ርዕይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአገር ደረጃ ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልፅግና ተምሳሌት የማድረግ ርዕይ ተነድፎ የቀጣይ 10 ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም የአገራችን የረጅም ጊዜ ርዕይን ለ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት መውሰድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን አገራዊ ርዕይ ዕውን በማድረግ ሂደት የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገ በቀጣይ 10 ዓመታት ተግባራዊ የሚሆን ዕቅድ ማዘጋጀት ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ 10 ዓመት የዕቅድ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ የልማት ተግባራት እንደ አገር የተቀመጠውን ርዕይ ማሳካት የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡

## 4.2. አገራዊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች

የመደመር ዕሳቤ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ማዕቀፎች ረጅም ዘመናትን ተሻጋሪ የመሆን ባህሪ ያላቸው ቢሆንም ወደ ተግባር የሚመነዘሩት በየዓመቱ እና በየአምስት ዓመቱ በሚነደፉ መርሃ ግብሮች እና ይህን ተከትሎ በሚዘጋጁ ዕቅዶች አማካይነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የቀጣዩ 10 ዓመታት፣ አምስት ዓመታት እና የአንድ ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅም የመሠረታዊ አቅጣጫዎች እና በእነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመመራት የመጣውን ለውጥ ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ ማድረግ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎቹን ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ አድርጐ መውሰድ በአንድ በኩል በፖሊሲዎቹ አማካይነት የመጣውን ለውጥ በአግባቡ ለመመዘንም ሆነ ከዚሁ ጋር አያይዞ ፖሊሲዎቹንና ስትራቴጂዎቹን በጥልቀት ለመገንዘብ የሚያግዝ ይሆናል፡፡

### 4.3. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም

የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ መሠረታዊ መነሻዎች ተቀምጠው የነበሩ ግቦችና ግቦቹን ለማሳካት በተደረገው ርብርብ የተገኙ ውጤቶች፣ ዕቅዱን በመተግበር ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በተለይም ለቀጣዩ መርሃ ግብር ዕቅድ ዝግጅት ካላቸው ፋይዳ አንፃር ታይቶ በዝርዝር መገምገምና ውጤቱን ለቀጣይ ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት መጠቀም የግድ ይላል። ስለሆነም የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም አጠቃላይ ግምገማ በማካሄድ በግምገማው ላይ ከሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች ጋር መግባባት መፍጠር፣ ለመጪው ዘመን ዕቅድ ዝግጅት ወሣኝ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል። በአጠቃላይ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ትግበራ ዘመን በዘርፍ እና በንዑስ ዘርፍ የታዩ ጉልህ ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ለ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዝግጅትም እንደ መነሻ ተወስደዋል።

### 4.4. የሕዝባችን አዳዲስ ፍላጐቶች እና ጥያቄዎች

የክልላችን ህዝብ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በመልካም አስተዳደር ዘርፍ በየጊዜው አዳዲስ ፍላጎቶችና ጥያቄዎችን ያነሳል። በመሆኑም የቀጣዩ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ዝግጅት እነዚህን አዳዲስ የሕዝብ ፍላጐቶች እና ጥያቄዎችን ለመመለስና ሕዝብን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ በመነሻነት መውሰድ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድ እያንዳንዱ ሴክተር ከዘርፉ አንፃር በቀጣይ የመርሃ ግብር ዓመታት የህዝቡን ተሳትፎ ባረጋገጠ መንገድ በዕቅድ ሊመለሱ የሚገቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ከወዲሁ መለየት እና በዕቅድ መመለስ እንዲቻል ተገቢው ትኩረት መሰጠት ይኖርበታል።

### 4.5. የፌደራል የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

በአገር ደረጃ የተቀመጠውን የረጅም ጊዜ ርዕይን ለማሳካት ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ የሴክተር አደረጃጀቶች የተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠይቃል። ስለሆነም የሴክተሮችን አገራዊ ዕቅድ ከክልል ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር በመቃኘት የመነሻ ዕቅድ ማድረግ ይገባል። በዚህ ደረጃ ያልተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀት የተቀመጡ አገራዊ አጀንዳዎችን ማሳካት ስለማያስችል በዝግጅቱ ሂደት ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ይሆናል።

### 4.6. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እና አጀንዳ አፍሪካ 2063

የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሲዘጋጅ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን ማሳካት እንደ አንድ መነሻ ተወስዶ ለተፈጻሚነቱ ሰፊ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም አበረታች ውጤት የተመዘገበባቸው መስኮች ያሉ ሲሆን ቀሪዎቹን ለማሳካት ጥረት በመደረግ ላይ ነው። እነዚህን የተለዩ ግቦች በተወሰነ ደረጃ ማሳካት ብቻ ሳይሆን ዘላቂነታቸውንም ማረጋገጥ ስለሚጠይቅ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዘመን ዘላቂ የልማት ግቦች በሚል በተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀውን የልማት ግቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ደረጃ ከግምት ማስገባት ከአገራችን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና የልማት ቅደምተከተል ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲሆኑና አገራችንም ኃላፊነቷን እንድትወጣ በሚደረግ ጥረት የክልል ድርሻን ከወዲሁ መውሰድ ስለሚገባ ተገቢነት ባላቸው ዘርፎች ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ጉዳዩን ከግምት ወስጥ ማስገባት ይገባል።

እ.ኤ.አ. ከ2013-2063 ለ50 ዓመታት የሚዘልቅና የአህጉሪቱ መሪዎችና አገራት የተስማሙበት አጀንዳ 2063 ተቀርጾ እየተተገበረ ይገኛል። በአጀንዳው ከተቀመጡ አቅጣጫዎች መካከል በአህጉሪቱ መልካም አስተደደር፣ ዴሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር፣ ፍትህና የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ጠንካራ ባህል እና የጋራ ዕሴትን መገንባት፣ በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ በተለይም ሴቶችንና ወጣቶችን ያሳተፈና በማደግ ላይ ያሉ ህጻናትን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ

ልማትን ዕውን ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ይህን በዕቅድ አካቶ መተግበር አስፈላጊ በመሆኑ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

# 5. ክልላዊ ርዕይ

**የክልሉ ርዕይ፡-** ክልሉ ከነበረበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ እና የመልማት አቅም እንዲሁም ወደፊት ሊደርስበት ከሚገባው የዕድገት ደረጃና በአገር ግንባታ ሊኖረው ከሚገባው ሚና አንፃር በመገምገም ***"ሠላምና አንድነቱ የተጠበቀ፣ የህዝብ ተጠቃሚነትና አካታችነት ባረጋገጠ መልኩ ጠንካራና የዳበረ ኢኮኖሚ የገነባ፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የቀነሰ፣ ከአቻ ክልሎች ጋር በጠንካራ ትብብር፣ በመደጋገፍና በወንድማማችነት መንፈስ የሚኖር እንዲሁም ለአገራዊ አንድነትና ብልፅግና በማበርከት ረገድ ወሳኝ ሚና ያለው ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ላይ የደረሰ ክልል መፍጠር"*** የሚል ርዕይ ተቀምጧል፡፡

# 6. የልማት መሪ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

## 6.1. ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ

በክልሉ ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት እና የሥራ አጥነት ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ከዚህም በላይ የአምራች ዘርፎች በተሟላ መልኩ በሙሉ አቅም ተግባሮቻቸውን እንዳይፈፅሙ የውጭ ምንዛሪ እና የብድር አቅርቦት ማነቆ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለዚህም መሠረታዊ ችግር የሆነው የምርታማነት ችግር እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ምርታማነትን ማረጋገጥ በመሪ ዕቅዱ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ለዚህም አቅርቦትን ወደሚያሳድጉ አምራች ዘርፎች በመሸጋገር በትኩረት ይሠራል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራቱ በፍትሐዊነቱ /የሀብት ክፍፍል/፣ በቀጣይነቱ፣ በምርታማነቱ፣ በአጠቃላይ በመዋቅራዊ ለውጥ አረጋጋጭነቱ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ይሆናል፡፡ በክልሉ በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትንና ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ አቅርቦትን የሚያበረታታ እንዲሆን ይሠራል፡፡ በዚህም የዋጋ ንረትንና ሥራ አጥነትን የሚቀንስ፣ የክልሉን ህብረተሰብ የኑሮ ደረጃ በተጨባጭ እንዲሻሻል በማድረግ ድህነትን በሁሉም መገለጫ ለመቀነስ በትኩረት ይሠራል፡፡ ለዘመናዊ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ትኩረት ይሰጣል፡፡ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ለዕድገት ምንጭ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት የሚሠራ ይሆናል፡፡

ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ያተኮሩ አምራች ዘርፎችን ከማስፋፋትና ከማሳደግ አኳያ የዕድገታችን ፍጥነት የሚለካው በማምረት አቅማችን ሲሆን ብዙ ማምረትና በማያቋርጥ ሁኔታ ሀብት መፍጠር ከቻልን ዕድገታችን የተፋጠነ ይሆናል፡፡ የክልላችንን ዋና ዋና አምራች ዘርፎችን ወስደን ብንመለከት የማምረት አቅማችን ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ነው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የሰብል ምርታማነትን መድረስ ይገባው ከነበረው የምርታማነት ድንበር የማድረስ ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በተለይም ለኤክስፖርት የሚሆኑ የሰብልና የጥራጥሬ ምርታማነትን ለማሳደግ ይሠራል፡፡ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን፣ የአበባ ልማትን፣ የመካናይዝድ እርሻን እንዲሁም የመስኖ ልማትን ለማዘመን ትኩረት ይሠጣል፡፡ የእንስሳትን ምርታማነት የሚያሳድጉ የመኖ ልማት፣ የዝርያ ማሻሻል እና የጤና ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በግብርናው ዘርፍ የግል ኢንቨስትመንትን የማሳደግ ሥራ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

የግብርና ዕድገትን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለማረጋገጥ የመሬት አቅርቦትና አጠቃቀም ጉዳይ ወሳኝ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ መሬትን የላቀ ልማታዊ አስተዋጽዖ ለማበርከት በሚያስችል አኳኋን የመጠቀም ጉዳይ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የግብርና ልማትን ቀጣይነት ባለው መልኩ የማሳደግና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ አቅርቦት መሠረት ሊሆን የሚችለው በየአግሮ ኢኮሎጂ ዞኑ ያለውን ተጨባጭ የልማት ዕድል በመለየት እነዚህን የልማት ዕድሎች አሟጦ ለመጠቀም በሚያስችል መንገድ ተለይቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያሉት ማለትም ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ያሉ የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚያመርቱት ምርት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም በክልላችን ነባሮችን አምራች ኢንዱስትሪዎች የማጠናከርና አዳዲስ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት ይሠራል፡፡ በአነስተኛ ደረጃ የተጀመሩ የማምረት እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራዞችን እያደራጁ ወደ ማምረት የሥራ ዘርፍ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

አምራች ዘርፎች አቅርቦት መር በሆነ አግባብ ምርቶችን እንዲያመርቱ የሚያስችላቸው የቴክኖሎጂና የሥልጠና ድጋፍ ይሠጣል፡፡ የክልሉ አምራች ዘርፎች ምርታማና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በገበያ ተነፃፃሪ ተጠቃሚነታቸውን (comparative advantage) ሊያረጋግጡ በሚችሉባቸው ምርቶች ላይ አተኩረው እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በአምራች ዘርፎች መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ በመከተል በዘርፎች ውስጥም ሆነ የጎንዮሽ ትስስር እንዲኖራቸው ይሠራል፡፡

ሌላው የክልላችን አምራች ዘርፍ የማዕድን ዘርፉ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ያለንን ሀብት አሟጠን ወደ ማምረት ካለማስገባት ጀምሮ በትክክል የክልላችንን የማዕድን ሀብት በጥናት የመለየትና ባለሀብቶችን የመሳብ እንዲሁም ህገወጥነትን መልክ ማስያዝ አለመቻላችን ትልቅ ጉድለት ነው፡፡ በመሆኑም የዘርፉን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ የጥናት ሥራ በማካሄድ ወደ ተሟላ የማምረት ሂደት ውስጥ በማስገባት ከዘርፉ የሚገኘውን የላቀ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ፡፡ በመሆኑም በአምራች ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ሲሆን ለዚህም የግሉ ዘርፍ በዋነኛነት ተሳታፊ የሚሆንበትን ሁኔታዎች የማመቻቸትና ከውጭም ይሁን ከአገር ውስጥ ወደ ክልሉ የሚመጡ ኢንቨስተሮችን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት በትኩረት ይሠራል፡፡

## 6.2. የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ብቁ የልማት መሪ ኃይል እንዲሆን ማድረግ

የክልሉ ኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ያለ ሲሆን ለዚህ ደግሞ መሠረታዊ መንስኤው የምርታማነት ችግር ነው፡፡ ለምርታማነት ማነቆው ደግሞ የአምራች ዘርፎች አለመስፋፋትና የመንግስት ኢንቨስትመንትም በከፍተኛ ሁኔታ የአምራች ዘርፎችን እንቅስቃሴ ያሳደገ አለመሆን ነው፡፡ በዚህም የግሉ ኢንቨስትመንት የሚገባውን ድርሻ ባለማግኘቱ ምክንያት የማምረት ሥራዎች ኢኮኖሚውን ከችግር ሊያወጡት አልቻሉም፡፡ መንግሥት መሠረተ ልማት ማስፋፋት ላይ ሲያተኩር የግል ዘርፉ ደግሞ ምርትና አገልግሎትን በማምረት ለገበያ እንደሚያቀርብ ታሳቢ ተደርጎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የመንግስት ኢንቨስትመንት የግል ዘርፉን በማነቃቃት ረገድ የሚፈለገውን ውጤት አላስገኘም፡፡

ስለሆነም የክልሉ ኢኮኖሚ አሁን ካለበት ደረጃ አድጎ ወደ ላቀ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማደግ የግድ ይላል፡፡ በዚህም መሠረት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ትብብር ላይ የተመሠረተ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ማስፋፋት፣ በግሉ ዘርፍ የሚስተዋሉ ውስንነቶችን በጋራ በማስተካከል ለጠንካራ የግል ዘርፍ ልማት ጥረት ይደረጋል፡ ፡ የክልሉ መንግስት ለግሉ ዘርፍ መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን ማለትም የህግ ማዕቀፎችን የማሻሻል፣ ማበረታቻዎችን የማቅረብ፣ የግሉን ዘርፍ በመሬት፣ በብድር አቅርቦት እንዲሁም አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት በሙሉ አቅም የመደገፍ ሥራዎች በትኩረት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢያዊ ሁኔታን በመፍጠር እንዲሁም ከመንግሥት የሚጠበቁ ድጋፎችን በመለየት በተለይም የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በወሳኝ ዘርፎች ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ግቦችን በማሳካት ረገድ የዘርፉ ዋና ተዋናይ የሆነው የግሉ ዘርፍ ያለበትን የቴክኖሎጂ አመራረጥና አጠቃቀም፣ የአሠራርና የአመራረት ዘዴ፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የገበያ ትስስር ችግሮች በመፍታትና ድጋፍ በመስጠት የዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ ትኩረት በመስጠት ይሠራል፡፡

እንዲሁም ብቃት ያላቸው ደጋፊ ተቋማት በማደራጀት የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪነት ለማጠናከርና የኢንዱስትሪ ልማትን በማፋጠን መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ሊሠራ ይገባል፡፡ ስለሆነም ነባር ተቋማት ያለማቋረጥ አቅማቸው እንዲገነባ ማድረግና የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ የሚያስችላቸውን አመራርና ማስተካከያ ወቅቱ ከሚጠይቀው ፍላጎት ጋር በማስተሳሰር የመስጠት፣ አዳዲስ የተቋቋሙትም መሠረተ-ልማት ከሟሟላት ጀምሮ የተሟላ ቁመና እንዲኖራቸው የማድረግ፣ የተቋማት ትስስርን በመፍጠር (ኢንዱስትሪውን ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከቴክኒክና ሙያ፣ ከምርምር ተቋማት) የሚፈለገው የሰው ኃይል ልማት የሚካሄድበትንና በሥራ ላይም የሚሰለጥንበት፣ የምርምርና ሥርፀት ሥራዎች የሚዳብሩበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

የግሉ ዘርፍ የማያቋርጥ የምርታማነትና የምርት ጥራት ማሻሻል ሥራ ዋነኛ ተግባር እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትኩረት የተሰጣቸውን ንዑስ ዘርፎች የማስፋፋትና አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና የድጋፍ ማዕቀፎች እንዲመቻቹና ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## 6.3. የሴቶችንና የወጣቶችን ተሳትፎ፣ ተጠቃሚነትና ብቃት ማሳደግ

የልማት መሪ ዕቅዱ ሊሳካ የሚችለው ያለንን የሰው ኃይል ወደ ልማት ማስገባት ሲቻል ነው። ከዚህ አኳያ ወጣቶችና ሴቶች በልማቱ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ የማይታለፍ ጉዳይ ነው። ስለሆነም የወጣቶችንና ሴቶችን አቅም የመገንባት፣ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ የማመቻቸት፣ የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የማስፋፋት እንዲሁም የሥራ ዕድሎችን መፍጠር የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ፡ በክልሉ እየተነደፈ ያለውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትና ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ ተግባራዊ በማድረግ የፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ የሴቶችና ወጣቶችን መብት እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማስጠበቅ ቁልፍ የልማት ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

## 6.4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት

ሁሉን አቀፍ ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት መገንባት ወሳኝ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰቱ የአየር ንብረት ለውጦች ሳቢያ በህዝብና በንብረት ላይ በርካታ አደጋዎች እየተከሰቱ መምጣታቸው ይታወቃል።ይህንን ሁኔታ ለመቀየር እና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በአገር ደረጃ ተቀርጾ ወደ ሥራ በመገባት ላይ ነው። በዚህ ረገድ በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በተፋሰስ ልማት ህዝባዊ ንቅናቄ ሰፊ ጥረት የተደረገና አጥጋቢ ውጤትም እየተመዘገበበት ያለ መሆኑ ይታወቃል።

በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመንም ይህ መልካም ጅምር በተለየ ትኩረት ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህም የተጀመሩ ተግባራትን በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ከማስፋት ባሻገር የተፋሰስ ልማት በተሠራባቸው አካባቢዎች ያሉ የተለያዩ ስትራክቸሮችን እና ማጠናከሪያ ተጨማሪ ሥራዎችን በመሥራት ዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግና ጥቅም መስጠት ወደ ሚችሉበት ደረጃ ማሸጋገር፣ የደን ልማት ሥራዎችን ማስፋትና ማጠናከር፣ የኢነርጂ ቆጣቢ ምድጃዎችንና ባዮጋዝ ማብለያዎችን በስፋት ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ በገጠር የኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራምን ሥራ ላይ ማዋል እና በአገር ደረጃ ከተቀረጹ ፕሮግራሞች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት በስፋት መፈጸም ይጠይቃል፡፡ በአጠቃላይ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ በሁሉም ደረጃዎች በሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች እንዲካተት እና ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ አፈፃፀሙን በቅርበት የመከታተል፣ የመገምገምና አስፈላጊ ድጋፎችን የመስጠት አቅጣጫ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

## 6.5. የክልሉን የሀብት አቅም መሠረት ያደረገ ቀልጣፋ ኢኮኖሚ መገንባት

ለአምራች ዘርፎች ልማት የልማት ቀጣና ምቹነት መሠረት ያደረገ የዕድገት ማዕከላት (Growth Corridors) አካባቢዎች ይለያሉ። በተለዩት ማዕከላት በተቀናጀ አኳኋን የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ተለይተው ተግባራዊ

ይደረጋሉ። በቀጣይነትም በየልማት ፀጋ ቀጣናዎች ሊኖሩ የሚችሉ የዕድገት ማዕከላትን በጥናት የመለየት ዘለቄታ ያለው የልማት ሥራ ይከናወናል። በክልሉ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የአካባቢን ፖቴንሻል መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን ይሠራል። ዘመናዊ የግብርና ልማት ሥራዎች በሰብልም ሆነ በእንስሳት ሀብት ልማት ያሉ አቅሞች እንዲለዩ በማድረግ ያለውን ከባቢያዊ ፀጋ ወደ ላቀ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ በማሸጋገር ለክልሉ የኢኮኖሚ ለውጥ የሚኖራቸውን ሚና የማሳደግ እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የአካባቢን ሀብት መሠረት በማድረግና ክልሉ የሚኖረውን ተነፃፃሪ ተጠቃሚነት እንዲሁም ጥሬ ዕቃንና የገበያ ዕድልን መሠረት በማድረግ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ተመርጠው እንዲቋቋሙ የሚያስችል አቅጣጫ መከተል የግድ ይላል። እንዲሁም ዘመናዊ የአገልግሎት ዘርፎችም አካባቢን በለየ መልኩ እንዲስፋፉ የተለየ ትኩረት ይሰጣል።

## 6.6. ፍትሐዊ ልማትን በሁሉም አካባቢዎች ማረጋገጥ

በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሠራሽ ምክንያቶች የክልላችን ሁሉም አካባቢዎች በተመጣጠነ የልማት ደረጃ ላይ ባለመሆናቸው የህዝቦች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በሚፈለገው ደረጃ የተረጋገጠበት አይደለም። ይህንን መሠረት ያደረገ የልማት ቀጣናዎች ጥናት በክልላችን መካሄዱ የሚታወስ ቢሆንም ከዚህ ጥናት አንፃር በዘርፎች በኩል ተጠያቂነት ያለው ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀት ወደ አፈጻጸም ማሸጋገር አልተቻለም። በተለይም የተከዜ ተፋሰስ አካባቢዎች የዝናብ አጠር አካባቢዎች በመሆናቸው እንደ ክልል ከሚቀመጡ ጥቅል አቅጣጫዎች አንፃር በአካባቢው ያሉ ህዝቦችን ችግር መፍታት ያዳግታል። በተመሳሳይ ሰፊ ሽፋን ባለው የክልሉ ደጋማ አካባቢዎች የሚኖሩ በርካታ ህዝቦች የሚያመርቷቸው የግብርና ምርቶች ከእጅ ወደ አፍ ያለፈ ባለመሆኑ የህዝቦች የኑሮ ደረጃም መሻሻል አይታይበትም። ይህ ባለመሆኑ በእነዚህ በተጎዱ የክልላችን አካባቢዎች ያሉ በርካታ ህዝቦች የእኩል ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ጥያቄ እያነሱ በመሆናቸው ጥያቄያቸው በተገቢው መንገድ መመለስ ይኖርበታል። ስለሆነም በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን በእነዚህ አካባቢዎች ያሉ ህዝቦች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን የሚያስችላቸውን በአካባቢ የመልማት አቅም ላይ የተመሠረተ እና በልማት ወደኋላ የቀሩ የክልላችን አካባቢዎችን ማዕከል ያደረገ የልማት አቅጣጫ መከተል ይገባል።

## 6.7. የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም በመገንባት፣ የህዝቡን ተሳትፎ በማጐልበት ፍትህንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን

የአንድን መንግስት ውጤታማነት ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ተልዕኮውን በአግባቡ የሚፈፅም ተቋም የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ነው። ውጤታማ ተቋም እንፍጠር ሲባል የመጀመሪያው ጉዳይ ለተቋማቱ ብቁ መሪ መፍጠር ነው። ብቁ መሪ ያለው ተቋም ውጤታማነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በክልሉ ተቋም የመገንባት ጉዳይ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ ተወስዷል። ሌላው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሁሉም ደረጃ የሚገኘውን የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ሲሆን በክልሉ የማስፈፀም አቅም በዕውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት የበቃ የሰው ኃይል እንዲፈጠር ማድረግ፣ በዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን የሚሰጡ አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ስታንዳርድ የወጣላቸው እና ለአካባቢው ነዋሪ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች ናቸው። ለውጡ የአገልግሎት ቅልጥፍናን፣ የሥራ ውጤታማነትን፣ ተጠያቂነትንና ግልፀኝነትን ባጣመረ አኳኋን እንዲፈፀም ለማድረግ ይሠራል። ከዚህም አኳያ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የተሠማራውን የሰው ኃይል ለማብቃት ልዩ ትኩረት ይሠጣል። የህግ የበላይነትን ለማስፈን የህግ አስከባሪ ተቋማትን በአመለካከት፣ በቁሳቁስና በሠለጠነ የሰው ኃይል የማጠናከርና የፍትህ አስተዳደር ሥርዓቱን የፍትህ አገልግሎት ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ማጠናከር ተገቢ ይሆናል። በአጠቃላይ የመንግስት ጉድለትን የሚሞላ ሥርዓት መዘርጋት፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ሊያረጋግጡ የሚችሉ ስትራቴጂዎች፣ የህግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ማድረግና ዘላቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት በትኩረት የሚሠሩ ይሆናል።

# 7. የ10 ዓመቱ መሪ የልማት ዕቅድ የትኩረት መስኮች

ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር መረጋገጥ እንዲሁም ተወዳዳሪ ኢኮኖሚ ከመገንባት አንፃር ያላቸውን የጎላ ድርሻ መሠረት በማድረግ በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ልዩ ትኩረት የሚደረግባቸው መስኮች ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 7.1. ብዝሀ ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮች ልማት ላይ ማተኮር

እስከ አሁን ከነበረው በተለየ መልኩ በአንድ ዘርፍ እና የዕድገት ምንጭ ከማተኮር ይልቅ ወደ ብዝሀ ዘርፍ እና ብዝሀ የገቢና የዕድገት ምንጭ ላይ ማተኮር የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ከማምጣት አንፃር እንደ ወሳኝ ጉዳይ ታይቷል። እነዚህም ግብርናውን ማዘመን፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ ማዕድን፣ ቱሪዝም እና የከተማን ዕድገት መሠረት ያደረገ የአይሲቲ (ICT) ዘርፍ እንደ ተጨማሪ የዕድገት እና የሥራ ዕድል ምንጮች ተደርገው ተለይተዋል።

### 7.1.1 የዘመናዊ ግብርና ልማት

የግብርና ዘርፍ በክልሉ በአብዛኛው በአነስተኛ አርሶ አደሮች የሚካሄድ ሲሆን ከክልሉ ህዝብ ከ75 በመቶ በላይ የሚገመተው መተዳደሪያው የሆነና ከክልሉ ዓመታዊ ጠቅላላ ምርት ውስጥ 53 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን ዘርፉ በዋናነት ከፍተኛ ድርሻው በሰብል ልማት የተያዘ ሲሆን ምርታማነቱን ሲታይ 24.1 ኩንታል በሄክታር ሲሆን ይህም ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የአርሶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ረገድ እና የምግብ ዋስትናን በክልሉ ለማረጋገጥ የነበረው ፋይዳ እንዲሁም ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እያበረከተ ያለው አስተዋጽዖ በጣም አናሳ ነው። ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቅ ሚና ሲታይ በምግብ እህል አቅርቦት በራስ አቅም ከማሟላት ባለፈ ኢኮኖሚውን የማሳደግ፣ ለኢንዱስትሪው በግብዓትነት ጥሬ ዕቃዎችን የማቅረብ፣ ገበያ የመፍጠር እና የውጭ ምንዛሬ የማስገኘት፣ የሥራ ዕድል የመፍጠር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ግብርናን በተመለከተ ባለ ሁለት ፍኖት አቅጣጫ መከተል በተለይም የአነስተኛ ባለይዞታ ግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ከማስቀጠል ጎን ለጎን ለዘርፉ መዘመን የሚያግዙ ሜካናይዝድ መሣሪያዎችን እና ግብዓቶችን የመጠቀም፣ የግል ባለሀብቶችን ያሳተፈ የግብርና ሥርዓት የማበረታታት ተግባራት በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል።

በመሆኑም ዘርፉ በልማት መሪ ዕቅዱ ዘመን ማነቆዎቹ ተፈተውለት ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም አርሶ አደሩ ፈጣን የሆነ የምርትና ምርታማነት ዕድገት በማምጣት የዘርፉ ዋና የዕድገት መሠረት ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል፣ የተማሩ ወጣቶችን በማደራጀት በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ፣ የመስኖ ልማትን ማስፋፋት፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በግብርና ኢንቨስትመንት እንዲሰማሩ ማበረታታት እና መሳብ፣ እንዲሁም ለሁሉም ተዋናዮች አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን በማምረትና በማቅረብ የግብርናውን ዘርፍ መደገፍ በመሪ ዕቅዱ ትኩረት የሚደረግባቸው ዋነኞቹ የትኩረት መስኮች ናቸው።

### 7.1.2 የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት

ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት አንፃር የኢኮኖሚ ሽግግር እና ኢንዱስትሪያላዊነት ያለዘመናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት የማይታሰብ ሲሆን በተለይም እያደገ የመጣውን ህብረተሰብ የኢንዱስትሪ ምርት ፍላጎት ለመሸፈን፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ ግብርናን ለማዘመንና በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ ለመሆን አዳጋች ያደርገዋል። በዚህ ወቅት ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መሬቱን አልምቶ ለማስተላለፍ እና ሌሎችንም የድጋፍ ሥርዓቶች ተግባራዊነት ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም ተግባራትን ለመፈጸም ከላይ እስከታች ያለው ፈጻሚ የአቅም ክፍተት እንዳለበት ይስተዋላል። በሌላ በኩል የግብዓት፣ የመሠረተ ልማት እና የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን

ድጋፎች እጥረት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ዘመን የአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሁለንተናዊ ችግሮች በጥናት ለመለየት ጥረት የተደረገ ሲሆን የተለዩ ችግሮችም የግብዓት፣ የመሠረተ ልማት፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ እና የፋናንስ አቅርቦት ችግሮች ነበሩ፡፡ ምንም እንኳን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ቢሆንም በጥናት የተለዩ ችግሮችን ከመፍታት አንፃር ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

የአምራች ኢንዱስትሪዎችና የሌሎች ፕሮጀክቶችን የመሠረተ ልማት አቅርቦት በማሳደግ በኩል የተደረገው ጥረት ሲታይ በቂ መሬት በማዘጋጀት እንዲሁም በኢንቨስትመንት መሬቶች በቂ መሠረተ ልማቶችን በማቅረብ በኩል ችግሩ ሰፊ በመሆኑ ባለው ኢንቨስትመንት ፍሰት ልክ መሬት ማዘጋጀትና መሠረተ ልማት ማሟላት ያልተቻለበት ሁኔታ በመኖሩ በመሪ ዕቅዱ ዘመን እነዚህን እና መሰል ችግሮች እንዲቀረፉ በትኩረት መሥራት ተገቢ ይሆናል፡፡

የዘርፉ ምርታማነት ማነስ አንዱ ምክንያት በክልሉ ያሉ የነባር ኢንዱስትሪዎች ቴክኖሎጂ በዝቅተኛ የማምረት አቅም ላይ የሚገኝ ከመሆኑም ባሻገር ኢንዱስትሪዎቹ በማምረት አቅማቸው ልክ እያመረቱ አለመሆኑ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን ዕድገት በመወሰን ረገድ የቴክኖሎጂ አቅምን ማሳደግ እና ኢንዱስትሪዎቹ በሙሉ አቅማቸው ሊያመርቱ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡ ፡ እንዲሁም የተቋማቸውን የሙያ አቅም ለማሳደግ እንዲነሳሱ የሚያበረታቱ የኢንዱስትሪ የህግ ማዕቀፎች ተቀርጸው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

ለማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚቀርበው የሰው ኃይል ከብዘት በተጨማሪ ጥራትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን የተጀመሩ የኢንዱስትሪ እና የትምህርት ተቋማት ትስስር እየተካሄዱ ባሉ የአቅርቦት-ፍላጎት ጥናቶች ግኝት መሠረት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ምርታማነትን፣ ጥራትንና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታን አስመልክቶ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው በዕቅድ ዘመኑ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ ነባር የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ያለባቸውን ችግሮች ለይቶ በመፍታት እና አቅማቸውን በማጠናከር፣ ሀብቱ ቢኖራቸውም የንግድና አገልግሎት እንዲሁም የኮንስትራክሽን የሥራ መስክን መልቀቅ የማይፈልጉትን በማስተማርና ከዚህ ጎን ለጎን የኪራይ ሰብሳቢነት በሩንም በማጥበብ ለውጥ እንዲያመጡ ማነሳሳት፣ ፕሮጀክት የመቅረጽ የብቃት ችግራቸውንም ግምት ውስጥ በማስገባት አትራፊ የሆኑትን ኢንዱስትሪዎች በመለየትና የአዋጭነት ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪውን እንዲቀላቀሉ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ይተገበራል፡፡

ነባር ኢንዱስትሪዎችን ማሻሻልና የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችንና የምርት ዓይነቶችን ማስፋፋት፣ የውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶችን በብዛትና በጥራት መሳብ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማስፋፋትና ክላስተሮች እንዲፈጠሩ ማድረግ፣ በውጭና በአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል የገበያ፣ የቴክኖሎጂ እና የማኔጅመንት ዕውቀት ሽግግር መፍጠር የሚያስችል ትስስርን ለመፍጠር ይሠራል፡፡

በተጨማሪም ስትራቴጂክ የሆኑና የገበያ ክፍተቶች የሚታይባቸውን የሥራ መስኮች በመለየት የመንግስትን ጣልቃ ገብነት በጋራ ልማትና በተናጠል ማመቻቸት፣ የግብርና እና የኢንዱስትሪን፣ የባለድርሻ አካላትን፣ የመንግሥትንና የግሉን ዘርፍ፣ የሠራተኛንና የባለሀብት ቅንጅትን በላቀ ደረጃ ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገት የሁሉንም ህብረተሰብ በተለይም የወጣቶችና ሴቶችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት (equitable & inclusive growth) ማረጋገጥ፣ ነፃ ውድድር የሚያሰፍን፣ ማህበራዊ ልማትን የሚደግፍ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ የማያስከትል አረንጓዴ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ዕድገት ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡

### 7.1.3 የማዕድን ሀብት ልማት

የግብርና ዝመና፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማትና የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማት ያለ መሠረታዊ የማዕድን ግብዓቶች የሚገኘው ውጤት አመርቂ አይሆንም፡፡ ከዚህ አንፃር ማዕድናትን ወደ ውጭ ሸጦ ከሚገኝ የውጭ ምንዛሬ በላይ በአገር ውስጥ ታንጸው ለብዝሀ ዘርፍ ልማት ቢውሉ የተሻለ አቅም የሚፈጥሩ ይሆናል፡፡

የማዕድን ልማት ዘርፍ ምንም እንኳን በበርካታ ፈተናዎች የታጠረ ቢሆንም በቀጣይ የልማት መሪ ዕቅዱ ዓመታት በሚደረግ ሰፊ ሥራና ልዩ ትኩረት የክልሉ መንግሥት ላቅ ያለ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ከዘርፉ ይጠብቃል። የማዕድን ዘርፍ ከሌሎች ዘርፎች አንፃር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ በማቅረብና በውጭ ገበያ ላይ በመቅረብ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል ቢሆንም ይሰጠው የነበረው ትኩረት አናሳ በመሆኑ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን የላቀ ጥቅም ሳያስገኝ ቀርቷል። የማዕድን ልማት ዘርፍ ሌሎች የልማት ሥራዎችን የሚያነቃቃ ይሆናል። የማዕድን ዘርፉ የማኅበረ-ፖለቲካዊ ልማት እና የመሠረተ-ልማት ግንባታዎችን እንዲያፋጥን ለማድረግ በአገር ደረጃ በአለፉት ዓመታት የማዕድን አምራች ኩባንያዎችን ለማነቃቃት የታክስ ቅናሽ የተደረገ ቢሆንም በክልላችን በዘርፉ ያለው እንቅስቃሴ ውስንነት ያለበት ነው።

ስለሆነም በቀጣይ በክልሉ በኢንዱስትሪ ማዕድናት ላይ ትኩረት ይደረጋል። ወርቅ፣ ብረት፣ ኦፓል፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናት ወዘተ የመሳሰሉ ማዕድናት አሉን። ሌላው ከፍተኛ የመሠረተ-ልማት ግንባታ በማካሔድ ላይ እንገኛለን። የግንባታው ዘርፍ ከማዕድን ልማት ግብዓት እየፈለገ ነው። ስለዚህ ይኸም ትኩረት የምናደርግበት ሌላው ሥራ ነው። ደካማው መሠረተ-ልማት፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል እጦት፣ እና በፈቃድ አሰጣጥ ዙሪያ ግልፅነት አለመኖሩ የዘርፉን እንቅስቃሴ ጎድተውታል። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በመፍታት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብና ነባር ኢንቨስትመንቶችን በማጎልበት ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ማዕድናትን በዓይነት፣ በጥራትና በመጠን በማሳደግ የምንዛሪ ግኝትና የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ የቀጣይ የትኩረት መስክ ነው።

### 7.1.4 የቱሪዝም ልማት

የቱሪዝም ሀብት ለውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ ለአገልግሎት ዘርፎች በተለይም ለሆቴል ኢንዱስትሪ እና ለትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት አስተዋጽዖው በጣም ከፍተኛ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የሚጫወተው ሚና የጎላ ነው። የአማራ ክልል ዓይነተ ብዙ የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መዳረሻዎች (የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሀብቶች) ያሉት ነው። ምንም እንኳን ክልላችን በርካታ የቱሪዝም ሀብቶች ቢኖሩትም ከዘርፉ የሚፈለገውን ያህል ጥቅም እያገኘ አይደለም። ይህ ዘርፍ ድህነትን ለማስወገድ እና ለልማት ቀጥተኛ አስተዋጽዖ የሚያበረክት ኢንዱስትሪ በመሆኑ ጥቅም ላይ በማዋል ተጨባጭ የሆነ ለውጥ ማምጣትና በዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ ማድረግ ያስፈልጋል።

ስለሆነም በዘርፉ በሥነ ምግባር፣ በዕውቀት፣ በክህሎት እና በአደረጃጀት የተቃኘ አገልግሎት መስጠት ይገባል። የክልሉን ባህላዊ፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች የሚወድ፣ የሚጠብቅ፣ የሚያበለፅግና ወደ ልማት ኃይልነት የሚቀይር ትውልድ በመፍጠር፣ ባህልና ኪነ-ጥበብን ዋነኛ የልማት ኃይል በማድረግ እና የቱሪስት መስህቦችን በማስተዋወቅ የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይሠራል። እንዲሁም ቅርሶችን በመጠበቅ፣ በማጥናትና በመመዝገብ ለቅርሶች ክትትል፣ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፣ ሙዚየሞችን ማደራጀት መምራትና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። በተጨማሪም የክልሉን ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥራቱን በጠበቀና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ገበያ መፍጠር፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የቱሪስት መረጃ ማዕከል እንዲኖር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

### 7.1.5 የኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት

የክልላችን ኢኮኖሚ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለኢንፎርሜሽን፣ ኮሚዩኒኬሽን ና ቴክኖሎጂ እየተሰጠ ያለው ትኩረት አናሳ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በዚህ ዘርፍ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ባለማደጉ ለኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ለፈጠራ ሥራዎች መንግስት ከፍተኛውን ድርሻ ሊወስድ ይገባል። ከዚህም አንፃር አስፈላጊ የመሠረተ ልማት ዓይነቶችን በአግባቡ በመለየት፣ ያሉትንና የተጀመሩትን ተቋማት የማጠናከርና የማስፋፋት እንዲሁም በቀጣይ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን የመገንባት ሥራ የሚከናወን ይሆናል። በአገርም ሆነ

በክልል ደረጃ ዕውቀት መር ኢኮኖሚን ለመገንበት በተያዘው አቅጣጫ መሠረት ለዕውቀት፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ልዩ የማበረታቻና ማትጊያ ሥልቶችበመቀየስ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት ጋር በመተባበር የሚሠራበት ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል። እንዲሁም በመንግስት በኩል ለጥናትና ምርምር ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምርምር ተቋማት በቴክኖሎጂ ማላመድና ፈጠራ ላይ አተኩረው እንዲሠሩ አቅማቸውን ለማሳደግ ይሠራል። በዚህም የጥናትና ምርምር ሥራው በክልሉ እንዲመጣ የሚፈለገውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ በሚደግፍና በሚያፋጥን መልኩ በተመረጡ የምርምር ሥራዎች፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ መቅዳት፣ ማላመድና ሥርፀት ላይ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራ ደረጋል።

## 7.2. ዘላቂ የከተማ ልማት

በክልሉ የሥነ ህዝብ ትንበያ መሠረት የክልሉ የህዝብ ብዛት እየጨመረ የሚገኝ እንደሆነ መረጃው ያመላክታል። በቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጨምርም ይገመታል። ከዚህም በተጨማሪ ከገጠር ወደ ከተማ ያለው ፍልሰት በየዓመቱ እየጨመረ የሚገኝ ሲሆን ከተሞችን በሥርዓት ለመምራትና ህዝቡን ከከተማው ክፍለ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በማያስችል መልኩ የሥነ-ህዝብ ሁኔታው እየተቀየረ ይገኛል። በመሆኑም ለመኖሪያ እና ለሥራ ምቹ የሆኑ ዘላቂ ከተሞችን በዕቅድ መምራት ለነገ የማይባል ጉዳይ በመሆኑ የከተማ ልማት አንዱ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ዘርፍ ይሆናል። ሚዛናዊ የሆነ የከተማ-ገጠር ትስስርም እንዲኖር በትኩረት ይሠራል ።

በክልሉ የከተሞች ስሪት እና የአከታተም ሁኔታ በሥርዓት ያልተመራና በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ስለሆነም ከተሞች ለአምራች ዘርፎች ዕድገት፣ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ ለሥራ ሥምሪትና ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆኑ በዘመናዊ የከተማ ዕቅድ የሚመራ የከተሞች አስተዳደር ሥርዓት ያስፈልጋል። በተለያዩ ገፊና ሳቢ ምክንያቶች የአምራች ዘርፍ እንቅስቃሴ ከታላላቅ ከተሞች ወደ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ፣ አነስተኛ ከተሞችና መንደሮች እየተስፋፋ መሄዱን ያለፉት ዓመታት አፈጻጸም ያሳያል። ከከተሜነት መስፋፋት፣ ከአምራች ዘርፉ ሚና ማደግ እና የኢኮኖሚ መዋቅር ለውጥ ጋር ተያይዞ ከተሞች የቤቶችና ሌሎች መሠረተ ልማት አቅርቦቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም በከተሞች ፈጣንና ፍትሐዊ ልማትን ለማረጋገጥ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ያላቸውን ሚና ያገናዘበ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በከተሞች የሚገነቡ መሠረተ ልማቶች ሰፊ የሥራ ዕድልና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በሚፈጥር መልኩ ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል። በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን የከተማ አስተዳደር በዘመናዊ የመሬት አጠቃቀም ፕላንና ጠንካራ የመሬት ግብይት ሥርዓት እየተመራ ቀልጣፋና ውጤታማ የከተማ ልማት እንደሚያረጋግጥ ይጠበቃል።

## 7.3. መሠረተ ልማት

በክልሉ በመሠረተ ልማት መስፋፋት ዙሪያ ያጋጠሙ ችግሮችን በመቅረፍ በዘርፉ የሚከናወኑ ኢንቨስትመንቶችን በከፍተኛ መጠን መጨመር፣ የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲፋጠን በተለይ የኢንዱስትሪውን ክፍለ ኢኮኖሚ በአግባቡ ለመምራት የተሟላ መሠረተ ልማት እንዲኖር ማድረግ በትኩረት ይሠራል። ለዚህም መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት የትራንስፖርት፣ የመገናኛና የኃይል አቅርቦትን በጥራትና በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ እንዲሁም ለመንገድ፣ ለኢነርጂ፣ ለመስኖ፣ ለመጠጥ ውኃ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ለማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። በክልሉ በተለይ በመንገድ መሠረተ ልማት ዙሪያ የገጠር ቀበሌዎችን ደረጃቸውን በጠበቁና ክረምት ከበጋ በሚያገለግሉ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር የማገናኘት ሥራ አንዱ የትኩረት መስክ ነው። የክልሉን የኢነርጂ ፍላጎት ለማሟላት ንፁህና አየርን የማይበክል የታዳሽ ኃይል ምንጮችን ማስፋፋት ማለትም ከውኃ ኃይል የመስኖ ግድቦችን በመጠቀምና የፀሐይ ኃይል አማራጮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

የክልሉን የውኃ ሀብት ለተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት እንቅስቃሴዎች ዘላቂና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠቀምና ማልማት፣ አጠቃላይ የውኃ ሽፋንን ማሳደግ፣ የመስኖ ግንባታዎችን ለማስፋፋት ይሠራል።

የኮንስትራክሽን መሠረተ ልማት ዘርፍ የሰው ኃይልን በብዛት የሚጠቀም፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበትና የግሉ ዘርፍ ከፍተኛ ሚና የሚጫወትበት እና ከሙስና በፀዳ መልኩ ለአጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚ የሚኖረውን አስተዋጽዖ ለማሳደግ በሥርዓት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

በክልሉ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መሠረተ ልማቶች በጥራት ባለመስፋፋታቸው በርካታ ችግሮች ይስተዋሉበታል፡፡ የትራንስፖርት አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረግ አንፃርና ከአመቺነት አኳያ ሲታይ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ሌላው በመንግስትም ሆነ በግል የትራንስፖርት መዳዳዣ አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በገጠርም ሆነ በከተሞች ደካማ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በክልል ደረጃ ያለውን የትራንስፖርት አቅርቦት የማሻሻልና አገልግሎቱን በጥራት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለማድረስ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 7.4. የሰው ኃብት ልማት እና የሥነ-ህዝብ ትሩፋት

እንደ ክልል ጥራት ያለው ትምህርት፣ አመለካከትና ክህሎት መኖር ለክልሉ የሰው ኃብት ልማት ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ በእጅጉ የጎላ ነው፡፡ ከጤና አኳያም ጥራት ያለው የጤና ሥርዓትን መገንባት ለሰው ኃብት ልማቱ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡

በመሆኑም በሰው ኃብት ልማት ዘርፍ በክልላችን የተሄደባቸው ስኬታማ ርቀቶች ለቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ትልሞች እንደ ወረት ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ኢኮኖሚው በሚፈልገው ደረጃ ብቁ፣ ተወዳዳሪ እና አምራች ዜጋ ከማፍራት አንፃር በሰው ኃይል ልማት ረገድ እየተደረገ ያለው ርብርብ በቀጣይም ተጠናክሮ ይከናወናል፡፡ በአሁኑ ወቅት የክልሉ የትምህርት ሽፋን እያደገ ያለ ቢሆንም አሁንም በትምህርት ዕድሜ ክልል ከሚገኙ ህጻናት የተወሰኑት በትምህርት ገበታ ላይ አይደሉም፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም በመዋዕለ ሕፃናት ደረጃና በ1ኛ ደረጃ ትምህርት የዕድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት ትምህርት ቤት እንዲገቡ በማድረግ የትምህርት ሽፋንን የማሣደግ እንዲሁም ተገቢነትንና ፍትሐዊነትን የማስጠበቅ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተቋማትን የማስፋፋት፣ ለደረጃው የሚመጥኑ በቂ መምህራንን የማሟላት እንዲሁም የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ የሚቀንሱ ችግሮችን የማቃለል ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በሚያስችላቸው አግባብ እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በገጠር በምርት ተግባር ከተሰማራው የሰው ኃይል አመዛኙ ማንበብና መፃፍ የማይችል እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ኃይል ቴክኖሎጂ በቀላሉ በመቀበል ምርታማነትን እንዲያሳድግ ከማድረግ አንፃር ሚናውን እንዲወጣ እንዲሁም በማህበራዊና ሌሎች መስኮች ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችል ለተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ትኩረት ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩልም የመሠረታዊ ጤና አገልግሎትን የማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራትን የማስጠበቅ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የንፁህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን እንዲሁም ሥርዓተ-ምግብ የቀጣይ ዓመታት የትኩረት መስኮች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ተቋማትን ከማስፋፋት አንፃር ሁሉም የልማት ኃይሎች ከመንግስት ጋር በተቀናጀ አግባብ ርብርብ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡ በማህበራዊ ልማት ዘርፍ ድንቅ ሥራዎች የተከናወኑበት የጤናው መስክ ነው፡፡ የጤና ፖሊሲያችን በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ የሚያተኮር ቢሆንም ከዚሁ ጐን ለጐን መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን የማስፋፋቱም ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ይሁን እንጂ በጤናው መስክ ለህብረተሰቡ የተሟላ የጤና አገልግሎት በመስጠት በኩል አሁንም በርካታ ተግዳሮቶች አሉ፡፡

በመሆኑም መሠረታዊ የህክምና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎችን በሁሉም የክልላችን አካባቢዎች ማስፋፋት፣ የጤና ተቋማቱን አገልግሎት የማሻሻልና ግብአቶችን የማሟላት ሥራም ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር የመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መሻሻልና በሽታን በመከላከሉ ሥራ ላይ

የህብረተሰቡን ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በትኩረት ይሠራል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በጤናው ዘርፍ የህብረተሰቡን ባለቤትነት በማሳደግ ጤናማና አምራች ዜጐችን ለመፍጠር ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡ ፡ መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን የሆስፒታል አገልግሎትን ለማሻሻልም የክልላችን አቅም በፈቀደ መጠን ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ይሆናል። በአጠቃላይ ሲታይ የክልሉ የሰው ኃይል ልማት የኢኮኖሚ ልማቱ ከሚጠይቀው አንፃር በጥራትም ሆነ በመጠን በማቅረብ በኩል ችግሮች ተስተውለውበታል፡፡

ስለሆነም በቀጣይ የመሪ ዕቅዱ ዓመታት የሰው ኃይል ልማት በወሳኝነት የሥራ ኃይሉ ጤናማ፣ የተማረና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚችል እንዲሆን በማድረግ ይበልጥ ምርታማ እንዲሆን ማድረግ ነው። ከዚህ አኳያ የትምህርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ጥራቱን ማሳደግ፣ ከመካከለኛ የክልሉ የትምህርት ተቋማት ሰልጥነው የሚመረቁ ወጣቶች የገበያውን ፍላጎት መመለስ የሚያስችላቸው አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ ሥልጠናው ለጥራት ትኩረት ይሰጣል። በአጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ሥራዎቻችን ከሀገራችን የትምህርት ግቦችጋር የሚጣጣሙ እና ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል በጥራት በማምረት በኩል ትኩረት ተሰጥቶቶት በየደረጃው እንዲፈፀም ይደረጋል። ጤናው የተጠበቀ የሰው ኃይል እንዲኖር ማድረግ ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ያለውን ትልቅ አስተዋጽዖ ከግምት ያስገባ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትና ጥራት የማሳደግ ሥራ የትኩረት መስክ ሆኖ ይሠራል።

**ከሥነ-ህዝብ ልማት አኳያም** የአንድ አገር መሠረታዊ የሥነ-ህዝብ ባህሪያት በአጠቃላይ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና በዜጎች ሁለንተናዊ የኑሮ ገፅታ ላይ ጉልህ ተፅእኖ አላቸው። በመሆኑም በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን በክልሉ የህዝብ ዕድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የክልሉን ህዝብ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት ለማሻሻል ይከናወናል፡፡ የሥነሕዝብን መሠረታዊ ባህሪያት ከኢኮኖሚው አቅም ጋር ለማጣጣምና የባህሪያቱን ተለዋዋጭነት መሠረት የሚጠበቀውን የዲሞግራፊ ትርፍ (Demographic Dividend) እንደቀጣይ የዕድገት ምንጭ ለማዋል የሚቻልበትን አግባብ አሁን ካለው የክልሉ የሥነ-ህዝብ ሁኔታና ቀጣይ ምልከታ አኳያ መወሰድ የሚገባቸው የፖሊሲ ርምጃዎች ተለይተው እንዲቀመጡ ለማድረግ የትኩረት መስክ ሆኖ ተወስዷል፡፡

## 7.5. ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ

በክልሉ የልማት ፋይናንስ ማመንጨትና ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአለፉት ዓመታት የክልሉን ገቢ በማሳደግ ረገድ አበረታች ሥራዎች የተከናወኑ ቢሆንም ክልሉ ለልማት ከሚያስፈልገው ወጪ እንዲሁም ከሚያመነጨው ሀብት አንፃር ሲመዘን የገቢ አሰባሰቡ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን በእጅጉ የማሳደግ እና በራስ ገቢ ወጪን የመሸፈን አቅምን ማጎልበት ትኩረት የሚሠጠው ይሆናል፡፡ ለዚህም የታክስ አስተዳደሩን ማዘመንና የአገልግሎት አሠጣጡን ፈጣንና ቀልጣፋ የማድረግ፣ የህግ መዕቀፎችን የማሻሻል፣ ግንዛቤን የማሳደግ፣ በልማት ፋይናንስ የህብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲጎለብት የማድረግ ሥራ እንዲሁም የታክስ ኦዲትን የማጠናከርና ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ ይሠራሉ፡፡

በክልሉ የሚመደብ በጀትን በሚመለከት ለልማቱ መፋጠን ይበልጥ አስተዋጽዖ ለሚኖራቸው ዘርፎች እንዲሁም ለቁሳዊ ሀብቶች መጨመር አስተዋጽዖ ላላቸው የካፒታል ፕሮጀክቶች ትኩረት በማድረግ የፋይናንስ ውጤታማነትን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ የካፒታል ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ወጪ መሠረት እንዲከናወኑ እና የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ ለማድረግ የፕሮጀክት አመራር አቅምን የማሳደግ ሥራ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በልማት ትብብር የሚገኙ የፋይናንስ አቅሞችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል፣ ወጪ ቆጣቢ አሠራሮች መከተል፣ ተጠያቂነት ሊያመጣ የሚችል አሠራር መዘርጋት ትኩረት ይሠጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ለኢንቨስትመንት የሚውለውን መዋዕለ ንዋይ ከማሳደግ አንፃር ቁጠባን በእጅጉ የማሳደግ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ለመደገፍ የብድር አሠጣጥ ሥርዓቱን ምቹና ተደራሽ የማድረግ ሥራ ትኩረት ይሠጠዋል፡፡

### 7.6. ተቋማዊ አቅም መገንባት

ከዚህ አኳያ በክልሉ ይስተዋሉ የነበሩ የተለያዩ ችግሮችን በመቅረፍ ክልላዊ የልሂቃን ሥምምነትና አገራዊ መግባባት፣ የጋራ ርዕይ መኖር እና የመንግስት ቅቡልነትን የሚያረጋግጡ የዴሞክራሲያዊና የፍትሕ ተቋማት እንዲኖሩ ጥረት የሚደረግ ሲሆን ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚተባበር በተወዳዳሪነት መርህ ላይ የተመሠረተ ቢሮክራሲ እንዲኖር ይሠራል። ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ተቋሞቻችን የመልካም ዜጋ ማፍለቂያ እንዲሆኑ ከቤተሰብ፣ ማህበረሰብና መምህራን ጋር የተቀናጀ ጥረት እንደሚደረግና ቤተሰብን፣ የማህበረሰብና የዕምነት መሪዎችን በማስተባበር የዕምነት ተቋሞቻችንና አስተምህሮቶቻቸው ድህነትን ለመቀነስ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው መሥራት ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ብልፅግናን ለማረጋገጥ የሚረዱ ተገቢ የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ እና የህግ ማዕቀፎችም የሚዘጋጁ ይሆናል።

## 8. የ10 ዓመቱ የልማት መሪ ዕቅድ ልዩ ባህሪያት

መሪ ዕቅዱ በዋናነት የክልሉን የልማት ዓላማ ከረጅም ጊዜ አንፃር በመጠቆምና አቅጣጫ በማሳየት ላይ ያለመ ሲሆን ዕቅዱ ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ 10 ዓመታትን የሚያካትት በመሆኑ ትላልቅ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ያመጡትን ለውጥ (impact) ለማየት በቂ ጊዜ ነው ተብሎ ይታሰባል። ይህ ዕቅድ አብዛኛውን ጊዜ አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆኑ ዝርዝር በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን አጠቃላይ በሆኑ አመልካቾች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ይሆናል።

**የክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑ፡-** በቀጣይ 10 ዓመታት የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ጥራት ላይ ያተኮረ ነው ሲባል ዕድገቱ በኢኮኖሚው ውስጥ የተከሰቱ አንኳር ችግሮችን በማስተካከል እና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን በማስፈን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቱሩፋቶችን ለህብረተሠቡ ማበርከት ማለት ነው። ስለሆነም በቀጣይ የሚመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፣ የግለሠቦችን የኑሮ ደረጃ በተጨባጭ የሚያሻሽል፣ ድህነትን ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚቀንስ፣ የዋጋ ንረትን፣ ሥራ አጥነትን የሚያስተካክል እና በኢኮኖሚ ዘርፎች ጠንካራ ትስስር ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ ለውጥን የሚያመጣ እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።

**የክልሉን ዕምቅ አቅምና የመልማት አቅም መሠረት ያደረገ መሆኑ፡-** እንደሚታወቀው ሁሉ ክልሉ ካለው ሰፊ የመሬትና የውኃ ሀብት አንፃር በግብርና ልማት፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግና ማኑፋክቸሪንግ፣ በቱሪዝም እንዲሁም በማዕድን ሰፊ የመልማት አቅም አለው። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ይህን አቅም ተጠቅሞ የሚፈለገውን ልማት ዕውን ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተት ይታያል። ስለሆነም በአገር በቀሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደ ተጠቀሰውም በዚህ ዕቅድ ይህን ሰፊ የልማት ዕምቅ አቅም መጠቀምን ታሳቢ ያደርጋል። ስለሆነም የት ቦታ ላይ ምን አለ የሚለውን በማየት፣ በጥናትና በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመሥርቶ በመርህ ደረጃና ሳይንሳዊ አሠራርን ተከትሎ ውጤታማ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ መዋእለ ንዋይን የማፍሰስ ሂደት ይኖራል ተብሎ ይታሰባል። በዚህም ውጤታማነትንና ተወዳዳሪነትን በእጅጉ ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል። እስከ አሁን በተገነቡ አቅሞች /የመስኖ ግድቦች፣ የኃይል አቅርቦት፣ የሰው ኃይል/ እና በአዲስ የአመራር ቁርጠኝነት የተሻለ የፖለቲካ ካፒታል ላይ የሚመሠረት መሆኑ ዕቅዱን ለየት ያደርገዋል።

**በክልሉ ተነፃፃሪ የሀብት አቅምና ብልጫ ላይ ተመሥርቶ የሚታቀድ መሆኑ፡-** ይህም ማለት በሁሉም የልማት ሥራዎች ላይ መሳተፍ ሳይሆን የትኞቹ የኢኮኖሚ ልማት መስኮች በአዋጭነት በልማት ሥራ ውስጥ ክልሉ ቢረባረብ ውጤታማ ይሆናል ማለት ነው። ይህም የሚመሠረተው ከሌሎች አካባቢዎች በየትኞቹ የዕድገት ምንጮች ወይም አቅሞች እንዲሁም የምርት መገልገያዎች ክልሉ እንደሚሻል የመለየትና በእነርሱ ላይ ያለውን ሀብት በማፍሰስ ውጤታማ መሆንን ያጠቃልላል። ስለሆነም በጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉና ክልሉን ይብልጥ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ የልማት መስኮችን በመምረጥ ርብርብ የሚደረግበት ሥርዓት ይፈጠራል።

**የልማት ኮሪደሮችን በመምረጥ ለፈጣን ዕድገት መነሻ መሆኑ:-** ከዚህ ቀደም ክልሉ ውኃንና ተፋሰስን መሠረት በማድረግ በ6 የልማት ቀጠና እንዲከፈል ተደርጎ ነበር። ይሁን እንጂ እነዚህን ቀጠናዎች መሠረት ያደረጉ ሥራዎች ሲከናወኑ አልቆዩም። በመሆኑም የክልሉን ልማት ባለው ሀብትና አንፃራዊ ጠቀሜታን (comparative advantage) መሠረት በማድረግ መፈፀም የሚገባ በመሆኑ የልማት ኮሪደሮችን በመምረጥ የልማት እንቅስቃሴውን ማካሄድ ተገቢ ነው። በሌላ በኩል ከ6ቱ የልማት ቀጠናዎች በተለየ መልኩ በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ በተጠናው ጥናት አካባቢዎች በኮሞዲቲ ወይም በምርት ክላስተር የተከፈሉ ሲሆን ይኸውም ጣና የሆርቲካልቸር፣ ሩዝና ወተት ክላስተር በማዕከላዊ ጎንደር፣ በደቡብ ጎንደርና በምዕራብ ጎጃም እንዲሁም የጎንደር የሰሊጥ፣ ጥጥና በግና ፍየል ክላስተር ማዕከላዊ ጎንደር እና ምዕራብ ጎንደር አካባቢዎች ምቹ እንደሆኑ የተመረጡ ሲሆን የበቆሎ፣ የወተትና አትክልትና ፍራፍሬ ክላስተር ደግሞ ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖች ተመርጠዋል። በተጨማሪም የብቅል ገብስና የበግ ክላስተር ሰሜን ጎንደር እንዲሁም የድንች፣ በግ እና የደጋ ፍራፍሬ ክላስተር ምሥራቅ ጎጃም፣ ምዕራብ ጎጃም እና አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር እንዲሆኑ ተደርገዋል። ሌላው የስንዴ፣ በቆሎ፣ ቡና እና የከብት ሥጋ ክላስተር ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም ሲሆኑ የጤፍ፣ ወተትና ጥራጥሬ ክላስተር በተመሳሳይ በእነዚሁ ዞኖች በተመረጡ ወረዳዎች እንደሚካሄድ በጥናቱ ተመላክቷል።

ከዚህም በተጨማሪ የፍየልና የቦሎቄ ክላስተር በሰሜን ወሎና በደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ጎጃም ለዚህ ልማት አቅም ያላቸው ወረዳዎች ተመርጠዋል። እንዲሁም የመንዝ በግ፣ የጅሩ ከብት ሥጋ እና ስንዴ ክላስተር እና ወተት ብቅል ገብስና ስንዴ ክላስተር በተመሳሳይ የምንጃር ጤፍ፣ የከብት ሥጋና የፍየል ክላስተር በሰሜን ሸዋ ሀብቱ ባለባቸው ወረዳዎች በጉድኝት ለማከናወን ተጠንቷል። ይፋት-ባቲ-የጁ ማሽላ፣ ፍየል፣ ሆርቲካልቸር እና ወተት ክላስተር በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ብሔረስብ አስተዳር ፣ ደቡብ እና ሰሜን ወሎ እንዲሁም የመቅደላ-ጊምባ በግ፣ የብቅል ገብስና ስንዴ ክላስተር በደቡብ ወሎ ማልማት እንደሚቻል በጥናቱ ተመላክቷል። በተጨማሪም በጥናቱ የተመላከተው የእስታይሽ-አንጎት በግ፣ ስንዴና የደን ክላስተር እንዲሁም የጉና የድንች፣ በግ፣ የብቅል ገብስና የጤፍ ክላስተር ልማት ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ኮሞዲት ክላስተር አቀራረቦችን በጥልቀት በመፈተሽ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እና ክልሉ ካለው ሀብት ጋር በማቀናጀት የግብርና ልማትን ምርትና ምራታማነትን ለማሳደግ በመሪ ዕቅዱ ዓመት ወደ ተሟላ የኮሞዲቲ ክላስተር ትግበራ መገባት ይኖርበታል።

በሌላ በኩል የኢንዱስትሪ ማዕድናት በምሥራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ዋግ ኽምራ፣ ደቡብ ወሎ፣ አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር እና ሰሜን ወሎ የጂፕሰም፣ ሲልካ ሳንድ፣ ኖራ ድንጋይ፣ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ብረት፣ ኳርትዝ፣ ፌልድሰፓር፣ ማንጋኔዝ፣ ኮባልት፣ ሰልፈር የሚገኙ ሲሆን የግንባታ ማዕድናትም እንደ ፑሚስ፣ ቀይ አሸዋ፣ እብነ በረድ፣ ግራናይት፣ ሳንድ ስቶን በሰሜን ሸዋ፣ በምዕራብ ጎጃም፣ በአዊ ብሔረስብ አስተዳደር፣ በዋግ ኽምራ፣ በምዕራብ ጎንደር ዞኖች እንደሚገኙ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ፍኖተ ካርታ ላይ ተመላክቷል። እንዲሁም የከበሩ ማዕድናት እንደ ወርቅ፣ ኦፓል፣ አምበር በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም ዞኖች እንደሚገኙ በጥናቱ ተመላክቷል። የኢነርጂና የማዕድን ውኃ እንደ የድንጋይ ከሰል፣ ኦይል ሽል እና ፍል ውኃ በምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፣ ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ብሔረሰብ አስተዳር እንዲሁም ምእራብ ጎጃም ዞኖች በተለያዩ አካባቢዎች ማዕድናቱ እንደሚገኙ ተመላክቷል። በመሆኑም እንዚህን ለአምራች ኢንዱስትሪና ለኮንስትራክሽን ዘርፎች በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ በመሆናቸው በጥናት ላይ ተመሥርቶ በማዘጋጀት የግሉ ባለሀብት እንዲሳተፍበትና ወደ ልማት እንዲገቡ የማድረግ ሥራ በቀጣይ ተጠናክሮ የሚሠራ ይሆናል።

**በተቋማት የጋራ መግባባት እና ተሳትፎ የሚታቀድ መሆኑ:-** በመሪ ዕቅዱ ዙሪያ ተቋማት እቅዶቻቸውን እንዲያቅዱ የሚደረግና የታቀደውም አቅድ በሁሉም ሴክተሮች ተመጋጋቢና ቅንጅታዊ አሠራርን የሚያመጣ መሆኑን ለጋራ ውጤታማነት የሚያዘጋጅ መሆኑን በጋር መግባባት ይጠይቃል። በልማት ሥራው ተሳታፊ የሚሆነውም ህብረተሰብ በዕቅዱ ዙሪያ የተሟላ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚደረግ መሆኑ ዕቅዱን ለየት ያደርገዋል። ከዚህም ሌላ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና አጋር አካላት በምን በምን ጉዳዮች እንደሚገናኙና በጋራ እንደሚሠሩ

በየጊዜው የሚገናኙበት፣ የሚመካከሩበት እና በጋራ የሚያቅዱበት ሁኔታ መኖሩ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖርና ዕቅዱም ትስስርና ተመጋጋቢነት ያለው እንዲሆን የተሻለ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

**በየደረጃው ያሉ አጋር እና ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ መሆኑ፡-** የዝግጅት ሂደቱ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት የተስማሙበት የልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት ሲሆን ሂደቱም አሳታፊና በምክክር ላይ የተመሠረተ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በዚህም ሂደት የግል ዘርፉ፣ የሙያ ማህበራት፣ የዜጋ ማህበራት፣ የልማት አጋሮችና የማህበረሰቡ ተወካዮች ወዘተ እንዲሳተፉበት ይደረጋል፡፡ በዚህ መሠረት ዕቅዱ የጋራ መግባባትና ፍላጎትን እንዲሁም የክልሉን ህዝብ ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቅ እና የህዝቦችን ተሳትፎ ያረጋገጠ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

**የሥርዓታት ድክመትን ለማሻሻል መያዙ፡-** ሥርዓታት የህብረተሰብን አመለካከት፣ የመንግሥትን ሚና፣ የማህበረሰብን ግንኙነቶች፣ የመንግሥትን እና የህብረተሰብን መስተጋብሮች የሚዳኙ ተቋማት፣ በተቋማቱ የሚወጡ ገዢ ሕጎችን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን፣ የባሕልና የዕምነት ህግጋትን እንዲሁም የፖለቲካ ሥርዓትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁሉ በአጠቃላይ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሚናቸውን በአግባቡ ለይቶ ለያዝነው የብልፅግና ጉዞ ውጤታማ በሚያደርጉ መልኩ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

## 9. የዘላቂ ልማት ግቦችና የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ትስስር

እንደሚታወቀው እ.ኤ.አ. እስከ 2030 ድረስ የሚዘልቁ 169 ዓላማዎች /Targets/ እና 230 አመልካቾች /Indicators/ የያዙ 17 የዘላቂ ልማት ግቦች /Goals/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀርፀው እና እ.ኤ.አ በ2015 በኒውዮርክ በተባበሩት መንግስታት አባል አገሮች ጸድቆ አገሮችም ከልማት ዕቅዳቸው ጋር በማስተሳሰር እየተገበሯቸው ይገኛሉ፡፡ በአገርም ሆነ በክልል ደረጃ ዘላቂ የልማት ግቦችን በተለይም ከ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ሲተገበር ቆይቷል፡፡ በይበልጥ ደግሞ በቀጣዩ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ የተለየ ትኩረት በመስጠት እና ከዕቅዱ ጋር በማስተሳሰር ውጤታማ አፈጻጸም የሚመዘግብበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረት ተደርጓል፡፡

በአገር ደረጃ ዘላቂ የልማት ግቦችን ከልማት ዕቅድ ጋር ለማስተሳሰር የተወሰደው የመጀመሪያ ርምጃ ከዘላቂ ልማት ግቦችና በውስጣቸው ከተካተቱ ዒላማዎች አንፃር መነሻችን /baseline/ የት ላይ ነው ያለ፣ በቀጣይ እ.ኤ.አ እስከ 2030 ከሚጠበቀው ደረጃ ለመድረስ ምን ያህል ክፍተት /gap/ አለ የሚለው እንዲሁም ይህን ለመተግበር ምን ያህል ሀብት ያስፈልጋል የሚለውን /Need Assessment/ ማጥናት ነው፡፡ በዚህ መሠረት የክፍተት እና የሀብት ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት በፌደራል ፕላንና ልማት ኮሚሽን አስተባባሪነት በኮንሰልታንት ከተጠና በኋላ ከየሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በተሰጠ ግብዓት ዳብሮ የመጨረሻ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡

በ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅዱ ትኩረት ከተሠጣቸው ወሳኝ ዘርፎች መካከል የማክሮ ኢኮኖሚ፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ የመሠረተ ልማት እና የባለ ብዙ ዘርፎች ይገኙበታል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ በተቀመጠው መሠረት በልማት ዕቅዱ የትኞቹ የልማት ግቦች እና በእነዚህ ሥር የተዘረዘሩ ዒላማዎች ከየትኞቹ ዘርፎች ጋር እንደሚተሳሰሩ ቀጥሎ በሠንጠረዥ ተመላክቷል፡፡ ስለሆነም ይህ የዘላቂ ልማት ግቦችና የዘርፎች ትስስር ሠነድ የዘርፎችና ክፍላተ ኢኮኖሚዎች ዕቅድ ከዚህ ጋር ተናባቢ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ እና እንዲተገበር ለማድረግ እንደ ማዕቀፍ ሆኖ እንደሚያገለግል ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ በእያንዳንዱ ግብ እና ዒላማ ከሌሎች አገሮች አፈጻጸም አንፃር የት ላይ እንዳለን እና ምን ክፍተቶች እንዳሉ የሚጠቁም ሲሆን ለማሳያ ያህል በተወሰኑ ጉዳዮች እንደ አገር የት ላይ እንዳለን ቀጥሎ በአጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ድህነትን መቀነስን /ግብ 1/ በተመለከተ ረሀብን እና የሥነምግብ ሥርዓት /ግብ 2/ ችግርን ለመቅረፍ ሰፊ ሥራ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም አሁን ያለንበት ደረጃ ዝቅተኛ የሚባል እንደሆነ እና የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የተሠራው ሥራም ደካማ እንደሆነ ሪፖርቱ ያሳያል፡፡ የጤናና የኑሮ ሁኔታ ማሻሻልን /ግብ 3/ በተመለከተም ጥረቶች የተደረጉ

ቢሆንም የእናቶችና ህጻናት ሞትን ከመቀነስ አንፃር ያለው አፈጻጸም ዝቅተኛ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡ የትምህርት ጥራትን ከማረጋገጥ /ግብ 4/ አንፃር በተለይም የመምህራንን አቅም ለማሳደግ ሰፊ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በቅድመ መደበኛ፣ መደበኛ እና 2ኛ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎ እንዲሁም የትምህርት ተሳትፎ ፆታዊ ምጥጥን ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

ከሥርዓተ ፆታ እኩልነት /ግብ 5/ አንፃር በተለይም የሴቶችንና ልጃገረዶችን የኢኮኖሚ አቅም በማሳደግ፣ በፖለቲካው ውስጥ ተሳትፎ ከማድረግ እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ከመቀነስ አንፃር አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም በፆታዊ ጥቃት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ በሥነተዋልዶ ጤና እንዲሁም ሴቶችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ከማድረግ እና ውሳኔ መስጠት በሚያስችሉ መስኮች ውሳኔ ከመስጠት አንፃር ክፍተቶች እንዳሉ ያመላክታል፡፡ የንጹህ መጠጥ ውኃ እና ንጽህናን ተደራሽ ማድረግ /ግብ 6/ በተመለከተ የማይናቁ ርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም በዚህ ረገድም ሰፊ ክፍተት እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡ የኃይል አቅርቦትን ለሁሉም ከማዳረስ /ግብ 7/ አንፃር እንደ አገር ሰፊ ሥራ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም ከኃይል ተደራሽነትና ቅልጥፍና /Efficiency/ አንፃር ዝቅ ያለ አፈጻጸም እንዳለ የጥናት ሪፖርቱ ያሳያል፡ ፡ ይህም ከሌሎች ሀገሮች አንፃር ዝቅተኛ አፈጻጸም ባሳየንባቸውና ክፍተቶች ባሉብን ጉዳዮች ይበልጥ በመጠንከር የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባ የሚያሳይ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 1፡- የዘላቂ ልማት ግቦችና የዘርፎች ትስስር**

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| **ማክሮ ኢኮኖሚ** | ግብ 1፣ ድህነትን ማስወገድ | 1.1. በ2022 ከ1.25 የአሜሪካን ዶላር በታች የቀን ገቢ መለኪያ በሁሉም ህዝብና አካባቢ አስከፊ ድህነትን ማስወገድ፣<br><br>1.3. ትክክለኛ/ተገቢ የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓት በመገንባት በ2022 ትርጉም ባለው መልኩ ድሃዎችንና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ማድረግ፣<br><br>1.5. በ2022 ድሃዎችንና ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጨምሮ እንደ የአየር ንብረት፣ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ችግር ያሉ ቀውሶችንና አደጋዎችን የመቋቋም አቅምን መገንባት፣ |
| | ግብ.8 ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ እና ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ እና የሥራ ዕድል መፍጠር | 8.1 የነፍስ ወከፍ ገቢን በዘላቂነት ማሳደግና እንደየ አገሮች ነባራዊ ሁኔታ በተለይ በዕድገት ወደኋላ በቀሩ ሀገሮች ቢያንስ በየዓመቱ የ7 በመቶ አማካይ ጥቅል የአገር ውስጥ ምርት ዕድገት ማስመዝገብ፣<br><br>8.2 የምርት ዓይነትን /diversification/ በመጨመር፣ በፈጠራ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ የኢኮኖሚ ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣<br><br>8.5 በ2022 ሴቶች፣ ወንዶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች በምርታማ እና በቂ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ እንዲሠማሩ በማድረግ የሥራ ዕድል መፍጠር፣<br><br>8.6 በ2022 ከሥራ፣ ትምህርትና ሥልጠና ውጭ የሆነውን የወጣት ምጣኔ ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ፣ |

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| | | 8.7 አፋጣኝና ውጤታማ ርምጃዎችን በመውሰድ አስገድዶ የማሠራት ሁኔታን ማስወገድ፣ ዘመናዊ ባርነትን እና የሰዎች ህገወጥ ዝውውርን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት፣ በ2017 ህጻናትን ለውትድርና አገልግሎት መመልመልና ማሠማራትን ጨምሮ በአስከፊ ሁኔታ ላይ ያለውን የህጻናት የጉልበት ብዝበዛ ማስቀረት፣<br><br>8.10 የገንዘብ ተቋማትን አቅም በማሳደግና ተደራሽነታቸውን በማስፋት ሁሉም ዜጋ የባንክና ኢንሹራንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፣ |
| ኢኮኖሚ ልማት | **ግብ 2**፣ ረሀብን ማስወገድ፣ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የአመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል እና ዘላቂ የግብርና ልማትን ማጠናር፣ | 2.1 በ2022 ረሃብን ማስወገድ፣ ለሁሉም ሰው በተለይም ለድሃዎችና ለልዩ ልዩ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ጨቅላዎች ዓመቱን በሙሉ የተመጣጠነና በቂ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ፣<br><br>2.2 በ2017 በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተደረሰው ሥምምነት አንፃር ከ5 ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ህጻናት ቁመት ከዕድሜ አንፃር አጭር መሆን /መቀንጨር/ እና ከቁመታቸው አንፃር ቀጭን የመሆን ችግርን እንዲሁም የአፍላ ወጣት ልጃገረዶችን፣ እርጉዝና አጥቢ እናቶችንና የአረጋዊያንን የምግብ ፍላጎት ጨምሮ በ2022 የሥርዓተ ምግብ መዛባት ችግርን ማስወገድ፣<br><br>2.3 የመሬት ዋስትናን በማረጋገጥ እና ተደራሽነትን ፍትሐዊ በማድረግ፣ በቂ ግብዓት በማቅረብ፣ የትምህርት ወይም የኤክስቴንሽን አገልግሎትን በማስፋፋት፣ የፋይናንስ ተደራሽነትን ከፍ በማድረግ እንዲሁም አርሶ አደሩ ለሚያመርተው ምርት የገበያ ዕድል በማስፋትና ዕሴት በመጨመር በ2022 የግብርና ምርታማነትንና የአርሶ አደሩን ገቢ በዕጥፍ ማሳደግ፣ |
| | ግብ.11 ከተሞች ምቹ የመኖሪያ ሥፍራ እንዲሆኑና ለዘላቂ ልማት ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፣ | 11.1 በ2022 ለሁሉም ዜጋ በቂ፣ ጥራት ያለው እና አቅምን ያገናዘበ የመኖሪያ ቤት እና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ እና የተጎሳቆሉ መኖሪያ አካባቢዎችን ማሻሻል፣ |
| ማህበራዊ ልማት | ግብ.3 የተሻለ የጤና እና የኑሮ ሁኔታ መፍጠር፣ | 3.1 በ2022 የእናቶች ሞት ምጣኔን መቀነስና ወደ 70 ከ100,000 በህይዎት የሚወልዱ እናቶች ማድረስ፣<br><br>3.2 በ2022 በቀላሉ መከላከል በሚቻሉ መንስዔዎች የሚከሰት የጨቅላና ከ5 ዓመት በታች ህጻናት ሞትን መቀነስ፣ በሁሉም አገሮች የጨቅላ ህጻናት ሞትን ቢያንስ 12 በ1000 በህይዎት የተወለዱ እና ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህጻናት ሞትን 25 በ1000 በህይዎት የተወለዱ ማድረስ፣<br><br>3.3 በ2022 የኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ ወባ እንዲሁም |

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| | | እንደ ጉበት በሽታ /ሄፓታይቲስ/ ፣ ውኃ ወለድ እና ተላላፊ በሽታዎች ያሉ ትኩረት ያልተሰጣቸው የሀሩራማ አካባቢ በሽታዎችን ማስወገድ፣<br><br>3.4 በ2022 አስቀድሞ በመከላከል እና በህክምና እንዲሁም የአእምሮ ጤና እና ደህንነትን በመጠበቅ ተላላፊ ባልሆኑ በሽዎችች የሚደርስ ሞትን በአንድ ሶስተኛ መቀነስ፣<br><br>3.5 ከአነቃቂ ዕጾች፣ መድኃኒቶች እና አልኮል መጠጦች ጋር በተያያዘ የሚታይ የአጠቃቀም ችግርን መከላከል እና መቅረፍ፣<br><br>3.7 የቤተሰብ ዕቅድ ሽፋንን ከማሳደግ ባሻገር መረጃዎችን ተደራሽ በማድረግ እና ትምህርት በመስጠት እንዲሁም የሥነተዋልዶ ጤና ፕሮግራሞችን ከአገራዊ ስትራቴጂዎች ጋር በማቀናጀት በ2022 የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ፣<br><br>3.8 መሠረታዊ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ፣ እንዲሁም ምቹ፣ ውጤታማ፣ ጥራት ያለው እና አቅምን ያገናዘበ የመድኃኒት አቅርቦትን በማሟላት የጤና አገልግሎት ሽፋንን ሙሉ በሙሉ ማሳካት፣<br><br>3.9 በ2022 በመርዛማ ኬሚካል፣ በአየር፣ ውኃ እና አፈር ብክለት ምክንያት የሚደርስ ህመምና ሞትን ትርጉም ባለው ደረጃ መቀነስ፣ |
| | ግብ 4፣ አካታች፣ ፍትሐዊ እና ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ፣ | 4.1 በ2022 ሁሉም ወንዶችና ልጃገረዶች ነፃ ፣ ፍትሐዊ እና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ እና የትምህርት ተገቢነት እና ውጤታማነትን ማሳደግ፣<br><br>4.2 በ2022 ሁሉም ወንድ እና ሴት ህጻናት ለመደበኛ ትምህርት የሚያዘጋጃቸውን ጥራት ያለው የቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት እና እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣<br><br>4.5 የአካል ጉዳተኞችን፣ የተረሱ ማህበረሰቦችን እና ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ህጻናትን ጨምሮ ሴቶችና ወንዶች በሁሉም የትምህርት እና የሙያ ሥልጠና እርከኖች እኩል የትምህርት ተደራሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ በ2022 የትምህርት ተደራሽነት ፆታዊ ክፍተትን ማጥፋት፣ |
| | ግብ 5፣ የሴቶችን እኩልነት ማረጋገጥ፣ ሁሉንም ሴቶችና ልጃገረዶች ማብቃት፣ | 5.2 የሴቶችን ህገወጥ ዝውውር፣ የፆታና ሌሎች ብዝበዛዎችን ጨምሮ በመንግስት መ/ቤትም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚታዩ በሴቶችም ሆነ በልጃገረዶች የሚደረጉ ሁሉንም ዓይነት ፆታዊ ጥቃቶች ማስቀረት፣<br><br>5.3 የህጻናት ያለዕድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት ያሉትን |

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| | | ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት ጎጂ ባህላዊ ድርጊቶችን ማስወገድ፣<br><br>5.5 በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በህዝብ አገልግሎት በአጠቃላይ በሁሉም የአመራር ውሳኔ በሚጠይቁ መስኮች ወሳኝ ሚና እና እኩል ዕድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣<br><br>5.6 በዓለምአቀፉ የስነህዝብና ልማት ኮንፈረንስ በተደረሰው የቤጅንግ የድርጊት መርሀ ግብር ሥምምነት መሠረት የሴቶችን የስነተዋልዶ ጤናን ተደራሽ ማድረግ እና የስነተዋልዶ መብትን ማረጋገጥ፣ |
| **መሠረተ ልማት** | ግብ 6፣ የንፁህ ውኃ አቅርቦትን እና ዘላቂ አጠቃቀምን ማረጋገጥ፣ ንጽህናን ለሁሉም ማዳረስ፣ | 6.1 በ2022 ንጹህና አቅምን ያገናዘበ የውኃ ተደራሽነትን ፍትሐዊነትን በጠበቀ መልኩ ለሁሉም ማዳረስ፣<br><br>6.2 በ2022 የንጽህና አገልግሎትን በተፈለገው መጠንና በፍትሐዊነት ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ እና በተለይም ለሴቶች፣ ልጃገረዶች እና በችግር ውስጥ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ትኩረት በመስጠት በሜዳ መጸዳዳትን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት፣<br><br>6.4 በ2022 በሁሉም ዘርፎች የውኃ አጠቃቀም ቅልጥፍናን ትርጉም ባለው ሁኔታ መጨመር እንዲሁም ዘላቂነት ያለው የውኃ አቅርቦትና አወጋገድ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ በውኃ እጥረት የሚቸገሩ ዜጎችን ቁጥር መቀነስ፣ |
| | ግብ 7፣ አቅምን ያገናዘበ፣ አስተማማኝነት እና ዘላቂነት ያለው ዘመናዊ የኃይል አቅርቦትን ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ፣ | 7.1 በ2022 አቅምን መሠረት ያደረገ፣ አስተማማኝነት ያለው፣ ዘመናዊ የኃይል አቅርቦት ለሁሉም ማዳረስ፣<br><br>7.2 በ2022 ከአጠቃላይ ዓለም አቀፍ የኃይል አቅርቦት መካከል የታዳሽ ኃይል አቅርቦት ድርሻ ትርጉም ባለው መልኩ እንዲጨምር ማድረግ፣<br><br>7.3 በ2022 የኃይል አጠቃቀም ቅልጥፍናን በዕጥፍ ማሳደግ፣ |
| | ግብ 9፣ ጥራት ያለው መሠረተ ልማት መገንባት፣ አካታች እና ዘላቂነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትን ማስፋፋት፣ ፈጠራን ማበረታታት፣ | 9.1 አስተማማኝ፣ ዘላቂነት ያለው እና የተለያዩ ችግሮችን እና አደጋዎችን መቋቋም የሚችል የክልል እና አገር አቋራጭ መሠረተ ልማት መገንባት እና መሠረተ ልማቱ የኢኮኖሚ ልማትን ሊደግፍ እና የሰዎችን የኑሮ ደረጃ ሊያሻሽል የሚችል አቅምን ያገናዘበና ለሁሉም ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ማድረግ፣<br><br>9.2 በ2022 አካታችና ዘላቂነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማትን በማጠናከር እና በማስፋፋት በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል እና ዘርፉ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው የሚኖረውን ድርሻ ትርጉም ባለው ደረጃ ከፍ እንዲል ማድረግ እና እንደየአገሮች ሁኔታ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ዘርፉ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው የሚኖረውን ድርሻ በዕጥፍ ማሳደግ፣ |

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| | | 9.4 በ2022 የመሠረተ ልማቶችን ደረጃ በማሻሻል እና የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በማሳደግ ዘላቂነት ያለው፣ ቅልጥፍናን የሚያረጋግጥ እና አካባቢን የማይጎዳ አሠራርን መከተል፣<br><br>9.5 በ2022 ፈጠራን የማበረታታት እና በግልም ሆነ በመንግስት የምርምር ተቋማት ለምርምር የሚመደብ በጀትን ከፍ በማድረግ በየአንድ ሚሊየን ህዝብ ያሉ ተመራማሪዎችን ቁጥር ማሳደግን ጨምሮ ሳይንሳዊ ምርምርን ማጠናከር እና የኢንዱስትሪዎችን የቴክኖሎጂና የማምረት አቅም ማሳደግ፣ |
| ባለ ብዙ ዘርፎች | ግብ 12፣ ዘላቂነት ያለው የአጠቃቀምና የአመራረት ሥርዓት ማረጋገጥ | 12.2 በ2022 ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣<br><br>12.4 ሥምምነት በተደረሰባቸው ዓለም አቀፍ ማዕቀፎች መሠረት በ2022 ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የኬሚካልና የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት የአየር፣ የውኃ እና የአፈር ብክለትን መቀነስና በሰዎች ጤና እና አካባቢ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ፣ |
| | ግብ 13፣ የአየር ንብረት ለውጥን እና በዚህ ሳቢያ የሚደርስ ተፅዕኖን መቀነስ የሚያስችል አፋጣኝ ርምጃ መውሰድ | 13.2 የአየር ንብረት ለውጥ ርምጃዎችን ከአገራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የልማት ዕቅዶች ጋር ማስተሳሰር፣<br><br>13.3 ከአየር ንብረት ማስተሰሪያ፣ ማጣጣሚያ እና ተጽዕኖ የሚቀንሱ እና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትምህርት የመስጠት፣ ግንዛቤን የማሳደግ እና የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማጠናከር፣ |
| | ግብ 15፣መሬትን ዘላቂነት ባለው መልኩ በመጠበቅ እና ደንን በማልማት በረሃማነትን መከላከል፣ የተራቆቱ መሬቶች እንዲያገግሙ ማድረግ እና የብዝሀ ህይዎት መጥፋትን መከላከል፣ | 15.1 ሥምምነት የተደረገባቸውን ዓለም አቀፍ አስገዳጅነት ያላቸው ሥምምነቶችን መሠረት በማድረግ የመሬትንና የውኃ አካላትን ሥርዓተ ምህዳር እና የሚሰጡትን አገልግሎት፣ በተለይም ርጥበት አዘል ቦታዎችን፣ ተራራዎችን እና ደረቃማ ቦታዎችን መጠበቅ፣ እንዲያገግም ማድረግና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ማረጋገጥ፣<br><br>15.2 በ2012 ዘላቂ የደን አያያዝ ሥርዓትን መተግበር፣ የደን መመንጠርን መግታት፣ የተጎዱና የተጎሳቆሉ ደኖች እንዲያገግሙ ማድረግ፣ የደን ተከላን ማስፋፋት፣<br><br>15.5 በዱር እንስሳት የተፈጥሮ መኖሪያ ቦታዎች የሚደርስ አደጋን ለመቀነስ አፋጣኝ ርምጃ መውሰድ፣ የብዝሀ ህይዎት መጥፋት ሁኔታን በአፋጣኝ መግታት እንዲሁም በ2012 የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸውን ዝርያዎች እንዳይጠፉ መከላከል፣ |

| ዘርፍ | የዘላቂ ልማት ግብ | ዒላማዎች /Targets/ |
|---|---|---|
| | | 15.6 በዓለም አቀፍ ደረጃ ሥምምነት እንደተደረገው ከብዝሀ ህይዎት የሚገኝ ጥቅምን በእኩል መጋራት እንዲሁም በተገቢው ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣<br><br>15.9 በ2012 የሥነምህዳርና ብዝሀ ህይዎት ዋጋን ወይም ጠቀሜታን ከአካባቢው ዕቅድ፣ የልማት ሂደት፣ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎችና የኢኮኖሚ ግመታ ሥራዎች ጋር ማስተሳሰር፣ |
| | ግብ 16፣ ለዘላቂ ልማት የሚያግዝ ሠላማዊ እና አካታች ማህበረሰብ መፍጠር፣ ፍትህን ለሁሉም ተደራሽ ማደረግ እንዲሁም ውጤታማ እና ተጠያቂነት ያለባቸው ተቋማትን በየደረጃው መገንባት፣ | 16.1 በተለያየ መልክ የሚደርሱ ግጭቶችና ከዚህ ጋር ተያይዞ በሁሉም አካባቢ የሚደርስ ሞትን ትርጉም ባለው ሁኔታ መቀነስ፣<br><br>16.5 በተለያየ መልኩ የሚገለጥ የሙስና እና ስርቆትን ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ፣<br><br>16.9 በ2022፣ ለውልደት ምዝገባ እና መሰል ወሳኝ ኩነቶች መነሻ የሚሆኑ ህጎችና አሠራሮችን መቅረጽ፣ |

# 10. የ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ

በዕቅድ ሠነዱ በማክሮ ኢኮኖሚ እና በዋና ዋና የኢኮኖሚና ማህበራዊ የልማት ዘርፎች በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የመጨረሻ ዓመት (2012) የተደረሰበትን የአፈፃፀም ግምትና በዚሁ ላይ በመመሥረት በ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅዱ የመጨረሻ ዓመት (2022) ይደረስባቸዋል የተባሉ ዋና ዋና ግቦች ትንበያ ማጠቃለያ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ 2 ላይ ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዠ 2፡- የማክሮ ኢኮኖሚና የዋና ዋና ዘርፎች ዕቅድ ትንበያ ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| I | **ማክሮ ኢኮኖሚ** | | | | |
| | **የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ** | | | | |
| | **ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ዕድገት በዋና ዋና ዘርፎች** | | | | |
| | • ግብርናና ተዛማጅ | መቶኛ | 2.5 | 6.5 | |
| | • ኢንዱስትሪ | መቶኛ | 2.0 | 15.4 | |
| | ➢ አምራች ኢንዱስትሪ | መቶኛ | 14.0 | 19.1 | |
| | • አገልግሎት | መቶኛ | 6.6 | 18.3 | |
| | • ጠቅላላ | መቶኛ | 3.6 | 12.8 | |
| | **ዋና ዋና ዘርፎች በክልል ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ /የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ/** | | | | |
| | • ግብርናና ተዛማጅ | መቶኛ | 53.7 | 38.8 | |
| | • ኢንዱስትሪ | መቶኛ | 15.7 | 23.6 | |
| | ➢ አምራች ኢንዱስትሪ | መቶኛ | 6.58 | 14.2 | |
| | • አገልግሎት | መቶኛ | 31.7 | 37.6 | |
| | • ጠቅላላ | መቶኛ | 100 | 100 | |
| | **የኑሮ ደረጃ** | | | | |
| | ❖ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት | መቶኛ | 8 | 7.7 | |
| | ❖ ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ህዝብ ብዛት | መቶኛ | 21 | 10 | |
| | **የሥራ ሥምሪትና ሥራ አጥነት** | | | | |
| | ❖ የዘርፎች የሠራተኛ ኃይል ሥምሪት/ስብጥር | | | | |
| | • ግብርናና ተዛማጅ | መቶኛ | 66.6 | 44.2 | |
| | • ኢንዱስትሪ | መቶኛ | 6.4 | 14.7 | |
| | • አገልግሎት | መቶኛ | 27.3 | 41.1 | |
| | ❖ የሥራ አጥነት ሁኔታ | መቶኛ | 20.4 | 7.56 | |
| | **የመንግስት በጀት** | | | | |
| | ❖ ጠቅላላ የመንግስት ገቢ በጀት | በቢሊዮን ብር | 47.35 | 323.47 | |
| | • በክልሉ የሚሰበሰብ | በቢሊዮን ብር | 14.99 | 227.42 | |
| | ➢ መደበኛ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 11.06 | 178.02 | |
| | ➢ የቀጥታ ታክስ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 7.30 | 98.23 | |
| | ➢ ቀጥታ ያልሆነ ታክስ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 2.775 | 67.26 | |
| | ➢ ታክስ ያልሆነ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 0.98 | 12.53 | |
| | ➢ የከተሞች አገልግሎት ገቢ | በቢሊዮን ብር | 1.82 | 20.23 | |
| | ➢ የውስጥ ገቢ | በቢሊዮን ብር | 2.11 | 13.60 | |
| | • የፌደራል ድጎማ | በቢሊዮን ብር | 32.36 | 96.04 | |
| | ❖ ጠቅላላ የመንግስት የወጪ በጀት | በቢሊዮን ብር | 47.35 | 323.47 | |
| | • መደበኛ በጀት | በቢሊዮን ብር | 37.42 | 194.08 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | • ካፒታል በጀት | በቢሊዮን ብር | 9.93 | 129.39 | |
| | • ከአጠቃላይ ወጪ የመደበኛ ወጪ ድርሻ | መቶኛ | 79.03 | 60 | |
| | • ከአጠቃላይ ወጪ የካፒታል ወጪ ድርሻ | መቶኛ | 20.97 | 40 | |
| | • የድህነት ተኮር ዘርፎች ወጪ | መቶኛ | 60.8 | 65 | |
| | ❖ በራስ ገቢ ወጪን የመሸፈን ምጣኔ | መቶኛ | 23.7 | 70 | |
| | ❖ የክልሉ ገቢ ከክልል ውስጥ ጥቅል ምርት ድርሻ | መቶኛ | 2.18 | 6.14 | |
| | ❖ አጠቃላይ ኢንቨስትመንት ከክልል ውስጥ ጥቅል ምርት ድርሻ | መቶኛ | 28.3 | 35.8 | |
| **II** | **ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ** | | | | |
| | **ግብርና ልማት** | | | | |
| | ❖ በመኸር በዋና ዋና ሰብሎች የተገኘ ምርት | በሚሊየን ኩንታል | 108.763 | 190.779 | |
| | ❖ አማካይ የሰብል ምርታማነት | ኩንታል/ሄክታር | 24.14 | 39.28 | |
| | ❖ የምግብ ሰብሎችን ምርት ማሳደግ | በሚሊየን ኩንታል | 81.48 | 122.18 | 8 ሰብሎች (ጤፍ፣ የምግብ ገብስ፣ ዳጉሳ፣ ሩዝ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣አተር፣ ምስር) |
| | ❖ የምግብ ሰብሎች ምርታማነት | ኩንታል/ሄክታር | 25.8 | 42.0 | |
| | ❖ የኢንዱስትሪ ሰብሎችን ምርት ማሳደግ | በሚሊየን ኩንታል | 18.2 | 57.8 | 5 ሰብሎች (የዳቦ ስንዴ፣የቢራ ገብስ፣ አኩሪ አተር፣ ኑግ፣ለውዝ) |
| | ❖ የኢንዱስትሪ ሰብሎች ምርታማነት | ኩንታል/ሄክታር | 24.9 | 46.82 | 5 ሰብሎች (የዳቦ ስንዴ፣ የቢራ ገብስ፣ አኩሪ አተር፣ ኑግ፣ ለውዝ) |
| | ❖ የኤክስፖርት ሰብሎችን ምርት ማሳደግ | በሚሊየን ኩንታል | 8.7 | 10.79 | 7 ሰብሎች (ሰሊጥ፣ ነጭ ቦሎቄ፣ ቀይ ቦሎቄ፣ ባቄላ፣ ነጭ ሽምብራ፣ ቀይ ሽምብራ፣ማሽ) |
| | ❖ የኤክስፖርት ሰብሎች ምርታማነትን ማሳደግ | ኩንታል/ሄክታር | 14.85 | 15.1 | |
| | ❖ በመስኖ የለማ መሬት | ሄክታር | 220,469 | 382,383 | |
| | ❖ በመስኖ የሚገኝ ምርት | ኩንታል | 27,683,072 | 51,864,960 | |
| | ❖ የመስኖ ምርታማነት | ኩንታል/ሄክታር | 128 | 135 | |
| | ❖ በበልግ የሚገኝ ምርት | በሚሊየን ኩንታል | 2.75 | 5.61 | |
| | **❖ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች አርሶ አደሮች ብዛት** | | | | |
| | ❖ አባዎራዎች | ቁጥር | 2,396,912 | 4,074,742 | |
| | ❖ እማዎራዎች | ቁጥር | 476,760 | 810,490 | |
| | ❖ ባለትዳር ሴቶች | ቁጥር | 1,143,515 | 2,439,750 | |
| | ❖ ወጣቶች | ቁጥር | 774,443 | 1,316,553 | |
| | ❖ የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች | ቁጥር | 888,774 | 5,271,522 | |
| | ❖ የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች | መቶኛ | 28.2 | 85 | |
| | ❖ የተቀናጀ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ የሚካሄድባቸው ንዑስ | ቁጥር | 16,880 | 43,530 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ተፋሰሶች ብዛት | | | | |
| | ❖ የሞዴል አርሶ አደሮችን ቁጥር ማሳደግ | ቁጥር | 793,895 | 2,442,616 | |
| | ❖ የሞዴል አርሶ አደሮችን ቁጥር ማሳደግ | መቶኛ | 25 | 50 | |
| | ❖ የክልሉ የደን ሽፋን | መቶኛ | 14.6 | 24.6 | |
| | ❖ ጥቅም ላይ የዋለ የአፈር ማዳበሪያ | ኩንታል | 5,039,855 | 9,989,407 | |
| | ❖ ጥቅም ላይ የሚውል ኮምፖስት መጠን | ሚሊየን ሜ/ኩብ | 33.5 | 159 | |
| | ❖ በመኸር በሄክታር ጥቅም ላይ የዋለ የአፈር ማዳበሪያ | ኩንታል/ሄክታር | 1.12 | 2.01 | |
| | ❖ ጥቅም ላይ የዋለ ምርጥ ዘር | ኩንታል | 123,159 | 809,331 | |
| | ❖ የግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚነት | መቶኛ | 7 | 56.5 | |
| | ❖ የሚመረት ድርቆ መኖ | በሚሊየን ሜትሪክ ቶን | 39 | 52 | |
| | ❖ የማዳቀል አገልግሎት መስጠት | በሺህ ቁጥር | 242 | 555 | |
| | ❖ ዝርያቸው የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች ብዛት | በሺህ ቁጥር | 103.39 | 168.65 | |
| | ❖ የክትባት አገልግሎት ያገኙ እንስሳት ብዛት | ሚሊየን ቁጥር | 46.2 | 95.8 | |
| | ❖ የክትባት አገልግሎት ሽፋን | መቶኛ | 95 | 100 | |
| | ❖ የህክምና አገልግሎት ያገኙ እንስሳት ብዛት | ሚሊየን ቁጥር | 11.68 | 8.38 | |
| | ❖ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋን | መቶኛ | 84 | 100 | |
| | ❖ ከዳልጋ ከብትና ፍየል የተመረተ የወተት ምርት | ሜትሪክ ቶን | 1,196,749 | 2,618,425 | |
| | ❖ የነፍስ ወከፍ የወተት ፍጆታ | በሊትር | 19 | 26. | |
| | ❖ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየል እና ከግመል የተመረተ የሥጋ ምርት | ሜትሪክ ቶን | 272,832 | 590,708 | |
| | ❖ የነፍስ ወከፍ የሥጋ ፍጆታ | በኪ/ግራም | 8 | 12 | |
| | ❖ የተመረተ የዕንቁላል ምርት መጠን | በሚሊየን ቁጥር | 523 | 792 | |
| | ❖ የተመረተ የዶሮ ሥጋ | ሜትሪክ ቶን | 12,172 | 25,913 | |
| | ❖ የተመረተ የዓሳ ሥጋ | ሜትሪክ ቶን | 22,672 | 22,498 | |
| | ❖ የተመረተ የማር ምርት | ሜትሪክ ቶን | 18,253 | 26,309 | |
| | ❖ የተመረተ የሰም ምርት | ሜትሪክ ቶን | 889 | 229 | |
| | ❖ የተመረተ ቆዳና ሌጦ | ቁጥር | 7,323,683 | 6,279,952 | |
| | ❖ የተቋቋመ መሠረታዊ የህ/ሥ/ማህበር ብዛት | ቁጥር | 2,484 | 2,484 | |
| | ❖ የተቋቋመ ዩኒየን ብዛት | ቁጥር | 43 | 5 | |
| | ❖ የተቋቋመ ሁለገብ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ፌደሬሽን | ቁጥር | 0 | 1 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ የማህበራት አባላት ብዛት | ቁጥር | 3,791,712 | 5,690,212 | |
| | ❖ የሴት አባላት ድርሻ | መቶኛ | 25.8 | 50 | |
| | ❖ የወጣት አባላት ድርሻ | መቶኛ | 29 | 50 | |
| | ❖ የመሠረታዊ ህ/ሥ/ማህበራት የካፒታል መጠን | ብር | 2,609,194,525 | 2,658,454,525 | |
| | ❖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የካፒታል መጠን | ብር | 985,905,799 | 2,557,191,731 | |
| | ❖ የመሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት መደበኛ ቁጠባ | ብር | 2,575,150,693 | 10,417,920,807 | |
| | ❖ **ብድር ሥርጭትና የገጠር ፋይናንስ ሥርዓትን ማጠናከር** | | | | |
| | ❖ የህብረት ሥራ ማህበራት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ዩኒዬኖች መደበኛ ቁጠባ | ብር | 538,719,525 | 4,179,420,940 | |
| | ❖ የመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ብድር ሥርጭት | ብር | 5,741,023,621 | 72,744,295,773 | |
| | ❖ የዩኒየኖች ብድር ሥርጭት | ብር | 4,167,885,086 | 24,804,581,833 | |
| | ❖ የፌደሬሽን ብድር ሥርጭት | ብር | | 3,050,748,626 | |
| | ❖ በዩኒየኖች የሚቋቋሙ ዕሴት በመጨመር የተለያዩ የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎች ብዛት | ቁጥር | 28 | 46 | |
| | ❖ በተለያየ አደጋ ምክንያት አስቸኳይ ድጋፍ የሚሻ ህዝብ ብዛት | ቁጥር | 753,000 | 813,357 | |
| | ❖ ከልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚወጣ ህዝብ ብዛት | ቁጥር | | 1,384,813 | በሶስት ዓመታት በሚሠሩ ሥራዎች ከፕሮግራሙ የሚወጡ |
| | ❖ በምግብ ዋስትና ድጋፍ የቀነሰ የምግብ ክፍተት | በወር | 1.4 | 0 | |
| | ❖ በግብርና ምርምር የፈለቁ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | ቁጥር | 140 | 942 | የ10 ዓመቱ ድምር |
| | **መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም** | | | | |
| | ❖ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ ባለይዞታዎች ብዛት | ቁጥር | 1,720,564 | 4,347,699 | |
| | ❖ ፕላን የተዘጋጀላቸው ቀበሌዎች ብዛት | ቁጥር | 1,683 | 3,321 | |
| | ❖ የመሬት መረጃ ወደ ኮምፒዩተር የገባላቸው ባለይዞታዎች ብዛት | ቁጥር | | 4,134,743 | |
| | ❖ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት ርክክብ ማድረግ | ቁጥር | 2,507,591 | 4,347,600 | |
| | ❖ በጥናት የተለየ እና ለኢንቨስትመንት የተሰጠ መሬት ስፋት | ሄክታር | 212,678 | 279,678 | |
| | ❖ የተሸነሸኑ የገጠር ማዕከላት ብዛት | ቁጥር | 2,515 | 3,425 | |
| | ❖ በልማት ምክንያት የተነሸ ባለይዞታዎች ካሳ ክፍያ | በቢሊዮን ብር | 13.835 | 324.92 | |
| | ❖ የቢዝነስ ፕላን ተሰርቶላቸው | በሺህ ቁጥር | 38.8 | 536.5 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ባላቸው የካፒታል አቅም በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሳተፉ ድጋፍ የሚደረግላቸው የልማት ተነሽዎች ብዛት | | | | |
| | ❖ በ77 ከተሞች የከተማ መሬት ይዞታ መብት በመመዝገብ የካዳስተር ሥርዓትን በመገንባት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የይዞታ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ | የባለ ይዞታዎች ብዛት በሺህ ቁጥር | | 733 | |
| | ❖ በከተማ አስተዳደሮች ህጋዊ የካዳስተር መረጃ ሥርዓት እንዲለማ ማድረግ | ቁጥር | | 77 | |
| | **ሥራና ሥልጠና** | | | | |
| | ❖ የቴ/ሙ/ኮሌጆች ብዛት | ቁጥር | 113 | 173 | |
| | ❖ የመንግሥት ቴ/ሙ/ኮሌጆች መደበኛ ሠልጣኝ ቅበላ | ቁጥር | 120,585 | 296,070 | |
| | ❖ የግል ቴ/ሙ/ኮሌጅ ሠልጣኝ ቅበላ | ቁጥር | 46,501 | 68,151 | |
| | ❖ ኢንተርፐርነርሽፕ ሥልጠና የወሰዱ ሠልጣኞች ብዛት | ቁጥር | 2,127,546 | 11,310,978 | |
| | ❖ የክህሎት ሥልጠና የወሰዱ ሠልጣኞች ብዛት | ቁጥር | 1,281,059 | 5,505,789 | |
| | ❖ የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | ቁጥር | 6,087 | 2,457 | |
| | ❖ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞች ብዛት | ቁጥር | 112,211 | 129,387 | |
| | ❖ የኢንተርፕራይዞች ብዛት | ቁጥር | 2,633,347 | 1,034,556 | |
| | ❖ ገጠር | | | **533,766** | |
| | ❖ ከተማ | | | **500,790** | |
| | ❖ አጠቃላይ የሥራ ዕድል የሚፈጠርላቸው ሥራ ፈላጊዎች ብዛት | ቁጥር | 6,048,374 | 12,236,616 | በ2022 የተቀመጠው ዒላማ የ10 ዓመቱ አጠቃላይ ድምር ነው |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | **6,312,928** | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | **5,923,688** | |
| | ❖ በማንፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 4,723,335 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 2,436,790 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 2,286,545 | |
| | ❖ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 1,174,715 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 606,042 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 568,673 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | ❖ በማዕድን ሀብት ልማት ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 587,358 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 303,021 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 284,337 | |
| | ❖ በከተማ ግብርና ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል (እንስሳትን ሳይጨምር) | ቁጥር | | 2,202,591 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 1,136,326 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 1,066,265 | |
| | ❖ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 954,457 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 492,409 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 462,048 | |
| | ❖ በአገልግሎት ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 2,080,225 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 1,073,197 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 1,007,028 | |
| | ❖ በንግድ ዘርፍ የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | | 513,935 | |
| | ❖ ገጠር | ቁጥር | | 265,143 | |
| | ❖ ከተማ | ቁጥር | | 248,792 | |
| | ❖ የገበያ ትስስር ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች | ቁጥር | 469,673 | 244,825 | |
| | ❖ ከገበያ ትስስር የተገኘ ገቢ | በቢሊየን ብር | 24.22 | 46.72 | |
| | ❖ አዲስ የተገነቡ ክላስተር ሼዶች | ቁጥር | 17,815 | 17,496 | |
| | ❖ አዲስ በተገነቡ ክላስተር ሼዶች ተጠቃሚ የጥ/አ/ኢንተርፕራይዞች ብዛት | ቁጥር | 43,208 | 91,488 | |
| | ❖ በአዲስ ሥራ የጀመሩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ብዛት | ቁጥር | 332 | 381 | |
| | ❖ **የሚደረግ ሽግግር** | | | | |
| | ❖ ከጥቃቅን ጀማሪ ወደ ጥቃቅን ታዳጊ | ቁጥር | | 57,036 | |
| | ❖ ከጥቃቅን ታዳጊ ወደ ጥቃቅን መብቃት | ቁጥር | | 34,683 | |
| | ❖ ከጥቃቅን መብቃት ወደ አነስተኛ ጀማሪ | ቁጥር | | 17,115 | |
| | ❖ ከአነስተኛ ጀማሪ ወደ አነስተኛ ታዳጊ | ቁጥር | | 12,376 | |
| | ❖ ከአነስተኛ ታዳጊ ወደ አነስተኛ መብቃት | ቁጥር | | 6,285 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ | ቁጥር | | 1,888 | |
| | **ማዕድን ሀብት ልማት** | | | | |
| | ❖ የክልሉ የማዕድን ልማት ቀጠና በ1፡100,000 መሥፈርት ማዕድን ሀብት ጥናት የተሸፈኑ ቦታዎች ስፋት | ካሬ ኪ/ሜ | 20,000 | 172,450 | |
| | ❖ የተሰጠ የማዕድን ሥራ ፈቃድ ብዛት | ቁጥር | 56,842 | 42,896 | |
| | ❖ በከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት የተሰጠ ፈቃድ | ቁጥር | 15 | 672 | |
| | ❖ በኮንስትራክሽን ማዕድናት የተሰጠ ፈቃድ | ቁጥር | 56 | 2,100 | |
| | ❖ በኢንዱስትሩ ማዕድናት የተሰጠ ፈቃድ | ቁጥር | 9 | 750 | |
| | ❖ ከማዕድን ሥራዎች የተሰበሰበ የመንግስት ገቢ መጠን | በሚሊየን ብር | 205.92 | 1,117 | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ የቀረበ የከበረ ማዕድን መጠን | በኪሎግራም | | 152,187 | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ ከቀረበ የከበረ ማዕድን የተገኘ የውጭ ምንዛሬ | በሚሊየን ዶላር | 9.2 | 110 | |
| | **ንግድና ገበያ ልማት** | | | | |
| | ❖ የተሰጠ ንግድ ፈቃድ ብዛት | ቁጥር | 96,046 | 139,148 | |
| | ❖ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ብዛት | ቁጥር | 326,678 | 1,483,682 | |
| | ❖ ህጋዊ የንግድ ሽፋን | መቶኛ | 50 | 70 | |
| | ❖ የተሟሉ የገበያ መሠረተ ልማቶች ብዛት | ቁጥር | 3049 | 5411 | |
| | ❖ ወደ ምርት ገበያ /ECX/ የገባ የግብርና ምርት | በሚሊየን ኩንታል | 2.62 | 5.37 | |
| | ❖ ለግብይት ብራንዳቸው የሚለዩ ሰብሎች ብዛት | ቁጥር | | 4 | |
| | ❖ ለግብይት ብራንዳቸው የሚለዩ እንስሳት ብዛት | ቁጥር | | 3 | |
| | ❖ አስገዳጅ (ቡና፣ ሰሊጥ፣ ነጭና ቀይ በሎቄ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር) እና አስገዳጅ ባልሆኑ የሰብል ምርቶች ለውጭ ገበያ የተላከ የሰብል ምርት መጠን | በሚሊየን ኩንታል | 3.2 | 6.04 | |
| | ❖ አስገዳጅ (ቡና፣ ሰሊጥ፣ ነጭና ቀይ በሎቄ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር) እና አስገዳጅ ካልሆኑ የሰብል ምርቶች ኤክስፖርት የተገኘ ገቢ | በሚሊየን ዶላር | 330.4 | 557.4 | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ የተላከ ቁም እንስሳት(ዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል) ብዛት | ቁጥር | 11,534 | 22,762 | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ ከተላከ ቁም | በሚሊየን ዶላር | 1.16 | 2.46 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንስሳት (ዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል) የተገኘ ገቢ | | | | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ የተላከ ዓሳ | በቶን | 15.1 | 24.6 | |
| | ❖ ለውጭ ገበያ ከተላከ የዓሳ ምርት የተገኘ ገቢ | በዶላር | 7,550 | 12,175 | |
| | **ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር መፍጠር** | | | | |
| | ❖ የምርት ገበያ ብዛት | ቁጥር | 15 | 7,593 | |
| | ❖ አነስተኛ | ቁጥር | 14 | 5,392 | |
| | ❖ መካከለኛ | ቁጥር | 1 | 1,168 | |
| | ❖ ከፍተኛ | ቁጥር | 0 | 1,033 | |
| | ❖ በተፈጠረው የገበያ ትስስር ተጠቃሚ የሆኑ አምራች ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 89 | 7,593 | |
| | ❖ አነስተኛ | ቁጥር | 46 | 5,392 | |
| | ❖ መካከለኛ | ቁጥር | 59 | 1,168 | |
| | ❖ ከፍተኛ | ቁጥር | 19 | 1,033 | |
| | ❖ ትስስር የተደረገበት ምርት የገንዘብ መጠን | በሚሊየን ዶላር | 4.055 | 1,052.4 | |
| | **አምራች ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያለው የወጪ ምርት በብዛትና በዓይነት አምርተው ወደ ውጭ እንዲልኩ መደገፍ** | | | | |
| | ❖ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | | 52 | |
| | ❖ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ውጭ የሚላክ ምርት ዓይነት | ቁጥር | | 111 | |
| | ❖ ከአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ምርት የተገኘ ገቢ | በሚሊየን ዶላር | | 154 | |
| | **ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት** | | | | |
| | ❖ ለባለሀብቶች የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ብዛት | ቁጥር | 14,890 | 38,488 | |
| | ❖ የተመዘገበ ካፒታል በቢሊየን | ብር | 307 | 2,221 | |
| | ❖ ወደ ተግባር የገቡ/የሚገቡ ፕሮጀክቶች ብዛት | ቁጥር | 9,325 | 18,347 | |
| | ❖ ወደ ተግባር የገቡ/የሚገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 3,603 | 8,263 | |
| | ❖ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች የተፈጠረና የሚፈጠር የሥራ ዕድል | ቁጥር | 134,705 | 1,043,825 | |
| | ❖ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ/የሚያደርጉ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 121 | 1,173 | (የ2011 እና የ2012 በጀት ዓመት ባለው መረጃ) |
| | ❖ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የደረጃ ሽግግር ያደረጉ/የሚያደርጉ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | ቁጥር | 13 | 472 | (የ2011 እና የ2012 በጀት ዓመት ባለው መረጃ) |
| | ❖ የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም | መቶኛ | 62..46 | 85 | |
| | ❖ የተለዩ ተኪ ምርቶች በዓይነት | ቁጥር | 62 | 80 | |
| | ❖ የተለዩ ተኪ ምርቶችን | ቁጥር | 524 | 712 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ብዛት | | | | |
| | ❖ የሚመረቱ ተኪ ምርቶች መጠን | በቶን | 16,041 | 60,078 | |
| | ❖ ተኪ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት የዳነ የውጭ ምንዛሬ መጠን | በሚሊየን ዶላር | 47.506 | 140.180 | |
| | ❖ ወደ ውጭ ምርት በመላክ የተገኘ ገቢ | በሚሊየን ዶላር | 7.6 | 998.5 | |
| | **ባህልና ቱሪዝም** | | | | |
| | ❖ የቱሪዝም መዳረሻ ልማት ብዛት | ቁጥር | 45 | 145 | |
| | ❖ የቱሪስት ፍሰት | | | | |
| | ❖ የአገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት | ቁጥር | 12,370,557 | 63,829,357 | |
| | ❖ የውጪ አገር ቱሪስት ፍሰት | ቁጥር | 23,594 | 907,033 | |
| | ❖ **ከቱሪስት ፍሰት የተገኘ ገቢ** | | | | |
| | ❖ ከውጪ አገር ቱሪስት የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ብር | 40.40 | 1,553.2 | |
| | ❖ ከአገር ውስጥ ቱሪስት የተገኘ ገቢ | ሚሊ/ብር | 1,867.9 | 9,638 | |
| | ❖ በኢኮ ቱሪዝም ማህበር የተደራጁ 500 የአካባቢ አስጎብኝዎች ዓመታዊ አማካይ ገቢን ማሳደግ (ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ደባርቅ እና ላሊበላ) | ብር | 13,500 | 17,220 | |
| | ❖ በየዞኑ የሚገኙ የኢኮ ቱሪዝም ማህበራት አማካይ ዓመታዊ ገቢን ማሳደግ (ሰሜን ጎንደር እና ሰሜን ወሎ) | ብር | 250,000 | 335,023 | |
| | ❖ የውጭ አገር ቱሪስቶች አማካይ የቆይታ ጊዜ | በቀን | 1.5 | 4 | |
| | ❖ በቱሪስት መዳረሻዎች የአገር ውስጥ ቱሪስቶች አማካይ የቆይታ ጊዜ | በቀን | 2.3 | 6 | |
| III | **የመሠረተ ልማት ዘርፍ** | | | | |
| | **መንገድ** | | | | |
| | ❖ የተገነቡ መንገዶች በኪ.ሜ | ኪ.ሜ | 27,962.46 | 51,665.06 | |
| | ❖ የተጠገኑ መንገዶች ርዝመት | ኪ.ሜ | 26,432.25 | 50,611 | |
| | ❖ አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት | ኪ.ሜ | 28,121 | 51,665 | |
| | ❖ የመንገድ ጥግግት | ኪ/ሜ በ1000 ካሬ ኪ.ሜ | 165 | 303.26 | |
| | ❖ ክረምት ከበጋ የሚያስኪድ መንገድ ለመድረስ በእግር ጉዞ የሚወስድ ጊዜ | ደቂቃ | 35.07 | 20.08 | |
| | ❖ በቅርብ ከሚገኝ የክረምት ከበጋ መንገድ ለመድረስ ያለው አማካይ ርቀት | ኪ.ሜ | 2.89 | 1.64 | |
| | ❖ የክልሉ የክረምት ከበጋ መንገድ ጥገና | መቶኛ | 3,544.52 | 6,303 | |
| | ❖ በመንገድ የተገናኙ ቀበሌዎች ብዛት | ቁጥር | 2,479 | 3,383 | |
| | ❖ በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ ዋና መንገድ | መቶኛ | 75 | 80 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ** | | | | |
| | ❖ ህዝብ የማጓጓዝ አቅም | ተሳፋሪ /ኪሎ/ሜትር | 1,614,496,160 | 1,682,218,217 | |
| | ❖ በትራፊክ አደጋ የሞት መጠን | ቁጥር በሺህ ሰው | 106 | 10 | |
| | **ውኃና ኢነርጂ** | | | | |
| | ❖ በስታንዳርዱ መሠረት የክልሉ መጠጥ ውኃ ሽፋን | መቶኛ | 66.82 | 90 | |
| | • የገጠር የመጠጥ ውኃ ሽፋን | መቶኛ | 67.57 | 90 | |
| | • የከተማ የመጠጥ ውኃ ሽፋን | መቶኛ | 63.7 | 90 | |
| | ❖ የገጠር ውኃ ተቋማት የብልሽት ምጣኔ | መቶኛ | 12.89 | 7 | |
| | ❖ የውኃ ብክነት ምጣኔ | መቶኛ | 22.85 | 15 | |
| | ❖ የተሻሻለ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ሽፋን | መቶኛ | 54.39 | 100 | |
| | ❖ በተሻሻሉ ምድጃች የተጠቃሚዎች ብዛት | ቁጥር | 11,800,925 | 23,374,085 | |
| | ❖ የቤተሰብና ተቋማት ባዮ ጋዝ የተጠቃሚዎች ብዛት | ቁጥር | 70,655 | 201,025 | |
| | ❖ ከአማራጭ የኢነርጂ ምንጭ ቴክኖሎጂዎች የሚመረት ኃይል መጥን | ሜጋዋት | 4.015 | 26.239 | |
| | ❖ የአማራጭ የኢነርጂ ምንጭ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ብዛት | ቁጥር | 904,737 | 1,978,741 | |
| | **መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት** | | | | |
| | ❖ ጥናትና ዲዛይን የተሠራላቸው ዘመናዊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ብዛት | ቁጥር | 427 | 1,419 | |
| | ❖ የማልማት አቅም | ሄክታር | 97,356 | 558,756 | |
| | ❖ ግንባታቸው የተጠናቀቀ ዘመናዊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ብዛት | ቁጥር | 5,721 | 8,281 | |
| | ❖ የዘመናዊ መስኖ ፕሮጀክቶች የማልማት አቅም | በሄክታር | 221,959 | 478,114 | |
| | **ከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን** | | | | |
| | ❖ የክትመት ምጣኔ ዕድገት | መቶኛ | 19.42 | 26.28 | |
| | ❖ በተሟላ የከተማ ፕላን የሚመሩ ከተሞች | መቶኛ | 100 | 100 | |
| | ❖ በተለያዩ አማራጮች የተገነቡ ቤቶች | ቁጥር | 32,186 | 774,893 | |
| | ❖ የከተሞች የመንገድ መሠረተ ልማት ሽፋን | መቶኛ | - | 90 | |
| | ❖ የከተሞች የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን | መቶኛ | 63.70 | 90 | |
| | ❖ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የከተማ መሬት ዝግጅትና አቅርቦት | መቶኛ | 25 | 75 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ የታወቀ የኘላን ወሰን ያላቸው ከተሞች ብዛት | ቁጥር | 660 | 996 | |
| | ❖ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት ሽፋን | መቶኛ | 40 | 80 | |
| | ❖ በከተሞች ልማት የህብረተሰቡ ተሳትፎ | መቶኛ | 39 | 60 | |
| | ❖ የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | መቶኛ | 45 | 85 | |
| | ❖ በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ብዛት | መቶኛ | 10 | 60 | |
| | **ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን** | | | | |
| | ❖ የተቋቋሙ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት ብዛት | ቁጥር | 86 | 163 | |
| | ❖ የለሙ አፕሊኬሽኖች ብዛት | ቁጥር | 26 | 118 | |
| | ❖ የለሙ ዌብሳይቶች ብዛት | ቁጥር | 20 | 180 | |
| **IV** | **ማህበራዊ ልማት ዘርፍ** | | | | |
| | **ትምህርት** | | | | |
| | ❖ በተማሪዎች ሥነምግባር እና ባህሪ የረኩ የማህበረሰብ ክፍሎች | መቶኛ | | 100 | |
| | ❖ ለማህበረሰብ በጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎች | መቶኛ | | 75 | |
| | ❖ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ | መቶኛ | 37.2 | 100 | |
| | ❖ የ1ኛ ክፍል ጥቅል የትምህርት ቅበላ ምጣኔ | መቶኛ | 86.9 | 100 | |
| | ❖ የ1ኛ ክፍል ንጥር የትምህርት ቅበላ ምጣኔ | መቶኛ | 74.14 | 100 | |
| | ❖ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 85.13 | 98.16 | |
| | ❖ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎ | መቶኛ | 71.3 | 100 | |
| | ❖ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 77.15 | 98.16 | |
| | ❖ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎ | መቶኛ | 47.17 | 100 | |
| | ❖ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 36.38 | 75 | |
| | ❖ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ንጥር ተሳትፎ | መቶኛ | 27.84 | 75 | |
| | ❖ የ1ኛ ክፍልን መጠነ መድገም | መቶኛ | 7 | 5 | |
| | ❖ የ7ኛ ክፍል የመዝለቅ ምጣኔ | መቶኛ | 73.4 | 75.6 | |
| | ❖ የቅድመ 1ኛ ደረጃ ፆታዊ ምጥጥን | ምጥጥን | 1.0 | 1.0 | |
| | ❖ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ፆታዊ ምጥጥን | ምጥጥን | 0.94 | 1.0 | |
| | ❖ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ፆታዊ ምጥጥን | ምጥጥን | 1.10 | 1.0 | |
| | ❖ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ፆታዊ ምጥጥን | ምጥጥን | 1.08 | 1.0 | |
| | ❖ የቅድመ 1ኛ ደረጃ የልዩ ፍላጎት የትምህርት ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 0.03 | 0.2 | |
| | ❖ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 2.4 | 8.87 | |
| | ❖ \ከ7ኛ-8ኛ ክፍል የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 1.19 | 5.81 | |
| | ❖ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ | መቶኛ | 0.34 | 2.74 | |
| | ❖ የቅድመ 1ኛ ደረጃ ሴት መምህራን ድርሻ | መቶኛ | 94.3 | 95 | |
| | ❖ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ሴት መምህራን ድርሻ | መቶኛ | 45.94 | 50 | |
| | ❖ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ሴት መምህራን ድርሻ | መቶኛ | 25.89 | 30 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ሴት መምህራን ድርሻ | መቶኛ | 15 | 25 | |
| | ❖ የቅድመ አንደኛ ደረጃ የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ | ጥምርታ | 1፡1 | 1፡1 | |
| | ❖ የመጀመሪያ ደረጃ የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ | ጥምርታ | 1፡1 | 1፡1 | |
| | ❖ የ6ኛ ክፍል ፈተና ወስደው 50 እና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት | መቶኛ | 71.7 | 100 | |
| | ❖ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት | መቶኛ | 71 | 90 | |
| | ❖ በ12ኛ ክፍል አገራዊ ፈተና 50 በመቶና በላይ አምጥተው ያለፉ | መቶኛ | 26.6 | 75 | |
| | ❖ በአግባቡ የተደራጀ የልህቀት ማዕከል መመስረት | ቁጥር | | 1 | |
| | ❖ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛና አንደኛ ደረጃ በትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽፋን | መቶኛ | 0.8 | 100 | |
| | ❖ የጎልማሶች የህይወት ክህሎት ትምህርት ፕሮግራሞች ያጠናቀቁ ጎልማሶችን ብዛት | ቁጥር | 111,082 | 8,137,363 | |
| | ❖ ወንድ | ቁጥር | 65,639 | 3,296,078 | |
| | ❖ ሴት | ቁጥር | 45,443 | 4,841,285 | |
| | **ጤና** | | | | |
| | ❖ የጤና አገልግሎት ሽፋን/ሁሉን አቀፍ የጤና ተደራሽነት (በጤና ጣቢያ ደረጃ) | ኢንዴክስ | 0.43 | 0.79 | |
| | ❖ የወጣቶች ጤና አገልግሎት ሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች ሽፋን | መቶኛ | 60 | 95 | |
| | ❖ የብልህ ጅምር/RICE/ ፕሮግራም አገልግሎት የሚሰጡ ወረዳዎች ሽፋን | መቶኛ | 10.1 | 95 | |
| | ❖ ሁሉም ዓይነት መፀዳጃ ቤት ያላቸው አባዎራዎች/እማዎራዎች ሽፋን | መቶኛ | 58 | 100 | |
| | ❖ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምጣኔ | መቶኛ | 50 | 55 | |
| | ❖ የቅድመ ወሊድ ክትትል 4 ጊዜ ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን | መቶኛ | 51 | 95 | |
| | ❖ የአፍላ ወጣቶች እርግዝና ሽፋን | መቶኛ | 15 | 5 | |
| | ❖ በሠለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን | መቶኛ | 56 | 95 | |
| | ❖ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን | መቶኛ | 61 | 95 | |
| | ❖ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ሞት ምጣኔ | ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት | 69 | 33 | |
| | ❖ ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ የህፃናት ሞት ምጣኔ | ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት | 58 | 25 | |
| | ❖ የጨቅላ ህፃናት ሞት ምጣኔ | ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ | 46 | 18 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ህጻናት | | | |
| | ❖ ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ህጻናት ምጣኔ | ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት | 17 | 10 | |
| | ❖ የሶስተኛ ዙር ፔንታቫለንት ክትባት ያገኙ ሕፃናት ሽፋን | መቶኛ | 76 | 99 | |
| | ❖ ሙሉ ለሙሉ የክትባት አገልግሎት ያገኙ ህጻናት ሽፋን | መቶኛ | 73 | 96 | |
| | ❖ የሁለተኛውን ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት (MCV2) ያገኙ ሕፃናት ሽፋን | መቶኛ | 60 | 98 | |
| | ❖ የአተነፋፈስ ችግር ለሚያጋጥማቸው ጨቅላ ህጻናት ድጋፍ ተደርጎላቸው የሚድኑ የህጻናት ሽፋን | መቶኛ | 73 | 95 | |
| | ❖ በጨቅላ ህጻናት ኢንፌክሽን በሽታ ተይዘው የሚታከሙ ህጻናት ሽፋን | መቶኛ | 38 | 90 | |
| | ❖ በሳንባ ምች ታመው በጸረ ተሀዋሲያን የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሽፋን | መቶኛ | 47 | 95 | |
| | ❖ በተቅማጥ ይጠቃሉ ተብሎ ከሚታሰበው ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት የህይዎት አድን ህክምና (ORS & Zink or Zink) አገልግሎት ያገኙ ሽፋን | መቶኛ | 15 | 90 | |
| | ❖ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ህፃናት የመቀንጨር መጠን (stunting prevalence) | መቶኛ | 41 | 13 | |
| | ❖ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ህፃናት የመቀጨጭ መጠን (wasting prevalence) | መቶኛ | 8 | 3 | |
| | ❖ የኤች.አይ.ቪ ምርመራ ውጤታቸውን ያወቁ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ሰዎች ምጣኔ | መቶኛ | 71 | 95 | |
| | ❖ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት ህክምና ሽፋን | መቶኛ | 74 | 95 | |
| | ❖ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት ከሚወስዱ ውስጥ በደማቸው ያለው የኤች.አይ.ቪ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1,000 ኮፒ በታች የሆኑት (viral suppression) | መቶኛ | 46 | 95 | |
| | ❖ የሁሉም ዓይነት የቲቢ በሽታ ልየታ መጠን | መቶኛ | 54 | 92 | |
| | ❖ የቲቢ ህክምና ሙሉ ለሙሉ ያጠናቀቁ የቲቢ ህሙማን ሽፋን | መቶኛ | 95 | 97 | |
| | ❖ መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ልየታ ሽፋን | መቶኛ | 59 | 98 | |
| | ❖ መድኃኒት የተላመደ ቲቪ ህሙማን ከበሽታው የመዳን መጠን | መቶኛ | 82 | 95 | |
| | ❖ በወባ በሽታ በአዲስ የመያዝ ምጣኔ | ከ1,000 ሰዎች | 17 | 0 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ በወባ በሽታ ምክንያት የሚደርስ ሞት ምጣኔ | በመቶኛ /ከ100,000/ | 0.02 | 0 | |
| | ❖ የካታራክት ቀዶ ህክምና ያገኙ ሰዎች ብዛት | ከ1,000,000 ህዝብ | 539 | 2,000 | |
| | ❖ ዕድሜያቸው ከ1-9 ዓመት የሚሆናቸውን ህጻናት የትራኮማ ኢንፍላሜሽን ሥርጭት ከ5 በመቶ በታች ያወረዱ ወረዳዎች ባዛት | ቁጥር | 51 | 166 | |
| | ❖ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ያለ ዕድሜ የሚከሰት የሞት ምጣኔ | ቁጥር | 18 | 10 | |
| | ❖ የደም ግፊት ልየታ ከተሰራላቸው ውስጥ ከፍተኛ የደም ግፊት ያለባቸውን አዳዲስ ታካሚዎች ልየት | መቶኛ | 45 | 80 | |
| | ❖ በልየታ ውስጥ የተገኘ የስኳር በሽታ መጠናቸው ከፍተኛ የሆነባቸው የህክምና አገልግሎት | መቶኛ | 46 | 80 | |
| | ❖ በአዋቂዎች የዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍል መካከል የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን | መቶኛ | 24 | 85 | |
| | ❖ የማህጸን ካንሰር ቅድመ ምርመራ ያደረጉ ከ30-49 ዓመት የሆኑ ሴቶች ድርሻ | መቶኛ | 2 | 70 | |
| | ❖ በአዋቂዎች የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን | መቶኛ | 26 | 85 | |
| | ❖ በአዋቂዎች የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን | መቶኛ | 24 | 85 | |
| | ❖ የድባቴ የአዕምሮ ህመም ህክምና ሽፋን | መቶኛ | 5 | 60 | |
| | ❖ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድህን ሥርዓት ሽፋን (ቤተሰቦች | መቶኛ | 62 | 100 | |
| | ❖ የጤና ባለሙያ-ህዝብ ጥምርታ | በ1,000 ህዝብ | 0.9 | 4 | |
| | **ወጣቶችና ስፖርት** | | | | |
| | ❖ በአዲስ አደረጃጀቶች የሚደራጁ ወጣቶች ብዛት | በሚሊየን ቁጥር | | 5.6 | |
| | ❖ በህግ አውጭ የሚሳተፉ ወጣቶች ብዛት | መቶኛ | | 36 | |
| | ❖ በህግ ተርጓሚ የሚሳተፉ ወጣቶች ብዛት | መቶኛ | | 36 | |
| | ❖ በህግ አስፈጻሚ የሚሳተፉ ወጣቶች ብዛት | መቶኛ | | 20 | |
| | ❖ በወጣት ማዕከል ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች ብዛት | ቁጥር | | 31,035,128 | |
| | ❖ በክረምት በጎ ፈቃድ ተሳታፊ ወጣቶች ብዛት | ቁጥር | 3,646,082 | 6,652,498 | |
| | ❖ በበጋ በጎ ፈቃድ ተሳታፊ ወጣቶች ብዛት | ቁጥር | 1,972,259 | 5,088,204 | |
| | ❖ ክልል አቀፍና አገር አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ተቋማት ብዛት | ቁጥር | 6,334 | 9,459 | |
| | ❖ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና የሥልጠና ተቋማት ብዛት | ቁጥር | 6,501 | 8,440 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ❖ የሚዘጋጁ ክልል አቀፍ የውድድር መድረኮች ብዛት | ቁጥር | 28 | 30 | |
| | ❖ በስፖርት ኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | ቁጥር | 409 | 700 | |
| | ❖ በታዳጊ ፕሮግራም የሠልጣኞች ብዛት | ቁጥር | 6,579 | 10,000 | |
| **V** | **ፍትህ፣ ሠላምና ህዝብ ደህንነት** | | | | |
| | **ፍትህ** | | | | |
| | ❖ የንቃተ ህግ ትምህርት የተሰጠው ህብረተሰብ ብዛት | መቶኛ | 1.6 | 30 | |
| | ❖ የወንጀል ምርመራ መዛግብት ይግባኝና ሰበር አቤቱታመዝገቦችን መርምሮ የመወሰን/ መዝገብ የማጥራት/ አቅም | መቶኛ | 98.95 | 100 | |
| | ❖ በወንጀል የቀጥታ ክስ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅም | መቶኛ | 94.46 | 97 | |
| | ❖ የይቅርታ አገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና በመቶኛ | መቶኛ | 93 | 95 | |
| | ❖ በፍትሀብሔር ጉዳዮች የመንግስትንና የህዝብን ሀብትና ንብረት ከብክነት መከላከል በመዝገብና በገንዘብ | መቶኛ | 99 | 100 | |
| | ❖ የክስ አመሠራረትና መልስ አቀራረብ ቅልጥፍና /መዝገብ የማጥራት አቅም/ | መቶኛ | 98.92 | 100 | |
| | ❖ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች ውስጥ የማስፈጸም አቅም በመዝገብና በገንዘብ | መቶኛ | 50 | 70 | |
| | **ሠላምና ህዝብ ደህንነት** | | | | |
| | ❖ አጠቃላይ ወንጀል በገጠር | በ1000 ሰው | 1.6 | 1 | |
| | ❖ አጠቃላይ ወንጀል በከተማ | በ1000 ሰው | 5.45 | 3.0 | |
| | ❖ ዋና ዋና ወንጀል በገጠር | በ1000 ሰው | 0.6 | 0.5 | |
| | ❖ ዋና ዋና ወንጀል በከተማ | በ1000 ሰው | 1.95 | 1.0 | |
| **VI** | **የባለብዙ ጉዳዮች ዘርፍ** | | | | |
| | **ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ** | | | | |
| | ❖ ሴቶች በምክር ቤት አባልነት ያላቸው ድርሻ በመቶኛ | | | | |
| | ▪ በክልል | መቶኛ | 47.7 | 50 | |
| | ▪ በብሄረሰብ ዞን | መቶኛ | 40.63 | 50 | |
| | ▪ በወረዳ | መቶኛ | 47.5 | 50 | |
| | ▪ በቀበሌ | መቶኛ | 41.34 | 50 | |
| | ❖ **በአመራር ሰጭነት የሴቶች ድርሻ በመቶኛ** | | | | |
| | ▪ በክልል በከፍተኛ አመራር | መቶኛ | 20 | 50 | |
| | ▪ በክልል በመካከለኛ አመራር | መቶኛ | 19 | 50 | |
| | ▪ በዞን በከፍተኛ አመራር | መቶኛ | 26 | 50 | |
| | ❖ በድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ተጠቃሚ የሆኑ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች | ቁጥር | 361,244 | 3,798,938 | |
| | ❖ በጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የሴቶች የባለቤትነት ድርሻ | መቶኛ | 32 | 50 | |
| | ❖ የገጠር መሬት ባለቤትነት | መቶኛ | 43.5 | 100 | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ ዓመት /2012 በጀት ዓመት/ | ግብ /2022 በጀት ዓመት/ | ተጨማሪ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተረጋገጠላቸው ሴቶች ብዛት | | | | |
| | **አካባቢ፣ ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ** | | | | |
| | ❖ ህጋዊ ዕውቅና የተሰጣቸው ጥብቅ ሥፍራዎች ብዛት | ቁጥር | 5 | 10 | |
| | ❖ የአካባቢ ተፅዕኖ በመገምገም የይሁንታ ፈቃድ የሚሰጠው ሠነድ ብዛት | ቁጥር | | 40,000 | ጠቅላላ በ10 ዓመቱ የሚሠራ |
| | ❖ የአካባቢ ክትትል፣ ምርመራና ቁጥጥር የተደረገላቸው ፕሮጀክቶች ብዛት | ቁጥር | | 73,000 | ጠቅላላ በ10 ዓመቱ የሚሠራ |
| | ❖ በጤና ኃይቅ ላይ በመስፋፋት ከፍተኛ ችግር እያደረሰ ያለውን የእንቦጭ አረምና በሌሎች ውኃ አካላትና ውኃ አዘል መሬቶች የተከሰቱትን መጤ አረሞች ችግር ወደማይሆኑበት ደረጃ ማድረስ /መቀነስ | መቶኛ | 70 | 100 | |
| | ❖ 6ቱን የልማት ቀጠና ወይም ተፋሰስን መሠረት ባደረገ በክልሉ ያሉ የተፈጥሮ/ሰው ሠራሽ ሀይቆችን እና ውኃ አዘል መሬቶችን በጥናት በመለየት የራሳቸው የሆነ የአያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ በካርታ በማዘጋጀት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎታቸውን በማጎልበት የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ህብረተሰብና አካባቢን መፍጠር | በሄክታር | 10,500 | 400,000 | ከዩኒቨርሰቲዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በመተባበር |
| | ❖ በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የሚያቋርጡ ወንዞችን ከውኃ ብክለት መከላከል እና የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ሥፍራ እንዲሆኑ ማድረግ | በቁጥር | 5 | 400 | ከመሬትና አካባቢ ጥበቃ ጋር በመተባበር |
| | ❖ በክልሉ የሚገኙ የውኃ አካላትን (ሀይቆችን፣ወንዞችን፣ የውኃ ምንጮችን) የበፈር ዞን መከለል እና መልሰ እንዲያገግሙ ማድረግ በዚህም ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ | በቁጥር | 1 | 100 | ከመሬት ቢሮ ጋር በመተባበር |
| | **ስነ ህዝብ** | | | | |
| | ❖ የክልሉ ህዝብ ብዛት | ቁጥር | 22,189,999 | 25,481,997 | |
| | ❖ ወንድ | ቁጥር | 11,068,826 | 12,651,358 | |
| | ❖ ሴት | ቁጥር | 11,121,173 | 12,830,639 | |
| | ❖ ከ30 ዓመት በታች ያለ ህዝብ ብዛት | መቶኛ | 69.67 | 69.76 | |
| | ❖ በማምረት ዕድሜ ክልል /ከ15-64 ዓመት/ ያለ ህዝብ ብዛት | መቶኛ | 55.87 | 56.78 | |

# 11. የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦች

የማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ ጥቅል የሆኑ አመልካቾችን የያዘ ሲሆን በአጠቃላይ ልማቱ ያለበትን ደረጃ ከማሳየቱም ባሻገር በክፍላተ ኢኮኖሚ ለሚታቀዱ ዕቅዶች መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ የክልሉ ዋነኛ የልማት አጀንዳ ድህነትን ማስወገድ ሲሆን በአገርና በክልል ደረጃ የወጡና እየተተገበሩ ያሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞች ይህንኑ ትልቅ አጀንዳ መሠረት በማድረግ በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ የታዩ ናቸው፡፡

በመሆኑም የቀጣይ 10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ መሠረታዊ ጉዳይ ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ድህነትን በግማሽ መቀነስ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ከዚህ አኳያ የክልሉ ማክሮ ኢኮኖሚ ዕቅድ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ይኖሩታል፡፡

## የኢኮኖሚ ዕድገት

የክልሉ ኢኮኖሚ በአለፉት 10 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት በአማካይ የ7.6 በመቶ ዕድገት ያስመዘገበ ሲሆን በቀጣይ 10 ዓመት በክልሉ የአምራች ዘርፎች ዝቅተኛ ምርታማነት ሊሻሻል እንደሚችል እና የግብርና ምርትን በእጥፍ በማሳደግ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ሚናውን ከፍ በማድረግ በእያንዳንዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ያሉ አቅሞችን በውጤታማነት መጠቀም እንደ መነሻ ታሳቢ በመውሰድ የክልሉ ኢኮኖሚ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3.6 በመቶ ዝቅተኛ የዕድገት ምጣኔ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 12.8 በመቶ የሆነ ባለሁለት አሀዝ /double digit/ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ከ2013 በጀት ዓመት እስከ 2022 በጀት ዓመት ባሉት 10 ዓመታት በየዓመቱ በአማካይ የ9.3 በመቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ታቅዷል፡፡ በዚህም አማካይ ዓመታዊ የክልሉ የነፍስ ወከፍ ገቢ በ7.7 በመቶ ያድጋል ተብሎ ተገምቷል፡፡

የክልሉን ኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ለማረጋገጥ የግብርናውን ዘርፍ የማዘመንና ከኋላ ቀር የአስተራረስ ሥርዓት በማውጣት አማካይ የግብርናውን ዘርፍ የኢኮኖሚ ዕድገት /Agricultural GDP/ በ5.9 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተይዟል፡፡ በግብርናው ዘርፍ የእንስሳት ሀብት ልማቱን በአማካይ በ6.15 በመቶ እንዲሁም የሰብል ልማትን በአማካይ በ5.87 በመቶ ለማሳደግ የታቀደ ሲሆን የእንስሳት ሀበት ልማቱን ዕድገት ምጣኔ ከፍ በማድረግ በሂደት የእንስሳት ሀብት ልማቱ የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ በግብርናው ዘርፍ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲኖር ታቅዷል፡፡ በኢንዱስትሪው ዘርፍም የኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ በአለፉት ዓመታት ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ ለዘርፉ ዕድገት አስተዋጽዖ የነበረው ሲሆን በቀጣይ 10 ዓመታት በአማካይ የ8.25 በመቶ ዕድገት ይኖረዋል፡፡

በተመሳሳይ በዚሁ ዘርፍ የአምራች ኢንዱስትሪው ሚና እየጨመረ እንደሚሄድ ታሳቢ የተደረገ ሲሆን በአማካይ በ2022 በጀት ዓመት 18.26 በመቶ ዕድገት እንዲያስመዘግብ በዕቅድ ተይዟል፡፡ ይህም ከኮንስትራክሽን ንዑስ ዘርፍ መሪነት ወደ አምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ መሪነት ለማሸጋገር ያስችላል፡፡ እንዲሁም የክልሉን ተወዳዳሪነት በማሳደግ በአምራች ኢንዱስትሪ ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብን እንዲሁም የልማት ፋይናንስ ምንጭ የሆነውን የክልሉን የገቢ አቅም በማሳደግ የልማት ፋይናንስ ዘላቂነት እና የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ማረጋገጥ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በክልሉ በቀጣይ 10 ዓመታት የክልሉን የካፒታል ክምችት ማሳደግ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በዚህም የሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች ዕድገት ለአጠቃላይ ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት የክልሉን ኢኮኖሚ ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎች ማሸጋገርን፣ በቀጣይ ዓመታትም ጉልበት፣ ካፒታልና የነገረ ምርቶች (TFP ወይም ቴክኖሎጂ) በክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የሚኖራቸው ሚና የሚቀጥልና ወደ ቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዟችን መሠረት ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽዖ ማሳደግ ተገቢ ይሆናል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገቱ በክፍላተ-ኢኮኖሚ ሲታይ በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እና የአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል በየዓመቱ በአማካይ የ5.9 በመቶ፣ የ13.49 በመቶ እና የ11.43 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግቡ ታቅዷል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡- ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ዕድገት በዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች በመቶኛ**

| የኢኮኖሚ ዘርፎች | አፈፃፀም | | | ግብ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2003-2007 (አማካይ) | 2008-2012 (አማካይ) | የ2012 መነሻ | 2013-2017 (አማካይ ዕድገት) | 2018-2022 (አማካይ ዕድገት) | 2013-2022 (አማካይ ዕድገት) | 2022 ዕድገት ምጣኔ |
| ግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች | 7.2 | 4.6 | 2.5 | 5.7 | 6.3 | 5.9 | 6.5 |
| ኢንዱስትሪ | 12.5 | 9.7 | 2.0 | 12.4 | 14.6 | 13.49 | 15.4 |
| አምራች ንዱስትሪ | 35.4 | 20.6 | 14.0 | 17.9 | 18.7 | 18.26 | 19.1 |
| አገልግሎት | 11.2 | 8.6 | 6.6 | 10.1 | 12.7 | 11.43 | 18.3 |
| ክልላዊ ጠቅላላ ምርት | 9.0 | 6.5 | 3.6 | 8.3 | 10.3 | 9.3 | 12.8 |

ምንጭ፡- የአማራ ክልል ፕላን ኮሚሽን

### ቁጠባንና ኢንቨስትመንትን ማሳደግ

ከተያዘው ከፍተኛ የልማት ግብ አንፃር ቁጠባ የራሱን ሚና እንዲወጣ ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች የሚሠራ ይሆናል፡፡ የግል ቁጠባን ለማሳደግ የተለያዩ የቁጠባ አማራጮችን የመጠቀም በተለይም ህብረተሰቡን በማስተባበር የቁጠባ ልምዱ እንዲጐለብት በማድረግ የቁጠባ መንገዶችን በማስፋት የቁጠባ ምጣኔ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማትን ጨምሮ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነትና የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲቀላጠፍ የሚያደርግ ሥራ ይሠራል ፡፡ በተጨማሪም በክልሉ በገጠር ቀበሌዎች የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማትንና የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራትን በገጠር ቀበሌዎች ተደራሽ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ ይህንን ግብ ለማሳካት በክልሉ የሚገኙ የመንግስትም ሆነ የግል ባንኮች አዳዲስ ቅርንጫፎችን በብዛት ከመክፈት በተጨማሪ አዳዲስ ባንኮች እንደሚጨመሩና በክልሉ አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት የውስጥ አቅማቸውን ከማጠናከር ባሻገር በሁሉም ቀበሌዎች ተደራሽ የማድረግና 75 በመቶ የክልሉ አርሶ አደር የቁጠባ ሂሳብ እንዲኖረው የሚያስችል ሥራ እንደሚተገበር ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አንዱና ዋናው ምንጭ ኢንቨስትመንት ነው፡፡ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ በተለይም በማኑፋግቸሪንግ፣ በመሠረተ ልማት፣ በማህበራዊ ልማት ዘርፎች እና በሌሎችም የልማት መስኮች ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ተገቢ ይሆናል፡፡ የግል እና የመንግስት ኢንቨስትመንት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ደረጃ እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ ስለሆነም ኢንቨስትመንት በሚፈለገው ደረጃ እንዲያድግ የክልል ውስጥ ቁጠባን የማሳደግና የመንግስትን በጀት በቁጠባ እና በውጤታማነት መጠቀም በመሪ የልማት ዕቅድ ዘመኑ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በክልሉ ህብረተሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን የመቆጠብ ባህል ይበልጥ በማጐልበት ከፍተኛ ቁጠባ እንዲሰበሰብ ከማድረግ ጐን ለጐን ይህንን ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብን ተቀማጭ ገንዘብ በብድር መልክ ወስዶ በመጠቀም ረገድ የሚታየውን ጉድለት በማስተካከል በተለይም የመበደር አቅምን በመገንባት ህብረተሰቡ በኢንቨስትመንት ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በስፋት እንዲሳተፍ የማድረግ ሥራ በትኩረት እንደሚሰራ ታቅዷል፡፡

ስለሆነም የአጠቃላይ የካፒታል ግንባታ ወይም ኢንቨስትመንትን ተወስዶ ሲታይ በ2012 በጀት ዓመት የ28.3 በመቶ ለጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት (Regional GDP) አስተዋጽዖ የነበረው ሲሆን ከ2013-2022 በጀት ዓመታት የ9.3 በመቶ አማካይ የኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ለማሳካት የ35.7 በመቶ የመዋዕለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) ድርሻ ማስመዝገብ እንደሚጠበቅ ተገምቷል፡፡ ይህም የኢኮኖሚና ማህበራዊ መሠረተ ልማት በማስፋፋት እና ሌሎች የመንግስትና የግል የልማት ፕሮጀክቶች አፈፃጸምን በማሳደግ፣ ብክነቶችን በመቀነስና የካፒታል ምርታማነትን በመጨመር ለማሳካት ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ

በክልሉ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም የመዋቅራዊ ለውጥ ሊመጣባቸው የሚገቡ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለይቶ በትኩረት መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡ በዚህም መሠረት የመዋቅራዊ ለውጡ በዘርፎች

በራሳቸው ውስጥ እና ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው ዘርፎች ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ዘርፎች ማሸጋገር ነው። ከዚህ አንፃር የግብርና ልማትን በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ በግብርና በራሱ እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችል አሠራር ተጠናክሮ ይቀጥላል። በዚሀም መሠረት ከግብርናው ዘርፍ ውስጥ የእንስሳት ንዑስ ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ እንዲሄድና በዘርፉ የሚኖረውን ድርሻ እንዲይዝ ለማድረግ ታቅዷል።

በተመሳሳይ የኢንዱስትሪ ዘርፍ በተለይ የአምራች ኢንዱስትሪው ዓመታዊ የተጨማሪ ዕሴት ድርሻ ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት አንፃር የማሳደግ ሥራ ይከናወናል። በመሆኑም ግብርና በምርት አስተዋጽዖው እና በሰው ኃይል ሥምሪቱ ለኢኮኖሚው የሚኖረው ድርሻ እንዲቀንስ ማድረግ እና በአንጻሩ የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ እንዲሁም የቱሪዝም፣ የትራንስፖርት እና የከተማ ልማት ዘርፎችን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ የአገልግሎት ዘርፍ ድርሻ እንዲጨምር ታቅዷል።

**ሠንጠረዥ 4፡- የኢኮኖሚ ዘርፎች ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ያላቸው ድርሻ (በመቶኛ)**

| **የኢኮኖሚ ዘርፎች** | **2003** | **2008** | **2011** | **2012** | **2017** | **2022** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 62.0 | 56.7 | 54.1 | 53.7 | **46** | **38.8** |
| ኢንዱስትሪ ዘርፍ | 12.5 | 14.8 | 16.0 | 15.7 | **19** | **23.6** |
| • አምራች ኢንዱስትሪ | 1.4 | 4.3 | 6.1 | 6.6 | **8.1** | **14.2** |
| አገልግሎት ዘርፍ | 26.8 | 29.6 | 31.1 | 31.7 | **35** | **37.6** |

ምንጭ፡- የአማራ ክልል ፕላን ኮሚሽን

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተገለፀው የግብርናው ዘርፍ ከጠቅላላው የክልል ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ 38.8 በመቶ እንደሚሆን የተገመተ ሲሆን ይህም ከመነሻው ዓመት ከ2012 በጀት ዓመት 53.0 በመቶ አንፃር ድርሻው በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱን ያሳያል። እንዲሁም የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 23.6 በመቶ ከፍ እንደሚል ዕቅዱ ያመለክታል። በኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪው የ14.2 በመቶ ድርሻ ሲኖረው የኮንስትራክሽን ዘርፉ የ8.3 በመቶ ድርሻ እንደሚኖረው ታቅዷል። ይህም የሚያመላክተው በቀጣይ የመሪ ዕቅድ ዘመን በኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ከኮንስትራክሽን ዘርፍ ወደ አምራች የኢንዱስትሪ ዘርፍ መሪነት ለውጥ እንደሚኖር ነው። በተመሳሳይ የአገልግሎት ዘርፍ ከጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የሚኖረው ድርሻ በ2022 በጀት ዓመት 37.6 በመቶ እንዲሆን ታቅዷል።

**ሠንጠረዥ 5፡- የኢኮኖሚ ዘርፎች ለጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ዕድገት የሚኖራቸው አስተዋጽዖ (በመቶኛ)**

| **የኢኮኖሚ ዘርፎች** | **የዕድገት ምጣኔ** | | **ከክልላዊ ምርት ድርሻ** | | **ለክልላዊ ምርት ዕድገት አስተዋጽዖ** | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **2008-12** | **2013-22** | **2012** | **2022** | **2008-12** | **2013-22** |
| **ግብርና** | 4.6 | 5.9 | 52.5 | 38.8 | 2.6 | 2.69 |
| ሰብል | 5.1 | 5.95 | 34.0 | 25.1 | 1.8 | 1.76 |
| የእንስሳት ሀብት | 3.4 | 6.15 | 14.4 | 10.7 | 0.5 | 0.77 |
| **ኢንዱስትሪ** | 9.7 | 13.49 | 16.3 | 23.6 | 1.5 | 2.69 |
| አምራች ኢንዱስትሪ | 19.8 | 18.26 | 6.5 | 14.2 | 0.9 | 1.89 |
| ኮንስትራክሽን | 4.7 | 8.25 | 9.2 | 8.3 | 0.5 | 0.72 |
| **አገልግሎት** | 8.8 | 11.43 | 31.2 | 37.6 | 2.6 | 3.93 |
| ንግድ፣ ሆቴል እና ሬስቶራንት | | 11.03 | 11.0 | 12.9 | | 1.32 |
| ትራንስፖርት እና ኮሚዩኒኬሽን | | 13.26 | 6.0 | 8.5 | | 0.96 |
| **ክልላዊ ምርት*** | **6.6** | **9.3** | **100** | **100** | **6.6** | **9.3** |

ምንጭ፡- የአማራ ክልል ፕላን ኮሚሽን

ከላይ በሠንጠረዡ እንደተመላከተው በመሪ የልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርና ዘርፍ ለጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ዕድገት በአማካይ የ2.7 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በአንጻሩ የኢንዱስትሪና አግልግሎት ዘርፎች በቅደምተከተል የ2.7 መቶኛ ነጥብ እና የ3.9 መቶኛ ነጥብ አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል።

## የኢኮኖሚ ዘርፎች የሥራ ሥምሪት

የመዋቅራዊ ለውጥ ዕቅድ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ከሚኖራቸው የድርሻ ለውጥ በተጨማሪ በየዘርፎቹ በሚሠማራው የሠራተኛ ኃይል ስብጥር ለውጥ እንደሚኖር ይመላከታል። በዚህም መሠረት የግብርና ዘርፍ ከአገራዊ ምርት የሚኖረው ድርሻ እንደሚቀንስ ሁሉ በዘርፉ የሚሠማራው የሰው ኃይል በሥራ ላይ እንደሚሆን ከሚገመተው አጠቃላይ የሰው ኃይል የሚኖረው ድርሻም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 66.6 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 44.2 በመቶ እንደሚቀንስ ተገምቷል። በተመሳሳይ ከአጠቃላይ በሥራ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ ውስጥ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማራው የሠራተኛ ኃይል ከነበረበት 6..4 በመቶ ወደ 14.7 በመቶ እንዲሁም በአገልግሎት ዘርፎች ላይ የሚሠማራው የሠራተኛ ኃይል ከ27.8 በመቶ ወደ 41.1 በመቶ እንደሚያድግ ታቅዷል።

**ሠንጠረዥ 6፡- የኢኮኖሚ ዘርፎች የሠራተኛ ሥምሪት በመቶኛ**

| የኢኮኖሚ ዘርፎች | 2005 | 2012 | 2022 |
|---|---|---|---|
| ግብርናና ተዛማጅ ዘርፎች | 77.9 | 66.6 | 44.2 |
| ኢንዱስትሪ ዘርፍ | 7.3 | 6.4 | 14.7 |
| • አምራች አንዱስትሪ | 4.84 | 3.28 | 11.7 |
| አገልግሎት ዘርፍ | 14.8 | 27.3 | 41.1 |

ምንጭ፡- የአማራ ክልል ፕላን ኮሚሽን

የመዋቅራዊ ለውጡ አንዱ መሠረታዊ አቅጣጫ የአምራች ኢንዱስትሪው በምርትና በሥራ ዕድል ፈጠራ ፈጣን ዕድገት እንዲያሳይ መታቀዱ ነው። ይህ ንዑስ ዘርፍ በ2012 በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ከተሰማራው የሰው ኃይል 51.39 በመቶ፣ ከአጠቃላይ የሰው ኃይል ደግሞ 3.28 በመቶ ለሚሆነው የሥራ ዕድል የፈጠረ ነበር። በ2022 በጀት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪ የሠራተኛ ድርሻ ከኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ 79.4 በመቶ፣ ከአጠቃላይ አገራዊ የሠራተኛ ኃይል ደግሞ 11.7 በመቶ እንዲደርስ ታቅዷል።

በአጠቃላይ እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የሥራ ዕድል እየፈጠረ ዜጎችን ተጠቃሚ እያደረገ ያለ እንደሆነ መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ። ሆኖም ተከማችቶ የቆየው የሥራ አጥ ዜጋ ብዛት እና ወደ ሥራ ሥምሪት ገበያ የሚቀላቀለው አዲስ የሰው ኃይል ከፍተኛ መጠን ያለው በመሆኑ የሥራ አጥነት ችግሩ አሁንም በገጠርና በከተማ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከዚህም በላይ የሥራ ዕድል የሚፈጥር እንዲሆን ለማድረግ በየዘርፉ የተቀየሱትን የልማት ፕሮግራሞች በላቀ ብቃት ተግባራዊ ማድረግ በመሪ ዕቅዱ ዓመታት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በ2010 በጀት ዓመት ባወጣው የከተሞች የሥራ እና የሥራ አጥ ምጣኔ ሰርቬይ ጥናት (Employment and Unemployment Survey) የክልሉ የሥራ አጥ ምጣኔ 19.7 በመቶ ሲሆን ይህም ወንድ 11.7 በመቶ ሴት 28.1 በመቶ የሥራ አጥ ምጣኔ እንደነበረ መረጃው ያመላክታል።

በገጠር ያለውን የሥራ አጥነት በተመለከተ በ1997 በጀት ዓመት እና በ2005 በጀት ዓመት በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሥራ ኃይል ሰርቬይ ጥናት (Labour Force Survey) 3.1 በመቶ እና 1.6 በመቶ በቅደምተከተላቸው እንደነበረ ያሳያል። የገጠር የሥራ አጥነት ምጣኔ በየዓመቱ የሚጠና ባለመሆኑ የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ማግኘት አልተቻለም። በተጨማሪም ጥናቶቹ በገጠር ስላለው ሥራ አጥ ሁኔታ በትክክል የሚገልፁ ናቸው ብሎ ለመውሰድ አስቸጋሪ እንደሆነ ከመረጃው መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ በቀጣይ 10 የመሪ ዕቅዱ ዓመታት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት ዘመናዊ ግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪ የማስፋፋት ሥራዎች በግብ የተያዙ ሲሆን

በተጨማሪም እንደ ማዕድን፣ ቱሪዝምና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የማስፋፋት ሥራዎች ዋነኛ የትኩረት መስኮች ተደርገው ታቅደዋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ተግባር በገጠርና በከተማ እየተስተዋለ ያለውን ሥራ አጥነት በእጅጉ ለመቀነስ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በ2012 በጀት ዓመት በከተማ የታየውን የ20.4 በመቶ ሥራ አጥነት ምጣኔ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7.56 በመቶ ለመቀነስ በግብ ተይዟል፡፡ ለዚህም የዘመናዊ ግብርናና አምራች ኢንዱስትሪ መስፋፋትና የቱሪዝምና ማዕድን ዘርፎች የመሪ ዕቅዱ ዋነኛ የትኩረት መስኮች መሆናቸው ለሥራ አጥ ምጣኔ ዕድገት መቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽፆ እንደሚኖራቸው ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## የዋጋ ግሽበትን መቀነስ

በአለፉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዓመታት በግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህም በክልሉ የሚከሰተውን የዋጋ ንረት ከመቆጣጠር አንፃር የበኩሉን አስተዋጽፆ ቢኖረውም በክልሉ እየተከሰተ ያለውን የዋጋ ንረት ከመቀነስ አንፃር የነበረው አስተዋጽፆ በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡ በዚሁም የዋጋ ግሽበቱ ባለ ሁለት አሃዝ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በመሆኑም በ10 ዓመቱ የመሪ ልማት ዕቅድ ዘመንም በክልል ደረጃ የተከሰተውን የዋጋ ንረት በነጠላ አሃዝ የመገደብ ግብ ለማሳካት የተጠናከረ ሥራ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ መረጃው ያመላክታል፡፡ ከዚህ አንፃር በክልሉ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ምርትና ምርታማነትን በአምራች ዘርፎች ማሳደግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡ በተለይም በግብርና ዘርፉ የዋና ዋና የምግብ ሰብሎችን ምርታማነት በማሳደግ፣ የገቢ ንግድን በሚተኩ ኢንዱስትሪዎች ምርታማነትን ማሻሻል በትኩረት ይሠራል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የክልል ውስጥ ግብይት በውድድር የሚመራና ግልፅነት የሰፈነበት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የኤክስፖርት ምርቶችን በጥራት እና በስፋት በማምረት በዓለም ገበያ ተወዳድሮ መሸጥ የሚያስችል አቅም ለመገንባት ይሠራል፡፡

## ድህነት ቅነሳ

የክልሉ መንግስት ከድህነት ወለል በታች የሚገኘውን የህዝብ ቁጥር ለመቀነስ በክልል ደረጃ ድህነት ተኮር ተግባራት ላይ በስፋት በመረባረብ በገጠር የግብርና እና ገጠር ልማት ሥራዎችን በተቀናጀና ህዝብን ባሳተፈ መልኩ በመፈፀም በተለይ በሰብል ልማት ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ እንዲሁም በምግብ ዋስትና ሥራችን ስኬታማ ተግባራት ይከናወናሉ። በተለይ ደግሞ በከተሞች አካባቢ ከሥራ አጥነት ጋር ተያይዞ የሚከሰት የድህነት ሁኔታን ለመቀነስ ህብረተሰቡን በማደራጀት በተለያዩ አነስተኛ እና ጥቃቅን የሥራ ዘርፎች እንዲሰማሩ በማድረግ እና የተቀናጁ የልማት ፕሮግራሞችን በመተግበር አዳዲስ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ይሠራል።

ከዚህም ባሻገር የትምህርትና የጤና ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለመፈፀም ጥረት ይደረጋል። በመሆኑም በ2012 በጀት ዓመት በክልሉ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል ተብሎ የተገመተው ህዝብ 21 በመቶ የነበረ ሲሆን በቀጣይ የወጡትን አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሞችን በተሟላ መልኩ በገጠርና በከተማ የልማት ሥራዎቻችን በመተግበር ድህነትን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይጠበቃል። ስለዚህም በቀጣይ 10 የመሪ ዕቅድ ዓመታት በዘርፎች ላይ የሚደረገው ርብርብ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ከማስቻል ባሻገር በድህነት ቅነሳው ረገድ ካላቸው ፋይዳ አንፃር በስፋት የሚታይ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በክልሉ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል ተብሎ የተገመተውን በ2022 በጀት ዓመት በዘላቂ የልማት ግቦች በተቀመጠው ድህነትን 50 በመቶ የመቀነስ ግብን ታሳቢ በማድረግ ወደ 10 በመቶ ለመቀነስ በግብ ተይዟል፡፡

## የልማት ፋይናንስ

የክልሉ የልማት ፋይናንስ መሠረታዊ አቅጣጫ የመንግስት ገቢን የማሳደግ፣ የመንግስት ወጪ በመሪ ዕቅዱ ዓመት ለማሳካት የተፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ለውጥ ለሚደግፉ በተለይም ድህነትን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በቀጣይ 10

የመሪ ዕቅዱ ዓመታት የክልሉን የኢኮኖሚ አቅም መሠረት ያደረገ የገቢ አሠባሰብ ሥርዓት የመዘርጋትና ባለው የኢኮኖሚ አቅም የተመጣጠነ ገቢ የመሰብሰብ እንዲሁም ወጪን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተገባራዊ ለማድረግ በአቅድ ተይዟል፡፡

የክልሉን ገቢ በተመለከተ አጠቃላይ የክልሉን የውስጥ ገቢ የማሳደግና ከፌደራል ድጎማና ከእርዳታ ጥገኝነት ቀስ በቀስ እየቀነሱ ክልሉ በራሱ ገቢ የክልሉን ሰፊ የልማት እንቅስቃሴዎች እያሟላ የሚሄድበት የገቢ ዕቅድ ተይዟል፡፡ በክልሉ ያለፉ 10 ዓመታት የገቢ አሰባሰብ እደገትን ስንመለከት በዓመት በአማካይ ጭማሪው ከ2 ቢሊዮን አይበልጥም፡፡ ይህም በገቢ አሰባሰብ ሥርዓታችን ላይ ጉድለቶች እንዳሉ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ከክልሉ አጠቃላይ ገቢን ለልማት የማመንጨት አቅም አንፃር ተወስዶ ሲታይ ብዙ መሥራት እንደሚገባ ያመለክታል፡፡

ስለሆነም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚገባ የተያዘ በመሆኑ ለዚህም የኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚስፋፋና በክልሉ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚመጣ ታሳቢ የተደረገ በመሆኑ እና ግብርናውን በማዘመን የግብርና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ እንደሚሰራ በመታቀዱና በክልሉ በጥሬ ዕቃነት ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ ዕሴት በመጨመር ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል አሠራር እንደሚዘረጋ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩልም በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት የታክስ ፖሊሲና አስተዳደር ማሻሻያዎችን በማድረግ የታክስ ሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን የታክስ ሥርዓቱን በማዘመን እንዲሁም ህጋዊ የንገድ አሠራሮችን በመዘርጋት በክልሉ የሚሰበሰብ ገቢን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 11.06 ቢሊዮን ብር ወደ 178.47 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

በፕላንና ልማት ቢሮ አስተባባሪነት የተዘጋጀው የህጻናት ተኮር የበጀት አጭር መግለጫ ዶክመንት /Child Focused Budget Brief Docment/ እንደሚያመለክተው ያለፉት 12 ዓመታት የወጪ በጀት በየዓመቱ በአማካይ የ18 በመቶ ጭማሪ እንዳለ ያሳያል፡፡ ከዚህ በመነሳትም በቀጣይ 10 ዓመታት የክልሉ ወጪና ገቢ በጀት በ10 ዓመቱ መጨረሻ ወደ 323 ቢሊዮን ብር ሊደርስ እንደሚችል ተገምቷል፡፡ የተጀመረውን ፈጣን ዕድገት በማስቀጠል ድህነትን ለመቀነስና ብሎም ወደ ብልፅግና ጎዳና ለማምራት የድህነት ተኮር ዘርፎችን የወጪ ድርሻ ከፍ በማድረግ የበጀት አመዳደቡን ውጤታማ የማድረግ ሥራ ትኩረት የሚሠጠው እንደሆነም ታሳቢ ተደርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡- የቀጣይ 10 ዓመታት የመንግስት ገቢና ወጪ ትንበያ /በቢሊዮን ብር/**

| ዝርዝር | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠቅላላ ገቢ | 47.35 | 62.69 | 75.23 | 90.27 | 108.33 | 129.99 | 155.99 | 187.19 | 224.63 | 269.56 | 323.47 |
| ከክልሉ የሚሰበሰብ ገቢ | 14.99 | 22.88 | 32.6 | 47 | 58.3 | 73.4 | 92.4 | 116 | 145.4 | 181.98 | 227.43 |
| መደበኛ ገቢ | 11.06 | 18.16 | 26.75 | 36.79 | 45.6 | 57.47 | 72.34 | 90.79 | 113.81 | 142.45 | 178.02 |
| የቀጥታ ታክስ ገቢ | 7.297 | 11.2 | 16.49 | 20.3 | 25.16 | 31.71 | 39.91 | 50.1 | 62.8 | 78.6 | 98.23 |
| ቀጥታ ያልሆነ ታክስ ገቢ | 2.775 | 5.6 | 10.96 | 13.9 | 17.23 | 21.71 | 27.33 | 34.3 | 43 | 53.82 | 67.26 |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 0.98 | 1.13 | 1.2 | 2.59 | 3.21 | 4.05 | 5.09 | 6.39 | 8.01 | 10.03 | 12.53 |
| የከተሞች አገልግሎት ገቢ | 1.816 | 2.4 | 3.3 | 4.18 | 5.18 | 6.53 | 8.22 | 10.32 | 12.93 | 16.18 | 20.23 |
| የውስጥ ገቢ | 2.11 | 2.32 | 2.55 | 2.81 | 3.48 | 4.39 | 5.52 | 6.93 | 8.69 | 10.88 | 13.6 |
| የፌደራል መንግሥት የድጋፍ በጀት | 32.36 | 39.81 | 42.63 | 46.49 | 43.27 | 50.08 | 56.57 | 63.58 | 71.2 | 79.24 | 87.58 |
| ጠቅላላ ወጪ | 47.35 | 62.69 | 75.23 | 90.27 | 108.33 | 129.99 | 155.99 | 187.19 | 224.63 | 269.56 | 323.47 |
| የመደበኛ ሥራዎች ወጪ | 37.42 | 49.85 | 58.64 | 68.82 | 80.6 | 94.15 | 109.65 | 127.29 | 147.2 | 169.47 | 194.08 |
| የካፒታል ሥራዎች ወጪ | 9.93 | 12.84 | 16.59 | 21.45 | 27.73 | 35.84 | 46.34 | 59.9 | 77.43 | 100.09 | 129.39 |
| የድህነት ተኮር ዘርፎች የወጪ ድርሻ በመቶኛ | 62 | 62.24 | 62.49 | 62.74 | 62.98 | 63.23 | 63.48 | 63.73 | 63.98 | 64.24 | 65 |

# 12. የክፍላተ ኢኮኖሚዎች የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ

## 12.1. ኢኮኖሚ ልማት ዘርፍ

### 12.1.1 ግብርና ልማት

የግብርናው ዘርፍ የአብዛኛው የክልላችን ህዝብ መተዳደሪያና የሥራ ኃይል የተሠማራበት መሆኑ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ድርሻው እየቀነሰ ያለ ቢሆንም ከክልሉ ኢኮኖሚ /RGDP/ 53.7 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚያበረክት መሆኑ አሁንም ሆነ ወደፊት ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት ተስፋ የሚጣልበትና ወሳኝ ሆኖ የሚቀጥል ዘርፍ እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡ በተጨማሪ በአለፉት ዓመታት የግብርናውን ምርታማት ለማሳደግ በተሰራው ሥራ የአርሶ አደሩ ገቢ በማደጉ ምክንያት ተንሰራፍቶ የነበረውን ድህነት ትርጉም ባለው ደረጃ ለመቀነስ ያስቻለ ከመሆኑ በተጨማሪ የመግዛት አቅም ከፍ በማለቱ ምክንያት የሌሎች ዘርፎችን ምርትና አገልግሎት የመጠቀም ዕድልን ስለሚጨምር ለሌሎች ዘርፎችም ዕድገት መሠረት የሚጥል ነው፡፡ በሌላ በኩል እንደ አገርም 1/3ኛ የሚሆነውን የግብርና ምርት የሚያበረክት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወደፊት ዘርፉን ይበልጥ ማዘመን ቢቻል የምግብ ምርት በማቅረብና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ገቢ በመጨመርና ድህነትን በመቀነስ፣ ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የምርቶችን ዋጋ በማረጋጋት፣ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት በማሟላት እንዲሁም የኤክስፖርት ግኝትን በማሳደግ በአጠቃላይም ከሌሎች ዘርፎች ጋር ትስስር በመፍጠር ኢኮኖሚው እመርታ እንዲያመጣ ከማድረግ አንፃር የሚኖረው አስተዋጽዖ የጎላ ነው፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የቀጣዩ አሥር ዓመታት የዘርፉ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ የግብርናውን ዘርፍ እንደ አዋጭ የቢዝነስ መስክ በመቁጠር አሁን ካለበት ከእጅ ወደ አፍ የሆነና ኋላቀር አያያዝና አመራረት ዘይቤ ወደ ዘመናዊና ገበያ ተኮር አሠራርና አመራረት ዘይቤ ማሸጋገር እንዲሁም ለእንስሳት ንዑስ ዘርፍ ልዩ ትኩረት መስጠት ነው። ከዚህ አንፃር የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ይሆናሉ።

**የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፡-** የክልላችን የግብርና ሥርዓት በዝናብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለምርትና ምርታማነት አለማደግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የምርቱ መጠን ከዝናብ መጠን መለያየት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ልዩነቶች ይታይበታል። ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት በቂ ስላልሆነ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ልማት ላይ ኢንቨስት በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህም ያሉንን የምርት ወቅቶች ከ2 እስከ 3 ጊዜ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በላይ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያመጣል።

የምንከተለው የመስኖ ልማት አካሄድ በሁለት ይከፈላል። ይህም የአነስተኛ መስኖ ልማት እና መካከለኛና ትላልቅ መስኖ ልማት ሲሆን አተገባበሩም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ይሆናል። የመስኖ ልማት ሥራዎች በተለያዩ ተዋንያኖች የሚፈፀምበትን አግባብ በማመቻቸት ለምሳሌ በመንግስት፣ በልማት አጋሮች፣ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በማህበረሰብ ተሳትፎ የሚሠራ ነው። የመስኖ ኢንቨስትመንት ቅደምተከትል በሚሰጡት ጥቅም እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ይደረጋል። በመስኖ ሥራ ላይ ትኩረት መስጠት በቤተሰብ ደረጃ ቢያንስ አንድ የውኃ አማራጭ እንዲኖረው በማድረግ የውኃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መጎልበት የራሱን አስተዋፅዖ ያደርጋል።

**የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት፡-** የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። ለክልሉ መልከዓ ምድር እና ለአግሮኢኮሎጂው ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነቱን ለአርሶ አደር በማረጋገጥ፣ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ እና የአርሶ አደሩን አቅም ያገናዘበ አገር በቀል የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ፣ ማኑፋክቸሪንግ እና የሥርጭት ሥርዓቱን በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን ከፍ በማድረግ የአርሶ አደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል።

የግብርናው ዘርፍ የሚጠቀማቸውን ማናቸውም የቴክኖሎጂ ግብዓት እና ማሽነሪዎች ከግብር ነፃ እንዲሆኑ በተደረገው መሠረት እና የሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ሥርዓት በመዘርጋት ግብርናን ለማዘመን ትኩረት ተሰጥቷል። ይህም የግብርና ሜካናይዜሽን የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማቋቋም ከፍተኛ ዕገዛ ይኖረዋል። ምርታማነትንና የምርት ጥራትን በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የሥራ ዕድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና መሳብ ያስችላል። የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዋና ምሰሶ የግሉ ዘርፍ መሆኑ ቢታወቅም የግብርና ዘርፍ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የቁጥጥርና ፍተሻ እንዲሁም የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል። የሜካናይዜሽን አሠራርና አጠቃቀም ለማሻሻል የአርሶ አደሮችን መሬት በኩታ ገጠም በማደራጀት ለእርሻ ምቹ እንዲሆኑ በማደረግ የግሉን ዘርፍ ለማሳተፍ በሚደረገው ሽግግር ላይ መንግስት የተለያዩ የማበረታቻ ሥልቶችን ይጠቀማል።

**እንስሳት ሀብት ልማት፣ መኖ ልማትና ጤና ማሻሻል፡-** የእንስሳት ሀብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ሥርዓትን ከማሻሻል እና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል። በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ትኩረት የሚደርግባቸው ጉዳዮች ናቸው። የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ከማሻሻል አኳያ የኳረንቲን ማዕከላትን አጠናክሮ ወደ ሥራ ማስገባትና

ሌሎች ከግብይት ጋር የተያያዙ መሠረተ ልማቶችን በመንግስት እ የግሉ ዘርፍ ሽርክና ለማሟላት ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል።

የወጪ ንግድን የሚያነቃቁና ወደ አዳዲስ ገበያዎች ዘልቆ ለመግባ የሚያግዙ ዘመናዊ የምርት መዳረሻዎች ሥርዓት መተግበር፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ሥርዓቶችን ማሻሻል፣ የእንስሳት ማርቢያ አካባቢዎችን ከበሽታዎች የፀዱ ማድረግ እና ህገወጥ ንግድን መቆጣጠር በሰፊው ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የዕሴት ጭመራን ለማቀላጠፍ በኤክስፖርት ቄራዎችና በአርቢዎች መካከል ቀጥታ የምርት ግብይት ግንኙነቶችን ማዳበር ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

**ለሆርቲካልቸር ልማት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፡-** የሆርቲካልቸር ልማት ዋና ምሰሶዎች የሚሆኑት በክላስተር የተደራጁ አነስተኛ አርሶ አደሮች እና ትላልቅ የግል አምራቾች መሆናቸው ይታወቃል። በዘርፉ የምርት ስፔሺያላይዜሽን ቢበረታታም የአገር ውስጥ ፍላጎትን መሠረተ ያደረገና የዋጋ ግሽበትን የሚያረጋጋ ስትራቴጂ የምንከተል ይሆናል። (ለምሳሌ የአቮካዶ ሃስ ዝርያ ምርት ኤክስፖርት ማስፋፋት፣ የፍራፍሬ ምርቶች ወደ አግሮኢንዱስትሪ ማስገባት፣ የአበባ ምርት ኤክስፖርት ማስፋፋት)

የሆርቲካልቸር ዋና ስትራቴጂ የሚሆነው የግብዓት አቅርቦት ሥርዓቱን ማዘመን ነው፣ ይህም ማለት ገበያ ተኮር የሆነና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟሉና ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዝርያዎችን ማፍለቅና ማሰራጨት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊነቱን አሁን ካለበት ማስፋፋት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ያጠቃልላል። የዘመናዊ ችግኝ ጣቢያ ልማት ስትራቴጂክ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማጠናከር፣ የግብይት ማዕከላትን ለአርሶ አደሩ ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች ማደራጀት፣ የተለያዩ የዘመናዊ ማቀዝቀዣዎች መሠረተ ልማትን ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማመቻቸት የሚሉ ተግባራት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። የገበያ ትስስርን በተመለከተ በትላልቅ የሆርቲካልቸር ምርት ሰብሳቢዎች እና በአርሶ አደሮች መካከል ቅርበት ፈጥሮ የአገር ውስጥ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የሚያመቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እና የኤክስፖርት ገበያዎች ውስጥ ክልሉ ያለውን ድርሻ ለማጠናከር በሰፋት ይሠራል ።

**በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፡-** ባለሀብቱ በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ይሆናል። ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርት፣ በግብይት መሠረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፍ እና ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከአገር በቀልና ዓለምዓቀፍ ባለሀብቶች ጋር በጥምረት የሚሠራ ይሆናል። በተጨማሪም ባለሀብቱን የዕሴት ጭመራ ሥራዎች ላይ ለማሳተፍ በተለይም አግሮ ኢንዱስትሪዎችን መሠረት ያደረገ የዕሴት ሰንሰለት ማጠናከር ሥራ የሚሠራ ይሆናል።

**ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፡-** የ10 ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት ዋናው መሠረት የዘርፉን የማስፈፀም አቅምና ክህሎት ማሳደግ ወሳኝ ተግባር በመሆኑ የሰው ሀብት ሪፎርም ተሰርቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። ይህ ሥራ የአገልግሎት ጥራትና ጊዜን የሚያፋጥን ሲሆን የውሳኔ አሰጣጥንም የሚያቀላጥፍ ይሆናል፡፡ በግብርናው ዘርፍ ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ባለሙያዎችን በመመደብ ተቋማዊ አደረጃጀትን በማጠናከርና አርሶ አደሩ በልማት ቡድንና በአንድ ለአምስት በማደራጀት የግብርና ተቋምን መመስረት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአዲስ የሥርዓተ ምግብ እና የኤች አይቪ/ኤድስ ባለሙያ መደብ በማስፈቀድና እንዲመድቡ በማድረግ በክልሉ ከሥርዓተ ምግብ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ በአዲስ የሚያዘውን ዜሮ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የአፈር ለምነትና ሜካናይዜሽን የሥራ መደቦችን በዳይሬክቶሬት ደረጃ የመክፈት እንዲሁም የቡና ልማትን ለማስፋፋት የቡና ልማት ቡድን ማዋቀርና የማጠናከር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ይህ ጅማሮ በክልል በዞንና በወረዳ መውረድ እንዳለበት ሲታመን፣ የተቋማዊ መስተጋብር ጎን ለጎን መቀናጀት አለበት። እነዚህም የቅንጅት ሥራዎች አብሮ በማቀድ፣ በጋራ ችግሮችን በመፍታት፣ ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን

በማድረግ፣ አገራዊ የሆነ የሥራ ድግግሞሽን፣ የሀብት አጠቃቀም ጉድለትን የሚቀንስ እና ያለውን የቴክኒክ አቅም በአገር ደረጃ እንድንጠቀምበት ያደርጋል።

**የሥራ ዕድል መፍጠር፡-** በገጠር የሚኖሩ ሥራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሐዊ፣ ዘላቂ እና ውጤታማ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በመሆን በዕቅድ ዘመኑ ለአገር ዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ።

**ለአየር ንብርት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ይሠራል ፡-** የክልላችን ግብርና በተለይ ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የተጋለጠ ነው። ከፍተኛ የዝናብ መጠን የአፈር መከላትን የሚያባብስና የሰብል ውድመትን የሚያስከትል ሊሆን ይችላል። በዝናብ መጠን መዋዠቅ፣ በዝናብ ወቅትና ሥርጭት ላይ በሚፈጠረው ለውጥ፣ በከፍተኛ ትነት፣ በድርቅና በጎርፍ በሚመጡ ጉዳቶች ምክንያቶች በምርት መጠን፣ በሰብል የእርሻ ሥራ፣ በሰብል አመራረት ሥርዓት፣ በተባይና በበሽታ ክስተት ድግግሞሽ እና ሥርጭት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

በመሆኑም የታቀዱ ሁሉም የግብርና ልማት ሥራዎች በዘርፉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ሥልቶችን ያካተቱ እና በትግበራ ወቅትም ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰት ምክንያት የሆኑ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን ለማስተሰርይ እና ለማጣጣም የሚያስችሉ እንዲሁም አሁን ያለውን ብሎም ወደ ፊት የሚጠበቀውን የአየር ፀባይ መለዋወጥ እና የአየር ንብረት ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ተፅዕኖዎች ማጣጣም/መቋቋም የሚችል ማህበረሰብ ለመፍጠር ድርሻ ያላቸው ይሆናሉ። በመሆኑም በግብርናው ዘርፍ ከአየር ንብረት ጋር የተጣጣመ ግብርና ሲተገበር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መቀነስ ብቻ ሳይሆን ድምር ውጤቱ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ላይ በማተኮር የድህነት ቅነሳ ግቦችን የሚያሳካ ይሆናል።

**የተቀናጀ የአፈር ለምነት እና ርጥበት አያያዝና አጠቃቀምን የማሻሻል አሠራርን መከተል፡-** የክልሉ የሰብል ምርትና ምርታማነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ዕድገት እንዲያስመዘግብ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን የበለጠ በማጠናከርና በአሠራር የታዩ ክፍተቶችን በመለየት የአፈር ለምነትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ተግባራት በተቀናጀ መልኩ በስፋት እንዲተገበሩ ይደረጋል። በመሆኑም የአፈር ለምነት ካርታ በተሰራላቸው አካባቢዎች አፈርን መሠረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቃም እንዲኖር ማድረግና ቀደም ሲል የነበሩ የአፈር ለምነት ተግባራትን በተናጠል የመፈፀም አሠራርን በማስቀረት አካባቢን መሠረት ተደርጎ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራዎችን ተግባራዊ ማድረግ የምንከተለው መሠረታዊ አቅጣጫ ይሆናል።

በሌላ በኩል በክልላችን ዕርጥበት አጠር አካባቢዎች አሁን በሚታው የአየር ንብረት መዛባት ምክንያት ለመኸርና ለበልግ ሰብል ምርት በቂ የሆነ ዝናብ ካለመዝነቡም ባሻገር ዝናብ በሚዘንብበት ወቅትም ሥርጭቱ ያልተስተካከለ የሚሆንበት አጋጣሚ እየሰፋ መጥቷል።

ስለዚህ በእነዚህ አካባቢዎች የሰብል ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ለማሣደግ እንዲቻል የማሣ ውስጥና በማሣ ዙሪያ የዕርጥበት ዕቀባ ሥራዎችን በስፋት መሥራት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሲሆን ትርፍ ውኃ በሚበዛባቸውና የኮትቻ አፈር በስፋት ባለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ትርፍ ውኃን በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ ዘዴ በማጠንፈፍ ምርትና ምርታማነትን የማሣደግ ጉዳይ ዋነኛ ቁልፍ ሥራ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዓላማ የሰብል ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪና ለውጪ ገበያ የሚውል ምርት በመጠንና በጥራት ማምረት ነው። ይህን ዓላማ ከማሳካት አንፃር የተጣሉ ዋና ዋና ግቦች በክልሉ በ2011/2012 ምርት ዘመን ከዋና ዋና ሰብሎች በመኸር የተገኘውን 108,763,528 ኩንታል ምርት በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 190,779,375 ኩንታል ማሳደግ እና የዋና ዋና ሰብሎች አማካይ ምርታማነት አሁን

ካለበት 24.1 ኩንታል በሄክታር ወደ 39.28 ኩንታል በሄክታር ማድረስ፣ የምግብ ሰብሎችን ምርት በ2011/2012 ምርት ዘመን ከነበረበት **81,48** ሚሊየን ኩንታል በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 122.18 ሚሊየን ኩንታል ማድረስ እና አማካይ ምርታማነትን ከ25.8 ኩንታል በሄክታር ወደ 42.0 ኩንታል በሄክታር ማድረስ፣ የኢንዱስትሪ ሰብሎችን ምርት ከነበረበት 18.2 ሚሊየን ኩንታል ወደ 57.8 ሚሊየን ኩንታል ማድረስ እና ምርታማነቱን ከ24.9 ኩንታል በሄክታር ወደ 46.82 ኩንታል በሄክታር ከፍ ማድረግ፣ የኤክስፖርት ሰብሎችን ምርት ከነበረበት 8.7 ሚሊየን ኩንታል ወደ 10.79 ሚሊየን ኩንታል ማሳደግና ምርታማነቱን ከነበረበት 14.85 ኩንታል በሄክታር ወደ 15.1 ኩንታል በሄክታር ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተጨማሪም በበልግ የሚገኝ ምርትን ከነበረበት 2.75 ሚሊየን ኩንታል ወደ 5.61 ሚሊየን ኩንታል ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

በ2011/2012 ምርት ዘመን በጠቅላላው ከለማው መሬት ውስጥ በዋና ዋና የኮሞዲቲ ሰብሎች በኩታ ገጠም አሠራር 981,285 ሄክታር በማልማት የተገኘውን 27,002,445 ኩንታል ምርት በአሥር ዓመቱ መሪ ዕቅድ መጨረሻ ማለትም በ2021/2022 ምርት ዘመን 2,100,103 ሄክታር (ጠቅላላ ከሚለማው መሬት ውስጥ 43 በመቶ የሚሆነውን) በማልማት 90,266,562 ኩንታል ምርት ለማምረት ይሠራል፡፡

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ አሠራሮችም በተጠናከረ መልኩ የሚሠሩ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃርም በ2011/12 ምርት ዘመን 22,351 ኩንታል ኖራ በመጠቀም የለማውን 1,784 ሄክታር አሲዳማ አፈር በየዓመቱ በአማካይ 20,000 ሄክታር በማልማት በአሥር ዓመቱ ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ላይ (በ2021/2022 ምርት ዘመን) 954,866 ኩንታል ኖራ በመጠቀም የሚለማውን መሬት ወደ 47,743 ሄክታር የማሳደግ፣ የኮምፖስት (መደበኛ፣ ቨርሚ፣ ባዮስለሪ ኮምፖስት) ዝግጅት እና አጠቃቀምን አስመልክቶም በ2011/12 ምርት ዘመን 33.5 ሚሊየን ሜትር ኩብ ኮምፖስት ተዘጋጅቶ በ1,004,072 ሄክታር ጥቅም ላይ የዋለውን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ አንድ አባዎራ/እማዎራ 20 ሜትር ኩብ ኮምፖስት በዓመት ሁለት ጊዜ እንደሚያዘጋጅ ታሳቢ ተደርጎ (በ2021/2022 ምርት ዘመን) 159 ሚሊየን ሜትር ኩብ በማድረስ ከውጭ ከሚገባው የሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ይልቅ በኮምፖስት መተማመንና በዚህም በአማካይ 5,236,078 ሄክታር መሬት ማልማት፣ የህያው ማዳበሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት በ2011/2012 ምርት ዘመን 62,284 ሳቸት ህያው ማዳበሪያ በመጠቀም የለማውን 15,571 ሄክታር መሬት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 195,108 ሳቸት ህያው ማዳበሪያ በማድረስ 48,777 ሄክታር በማልማት የጥራጥሬ ሰብል ምርታማነትን የማሳደግ እንዲሁም በ2011/12 ምርት ዘመን በክልሉ በማጠንፈፍ የለማውን 342,916 ሄክታር ኮትቻ አፈር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 400,350 ሄክታር (16.7 በመቶ) በማሳደግ ቀደም ሲል በክልል ደረጃ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረውን የኮትቻ አፈር ልማት ህዝባዊ ንቅናቄ በሚፈለገው ደረጃ ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

በሌላ በኩለ የተሻሻሉ የሰብል አመራረት ሥርዓትን ማለትም ዳገም ሰብል ልማት፣ አሰባጥሮ መዝራት፣ በቅብብሎሽ ማልማት እና በመስመር መዝራት በትኩረት በመፈጸም በ2011/12 ምርት ዘመን እነዚህን አሠራሮች በመተግበር የለማውን 2,460,613 ሄክታር መሬት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በ2021/2022 ምርት ዘመን 4,309,850 ሄክታር መሬት በማልማት ተጨማሪ ምርት የማምረት፣ በተለያዩ የመስክና የጎተራ ተባዮች በቅድመና በድህረ-ምርት በአማካይ የሚደርሰውን 35 በመቶ የምርት ብክነት በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 15 በመቶ ዝቅ በማድረግ የምርት ብክነትን የማዳን፡፡ የግብርና ሜካናይዜሽን ተጠቃሚነትን አሁን ካለበት 7 በመቶ በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 56.5 በመቶ በማሳደግ የሜካናይዜሽን አገልግሎትን የማስፋፋት፣ የኩታ ገጠም ልማት ተግባራዊ በሚደረግባቸው አካባቢዎች የቴክኖሎጂዎችን ፍላጎት በማሰባሰብ ለየአካባቢው ተስማሚ የሆኑትን በህብረት ሥራ ማህበራት፣ በግል ባለሀብቶች፣ ወጣቶችን በማደራጀት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች በኩል እንዲቀርቡ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

የግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ የሰብል ዘር ብዜት በ2011/12 ምርት ዘመን የቀረበውን 123,159 ኩንታል ምርጥ ዘር በ2021/2022 ምርት ዘመን ወደ 809,331 ኩንታል ምርጥ ዘር በመንግስት፣ በግልና በዘር አባዥ ዩኒዬኖች እንዲባዛ በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ የተመሰከረለት ዘር ለተጠቃሚው ማቅረብ፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አጠቃቀም 2011/12 ምርት ዘመን በመኸር፣ በበልግና በመስኖ ሰብል ልማት ጥቅም ላይ የዋለውን 5,039,855 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 9,989,407 ኩንታል (98 በመቶ) ማሳደግ እንዲሁም በተለያዩ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎች በ2011/12 ምርት ዘመን የተካሄደውን 29,988 ሠርቶ ማሳያ በ2021/22 ምርት ዘመን ወደ 44,147 (47 በመቶ) የማሳደግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር 2021/2022 ምርት ዘመን 5,348,138 ኩንታል ምርት በግል ባለሀብቱ እንዲመረት የማድረግ፣ በግብርና ልማት ሥራ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች እስከ አሁን የተደረገው ድጋፍና ክትትል ራሱን የቻለ ችግር ያለበት ሲሆን በመጪው አሥር ዓመት መሪ ዕቅድ ዘመን ለግል ባለሀብቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ድጋፍ የማደረግ ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ሥራ በተሠራባቸው እና ወደፊት በሚሠራባቸው 23,966 ተፋሰሶች 3.6 ሚሊየን ህብረተሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የማድረግ፣ ለ23,966 ተፋሰሶች በራሳቸው ህገ ደንብ እንዲተዳደሩ በማድረግ የተጠቃሚዎች ኅ/ሥ/ማህበር እንዲያስተዳድሯቸው የማድረግ፣ በ1.25 ሚሊየን ሄክታር መሬት ላይ የጥምር ደን እርሻ ፓኬጆችን ተግባራዊ የማድረግ እና በአጠቃላይ የክልሉን የደን ሽፋን አሁን ከተደረሰበት 14.6 በመቶ በየዓመቱ በ1 በመቶ በማሳደግ 24.6 በመቶ ለማድረስ ይሠራል፡፡ 60,592 ሄክታር መሬት ላይ ሥነ-አካላዊ እና ሥነ-ህይዎታዊ ሥራዎችን ተግባራ በማድረግ የተጎሳቆለውን መሬት የማዳን ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

የመስኖ ልማትን በሚመለከት የክልሉን የመስኖ ሽፋን በ2012 ሄክታር ከነበረበት ነባር የመስኖ 220,469 ሄክታር የመሬት ሽፋን በተጨማሪ  አዲስ መስኖ ሽፋንን በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ በ1ኛ ዙር የሚለማውን 382,383 ሄክታር ማድረስ፣  በ2ኛ ዙርና ከዚያ በላይ መስኖ ልማት በ2012 ዓ.ም 63,870 ሄክታር ከነበረበት የመሬት ሽፋን በየዓመቱ 5 በመቶ በማሳደግ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 138,089 ሄክታር መሬት ሽፋን ለማድረስ ይሠራል፡፡

በተጨማሪም በ2011/12 የምርት ዘመን የተለያዩ የሥራስር ሰብሎችን ከነበረው 165,024 ሄክታር የመሬት ሽፋን የተገኘ 19,836,313 ኩንታል ምርት እና 120.2 ኩንታል በሄክታር ምርታማነት በ2021/22 የምርት ዘመን በየዓመቱ በአማካይ 15 በመቶ የመሬት ሽፋን በማሳደግ  ወደ 318,005 ሄክታር እና 4.2 በመቶ ምርታማነትን በማሳደግ 37,734,478 ኩንታል ምርት ለማድረስ እንዲሁም በ2011/12 የምርት ዘመን ከነበረው 1,551,994 የተሳታፊ አርሶ አደር ቁጥር በ2021/22 የምርት ዘመን 2 ሚሊየን ለማድረስ ይሠራል፡፡

ክላስተርን መሠረት ያደረገ የቡናና ፍራፍሬ ኮሞዲቲ ልማት ከማካሄድ አንፃር በቡና ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 5.08 ሚሊየን ችግኝ ዝግጅት እና 4.06 ሚሊየን ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 8.64 ሚሊየን እና ተከላን ወደ 6.91 ሚሊየን በማድረስ የነበረውን 1,626 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 2,765 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 20 በመቶ ማሳደግ፣ የተሳታፊ አርሶ አደርን ቁጥር ከ26,010 ወደ 64,604 ማድረስ፣

በማንጎ ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 0.5 ሚሊየን ችግኝ ዝግጅት እና 0.4 ሚሊየን ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 2.7 ሚሊየን እና ተከላን ወደ 2.5 ሚሊየን በማድረስ የነበረውን 800 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 5015 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ/ የተሳታፊ አርሶ አደርንም ከ16,000 ወደ 140,000  ማድረስ፣

በአቮካዶ ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 1.04 ሚሊየን ችግኝ ዝግጅት እና 0.83 ሚሊየን ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 1.9 ሚሊየን እና ተከላን ወደ 1.79 ሚሊየን በማድረስ የነበረውን 596 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 3,576 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ ማሳደግ/፣ የተሳታፊ አርሶ አደርንም ከ1,920 ወደ 19,865 ማድረስ፣

በብርቱካን ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 2,500 ችግኝ ዝግጅት እና 2,000 ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 206,391 እና ተከላን ወደ 165,113 በማድረስ የነበረውን 5,200 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 26,418 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ ማሳደግ/ እና የተሳታፊ አርሶ አደርንም ከ1,326 ወደ 2,700 ማድረስ፣

በሙዝ ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 85,839 ችግኝ ዝግጅት እና 77,255 ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 619,173 እና ተከላን ወደ 557,256 በማድረስ የነበረውን 52 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 372 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ ማሳደግ/ እና የተሳታፊ አርሶ አደርንም ከ1,030 ወደ 7,802 ማድረስ፣

በአፕል ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከተዘጋጀው 510,000 ችግኝ ዝግጅት እና 357,000 ተከላ በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ በማሳደግ ችግኝ ዝግጅትን ወደ 1,414,768 እና ተከላን ወደ 1,131,815 በማድረስ የነበረውን 413 ሄክታር የመሬት ሽፋን በ2022 በጀት ዓመት 1,019 ሄክታር ማድረስ /በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ በማሳደግ/ እንዲሁም የተሳታፊ አርሶ አደርንም ከ7,437 ወደ 18,337 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

ከግብርና ኤክስቴንሽን ሥራ አንፃር በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ የነበረውን የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ አባዎራ ቁጥር 2,396,912 ወደ 4,074,742 ማሳደግ፣ እማዎራ ከነበረበት 476,760 ወደ 810,490 የማሳደግ፣ ባለትዳር ሴቶች አሁን ካለበት 1,143,515 ወደ 2,439,750 ማሳደግ እንዲሁም ወጣቶች አሁን ካለበት 774,443 ወደ 1,316,553 ማሳደግ፣ የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ቁጥር አሁን ከተደረሰበት 888,774 /28.2 በመቶ/ በሚቀጥሉት አሥር ዓመት ወደ 5,271,522 (85 በመቶ) ማድረስ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ የሚያመርቱ አርሶ አደሮችን ቁጥር ከነበረበት 1,346,600 ወደ 1,502,168 ለማሳደግ እንዲሁም ለኤክስፖርት የሚያመርቱ አርሶ አደሮችን ቁጥር ከነበረበት 1,266,193 ወደ 1,333,996 የማሳደግ ሥራ ይከናወናል፡፡

የእንስሳት መኖ አቅርቦትን በማሳደግ፣ ዝርያን በማሻሻል እና የእንስሳት ጤና አገልግሎትን በማጠናከር ከዳልጋ ከብት እና ከፍየል የሚመረተውን የወተት ምርት በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት 1,196,749 ቶን በ2022 በጀት ዓመት ወደ 2,618,425 ቶን የማድረስ ግብ ተይዟል፡፡ በዚህም አግባብ የክልሉን አማካይ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የወተት ፍጆታ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 19 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 26 ሊትር በነፍስ ወከፍ የማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካት በ2012 በጀት ዓመት አማካይ የወተት ምርታማነት በማሳደግ ከአንድ የአገር በቀል የወተት ላም ዝርያ በቀን እየተመረተ ያለውን 1.3 ሊትር ወደ 2.5 ሊትር ከተሻሻሉ ላሞች በቀን እየተመረተ ያለውን 10 ሊትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 16 ሊትር፣ ለማድረስ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የሥጋ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር የእንስሳት ማድለብ ሥራዎችን በማዘመን እና የገበያ ትስስሩን በማሳለጥ ከዳልጋ ከብት፣ ከበግ፣ ከፍየል እና ከግመል በ2012 በጀት ዓመት የተደረሰበትን ዓመታዊ የሥጋ ምርት 272,832 ቶን በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 590,708 ቶን የሥጋ ምርት በማሳደግ ዓመታዊ የክልሉን ህዝብ የነፍስ ወከፍ የሥጋ ፍጆታ አሁን ካለበት 8 ኪሎ ግራም በ2022 በጀት ዓመት 12 ኪሎ ግራም በማድረስ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ይሠራል፡፡ በዚህም በ2012 በጀት ዓመት የተደረሰበትን ከዳልጋ ከብት 179,197 ቶን፣ ከበግ 73,458 ቶን፣ ከፍየል 45,411 ቶን፣ ከዶሮ 12,172 ቶን እና ከዓሣ 22,672 ቶን የሥጋ ምርት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ከዳልጋ ከብት 383,664 ቶን፣ ከበግ 97,467 ቶን፣ ከፍየል 61,166 ቶን፣ ከዶሮ 25,913 ቶን እና ከዓሣ

22,498 ቶን እንዲመረት ለማድረግ የሚሠራ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃርም አርቢው ህብረተሰብ የሥጋ ምርትን ለማሳደግ የሚያስችል የሚደልቡ እንስሳት /በሬ፣ ወንድ ጥጃ፣ ፍየል፣ በግ/ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረግ እና አዋጭነትን ታሳቢ ያደረገ የተቀነባበረ ምጥን መኖ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡

የዶሮ ሀብት ልማት ሥራዎችን በማዘመን የዕንቁላል ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 523 ሚሊየን በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 792 ሚሊየን ዕንቁላል በማድረስ የአምራቹን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ሥነ-ምግብን ማሻሻልና በገበያ የሚመራ ኢንዱስትሪ ለማድረግ በቀጣይ የልማት ዕቅድ ዓመታት ተጠናክሮ የሚሠራ ይሆናል፡፡

የማር ምርትን ከማሳደግ አንፃር በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 18,253 ቶን የማር ምርት እና 889 ቶን የሰም ምርት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 26,309 ቶን እና 229 ቶን በቅደምተከተል ማድረስ፡፡ ለዚህም በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከአንድ ቀፎ እየተገኘ ያለውን አማካይ ዓመታዊ የማር ምርታማነት ከባህላዊ ቀፎ 8.5 ኪሎ ግራም፣ ከኢትዮ ርብራብ ቀፎ 19 ኪሎ ግራም እና ከዘመናዊ ቀፎ 25 ኪሎ ግራም በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ከባህላዊ ቀፎ 10 ኪሎ ግራም፣ ከኢትዮ ርብራብ ቀፎ 25 ኪሎ ግራም እና ከዘመናዊ ቀፎ 39 ኪሎ ግራም የማድረስ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

በሌላ በኩል ለሃር ልማት ምቹ የሆኑ አካባቢዎችን በመምረጥ፣ የሃር ትል መኖ ልማትን በማስፋፋት፣ ለጉሎ ሃር ልማት /Eri Silk production/ የሚውሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማስገባት እና በማስተዋወቅ ጥራቱን የጠበቀ 2,795 ኩንታል የሃር ኮኮን ምርት ለገበያ በማቅረብ አምራቹን ተጠቃሚ የማድረግ እንዲሁም ከማርና ሰም ምርት በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ገበያ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ የንብ ውጤቶች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እና ለሥራው የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማሟላት 100 ኩንታል ፕሮፖሊስ፣ 30 ኩንታል የንብ ወተት፣ 20 ኩንታል የንብ መርዝ አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ከንብ ሀብታችን የሚገኘውን የገቢ አማራጭ የማስፋትሥራዎች ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ፡፡

የዓሣ ሀብት ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር ዘርዘር ባለ መልኩ ሲታይ በክልሉ በሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የውኃ አካላት በመጠቀም በ2012 በጀት ዓመት የተመረተውን 22,673 ቶን የዓሰ ምርት (7,935 ቶን የዓሣ ሥጋ) (ከኃይቆች 13,271 ቶን፣ ከወንዞች 3,986 ቶን፣ ከግድቦች 5,352.6 ቶን እና ከአኳካልቸር 63.1 ቶን) በ2022 በጀት ዓመት ከኃይቆች 307,909 ቶን፣ ከወንዞች 70,147 ቶን፣ ከግድቦች 68,508 ቶን እና ከአኳካልቸር (ከነባር እና አዲስ ኩሬወች) 2,525 ቶን በ10 ዓመቱ ውስጥ በድምሩ 449,088 ቶን የዓሣ ምርት (157,181 ቶን የዓሣ ሥጋ) በማሳደግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ የቆዳና ሌጦ ምርትን ከማሳደግ አንፃር በ2012 በጀት ዓመት ያለውን 7,323,683 የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅርቦት በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ 6,279,952 በማድረስ በ10 ዓመቱ በድምሩ 58,491,968 ለማምረት ይሠራል፡፡

ከመኖ ልማት አንፃር የሚመረተውን ድርቆ መኖ ከነበረበት 39 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን ወደ 52 ሚሊየን ሜትሪከ ቶን ለማሳደግ፣ በሰው ሠራሽ ዘዴና በተሻሻለ ኮርማ የተዳቀሉ ላሞችና ጊደሮች ቁጥር ከነበረበት 241,653 ወደ 555,000 በማድረስ ዝርያቸው የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች ቁጥር ከነበረበት 103,389 ወደ 168,651 ለማድረስ ይሠራል፡፡ በእንስሳት ጤና አገልግሎት ረገድም የእንስሳት ክትባትና ህክምና አገልግሎት 100 በመቶ ለማድረስ ይሠራል፡፡

በሌላ በኩል የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርን በማጠናከር የክልሉን ህዝብ የአደጋ መከላከልና መቋቋም አቅም ማጎልበትና ሥር በሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ የሚገኘውን ህዝብ የምግብ ዋስትናውን ማረጋገጥ የግብርና ችግሮችን ከመፍታትና እየጨመረ የመጣውን የምርት ፍላጎት ከመሟላት አንፃር በ10 ዓመቱ በጠቅላላው ለተለያዩ ሥነ-ምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን በ272 የሰብል፣ 226 የእንስሳት፣ 151 የአፈርና ውኃ፣ 86 የደን፣ 20 የዘር፣ 55 የግብርና ባዮቴክኖሎጂ፣ 55 የምግብ ሳይንስና ድህረ

ምርት እና 77 የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት በድምሩ 942 ቴክኖሎጂዎችና ምክረ ሀሳቦችን የማውጣት ሥራዎች በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት የተጣሉ ግቦች ናቸው፡፡

በግብርናው ዘርፍ የግል ባለሀብቶችን ተሳትፎ የማሳደግ እና የከተማ ግብርናን የማጠናከር ሥራዎች ትኩረት የሚሠጣቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡ ዘርፉን ውጤታማ ከማድረግ አንፃር በግብርና ግብዓትና ምርት አቅርቦት ያለውን የግብይት ሥርዓት ቀልጣፋ የማድረግ ሥራ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የገጠር የፋይናንስ ሥርዓት እንዲሻሻል በማድረግ ረገድ ማህበራት ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት የመሠረታዊ ማህበራት የብድር ሥርጭት ከ5.74 ቢሊየን ወደ 72.74 ቢሊየን፣ የዩኒየኖችን ብድር ሥርጭት ከ4.17 ቢሊየን ወደ 24.8 ቢሊየን እንዲሁም የፌደሬሽን ብድር ሥርጭት ወደ 3.05 ቢሊየን ብር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን በዚህ ረገድ የህብረት ሥራ ማህበራት ሚናን የማሳደግ ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም በዩኒየኖች የተቋቋሙ እና ዕሴት በመጨመር የተለያዩ የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አግሮ ፕሮሰሲንግ ፋብሪካዎች ቁጥር ከ28 ወደ 46 ለማሳደግ የሚሠራ ይሆናል፡፡

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

የሁለት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች አፈጻጸምን እንደ መነሻ በመጠቀም በቀጣይ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ የታቀዱትን ተግባራት ውጤታማ ለማድረግ አዳዲስ አሠራርን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የክልል እና የዞን አመራር የዓመቱን ዕቅድ የጋራ በማድረግ በየደረጃው አስፈላጊ የሆኑ የችሎታ፣ የዕውቀት፣ የአመራር ሥልት ማዳበር፣ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጎልበትና መተግበር፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ማስፈጸሚያ ሥልቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ማጠናከር፡-** የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ሥርዓት መጠናከር እና ጠንካራ የመረጃ ሥርዓት መኖር በሁሉም ደረጃ ለሚደረገው የወሳኔ አሰጣጥ ትልቅ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የክትትል ሥርዓቱ በተናጠልም ሆነ በቡድን ይከናወናል፡፡ በአፈጻጸም ሂደት የሚገኙ ልምዶችን ለመቀመርና ለማስፋት እንዲሁም ክፍተቶችን ለይቶ ለመፍታት ከላይ እስከታች የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው የሚገኝ የአመራርና የባለሙያ ውጤታማ አሠራር እንዲጎለብት የተቀናጀ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**የፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞች ሀብትና መደበኛ በጀት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ማዋል፡-** የግብርናውን ዘርፍ የሚደገፉ የተለያዩ ፕሮጅክቶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ያላቸውን ሀብት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የጋራ የአፈጻጸም የመግባቢያ ሠነድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ በዚህም መሠረት ለዕቅድ ማስፈፀሚያ የተያዘው በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

**አደረጃጀቶችን በመጠቀም የግብርና ተግባራትን መፈጸም፡-** የሥራ ማሳለጫ የሆኑ የልማት ቡድንና የ1ለ5 አደረጃጀቶችን በማጠናከር በግብርና ዘርፍ የታቀዱ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸሙ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም ለሥራዎች መቀላጠፍ አጋዥ የሆነ የካይዘን አሠራር በየደረጃው ተፈጻሚ በማድረግ የታቀዱ ዝርዝር ተግባራትን ማከናወን ይቻላል፡፡

**ተርፎ የሚያድር ግብዓት እንዳይኖር መሥራት፡-** ለግብርና ምርትና ምርታማነት አጋዥ የሆኑ ሰው ሠራሽ የአፈር ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ላይም፣ ኬሚካልና ሌሎች ግብዓቶች በወቅቱና በበቂ መጠን ማቅረብና ማሠራጨት እንዲሁም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል ፡፡

**አዳዲስ መልማት የሚችሉ የእርሻ መሬቶችን ወደ ልማት ማስገባት፡-** በክልላችን ያሉትን መልማት የሚችሉ በግል ባለሀበት እና በመንግስት ተይዘው ወደ ልማት ያልገቡ የእርሻ መሬቶችን ወደ ሰብል ልማት በማስገባት የሚገኘውን ምርት የመጨመር ሥራ ይከናወናል፡፡

**የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፡-** የተለያዮ ቴክኖሎጂዎች እንደ ኮምፖስት፣ ቨርሚ ኮምፖስት፣ አፈርን በኖራ ማከም እና ህያው ማዳበሪያ በስፋት በመጠቀም የአፈር ለምነትን በማሻሻል እና የአፈር አሲዳማነትን በመቀነስ የምርትና ምርታማነት ዕድገት የማምጣት ሥራ ይተገበራል ። በዚህም የደጀን እና የመርሃቤቴ የኖራ ወፍጮ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅም እንዲሠሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

**በምርምር የሚወጡ አዳዲስ አሠራሮች እና ቴክኖሎጂዋችን በስፋት መጠቀም፡-** የግብርናውን ዘርፍ በማዘመንና ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዙ የተለያዩ በምርምር የሚወጡ አዳዲስ አሠራሮችን እና ቴክኖሎጂዎችን በክልሉ የሚገኙ አርሶ አደሮች እንዲጠቀሙ እና ምርትና ምርታማነትን እንዲያሳደድጉ የማድረግ ሥራ ይተገበራል። ይህንን ለማከናወን የምርምር ማዕከላት እና የግብርና ኤክስቴንሽን ቅንጅታዊ አሠራር ይበልጥ ጠንካራ እንዲሆን ይሠራል ። በተጨማሪም የግብርና ኮሌጆች፣ የምርምር ማዕከላት እና ዩኒቨርሲቲዎች የሚያወጧቸውን ምክረ ሃሳቦች ወደ ተግባር እንዲገቡ ይሠራል።

### 12.1.2. መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም

### የትኩረት አቅጣጫዎች

ክልሉ ኢስላ ሶፍትዌርን በማበልጸግ ሁሉም የገጠር መሬት መረጃዎች ወደ ኮምፒዩተር እንዲገባ የማድረግ ሥራ በትኩረት ሲሰራ የነበረ ቢሆንም ማጠናቀቅ ባለመቻሉ በቀጣይም በትኩረት የሚሠራ ይሆናል። የኢስላ መረጃ እና ባሕረ-መዝገብ እርስ በርሳቸው የሚናበቡ ለማድረግ የመረጃ ማጥራት ሥራዎችን መሥራት፣ ለሁሉም ይዞታዎችና ማሳዎች በካርታ የተደገፈ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ማጠናቀቅ፣ በሁሉም የክልል ወረዳዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የበለጸገውን ሶፍትዌር (NRLAIS) በመጫን የመሬት ግብይቶችን እንደ አመጣጣቸው ማከናወን፡ ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመልካም አስተዳድር ችግሮችን መፍታት የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

### ዓላማዎችና ግቦች

የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዋነኛ ዓላማ በክልሉ ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ሥርዓትን በመገንባት ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት እና ፍትሐዊ የመሬት ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት ማሻሻል ሲሆን ዓላማውን ለማሳካት ተጣሉ ዋና ዋና ግቦችም ለአሠራር ምቹ ያልሆኑ የህግ ማዕቀፎችን ማሻሻል እንዲሁም ፖሊሲና ስትራቴጂ በማውጣት የመሬት አስተዳደርርና አጠቃቀም የአሠራር ሥርዓትን ማሻሻል፣ የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት አሁን ካለበት 1,826,517 ይዞታ እና 7,710,465 ማሳ በ2022 ወደ 4,347,699 ይዞታ እና 18,015,156 ማሳ በማድረስ የይዞታና የመጠቀም መብት ዋስትና ማረጋገጥ እንዲሁም የማሳ ካርታን የብድር ዋስትና በማድረግ ባለይዞታዎች የብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣ በኮምፒውተር ሳይመዘገቡ የቀሩትን የሁሉንም የመሬት ባለይዞታዎች የመሬት መረጃ ምዝገባና ወቅታዊ በማድረግ 100 በሙቶ ወደ ISLA (Information System for Land Administration) Software በማስገባት የሚቀርቡትን ሁሉንም የመሬት ይዞታ ግብይቶች በማረጋገጥና በማጽደቅ በመሬት መረጃ ሥርዓት በመመዝገብ የመሬት ግብይት ሥርዓትን ቀልጣፋ ማድረግ፣ በገጠር መሬት ያለውን ህገወጥ ተጠቃሚነትን በመከላከል የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በ85 በሙቶ መቀነስ፣ ለአዲስ መሬት ጠያቂዎች እና ለሥራ አጥ ወጣቶች በቡድንም ይሁን በተናጠል በቋሚነትና በጊዜያዊነት መሬት በማቅረብ የሥራ ዕድል መፍጠር።

በመሬት በማምረት አቅም ደረጃ ለ1,262,228 ባለይዞታዎች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አዘጋጅቶ ርክክብ በማድረግ አሁን ካለው 3,295,370 ባለይዞታዎች ወደ 4,347,699 ባለይዞታ ማሳደግ፣ በመሬት በተሰማሚነት ደረጃ የተጠኑ የልማት ኮሪደሮችን ከ4 ወደ 6 ከፍ በማድረግ የመሬትን ምርታማነት ማሳደግ፣ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም

ማስተር ፕላን (ፍኖተ ካርታ) እና ጥናት ማዘጋጀት እንዲሁም በተበታተነ ሁኔታ የሚኖረውን አርሶ አደርና ወጣቱን በቀበሌ ማዕከል ለማሰባሰብ በ910 ቀበሌዎች ሽንሽና በማካሄድ ሽፋኑን ከ2,515 የቀበሌ ማዕከላት ግንባታ ወደ 3,425 ቀበሌዎች ማዕከላት ግንባታ ማሳደግ። በተጨማሪም በልማት ምክንያት ለተነሺ ባለይዞታዎች የሚከፈል ካሳ መጠንን ከ13.84 ቢሊየን ወደ 324.92 ቢሊየን ብር ማሳደግ፣ የቢዝነስ ፕላን እየተዘጋጀላቸው ባላቸው የካፒታል አቅም መሠረት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሳተፉ ድጋፍ የሚደረግላቸው የልማት ተነሽዎችን ብዛት ከ38,800 ወደ 536,500 ማሳደግ፣ 67,000 ሄክታር የኢንቨስትመንት መሬት በመለየት በባለሀብቶች አሁን በመልማት ላይ ያለውን 212,678 ሄክታር የኢንቨስትመንት መሬት ወደ 279,678 ሄክታር ማሳደግ፣

በ77 ከተሞች የከተማ መሬት ይዞታ መብት በመመዝገብ እና የካዳስተር ሥርዓትን በመገንባት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የይዞታ አገልግሎት ተደራሽነትን ወደ 733 ማድረስ፣ በከተማ አስተዳደሮች ህጋዊ የካዳስተር መረጃ ሥርዓት እንዲለማ ማድረግን ወደ 77 ከተሞች ማድረስ፣ ለመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ግብዓት የሚሆኑ ስፓሻል መረጃ እና ተያያዥ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ትንተና ማድረግ፣ ማደራጀት፣ መጠበቅ እና ለተጠቃሚ ተደራሽ ማድረግ፣ የህጋዊ ካዳስተር ሥርዓት በከተማ መሬት ዙሪያ በመገንባት የ733,000 የከተማ መሬት ይዞታዎችን መረጃ በሠነድና በልኬት በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ በማሰተሳሰር እና በማረጋገጥ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ትክክለኛ መረጃ ማመንጨት የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

የተቋሙን የአደረጃጀት ችግር ከዓለም አቀፋዊ የመሬት አስተዳደር አደረጃጃት አንፃር በጥናት በመፈተሽ እንደገና አደራጅቶ በቂ የሰው ኃይል በማሟላትና ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓቱ ተደጋጋፊነትና ተመጋጋቢነት እንዲኖረው ይደረጋል፣ ቴክኖሎጂዎችን በላቀ ደረጃ የመጠቀም እንዲሁም ለሁሉም ወረዳዎችና ዞኖች ምቹ የሥራ አካባቢ ለመፍጠር ተሽከርካሪ (ሞተር ሳይክል/መኪና) እንዲኖራቸው ጥረት ይደረጋል፣ በሥራ ላይ ያሉትን የህግ ማዕቀፎች ሳይሸራረፉ የመተግበርና በጥናት ላይ ተመሥርቶ የማሻሻል ስትራቴጂ በመከተል ክፍተቶችን መሙላት፣ እንዲሁም ለአፈፃፀም አጋዥ የሆኑ ግልፅ የአሠራር ማንዋሎችን በማዘጋጀት በዚሁ መሠረት መተግበር፣ መልካምና የተሻለ አፈፃፀም ለሚኖራቸው ባለሙያዎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች የማበረታቻ ሥርዓት በመዘርጋት በጎ የውድድር መንፈስ እንዲኖር ይደረጋል።

ሁሉም የልማት ሥራዎች የህብረተሰቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፣ ከአጋር አካላትና ከህብረተሰቡ ጋር ሰፋፊ የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀትና ግንዛቤዎችን በመፍጠር በመግባባት ላይ የተመሠረተ የዕቅድ አፈፃፀም እንዲኖር ይደረጋል፣ የመፈፀም አቅምን ለማሳደግ በየደረጃውና በየሥራ ክፍሉ ክፍተትን በመለየት የረጅምና የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን በመስጠት የሚከናወኑ ሥራዎች በጥራት እንዲፈፀሙ ትኩረት ይደረጋል፣ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የልምድ ልውውጦችን በማድረግና ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ማስፋት ዋነኛ ስትራቴጂ ሆኖ ይቀጥላል።

ከባለድርሻ አካላትና ከህዝብ ክንፍ ጋር በቅርብ በመተጋገዝና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ አፈጻጸም ተግባራዊ ይደረጋል፣ ተቋማዊ አመራርና ፋፃሚ ኃይልን በሥነምግባር ግንባታ ማጠናከር፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ተቋማዊ የሥነምግባር መመሪያንና የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ቀርፆ ተግባራዊ ማድረግና የመሬት አስተዳደር ግብይት ተግባራት ኦዲት (land transaction audit) በአሠራርና በመዋቅር መመለስና ወደ ሥራ ማስገባት፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት የአገልግሎት አሰጣጥ ተግባራት ግልጽ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ በማድረግ፣ ለተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች (ለሴቶች፣ ለህጻናት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አዛውንቶች) ልዩ ድጋፍ በመስጠትና የህብረተሰቡን እርካታ በማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ይሆናል።

### 12.1.3. ሥራና ሥልጠና

ዘርፉ በመካከለኛ ደረጃ ጥራት ያለው ባለሙያ በማሠልጠን እና ለኢንዱስትሪው በመመገብ እንዲሁም የኢንተርፕራይዞች ልማትና ሽግግርን በማጠናከር የገበያ ትስስር በመፍጠር እንዲሁም ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የማይተካ ሚና አለው፡፡

### የትኩረት አቅጣጫዎች

የሥራ ዕድል ፈጠራው ዘላቂ እንዲሆን መሥራት፣ ወጣቶችና ሴቶች ሥራ ዕድል ላይ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ትኩረት አድርጎ መስራት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራው የበለጠ የሰው ኃይል ሊሸከም ወደሚችሉት የትኩረት ዘርፎች በተለይም ግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራው መንግስታዊ ድጋፎች በአግባቡ እንዲቀርቡ ከአጋር አካላት ጋር ተቀናጀጅቶ መሥራት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራው የወላጆችና የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ስለሆነ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ትኩረት አድርጎ መሥራት፣ በሁሉም ዘርፎች አሠልጣኞችን በተፈላጊው ደረጃ፣ ብዛትና ጥራት ማፍራት፣ የትብብር ሥልጠና ሽፋን እና ጥራትን ለማረጋገጥ በኢንዱስትሪ ብቃቱ የተረጋገጠ ሙያተኞን ለአሠልጣኝነት ማብቃት፣ ኮሌጅና ሼድ ግንባታዎችን ከሚጠበቅባቸው ስታንዳርድ ለመድረስ የህዝብ ተሳትፎን በአማከለ መንገድ ማስፋፋትና መገንባት፣ በየኮሌጁና በየሼድ የሚገኙ ማሽኖች አቅርቦትና አጠቃቀም ውጤታማነት የማሻሻል አቅጣጫ መከተል፣ ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት ብቃት ያለው ሙያተኛ ለማፍራት ሥልጠናውን በተቋማትና በሥራ ቦታ ትብብር በመስጠት ጥራቱና ሽፋኑ ተፈላጊው ደረጃ ላይ እንዲደርስ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የበቁ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የትብብርና ሥልጠና መድረክ እንዲሆኑ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣ ሥራ ፈላጊ ዜጐች በገበያ-ተኮር አጫጭር ሥልጠና በቅተው የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ እና በልማት እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ የሚሆኑበትን አቅጣጫ መከተል እንዲሁም ከልማት መሪ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ሠልጣኝ የማፍራት አቅጣጫ መከተል ተገቢ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በየዘርፉቸው የተሰማሩትን ሙያተኞች ብቁ የማድረግ እና የልማት ፕሮግራሞቻቸውን የዕሴት ሰንሰለት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን የማቅረብ ተግባራት እንዲፈጸሙ ጠንካራ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙ እየተገመገመ የሚሄድበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣ በዕድገት ተኮር ዘርፍ ለተሠማሩ ኢንተርፕራይዞች የተመረጠ፣ የተቀናጀ እና ሁሉን አቀፍ ደጋፍ በማቅረብ ተወዳዳሪነታቸውን በማሳደግ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚፈጠር ትስስር ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች ወደ ኤክስፖርት ገበያ እንዲገቡ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣ በኤክስቴንሽን ድጋፉ ማጠናቀቂያ ላይ የሁሉንም አንቀሳቃሾች ብቃት በምዘና የማረጋገጥና ኢንተርፕራይዞቹ በመሪ ሙያተኛ እንዲመሩ የማብቃት አቅጣጫ መከተል፣ በገበያ ፍላጐትና የዕሴት ሰንሰለት ጥናትን መሠረት ያደረገ ምርትና አገልግሎት የሚያቀርቡ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር የሚያስችል የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በስፋትና በጥራት ለማከናወንና የቴክኒክ ሙያና ትምህርት/ስ/ ተቋማት የራሳቸውን የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት እንዲችሉ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር ተሳስረው በተጠናከረ ሁኔታ በመሥራት የምርት ጥራትና ምርታማነትን የማሻሻል አቅጣጫን መከተል፣ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን መሠረት ያደረገ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት አቅጣጫ መከተል ናቸው፡፡

### ዓላማዎችና ግቦች

በክልሉ ያለውን የሥራ ገበያ ክፍተት መነሻ በማድረግ አዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞችን (ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን) በማቋቋምና በመደገፍ፣ በመንግስት ትላልቅ ፕሮጀክቶች እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች

እንዲሁም በመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና የውጭ አገር የሥራ ትስስር ቅጥር፣ በከተሞች ለ5,923,688 እና በገጠር ለ6,312,928 በጠቅላላ በዕቅድ ዘመኑ በገጠርና በከተማ ለ12,236,616 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ይሠራል፡፡ ከሚፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥም 80 በመቶው ዘላቂነት ያለው እና ቋሚ እንዲሆን የማድረግ፣ የሴቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት 50 በመቶ የማድረስ፣ የወጣቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት 80 በመቶ የማድረስ እንዲሁም በሥራ ፈላጊነት የሚመዘገቡ ሁሉም የአካል ጉዳተኞችና ከስደት ተመላሾች 100 በመቶ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሠራ ሲሆን በየዘርፉ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በዚህ መሠረት በማኑፋክቸሪንግ በገጠር ለ2,436,790፣ በከተማ ለ2,286,545 በድምሩ ለ4,723,335 ዜጎች፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በገጠር ለ606,042፣ በከተማ ለ568,673 በድምሩ ለ1,174,715 ዜጎች፣ በማዕድን ዘርፍ በገጠር ለ303,021፣ በከተማ ለ284,337 በድምሩ ለ587,358 ዜጎች፣ በከተማ ግብርና ዘርፍ (እንስሳትን ሳይጨምር) በገጠር ለ1,136,326፣ በከተማ ለ1,066,265 በድምሩ ለ2,202,591 ዜጎች፣ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ በገጠር ለ492,409፣ በከተማ ለ462,048 በድምሩ ለ954,457 ዜጎች፣ በአገልግሎት ዘርፍ በገጠር ለ1,073,197፣ በከተማ ለ1,007,028 በድምሩ ለ2,080,225 ዜጎች እንዲሁም በንግድ ዘርፍ በገጠር ለ265,143፣ በከተማ ለ248,792 በድምሩ ለ513,935 ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ይሠራል፡፡

የሥራ ሥምሪትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ አገልግሎቱን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ክልል አቀፍ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን ማሳደግ፣ የውጭ አገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎቶችን ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፣ የስደት ተመላሽ ዜጎችን መረጃ በዘመናዊ መንገድ ማደራጀትና በመልሶ ማቋቋም ሂደት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ አግኝተው እንዲቋቋሙ የሚያስችል ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዲሁም የሥራ ሥምሪት ዘርፉን ለማሻሻል የአሠራር ማንዋሎችን ማዘጋጀት የሚሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡

ለክልላችንና ለአገራችን ኢንዱስትሪ ዕድገት መሠረት የሚጥሉ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ምርት እና አገልግሎት የሚያቀርቡ፣ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ዕድገትና ለቴክኖሎጂ አቅም ፈጠራ ትኩረት የሚሰጡ ልማታዊ አስተሳሰብ ያጎለበቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉ የሚያስችል ጠንካራ ድጋፍ ከመስጠት አንፃር በዕድገት ተኮር ዘርፎች ክፍተትን እና የዕድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ ለ265,213 ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች (ለ831,282 አንቀሳቃሾች) የተሟላ የኢንዱትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት 237,778 አንቀሳቃሾችን አስመዝኖ በማብቃት ምርታማነትን እና ጥራትን ማሻሻል፣

በተጨማሪም ፍላጎትንና ክፍተትን መሠረት ያደረጉ 125 የዕሴት ሰንሰለት ትንተና በመሥራት 2,654 ፕሮቶታይፖችን በመኮረጅ እና በማሸጋገር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርታማነት እና የምርት ጥራት ማሳደግ፣ ኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነታቸውን የሚያሳድግና ጥራት ያለው ምርት ማምረት እንዲችሉ በማኑፋክቸሪንግ የተሰማሩ 17,540 ነባር ኢንተርፕራይዞች የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እና ውጤታማነታቸውን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ 12,947 ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመፍጠር የኢንተርፕራይዞችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ የ5,234 ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ በመቀመር ለ2,380 ኢንተርፕራይዞች በማስፋት ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሰማሩ 129,383 ኢንተርፕራይዞች ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

ለክልል ብሎም በአገር ደረጃ ልማት እንዲፋጠን ለማድረግ ተገቢውን ድርሻ የሚጫወት በቴክኒክ ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ብቁ የሆነ የሰው ኃይል በብዛት ማፍራትና ወደ ሥራ ሥምሪቱ እንዲገባ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የኢንዱስትሪውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ዓመታዊ የመደበኛ ሠልጣኝ ቅበላ በ2012 በጀት ዓመት በ1፡12፡10 ጥምርታ ከነበረበት 52,596 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 136,418 ማሳደግ፣ ገበያ ባላቸው ሙያዎች መደበኛ ባልሆነ አጫጭር ሥልጠና በ2012 ከነበረበት 2,934,886 ወደ 12,236,616 ከፍ በማድረግ የሠልጣኝ ዜጎችን የሥራ ፈጠራ አመለካከት እና ክህሎት ማሳደግ፣

ከዚህም በላይ የአሠልጣኝ ልማት ሥራዎች በመጠን እና በጥራት በማሳደግ እና በማሻሻል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ አሠልጣኞችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 6,507 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 12,621 ማድረስ እና የአሠልጣኝ ሠልጣኝ ጥምርታን በማስጠበቅ የሥልጠና ጥራትን እና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ውስጥ አሠልጣኝ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 4,456 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7,292 ማድረስ እና የአሠልጣኝ ሠልጣኝ ጥምርታን በማስጠበቅ የትብብር ሥልጠና ጥራትን እና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ ሥልጠና የሚሰጥባቸው የሙያ ዓይነቶችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 184 ወደ 250 በማድረስ የሥልጠና ፍላጎትን ማርካት እንዲሁም ኢንዱስትሪውን እና የባለድርሻ አካላትን በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ትግበራ ያላቸውን ተሳትፎ የማሳደግ ሥራ ይከናወናል፡፡ በሌላ በኩል የኢንዱስትሪውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፈላጎት ለማሟላት የግል እና መንግታዊ ያልሆኑ ኮሌጆች የመደበኛ ሠልጣኝ ቅበላ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 47,240 በ2022 በጀት ዓመት ወደ በ68,151 ማሳደግ እንዲሁም ገበያ ባላቸው ሙያዎች መደበኛ ባልሆነ አጫጭር ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማትን እንዲጠናከሩ ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ ከነበረበት 13,914 ወደ 233,678 በማድረስ የኢንዱስትሪውን የሠለጠነ  የሰው ኃይል እጥረት የመቀነስ ግብ ተጥሏል፡፡

በቀጣይ 10 ዓመታት የጥቃቅን ተቋማትን እና ከማኑፋክቸሪንግ ውጭ የሆኑ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እና ተቋማት ጋር በጎንዮሽ እርስ በእርስ በምርትና በግብዓት አውት-ሶርሲንግ እና ሰብ-ኮንትራት የግብይት ሥርዓቶች ለ244,825 ኢንተርፕራይዞችና 77,751 አንቀሳቃሾች የገበያ ዕድሎችን በመፍጠርና በማስተሳሰር በ2012 በጀት ዓመት ተፈጥሮ ከነበረው ብር 24.22 ቢሊየን የገበያ ትስስር ወደ ብር 46.72 ቢሊየን ማድረስ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ከዚህም በላይ ከአበዳሪ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ለ311,128 አዳዲስ እና ነባር ኢንተርፕራይዞች ብር 21,503,328,968 የብድር አገልግሎት በማቅረብ በዘመኑ መመለስ ያለበት ብድር 100 በመቶ እንዲመለስ እና የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል እና ግንዛቤ በማሳደግ የብድሩ 80 በመቶ ከህብረተሰቡና ከትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በሚሰበሰብ ቁጠባ እንዲሸፈን ማድረግ የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችን ተደራሽነትን በማስፋት የማሠልጠኛ ኮሌጆችን በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበረት 94 ወደ 154 ማሳደግ፣ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችን አሁን ካለበት ከ23 ወደ 28 በማሳደግ ጥራትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎች በ2012 በጀት ዓመት ከነበሩበት 332 (በአዲስ 338 በመጨመር) በ2022 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 670 በማድረስ ተደራሽነቱን ማሳደግ እና ለህብረተሰቡ የተሟላ አገልግሎት መስጠት፣ ከዚህም ባሻገር በገጠር እና በከተማ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከነበሩት 15,518 ሼዶች ወደ 35,518 ማሳደግ እንዲሁም ሼዶቹ መሠረተ ልማት እንዲሟላላቸው እና ለኢንተርፕራይዞች እንዲተላለፉ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣ ለኢንተርፕራይዞች የማምረቻና መሸጫ ቦታ አገልግሎት የሚውል 413 ሄክታር የለማ መሬት ለሼድ መገንቢያ፣ ለከተማ እና ገጠር ግብርና፣ ለአሸዋ፣ ለድንጋይ እና ለጠጠር ማምረቻ አዘጋጅቶ ማስተላለፍ እና ተጠቃሚነታቸውን ከፍ ማድረግ፣ የዘርፉን የልማት መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት እና ለመተንተን የሚያስፈልጉ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የተቋሙን አሠራር ማሻሻል፣ በቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ውስጥ በሥራ ዕድል ፈጠራ ከ32.1 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በገበያ ልማትና ግብይት ወደ 35

በመቶ ለማሳደግ፣ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ወደ 50 በመቶ ለማሰደግ እንዲሁም በቴክኒክ ሙያ ኮሌጆች በሁሉም ሙያዎች የሴት ሠልጣኞችን ተሳትፎ የተደረሰበትን 55 በመቶ በማስጠበቅ በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ የሴቶች ተጠቃሚነት ማሳደግ እንዲሁም የወጣቶች ተጠቃሚነትን ከ83.7 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች መካከል በትኩረት ዘርፍ የተሠማሩ 129,383 ኢንተርፕራይዞች እንዲሸጋገሩ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ከማሳደግ አኳያ ከጥቃቅን ጀማሪ ወደ ጥቃቅን ታዳጊ 57,036፣ ከጥቃቅን ታዳጊ ወደ ጥቃቅን መብቃት 34,683፣ ከጥቃቅን መብቃት ወደ አነስተኛ ጀማሪ 17,115፣ ከአነስተኛ ጀማሪ ወደ አነስተኛ ታዳጊ 12,376፣ ከአነስተኛ ታዳጊ ወደ አነስተኛ መብቃት 6,282 እንዲሁም ወደ ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ 1,888 ኢንተርፕራይዞችን ለማሸጋገር የሚሠራ ይሆናል፡፡

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

**ተቋማዊ አቅም ግንባታ፡-** በዘርፉ ያለውን የአደረጃጀት፣ የአሠራር፣ የክህሎት፣ የዕውቀት እና የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን የሚፈታ ተቋማዊ አቅም በመገንባትና የህዝብ ክንፉን በማሳተፍ የሚሠራ ተቋም የመፍጠር አቅጣጫን መከተል፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን እና ኪራይ ሰብሳቢነትን በመድፈቅ ልማታዊ አስተሳሰብን የማጎልበት አቅጣጫ መከተል፣ በተቋማትና በዘርፎች መካከል ያለውን የአፈጻጸም ልዩነት የሚያጠብ፣ የመረጃ ታማኝነት ችግርን የሚፈታ እና የግብ ስኬትንና የደንበኞች ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ

**የአመራርና አሠልጣኝ ልማት፡-** የኮሌጅ አመራር ክፍተትን ለይቶ በተከታታይ ሥልጠና ማብቃት እና በቀጣይም የአመራር ምደባን ባላቸው የተሻለ አፈፃጸም መሠረት ማከናወን እና የተጠያቂነት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፣ በሁሉም ዘርፎች አሠልጣኞችን በተፈላጊው ደረጃ፣ ብዛት እና ጥራት ማፍራት፣ የትብብር ሥልጠና ሽፋን እና ጥራትን ለማረጋገጥ በኢንዱስትሪው ብቃቱ የተረጋገጠ ሙያተኛን ለአሠልጣኝነት ማብቃት፣ በፕሮጀክት-ተኮር የአሠለጣጠን ዘዴ የሲ እና ቢ ደረጃ አሠልጣኞች ቴክኖሎጂን መቶ በመቶ የመቅዳት እና የኤ ደረጃ አሠልጣኝ ቴክኖሎጂን ከመቅዳት አልፎ የማሻሻል አቅሙን መገንባት፣

**የግንባታና ግብዓት አቅርቦት አቅም ግንባታ፡-** ኮሌጅና ሼድ ግንባታዎችን ከሚጠበቅባቸው ስታንዳርድ ለመድረስ የህዝብ ተሳትፎን በአማከለ መንገድ ማስፋፋት፣ መገንባትና ማስተዳር፣ በየኮሌጁና በየሼዱ የሚገኙ ማሽኖች አቅርቦት እና አጠቃቀም ውጤታማነት የማሻሻል አቅጣጫ መከተል፣ የሚገነቡ ሼዶች እና ወርክሾፖች መሠረተ ልማታቸው የተሟላላቸው እና ለሥራ የተመቹ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ የመንግስታዊ ድጋፍና ሕጋዊነት የማስፈን ሥራዎችን መሠረት ያደረገ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚመቻችብት አቅጣጫን መከተል፣

**የሠልጣኝ ልማት፡-** ከኢንዱስትሪው ፍላጎት በመነሳት ብቃት ያለው ሙያተኛ ለማፍራት ሥልጠናውን በተቋማትና በሥራ ቦታ ትብብር በመስጠት ጥራቱ እና ሽፋኑ ተፈላጊው ደረጃ ላይ እንዲደርስ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የበቁ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የትብብር ሥልጠና መድረክ እንዲሆኑ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣ ሥራ ፈላጊ ዜጐች በገበያ-ተኮር አጫጭር ሥልጠና በቅተው የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩና በልማት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ የሚሆኑበትን አቅጣጫ መከተል፣ በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ደረጃ ISO (International standard) እንዲያሟሉ ማድረግ እንዲሁም ከልማት መሪ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ሠልጣኝ የማፍራት እንዲሁም የሥልጠና ጥራትን የማስጠበቅ ሥልት መከተል፣

**የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት፡-** የትኩረት ዘርፍ መሪ መሥሪያ ቤቶች በጋራ የተነደፉ ግቦችና ተግባራትን የመደበኛ ዕቅዳቸው አካል አድርገው እንዲይዙት በማድረግ በየዘርፋቸው የተሠማራውን ሙያተኛ ብቁ የማድረግ እና የልማት ፕሮግራሞቻቸውን የዕሴት ሰንሰለት ተወዳዳሪ የሚያደርጉ አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን የማቅረብ ተግባራት እንዲፈጸሙ ጠንካራ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት በመዘርጋት አፈጻጸሙ እየተገመገመ የሚሄድበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣ ኢንተርፕራይዞቹ የውጭ ምርት መተካት ከሚችሉበት ደረጃ ለመድረስ ያሉባቸውን ክፍተቶች በማሟላት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣ በማኑፋክቸሪግ ዘርፍ ለተሠማሩ ኢንተርፕራይዞች የተመረጠ፣ የተቀናጀ እና ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማቅረብ ተወዳደሪነታቸውን በማሳደግ ከመካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚፈጠር ትስስር ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች የኤክስፖርት ገበያ ላይ እንዲገቡ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣

በኤክስቴንሽን ድጋፉ ማጠናቀቂያ ላይ የሁሉንም አንቀሳቃሾች ብቃት በምዘና የማረጋገጥና ኢንተርፕራይዞቹ በመሪ ሙያተኛ እንዲመሩ የማብቃት ሥልት መከተል፣ በገበያ ፍላጐት እና የዕሴት ሰንሰለት ጥናትን መሠረት ያደረገ ምርት እና አገልግሎት የሚያቀርቡ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር የሚያስችል የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በስፋት እና በጥራት ለማከናወን እና የቴክኒክ ሙያና ትምህርት ሥልጠና ተቋማት የራሳቸውን የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት እንዲችሉ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር ተሳስረው በተጠናከረ ሁኔታ በመሥራት የምርት ጥራትና ምርታማነትን የማሻሻል ሥልት መከተል፣ በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ኢንተርፕራይዞችን በዘርፍ ክላስተር ማድረግና ከየክላስተሩ ሞዴል መምረጥ እና ሞዴሎችን ማዕከል አድርጎ ሥልጠና መስጠት፣የዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገ የመንግስታዊ ድጋፍ እና ሕጋዊነት የማስፍን ሥራዎችን መሠረት ያደረገ አንድ ማዕከል አገልግሎት የሚመቻቸብት ሥልት መከተል፣ ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን መሠረት ያደረገ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመርና የማስፋት ሥልት መከተል፣

**ኢንተርፕራይዝ ልማትና የሥራ ዕድል ፈጠራ:-** በሥራ ዕድል ፈጠራ ሂደት ለግሉ ዘርፍ የተሻለ ድጋፍ በማድረግ የሥራ ገበያ ቅጥር ለዜጎች ሰፊ ሥራ ዕድል እንዲፈጥር ማድረግ፣ የሥራ ፈጣሪነትን ባህል በማዳበር ዘርፉ የአዳዲስ ፈጠራ መፈልፈያ እንዲሆን የማድረግን አቅጣጫ መከተል፣ ለፈጠራ ሥራ ማበረታቻ የሚሆን የዋስትና ፈንድ ማመቻቸት፣ ሰፊ የሥራ ዕድል ለሚፈጥሩ ተቋማት የማበረታቻ ሥርዓት የሚፈጠርበትን አቅጣጫ መከተል፣ የጥቃቅን፣ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ወጥነት ባለው መልኩ የሚመራበት የፖሊሲ ማሻሻያ እንዲደረግ ለፌደራል መንግስት ግብዓት በመስጠት ተመጋግቦ እንዲያድጉ የማድረግ ሥልትን መከተል፣ የቁጠባ ባህላቸውን የሚዳብርበትን፣ የጥ/አ/መ/ኢንተርፕራይዞች ባንክ የሚቋቋምበትን እና የአነስተኛ ብድር ተቋማትን የሚዘምኑበት አቅጣጫን መከተል፣ የሚሰጡ የቴክኒክና የክህሎት ሥልጠናዎች፣ የንግድ ልማት አገልግሎትና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥራታቸውን የጠበቁ እና ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ሥልትን መከተል፣ በዘርፉ ሥራዎች አጋርነትና ቅንጅታዊ አሠራር የሚጎለብትበትን አቅጣጫን መከተል፣ በአካባቢ ልማት የተሰማሩ ተጠቃሚዎች በኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ የራሳቸውን ሥራ እንዲጀምሩ የሚደረግበትን አቅጣጫ መከተል፣ የመንግስታዊ ድጋፍ አቅርቦት ተግባራትን በጊዜ፣ በጥራት እና በመጠን ውጤታማ ማድረግ፣

**ገበያ ልማትና ግብይት፡-** የሥራ ገበያ ትስስር ክፍተት ያለባቸውን ዘርፎች እና ኢንተርፕራይዞች ችግር የሚፈታ የገበያ ትስስር መፍጠር፣ ለኢንተርፕራይዞች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ገበያ በምርትና በግብዓት የገበያ ትስስር የሚፈጥሩ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ትስስር በማጠናከር ቀጣይነት እንዲኖራቸው የተጠናከረ የምርት ትውውቅ ሥራ በመተግበር የመደገፍ አቅጣጫ መከተል፣ ተደራሽ፣ ወጥና ቁጠባ መር የብድር አቅርቦት እና አመላለስ ሥልትን መከተል፣ ኢንተርፕራይዞች ዘመናዊ የሂሳብ ሥርዓት ዝርጋታን ተግባራዊ እንዲያደርጉ መደገፍ እንዲሁም ገቢ ምርትን የሚተኩና ለውጭ ገበያ የሚያምርቱ ኢንተርፕራይዞችን የውጭ ገበያ ትስስር ችግር በመፍታት ምርታማነትን ማሳደግና የምንዛሬ አቅርቦት ምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ ስደተኞችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና ሥልቶች ናቸው።

### 12.1.4. ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት

በክልሉ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ለማሳደግ ሁነኛ መንገድ ነው። የኢንዱስትሪ ልማት፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልፅግና ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። ጠንካራ ኢንዱስትሪን መሠረት አድርጎ የተገነባ ኢኮኖሚ በተለያየ ቀውሶች ተጽዕኖ በቀላሉ የመጋለጥ ዕድሉ ዝቅተኛ ነው። በአጠቃላይ ጠንካራና ተወዳዳሪ የሆነ የኢንዱስትሪ ልማት መገንባት ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና የጉልበት ምርታማነትን እና የቴክኖሎጂ አቅምን ለማሳደግ፣ ለተለያዩ ቀውሶች የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት፣ የክልል ውስጥ ምርትን /RGDP/ በማሳደግ ረገድ ድርሻውን ለማበርከት፣ ኢንዱስትሪው በራሱ እና ከሌሎች ዘርፎች ጋር ትስስር በመፍጠር አጠቃላይ ኢኮኖሚው በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ የማይተካ ሚና ይኖረዋል።

### ኢንቨስትመንት

### የትኩረት አቅጣጫ

በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ቀዳሚ ሚና እና ትስስር ተመሥርቶ በክልሉ ኢኮኖሚ ላይ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አማራጮችን በጥናት በመለየት እና ማሻሻያዎች እንዲደረጉ በማመቻቸት ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ የኢንቨስትመንት ከባቢ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በመፍጠር፣ በተቀናጀ ግብርና እና የግብርና ውጤቶች ማቀነባበር፣ በተቀናጀ የማዕድን ልማትና ማኑፋክቸሪንግ፣ በቱሪዝም እንዲሁም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ በማተኮር ለዘላቂ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ እና የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በብዛት እና በጥራት ወደ ክልሉ መሳብ እንዲሁም ኢንቨስትመንት ወደ አልተዳረሰባቸው የክልሉ አካባቢዎች የኢንቨስትመንት ሥርጭቱን ማመጣጠን ይገባል።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ (የማዕድንና ማኑፋክቸሪንግ፣ የግብርና ውጤቶች ማቀነባበር) ኢንቨስትመንትን በጥንድ ምልከታ፣ በቀጣናዊ የዕሴት ሰንሰለት ትስስራቸውን በማጠናከር የማምረት አቅማቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን በማጎልበት ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ማረጋገጥ፣ በቱሪዝም እና በሌሎች የአገልግሎት ዘርፎች (ትምህርት፣ ጤና፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች ወዘተ) ኢንቨስትመንትን በማስፋፋትና ተወዳዳሪነታቸውን በማጠናከር ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ፣ የኢንቨስተሩን ፍላጎት ያገናዘበ እና በዘመናዊ የአሠራር እና የመረጃ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶ በብቁ የሰው ሀብት የሚመራ የአገልግሎት ከባቢ መፍጠር፣ የተሟላ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጠት እና በቅንጅታዊ አሠራር በክልሉ ተገልጋይ ተኮር የኢንቨስትመንት አገልግሎትን ማስፈን የኢንቨስትመንት ዕድገትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### ዓላማዎችና ግቦች

ክልሉን ተወዳዳሪ እና ቀዳሚ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ በክልሉ ፀጋዎች ላይ ተመሥርቶ በተመረጡ ቦታዎች ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን በመከለል እና በማቋቋም አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የሚወጡ እና በትስስር የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዕድሎችን የሚፈጥሩ፣ የከተሞችን ልማት የሚያፋጥኑ፣ ለኢኮኖሚያዊ ሽግግር ጉልህ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ዓላማ በማድረግ የሚከተሉት

ግቦች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የኢንቨስትመንት ፀጋዎች መለያ ጥናት ክልላዊ ሽፋንን ለማሳደግ የክልሉን ዕምቅ ሀብት በአማካሪ 2 ጊዜ በማስጠናት ቀዳሚ ዘርፎችን መለየት እና መረጃዎችን ወቅታዊ ማድረግ፣ የክልሉን የትኩረት መስኮች መሠረት በማድረግ በጥናት የተለዩ 6ቱን የልማት ቀጠናዎች የዕሴት ሰንሰለትና ጥልቅ ትንተና በመሥራት የልማት ቀጣናዎችን ለኢንቨስትመንት ዝግጁ ማድረግ፣ ውጤታማ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን በመተግበር የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያመጡ በሚችሉ ዘርፎች 45,473 ኢንቨስትሮችን በመመልመል እና በማስተዋወቅ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ማሳደግ፣ በሁሉም የኢኮኖሚ ዞኖች ለሚለዩ ቀዳሚ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚውል 26,210 ሄክታር መሬት እንዲቀርብ እና መሠረተ ልማት እንዲሟላ ማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመገምገም፣ በመምረጥ ወደ ሥራ በማስገባት በመከታተል እና በመደገፍ በመምረት/አገልግሎት በመስጠት ውጤታማ እንዲሆኑ በማስቻል ዘላቂ ኢንቨስትመንትን በማረጋገጥ ወደ ማምረት/አገልግሎት መስጠት በሚገቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ ውጭ ምርታቸውን በመላክ ገቢያቸውን ከ15.2 ሚሊየን ዶላር ወደ 998.5 ሚሊየን ዶላር እንዲያድግ ማድረግ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ድጋፍ በማድረግ ወደ ማምረት/አገልግሎት በሚገቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወንድ 461,352 ሴት 455,081 በድምሩ 916,433 ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ይደረጋል የሚሉት በአሥር ዓመቱ የሚፈጸሙ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

ባለሀብቶችን በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ እንዲሳተፉ የማድረግ ሥራ በመሥራት ዘርፉን የማሳደግ ሥራ ይከናወናል፡፡ በከተሞች ጠንካራ የኮሚቴ አደረጃጀት በመፍጠር በየከተማው ያለውን የኢንዱስትሪ ችግር ለመፍታት ይሠራል፡፡ ይኸውም ከባለሀብት፣ ከመሠረተ ልማት አቅራቢ ድርጅቶች በዋናነት ከመብራት ኃይል እና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የምክክር መድረኮችን በማዘጋጀት ያሉትን ችግሮች በቅንጅት ለመፍታት ይሠራል፡፡ በኢንዱስትሪ መንደሮች፣ በፓርኮች እንዲሁም ከነዚህ ውጭ ባሉ የልማት ቦታዎች በአምራች ኢንዱስትሪ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች ቀድሞ የመሬት አቅርቦት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ዝግጁ የማድረግ ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በክልሉ ኢንቨስትመንት በበቂ ሁኔታ ለማስፋፋት ስለክልሉ አጠቃላይ መልካም ገጽታዎች እና ምቹ ሁኔታዎች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የማስተዋወቅ ሥራ እንደ አንድ የማስፈፀሚያ ሥልት ተወስዶ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በተለያዩ የፕሮሞሽን ገጽታ ግንባታ ሥራዎች ወደ ክልሉ ለኢንቨስትመንት የመጣውን ባለሀብት አስቀድሞ በታቀደ ድጋፍና ክትትል ሥርዓት ደግፎ በክልሉ ኢንቨስትመንት ተሳታፊ የማድረግ ሥራ ይከናወናል፡፡

ለኢንቨስትመንት አፈፃፀም ውጤታማነት ጉልህ ድርሻ ካላቸው አካላት ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር ውይይት ይካሄዳል፡፡ ህጋዊ የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻል ተግባራዊ የማድረግ፣ የተፈቀደን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የመከታተልና የመደገፍ ሥራ የመሥራት፣ የመሬት የመብራት፣ የብድርና ሌሎች የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሮቹ እንዲፈቱ የማድረግ ሥልቶች ይከናወናሉ፡

በተጨማሪም ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን መተግበር፣ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር፣ አጋር አካላትን በላቀ ደረጃ ማሳተፍ፣ ቀጣይነት ያለው የውድድርና የማበረታቻ ሥርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣ ጠንካራ የመረጃ ሥርዓትን መዘርጋት፣ መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በትኩረት ለይቶ የመፍታት አቅጣጫን መከተል፣ ውጤታማና ቀልጣፋ የሀብት አጠቃቀምን የማዳበር ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

## የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት

## የትኩረት አቅጣጫዎች

በየደረጃው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፣ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፣ የነባር ኢንዱስትሪዎችን ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ የምግብ የልብስና የመጠለያ ምርቶችን ተወዳዳሪ በሆነ መልኩ በማምረት የአገር ውስጥ ፍላጎቶችን ማሟላትና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ የአገር ውስጥ ግብዓቶችን ለሚጠቀሙ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አምራቾች ቅድሚያ ትኩረት መስጠት፣ የወጪ ንግድ ምርቶችን በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ማሳደግና የማኑፋክቸሪንግን የዕሴት ሰንሰለት፣ ትስስርና ተመጋጋቢነት ማጠናከር ከማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ልማት አንፃር ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ናቸው። በተጨማሪም በጥናት ላይ የተመሠረቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችና የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በዘርፉ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይነት መሳብ፣ ለዚህም የግሉን ዘርፍ ሚናና አጋርነት ማሳደግ፣ የዘርፉን ትስስር ለማሳለጥ በቀጣይ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ልማት ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ማስተሳሰር፣ የክላስተር አደረጃጀትን ማጠናከር፣ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና በሂደት ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ምቹ መደላድል መፍጠር እንዲሁም የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግ የልማት ዕቅዱ ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

በክልሉ ያለውን የሰው ኃይል፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ ምርቶችን ለማምረት የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ፣ ምርቶቹ በዓለምና በአገር ውስጥ ገበያ ያላቸውን ተፈላጊነት እንዲሁም በዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር ግምት ውስጥ በማስገባት በልማት ዕቅዱ የመጀመሪያ አምስት ዓመታት (2013-2017) የግብርና ምርቶችን በጥሬ ዕቃነት በሚጠቀም ማኑፋክቸሪንግ ላይ በማተኮር አስተማማኝ የኢንዱስትሪ መሠረት ለመገንባት የሚሠራ ይሆናል። ከዚህ አኳያ በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ በተለይም በምግብና ተያያዥ ምርቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

በተጨማሪም በአግሮፕሮሰሲንግ በተለይም በምግብ፣ መጠጥ፣ ጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ላይ ትኩረት በመስጠት ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ይሠራል። እንዲሁም እያደገ የመጣውን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ለማስቀጠል በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን በተለይም ብረታብረትና ሲሚንቶ የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በክልል ውስጥ ለማምረት ትኩረት ይደረጋል። ከዚህ አኳያ በመጀመሪያዎቹ አምስት የልማት ዕቅዱ ትግበራ ዓመታት ቀላል ቴክኖሎጂዎችንና ብዙም የተማረ የሰው ኃይል በማይጠይቁ ዘርፎች ላይ በማተኮር የሚሠራ ሲሆን ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር በሚያስችሉ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

በልማት ዕቅዱ ሁለተኛ አምስት ዓመታት (2018-2022) በቂ ዝግጅት በማድረግ ከፍተኛ ካፒታልና የሠለጠነ የሰው ኃይል ወደሚጠይቁ የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፎች በመሸጋገር ኢንዱስትሪ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል። ይኸውም በመጀመሪያው የአምስት ዓመት የኢንዱስትሪ ልማት መርሃ ግብር የተተገበሩ ኢንዱስትሪዎችን በማሻሻል ጥራታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ሁለተኛው ከፍተኛ ዕውቀትና ካፒታል ላይ የተመሠረቱ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ነው። ከዚህ አኳያ ዘርፉን የማበረታታት እና የማዘመን ሥራ ትኩረት ይሰጠዋል። በአጠቃላይ በዕቅዱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት መርሃ ግብር በውጭና በአገር ውስጥ ገበያ ያለውን ተፈላጊነት፣ ምርቶቹን ለማምረት የሚያስፈልገውን የቴክኖሎጂ ደረጃ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅማቸውን፣ ያላቸውን የፊትዮሽና የኋልዮሽ የዘርፎች ትስስርን፣ የሚጠይቁትን የሙያ ክህሎት ደረጃ፣ የሚያስፈልጋቸውን ካፒታል መጠንና የመሠረተ ልማት ፍላጎትን ታሳቢ በማድረግ ትኩረት ይደረጋል።

## ዓላማዎችና ግቦች

የነባር አምራቾችን ምርትና ምርታማነት በማሻሻል፣ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ዘርፉ ለሥራ ዕድል ፈጠራ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማስቻል፣ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፍ በስፋት እንዲሠማራ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ለጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ማሳደግ እና የንዑስ ዘርፉ ከክልሉ ዘላቂ ልማት እንዲሁም ከዘላቂና አረንጓዴ የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚሉትን ዓላማ በማድረግ የሚከተሉት ግቦች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን አማካይ የማምረት አቅም በ2012 ከነበረበት 62 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ የደረጃ ሽግግር እንዲያደርጉ 1,475 አምራች ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ፣ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,365 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7,094 ማሳደግ፣ ወደ ውጭ ምርት በመላክ የሚገኝ ገቢን ከ7.6 ሚሊየን ዶላር ወደ 998.5 ሚሊየን ዶላር ማሳደግ፣ ጥራት ያለው ኢንቨስትመንት በመሳብ እና ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ውጤት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ አተኩሮ በመሥራት የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪን /ማኑፋክቸሪንግ/ ብዛት በድምሩ ከ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,603 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 8,234 በማሳደግ በዘርፉ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2022 በጀት ዓመት ለ220,520 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

በተጨማሪም በኢንዱስትሪ የሚመረቱ ተኪ ምርቶችን ከነበረበት 62 ወደ 80 ማሳደግ፣ የተለዩ ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን ብዛት ከነበረበት 524 ወደ 712 ከፍ ማድረግ፣ የተኪ ምርቶችን መጠን ከ16,041 ቶን ወደ 60,078 ቶን ማሳደግ እና ተኪ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት የሚድን የውጭ ምንዛሬን ከ47.506 ሚሊየን ዶላር ወደ 140.180 ሚሊየን ዶላር ማድረስ የተጣሉ ግቦች ናቸው፡፡ እንዲሁም ለግብርና ሜካናይዜሽን እና ሌሎች የእርሻ መሣሪያዎች ፍላጎት ማሟላት በሚያስችል መልኩ የብረታ ብረት ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል ግንባታ ትኩረት የሚሠጠው ይሆናል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

በማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚሠማራውን የሰው ኃይል ከኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰርና የሥራ ላይ ሥልጠና በመስጠት የሠራተኛው ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና የኢንዱስትሪ ሥራ ባህል እንዲዳብር ይደረጋል፡፡ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና ቅንጅታዊ አሠራሮች ለዘርፉ ግቦች ስኬት በሚጠቅም መልኩ ይቃኛሉ፡፡ የዕድገት ኮሪደርን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማቶች አቅርቦት ከፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የምርት እና ምርታማነት እንዲሁም የምርት ስብጥር እና ጥራት ማሻሻያ ሥራዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡ የጥራት ደረጃውን ያሟላ፣ ያልተቆራረጠ፣ በቂና ፈጣን የምርት ግብዓት አቅርቦት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንፃር አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን እርስ በእርስ እንዲሁም ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ግብዓት እንዲያቀርቡ የሚደረግ ሲሆን በአገር ውስጥ ሊመረቱ የማይችሉ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከውጭ ለማስገባት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ቅድሚያ እንዲሰጥ ከፌደራል መንግስት ጋር በጋራ የሚሠራ ይሆናል፡፡

የምርምርና ሥርፀት፣ የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና፣ የጥራት ሥራ አመራር፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማትን ጨምሮ ትስስር እንዲጎለብትና እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የተጠናከረ ሥራ አመራር እና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን የዘርፉ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብና በኮንስትራክሽን፣ በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሠማሩ የአገር እና የክልል ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲገቡ ምቹ መደላድል ይፈጠራል፡፡ ከዚህ አኳያ የተቀናጀ የአግሮ

ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት፣ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት፣ አስተማማኝ እና ዘመናዊ የንግድና ኢንዱስትሪ መረጃ ሥርዓት ግንባታ እና አዳዲስ በውጤት ላይ የተመሠረቱ የኢንዱስትሪ ማበረታቻዎችን ወደ ተግባር ማስገባት ትኩረት ይሰጠዋል።

### 12.1.5. ማዕድን ሀብት ልማት

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

ኢትዮጵያ በቀጣይ አሥር ዓመታት የምታደርገውን የብልፅግና ጉዞ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በተጨባጭ ለውጦች የታጀበ ለማድረግ የተሰነቀውን ርዕይ ለማሳካት ዘርፉ በተልዕኮ ደረጃ ስትራቴጂያዊ ግቦችንና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት እና በተጠያቂነት መንፈስ መምራት ይጠይቃል። ፍትሐዊ የማዕድን ሀብት ልማትና ግብይት ለማጠናከር የማዕድን ምርትና ግብይት ካለፉት ዓመታት የአገሪቱ ብሎም የክልሉ ማዕድን ሥራዎችና ግብይት ሲንከባለሉ የመጡትን የፍትሐዊነት ችግሮች በአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ በማስወገድ ፍትሐዊ የማዕድን ሀብት ልማትና ግብይት በክልላችን በዘላቂነት ይፈጠር ዘንድ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ።

በዘርፉ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት በዋናነት አስቻይ ሁኔታዎችን ለይቶ መሥራት ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የማዕድን አለኝታ መረጃዎችን በማደራጀትና የፕሮጀክት ፓኬጆችን በመቅረጽ በተለያዩ የፕሮሞሽን ዘዴዎች እና በዘርፉ በአገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ፎረሞችና ኮንፈረንሶች የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት ይሠራል ። በዘርፉ ሰፊ ልምድ ያላቸው ዓለም አቀፍ ባለሀብቶች ከአገር በቀል ባለሀብቶችና የመንግሥት የልማት ድርጅት ጋር በሽርክና እንዲሰሩ የማስማማትና የመሳብ ሥራዎች ይሰራሉ። ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪና የአገር ውስጥ ገቢ ለማሳደግ በዋናነት የትኩረት አቅጣጫ የሚሆነው የማዕድን ልማት ምርቶችን አቅርቦት በብዛት፣ በዓይነት፣ በጥራትና በዋጋ ማሻሻልና ማሳደግ፣ የዘርፉን ዕሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋት፣ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪና የአገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ የማዕድን ልማት ምርቶችን አቅርቦት በብዛት፣ በዓይነት፣ በጥራትና በዋጋ የማሻሻል ተግባር ማከናወን፣ የአካባቢ ጥበቃና ማህበረሰብ ልማት ማስፋት፣ የሥነ-ምድር መረጃ ሽፋንን ማሳደግ የሚሉት ዋነኛ የመሪ ዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

#### ዓላማዎችና ግቦች

የማዕድን ልማት ዘርፍ ዕቅድ ዋና ዋና ዓላማዎች የማዕድን ፍለጋና ክምችት የሥነ-ምድር ግመታ መረጃ ሽፋንን በማሳደግ የዘርፉን ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፣ የማዕድንን ዘርፍ ዕሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንደስትሪዎችን ማስፋፋት፣ የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅምን ማሳደግ፣ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪና የአገር ውስጥ ገቢ ማሳደግ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማትን ማስፋፋት ሲሆን የተቀመጡትን ዓላዎች ለማሳካት የሚከተሉት ግቦች ተቀምጠዋል።

የሥነ-ምድር እና ማዕድን ሀብት ሽፋንን ለማሳደግ የክልሉን የሥነ-ምድር ጥናትና ካርታ ሥራ ሽፋን በ1:50,000 መሥፈርት አሁን ካለው 20,419.56 ወደ 149,580 ካሬ ኪሎ ሜትር ማሳደግ የማዕድን ፍለጋና ክምችት የሥነ-ምድር ግመታ መረጃ ሽፋንን አሁን ካለበት 3,135.4 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ወደ 5,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ሽፋን ማሳደግ፣ የሥነ-ምድር ካርታ ሽፋንን ከፍ ማድረግ፣ በራስ አቅም የማዕድን ቅኝትና ክምችት ግመታ ጥናት ሽፋንን ማሳደግ፣ የማዕድን ዘርፉን ኢንቨስትመንት እና ኢንተርፕራይዞች ለማስፋፋት የውጭ የማዕድን ሥራዎች ኢንቨስትመንትን በመሳብ በ30 በመቶ ማሳደግ እና የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ ከፈቃድ መስጠት ጋር ተያይዞ

በከበሩና በከፊል በከበሩ ማዕድናት የሚሰጥ ፈቃድ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 129 በ2022 ወደ 730 ማሳደግ፣ የዘርፉን ዕሴት የሚጨምሩ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ሥራ ፈቃድ በመስጠት ዕሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ከተደረሰበት 56 ወደ 500 ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ዕሴት ጨማሪ ኢንዱስትሪዎችን ፈቃድ ከተደረሰበት 44 ወደ 209 ለማስፋፋት ይሠራል፡፡

የሥራ ዕድል የመፈጠር አቅምን ለማሳደግ በዘርፉ በዚህ ወቅት በሥራ ላይ ካሉት እና ወደፊት ይሠማራሉ ተብለው ከሚታሰቡት ባለሀብቶች፣ ኩባንያዎች እና ኢንተርፕራይዞች የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምርት መጠን ወደ 152,157 ኪሎ ግራም ማሳደግ፣ የዘርፉን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ከተደረሰበት ዝቅተኛ 74.5 ሚሊየን ዶላር ደረጃ በአሥር ዓመቱ መጨረሻ ወደ 170 ሚሊየን ዶላር ለማሳደግ ይሠራል፡፡ እንዲሁም ከማዕድን ዘርፍ የሚገኘውን የአገር ውስጥ የክልል ገቢ ከተደረሰበት ብር 205.95 ሚሊየን ወደ ብር 1.1 ቢሊዮን ለማሳደግ የሚሠራ ይሆናል፡፡

የልማት ቦታዎች በኬሚካል የመበከል እና በአካባቢው ሠብዓዊ እና ተፈጥሯዊ ሀብቶች ላይ ጉዳት ሲያስከትል እና የግጭት ምንጭ ሲሆን ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም የአካባቢ ጥበቃና የማህበረሰብ ልማትን በማስፋፋት ዓመታዊ የአካባቢ ጥበቃና መልሶ የማቋቋም ፈንድ በመሰብሰብ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት 100 በመቶ ማረጋገጥ፣ ከአካባቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ አንፃር በፀደቁ የዛፍ ችግኞች የሚሸፈኑ ቦታዎችን 130 ሺህ ሄክታር ለማድረስ ታቅዷል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

ከህግ እና የአሠራር ሥርዓት አንፃር ሉላዊ፣ አገራዊ እና ክልላዊ ተጨባጭ ወቅታዊ ሁኔታን መሠረት በማድረግ የማዕድን ሥራዎች እና የግብይት ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች ተያያዥ የአሠራር ሥርዓቶች በጥናት እየተፈተሹ ከአሥር ዓመቱ የዘርፉ የዕድገት እና የብልፅግና ዕቅድ ጋር (2013-2022) በተጣጣመ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ እንዲሻሻሉ በማድረግ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ከአደረጃጀት አንፃር ነባሩ መዋቅር ያለበትን የአመለካከት፣ የክህሎት፣ የአሠራር፣ የአደረጃጀት እና የግብዓት አቅርቦት ችግሮች (የአቅም ክፍተት) በዘላቂነት የሚፈታና ወቅቱ የሚጠይቀውን ተግባርና ሃላፊነት በብቃትና በተጠያቂነት በመፈጸም በተከታታይ ያለማቋረጥ ተፈላጊውን ውጤት በማስመዝገብ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን የኢኮኖሚ ሽግግር የሚደግፍ አደረጃጀት በዘላቂነት መፍጠር እና መገንባት በመሪ ዕቅዱ የበጀት ዓመታት (2013-2022) የማይታለፍ ጉዳይ ተደርጎ ይሠራል፡፡

### 12.1.6. ንግድና ገበያ ልማት

ንግድ በተለይም የአገር ውስጥ እና የወጭ ገበያን መሠረት ያደረገ የንግድ እንቅስቃሴ የአካባቢውን አንፃራዊ ጠቀሜታ /Comparative Advantage/ ወይም ፀጋ በአግባቡ ለመጠቀም፣ በብዛት ለማምረት እና የማምረቻ ዋጋ ለመቀነስ፣ የማምረት አቅምን ለማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማጎልበት፣ ቁጠባን እና ኢንቨስትመንትን (የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን) ጨምሮ ለማሳደግ እና ብሎም የሚታሰበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እና መዋቅራዊ ለውጥ ዕውን እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ሚናው የጎላ ነው፡፡ በተጨማሪም የከተማ እና የገጠር ትስስርን በመፍጠር የከተሞች ዕድገት እንዲፋጠን ከማድረግ አኳያ ንግድ እንደ አንድ የአገልግሎት ንዑስ ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ሲያስዝመግብ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት የራሱ የሆነ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

በበጋ/ቆላ የስንዴ ምርት ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና ከዚያም ባሻገር ስንዴ አምርቶ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ያለመ ሥራ እየተሠራ ያለ መሆኑ የሚያበረታታ ነው፡፡ በአጠቃላይ በግብርናው፣

በአምራች ኢንዱስትሪው እና በሌሎች ዘርፎች የሚመረቱ ምርቶች የውጭ ስታንዳርድ በማሟላት በውጭ ገበያ ተወዳድረው ማሸነፍ የሚችሉ እንዲሆኑ ይሠራል፡፡ ይህ ሲሆን የሚፈለገውን የውጭ ምንዛሬ ያስገኛሉ፡፡ እነዚህ የውጭ ስታንዳርዳቸውን ጠብቅው በአገር ውስጥ የተመረቱ ምርቶች ወደ ውጭ ባይላኩ እንኳን የአገሬው ሰው ከሌሎች የውጭ ምርቶች የበለጠ የሚመርጣቸው ስለሚሆኑ ይገዛቸዋል፣ ስለሆነም ከውጭ የሚመጡ ምርቶችን የማስቀረት እና በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን የመጠቀም ዕድል ያሰፋል፡፡ ስለዚህ የሚመረቱ ምርቶችን በጥራትና በብዛት ከማምረት አንፃር የምርምር ተቋማትና የዩኒቨርሲቲዎች ሚና ከፍ እንዲል ይደረጋል፣ የሚመረቱ ምርቶችን ደረጃ እና ብራንድ የማዘጋጀት ሥራ በተጠናከረ መንገድ ይሠራል፣ ምርቶችን በብዛት እና በጥራት ለማምረት የግል ባለሀብቶች ሚናም ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት መንግስት የግብር እፎይታ በመስጠትም ሆነ ከውጭ ለሚመጡ ግብዓቶች ከግብር/ቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማድረግ፣ የገበያ ትስስር የመፍጠር እና የሙያ ድጋፎችን/የኤክስቴንሽን አገልግሎት የመስጠት ሥራዎች ተጠናክረው ይሠራሉ፡፡

አምራች ዘርፎች ይበልጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃርም ግብዓቶችን ከውጭ በማስመጣት ከመጠቀም ይልቅ ቀስ በቀስ በአገር ውስጥ የተመረተ ግብዓት እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ በአጠቃላይ የመፈጸም እና የማስፈጸም ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ፣ የዘርፉን ዕድገት ማሳለጥ የሚያስችሉ ቅንጅታዊ አሠራሮችን ማጠናከር፣ የንግድ አሠራሮችን ማዘመን፣ የወጪ ንግድ የምርት መጠን፣ ስብጥር እና ጥራትን ማሳደግ፣ ጤናማ ውድድር የሰፈነበት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ወደ ንግድ ሥራ ለመግባት አመቺ የሆነ የንግድ ሥርዓት መዘርጋትና የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማረጋገጥ ትኩረት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ዘመናዊ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት የምርትና አገልግሎት ጥራትና ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል።

ከዚህ በፊት የነበረውን የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለት ሪፎርም በማድረግ እና የንግድ ተወዳዳሪነትን በማስፈን የሸማቹን ህብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። በተጨማሪም የምርት ጥራት ኢንስፔክሽን እና ሬጉሌሽን ሥራን በማሻሻል ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ አስፈላጊው ሥራ ይሠራል። ዘመናዊ፣ ፍትሐዊ እና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥርዓት በመዘርጋት እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሠጣጥን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ አገልግሎት የመስጠት አቅምን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ጥረት ይደረጋል፡፡

የህብረተሰቡን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የምርቶች እና አገልግሎቶች ጥራትና ደህንነት የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም ቀልጣፋና የላቀ የገበያ ማስፋፊያና ትስስር ሥርዓት በመገንባት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የላቀ ዘመናዊ የምርት ግብይት ሥርዓት የመገንባት፣ አዳዲስ የግብርና ምርቶች ወደ ግብይት ሥርዓቱ የማስገባት፣ የዓለም ንግድ ድርጅት እና የክልላዊ ነፃ የንግድ ቀጣና አባልነት ድርድሮችን በማካሄድ አስተማማኝ የገበያ ዕድል የማስፋፋት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ አምራቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብ እና ሸማቹን ያረካ፣ ውድድርን መሠረት ያደረገ፣ ፍትሐዊ የንግድ አሠራር ሥርዓትን የመፍጠር እና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የገበያ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግ የላቀ የውጭ ምንዛሪ የማስገኘት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን የሚታገል የንግድ ዘርፍ አስተማማኝ ደረጃ ላይ የማድረስ፣ የህብረተሰቡን ጤንነት፣ ደህንነት እና የአገርን ጥቅም ለማስጠበቅ ከጥራት ደረጃቸው በታች የሆኑ ምርቶች እና አገልግሎቶች በገበያ ላይ እንዳይውሉ ጠንካራ የኢንስፔክሽን ሥራ ማከናወን ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ ለባለሀብቶች የሚሰጠውን ሁሉን አቀፍ እገዛና ድጋፍ በማጠናከር በውድድር አሸናፊ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡ ለማድረግ ጠንካራ የሬጉላቶሪ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በዘርፉ ውስጥ ያሉ የባለድርሻ አካላትን፣ የንግዱን ማህበረሰብና የሸማቹን ህብረተሰብ ግንዛቤና አቅም የማጎልበት ተግባር ይከናወናል፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

በክልል ውስጥ ዘመናዊ፣ ፍትሐዊ እና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ አሠራር እና የግብይት ሥርዓትን ማስፈን፣ በዕሴት ጭማሪ የላቁ የወጪ ንግድ ምርቶችን በብዛት፣ በጥራት እና በዓይነት ለአገር ውስጥ እና ለዓለም ገበያ

ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የንግድ ትስስሮችን በማጠናከር የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋትና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፣ የግብይት መሠረተ ልማት በማስፋፋት፣ ቀልጣፋ እና የላቀ የትስስር ሥርዓት መገንባት፣ ጠንካራ የንግድ ሬጉላቶሪ ሥርዓት በመዘርጋት የህጋዊ ነጋዴዎችን እና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና መሠረተ ልማት በማስፋፋት የዘርፉን አገልግሎት ቀልጣፋ እና ተደራሽነት ማሳደግ የሚሉት ዓላማዎችን መሠረት በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ የሚከተሉት ግቦች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ለንግዱ እና ለሸማቹ ማህበረሰብ፣ በሰብል ምርቶች ግብይት፣ በእንስሳት እና በእንስሳት ተዋፅኦ ምርት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት በስትራቴጂክ ዘመኑ በአዋጆች፣ በመመሪያዎች፣ በህገወጥነት እና በኪራይ ሰብሳቢነት እንዲሁም በመረጃ አጠቃቀም ዙሪያ በአጠቃላይ ለ11,244,970 የንግዱ ማህበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የሸማቾች ጥበቃ ሲቪክ ማህበራትን ቁጥር ከ2 ወደ 38 ማድረስ፣ የንግድ/ዘርፍ/ማ/ም/ቤትን፣ የዘርፍ/ማ/ም/ቤት በማጠናከር 816 የነበረውን የዘርፍ ማህበራትን ወደ 1,387 ማድረስ፣ 89 የነበረውን የነጋዴ ሴት ማህበራት ወደ 176 ማድረስ፣ የሴቶችን ድርሻ 50 በመቶ ማሳደግ፣ በ2012 መጨረሻ ለአገር ውስጥ ገበያ ቀርቦ የነበረውን 22,935,717 ኩ/ል የሰብል ምርት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 34,100,085 ኩ/ል በማድረስ የአምራቹን፣ የነጋዴውን እና የሸማቹን ተጠቃሚነት ማሳደግ እና የአምራች ፋብሪካዎችን የጥሬ ምርት ፍላጎት ማርካት፣ ለአገር ውስጥ ገበያ የቁም እንስሳት በ2012 መጨረሻ ቀርቦ ከነበረው በቁጥር 5,539,871 ወደ 17,814,516 ማድረስ፣ የቆዳና ሌጦ ምርት ከነበረበት 28.85 ሚሊየን ወደ 45.063 ሚሊየን ማድረስ፣ የእንስሳት ተዋፅኦን ከ1.05 ሚሊየን ቶን ወደ 2.103 ሚሊየን ቶን ማድረስ፣ በክልላችን የሚገኙ ብራንድ ሊሰጣቸው የተለዩ በሰብል ግብይት 4፣ በእንስሳት 3 ምርቶች ብራንድ እንዲያገኙ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ በክልሉ የሚመረቱ አስገዳጅ (ቡና፣ ሰሊጥ፣ ነጭና ቀይ ቦለቄ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተር) እና አስገዳጅ ባልሆኑ የሰብል ምርቶች ለውጭ ገበያ የተላከ የምርት መጠን በ2012 መጨረሻ ከቀረበው 3.2 ሚሊየን ኩንታል ወደ 6.04 ሚሊየን ኩንታል በማድረስ በ2012 ተገኝቶ የነበረውን 330.4 ሚሊየን ዶላር ወደ 557.4 ሚሊየን ዶላር ማድረስ፣ ለውጭ ገበያ የተላከ ቁም እንስሳት (ዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል) ብዛት በ2012 በጀት ዓመት የነበረውን 11,534 ወደ 22,762 በማድረስ የሚገኘውን ገቢ ከነበረበት 1.16 ሚሊየን ዶላር ወደ 2.46 ሚሊየን ዶላር ማደረስ፣ ለውጭ ገበያ የተላከ የዓሳ ምርት መጠን ከነበረበት 15.1 ቶን ወደ 24.6 ቶን በማድረስ የሚገኘውን ገቢ ከ7,550 ዶላር ወደ 12,175 ዶላር ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡ በተጨማሪም የግብርናው ምርት ግብይት ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዙ የገበያ መረጃ ለግብይት ተዋንያን ተደራሽ ማድረግ እና የተለያዩ ዋና ዋና የገበያ መሠረተ ልማቶችን ቁጥር በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 3,049 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 5,411 በማድረስ በ2012 የነበረውን 376,404 የነጋዴ እና 400,254 የንግድ ፈቃድ ብዛት እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 1,397,132 እና 1,622,830 ለማድረስ ታቅዷል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

ዘርፉ በአሠራር፣ በሰው ኃይል እና በአደረጃጀት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ከዚህም አንፃር ቅንጅታዊ አሠራርን የማጎልበት፣ የሥራ አመራር እና የቴክኖሎጂ አቅምን የመገንባት እና የንግድ አሠራር ምቹነት እና የሪፎርም ሥራዎችን ውጤታማ የማድረግ ሥራዎች ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡ በተጨማሪም የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት የማዘመን፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ የግብይት ሰንሰለት እና የጥራት ቁጥጥር ሬጉላቶሪ ሥራዎች ሪፎርም ይካሄዳሉ፡፡ በዚህም የተሟላ እና የተጠቃለለ የንግድ ፖሊሲ ይቀረጻል፡፡ ህገወጥ ንግድን በተጠናከረ መልኩ ለመቀነስ የተሻሻለ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ አስተማማኝና ዘመናዊ የንግድ መረጃ ሥርዓት ይገነባል፡፡ እንዲሁም ዘመናዊ የምርት ማቆያ፣ የማዘጋጃና የግብይት ማዕከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የምርት ጥራት ደረጃዎች መወሰኛ ስትራቴጂን ቀርፆ ተግባራዊ በማድረግ ምርቶች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ደረጃዎችን የማውጣት እና የመቆጣጠር ሥራ ይሠራል፡፡

ንግድን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎች (Ease of Doing Business) እንዲዘምኑ፣ ዲጂታል መር የሆነ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን እና መሠረታዊ የሆኑ እና ለንግድ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ አስፈላጊው ፋይናንስ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ በሌላ መልኩ ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር የመንግስት ግዥ ለአገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ የሚሰጥበት ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የመረጃ ሥርዓቱ ከአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ጀምሮ ትስስር ያለውና ፍሰቱን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በየደረጃው ያሉ አመራር እና ፈጻሚ አካላት የመረጃ ልውውጥ እና አጠቃቀማቸውን የተሻለ ለማድረግ የሚያስችል ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ እና የተጠናከረ የንግድ መረጃ ማዕከል /Trade Point/ ይቋቋማል፣ እንዲሁም መረጃን በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስና የህትመት ሚዲያዎች በመጠቀም ተደራሽነቱ ይረጋገጣል፡፡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅም እና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመገንባት ወቅታዊ የገበያ መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ዘመናዊ የወጪ እና የገቢ ንግድ መረጃ ቋት በማደራጀት እና በመተንተን ወቅታዊና ታዓማኒ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የንግድ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ሥራ ይሠራል ፡፡

የኢንስፔክሽን ጣቢያዎችን በማስፋፋት የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት የማስጠበቅ ሥራ ይከናወናል፡፡ እንዲሁም በዓለም ገበያ ላይ የክልሉን ብሎም የአገራችን መልካም ገፅታ በማስጠበቅ ፍትሐዊ የገበያ ውድድርን ለማጠናከር በየጊዜው ምርቶች በሕብረተሰቡ ላይ የሚያስከትሉትን ጥቅም እና ጉዳት በማየት ወደ አስገዳጅ ቁጥጥር ጥላ ሥር እንዲገቡ ማድርግ እንዲሁም የህጋዊ ሥነ-ልክ የመለኪያ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ህብረተሰቡ ለከፈለበት ዋጋ ተመጣጣኝ ምርት እና አገልግሎት እንዲያገኝ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ፡፡

ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ጀምሮ ያለውን የዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ የሁሉንም የግብይት ተሣታፊዎች ተሳትፎ ማጐልበት፣ የገበያውን ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ እና የህብረተሰቡን ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቻል ለሁሉም የግብይት ኃይሎች የአቅም ግንባታ ሥራ ይከናወናል፡፡ የግብይት ተዋናዮች በተለይም አርሶ አደሩ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መረጃ እንዲደርሰው በግብይት ሥርዓቱ ሂደት ማነቆ የሚሆኑ አሠራሮችን በጥናት በመለየት እና የመፍትሄ ሀሳቦችን በመተግበር የዘመናዊ ምርት ግብይት ሥርዓት ግንባታው እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ አዳዲስ የግብርና ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ በማስገባት እና ዓመታዊ የግብይት አቅምን በማሣደግ የግብይት ተዋናዩን እርካታ የማሟላት ሥራ ይከናወናል፡፡

የኤሌክትሮኒክ ግብይትን ተግባራዊ በማድረግና የነበሩ አሠራሮችን በማሻሻል የግብይት ተዋንያኑ በምርት ገበያው አሠራር ያላቸውን አመኔታ እና እርካታ ለማሻሻል ጥረት ይደረጋል፡፡ የተመረጡ የገበያ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም የክልሉን ምርት በማስተዋወቅ እና የገበያ ትስስር በመፍጠር ለምርቶቻችን አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያለው ገበያ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ የንግዱን ማህበረሰብ ግንዛቤ የማሳደግ፣ በተከታታይ የማማከር ሥራን የማበልፀግ፣ አዳዲስ የወጪ ምርት ላኪዎች እንዲፈጠሩ የመደገፍ እና የግብይት ተሳትፏቸውን የማሳደግ፣ አዳዲስ ገበያዎችን ሰብሮ የመግባትና በተወሰኑ ገበያዎች ላይ ያለውን ጥገኝነት በሂደት የማስወገድ፣ በነባር እና አዳዲስ ገበያዎች ውስጥ ያለንን እና የሚፈጠረውን የገበያ ድርሻ የማስፋትና የማጠናከር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

### 12.1.7. ባህልና ቱሪዝም

የአማራ ክልል ሰፊ የሆነ ተፈጥሯዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ የቱሪስት መስህብ ዕምቅ ሀብት አለው፡፡ እነዚህን ጥንታዊና ያልተበረዙ ባህላዊና ሀይማኖታዊ የቱሪስት መስህቦች፣ ሳቢና አስደሳች ተራሮችና የውኃ አካላት እንዲሁም ልዩ ልዩ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት በአግባቡ በማልማት እንዲሁም ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ከቱሪዝም የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግና ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ዕድገት ትልቅ አቅም አለው፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የባህል ሀብቶችን በማጥናት፣ በመንከባከብ እና በመጠበቅ ለክልል ልማት አስተዋጽዖ ያላቸውን ማህበራዊ ሀብቶች በአግባቡ ለመጠቀምና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውን ለይቶ ጥቅም ላይ ለማዋል በትኩረት ይሠራል። የክልሉ የቱሪዝም አለኝታዎች በአግባቡ መለየት እና ማልማት፣ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መሠረተ ልማት ማጠናከር እና ተጨማሪ አዳዲስ መሠረተ ልማቶችን መገንባት፣ በክልሉ የሚገኙ አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦችን በማልማትና ነባር መዳረሻዎችን በማጎልበት ብሎም የቱሪዝም ምርቶችን ዓይነት እና መጠን በማስፋፋት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፣ ውጤታማ የገበያ ትስስር፣ ብራንዲንግ እና ፕሮሞሽን ሥራዎችን በማከናወን አዳዲስ የቱሪዝም ገበያዎችን መፍጠር እና የገበያ ድርሻን ማሳደግ፣ ዘርፉን በቴክኖሎጂ፣ በጥናት እና ምርምር በመደገፍ ለአገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

በዘርፉ የተሠማራውን የሰው ኃይል በዕውቀት እና በክህሎት በማብቃት የአገልግሎት አሠጣጡን ማሳለጥ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ ወጥ በሆነ አደረጃጀት እና ማዋቀር የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ ማዘመን እንዲሁም የመንግስትን ሚና መቀነስ እና የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ አጋርነት ማጠናከር ትኩረት ይሰጣቸዋል።

በልማት ዕቅዱ ዘመን በዘርፉ የተስተዋሉ ክፍተቶችን በማረም ለክልሉ ሁለንተናዊ ብልፅግና አስተዋጽዖ ማበርከት በሚያስችል መልኩ ማደራጀት እና መምራት ይጠበቃል። የክልላችን የቱሪዝም ሀብቶችን በባለድርሻ አካላትና በማህበረሰቡ ተሳትፎ ማልማት፣ ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በመፍጠር የቱሪስት አገልግሎቶችን ጥራት ማጎልበት እንዲሁም ጠንካራ የገበያና ፕሮሞሽን ስትራቴጂዎችን በመተግበር አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እና ከዘርፉ የሚገኘውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ማጎልበት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

## ዓላማዎችና ግቦች

ቅንጅታዊ አሠራርን በሁለንተናዊ መልኩ በማጠናከርና የማህበረሰብ ተሳትፎን በማጎልበት የባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሀገራችን ዘላቂ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ እምርታ የበኩሉን ትርጉም ያለው አስተዋጽዖ እንዲያበረክት በማድረግ የባህል ኢንዱስትሪዎችን ልማትና የገበያ ትስስርን ማሳደግ፣ የባህላዊ ቅርሶችን ጥበቃና ልማት ማሳደግ፣ የቱሪዝም ገበያ ሥርዓትን ማሻሻልና ውጤቱን ማሳደግ፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በዓይነት እና በመጠን ደረጃ ማሳደግ፣ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ማሳደግ እንዲሁም የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ የሚሉ ዓላማዎችን መሠረት በማድረግ በዕቅድ ዘመኑ የሚከተሉት ግቦች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። የቋሚ ቅርሶችን የጉዳት መጠን የመለየት ሥራ መሥራት፣ በጥገና ላይ የሚገኙ 20 ቋሚ ቅርሶችን ጥገና ማጠናቀቅና 5,452 ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የመጠገን ሥራ መሥራት፣ 2 የፍርስራሽ ቤተ-መንግስት ህንጻዎችንና ቅርሶችን መልሶ መግንባት፣ ለቅርስ ጥገናና እንክብካቤ ግብዓት የሚሆኑ የአገር በቀል ዕጽዋትን ማልማት፣ ቅርስ ለሚጠግኑ ባለድርሻ አካላት በየሙያ ዘርፉ የሙያ ብቃት ዕውቅና በመስጠት ወደ ሥራ ማስገባት፣ በከተሞች መሪ ፕላንና የከተማ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሲዘጋጅና ሲከለስ የቅርሶችን ልማትና አስተዳደር ያካተተ እንዲሆን ክትትል ማድረግ፣ የአርኪዎሎጅ እና ፓሊዮንቶሎጂ መካነ ቅርሶች የወሰን ክለላና የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ እንዲኖራቸው ማድረግ እና የወሰን ክለላ የሚሠራላቸውን ቋሚ ቅርሶች ማሰራት፣ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን መመዝገብ፣ በዩኔስኮ የሚመዘገቡ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን መረጃ ማደራጀት እንዲሁም አዲስ በተገነቡ ሙዚየሞች ቅርሶችን በማሰባሰብ በዘላቂነት የማደራጀት ሥራ ይሠራል።

የክልሉ የባህል እና ቋንቋዎች ልማትና አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የክልሉን የሥነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ሥራዎችን ማጎልበት፣ የዕደ-ጥበብ ምርትን ማስፋፋት እና ገበያን ማጎልበት፣ በባህል ዕሴቶች ልማት እና በማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑ 20 አገር በቀል ዕውቀቶችን እና ባህላዊ ዕሴቶችን ማልማት እና መጠበቅ፣ የዕውቀት

አስተዳደርና መረጃ ማህበረሰብ የመፍጠሩን ሥራ ማጎልበት በዚህም 130 የህዝብ ቤተመጻሕፍትን በቴክኖሎጂ፣ በቁሳቁስ እና በአደረጃጀት ማጠናከር፣ 1,000,000 መጻሕፍትን በድጋፍና በግዥ በማሰባሰብ ለህዝብ ቤተ መጻሕፍት ተደራሽ ማድረግ፣ መጤ ባህሎችን፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን፣ አመለካከቶችና አሠራሮችን ለመቀነስ 9 ሚሊየን የህብረተሰብ ክፍሎችን ግንዘቢያቸውን በማሳደግ የሚደርሰውን ጉዳት በ80 በመቶ መቀነስ፣ በክልሉ ጠቃሚ ባህላዊ ዕሴቶች፣ አገር በቀል እውቀቶች እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ 320 ጥናቶችን ማካሄድ እንዲሁም በባህል ኢንዱስትሪ ለተሰማሩ 500 ተቋማት በክልሉ እና ከክልሉ ውጭ የገበያ ትስስርን የመፍጠር ሥራ ይሠራል፡፡

የቱሪዝም መሠረተ ልማት አቅርቦት በማስፋፋት ለ400 የመስህብ ሀብቶች የተለያዩ የመሠረተ ልማት አውታሮች መዘርጋት፣ በነባርና አዲስ መዳረሻዎች 200 የቱሪስት ዕረፍት ማድረጊያ መጠለያዎችን /break stop shelters/ መገንባት፣ የገጸ-ምድር ማስዋብ /landscape leveling/ የተሰራላቸውን የመስህብ ሀብቶች ከ3 ወደ 293 ማድረስ፣ በ5 ኃይቆች ዳር ለዳር፣ በ2 ጥብቅ ሥፍራዎች እና 3 ብሄራዊ ፓርኮች የ500 ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ እግረኛ መንገድ /walk way/ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የጢስ ዓባይ ፏፏቴን ከንክኪና ከልማት ተጽዕኖዎች ነፃ በማድረግ ወደ ነበረበት ውበቱ እንዲመለስ ማድረግ፣ በዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎች 4 የመዳረሻ አስተዳደር ድርጅት /Destination Management Organization/ የማቋቋም እና ወደ ሥራ የማስገባት፣ የማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም በሚተገበርባቸው ዋና ዋና መዳረሻዎች እና መስህብ ሥፍራዎች መሠረት በማደረግ 10 የማህበረሰብ አቀፍ ቱሪዝም አስተዳዳሪ ድርጅቶች /Administrative Organization/ የማቋቋም፣ 100 አዳዲስ የማህበረሰብ አቀፍ እና ኢኮ-ቱሪዝም ማህበራት የማደራጀት እና 45 ነባሮችን የማጠናከር ሥራ ይሠራል፡፡ ከፀጥታ እና መሰል ጉዳዮች አኳያ እና ከሚመለከታቸው የአስተዳደርና የፀጥታ አካላት እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት ይሠራል፡፡ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ከ17 ባለድርሻና አጋር አካላት የጋራ መግባቢያ የሥምምነት ሠነድ በመፈራረም 28 የቅንጅት ሥራዎች እና አፈጻጸሙን በየጊዜው የመገምገም ሥራ ይከናወናል፡፡

አዲስ የሚለሙ የተፈጥሮ ቱሪዝም ምርቶችን ለማስፋፋት በክልሉ የሚገኙ 10 የፍል-ውኃ ምርቶች፣ 2 ወንዞች፣ 5 ሀይቆች፣ 3 ፏፏቴዎች፣ 8 ብሄራዊ ፓርኮች፣ 3 ጥብቅ ሥፍራዎች፣ 5 ልዩ መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያላቸው ሥፍራዎች በማልማት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣ አዲስ የሚለሙ ባህላዊ የቱሪዝም ምርቶችን ለማስፋፋት በክልሉ 4 ጦርነት የተካሄድባቸው ጥንታዊ ሥፍራዎችን /የጦርነት አውድማዎች/፣ 6 ጥንታዊ ገዳማትን፣ አብያተ ክርስቲያናትን እና መስጅዶችን፣ 20 ኃይማኖታዊ የጠበል ሥፍራዎችን፣ 3 ጥንታዊ አብያተ መንግስታትን፣ 50 ባህላዊና ኃይማኖታዊ ሁነቶችን፣ 2 አዲስ ታሪካዊ ቲም-ፓርኮችን በማልማት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣ ዋና ዋና የቱሪስት መዳረሻዎችን መሠረት በማድረግ 10 አዳዲስ የጉብኝት መስመሮችን በመለየት ወደ ቱሪዝም ገበያ ማስገባት፣ የክልሉን የቱሪዝም ሀብቶች በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የኤሌክትሮኒክስ እና ህትመት ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

የውጭ አገር ቱሪስት ፍሰትን በየዓመቱ በ50 በመቶ በማሳደግ በ2013 በጀት ዓመት የነበረውን 29,594 የቱሪስት ቁጥር ወደ 907,033 /የሴቶች ድርሻ 50 በመቶ/ የሚገኘውንም ገቢ ወደ 1,553,203,637 ለማሳደግ እና የአገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰትን በየዓመቱ በ20 በመቶ በማሳደግ የቱሪስት ቁጥርን በ2013 በጀት ዓመት ከነበረበት 12.37 ሚሊየን ወደ 63.83 ሚሊየን /የሴቶች ድርሻ 50 በመቶ/ በማሳደግ የሚገኘውን ገቢ ወደ 9,638,055,419 ከፍ ከማድረግ አንፃር በውጭ አገር ቱሪስቶች የሚጎበኙ የቱሪስት መስህብ ሀብቶችን/ምርቶችን ወደ 100 ከፍ የማድረግ፣ የአካባቢውን ህብረተሰብ ከቱሪዝም ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር በቱሪዝም ማህበር የተደራጁ 500 የአካባቢ አስጎብኝዎች ዓመታዊ አማካይ ገቢ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ብር 13,500 በ2022 በጀት ዓመት ወደ ብር 17,220 እና በየዞኑ የሚገኙ የኢኮቱሪዝም ማህበራት አማካይ ዓመታዊ ገቢን ከብር 250,000 ወደ ብር 335,023 የማሳደግ፣ በዝቅተኛ የቱሪስት ፍሰት ወቅት የቅናሽ ዋጋ አገልግሎት ከ2,000 የቱሪስት አጓጓዥ ድርጅቶች፣ ከ45 የመስህብ ሀብት ባለይዞታዎች እና ከ500 የመስተንግዶ ድርጅቶች ጋር ሥምምነት በመፍጠር ተግባራዊ የማድረግ፣ የክልሉን ገጽታ በመገንባት ልዩ ልዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት የመስህብ ሀብቶችን እና የኢንቨስትመንት አማራጮችን

በማስተዋወቅ 250,000 /50 በመቶ የሴቶች ድርሻ/ ኢትዮ ያውያን እና ዲያስፖራዎች ወደ ክልሉ የመሳብ ሥራዎች ይሠራሉ።

በቱሪዝም፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታዎች ዙሪያ 20,000 የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ5 ሚሊየን/50 በመቶ የሴቶች ድርሻ/ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት መስጠት፣ በልዩ ልዩ ተቋማት የሚቋቋሙ የአገርህን እወቅ ክበባትንና የጉዞ ማህበራትን ቁጥር ወደ 15,000 በማድረስ 2 ሚሊየን /50 በመቶ የሴቶች ድርሻ/ የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ጉብኝት ሥርዓት የማስገባት፣ በቱሪስት መዳረሻዎች የውጭ አገር ቱሪስቶች አማካይ የቆይታ ጊዜን ከ1.5 ቀን ወደ 4 ቀን እንዲሁም የአገር ውስጥ ቱሪስቶች አማካይ የቆይታ ጊዜን ከ 2.3 ቀን ወደ 6 ቀን የማድረስ ሥራዎች ይከናወናሉ።

የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶች መጠን፣ ዓይነት እና ደረጃ ማሻሻል፣ የህዝብ ግንኙነትና የተግባቦት አሠራርን ማሳደግ፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ የባህልና ቱሪዝም መረጃ ሀብቶች አያያዝ ሥርዓትን መገንባት እና በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የባለድርሻና አጋር አካላት ቅንጅታዊ አሠራርን ማሳደግ፣ በየዓመቱ ግንባታቸውን አጠናቀው ወደ አገልግሎት የሚገቡ የሆቴልና ቱሪዝም ኢንቨስትመንቶች ብዛትን 1,430 ማድረስ፣ ምርትና አገልግሎታቸውን ያሻሻሉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን 66,770 ማድረስ፣ የኮከብ ደረጃ የሚኖራቸውን አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን 200 ማድረስ፣ ለ19,970 ተቋማትና ግለሰቦች የሙያ እና የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ መስጠት፣ በሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎቶች ዘርፍ የተሰማራውን የሰው ኃይል አቅም ለመገንባት 22,500 ሙያተኞች የአጭር ጊዜ የሥራ ላይ ሥልጠና (50 በመቶ የሴቶች ድርሻ) መስጠት፣ በጦርነቱ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 416 የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ተግባራት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር የመሥራት እንቅቃሴዎች ይከናወናሉ።

በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ፣ በአርኪዎሎጅና ፓሊኦንቶሎጅ የጥናትና ምርምር ሥራ፣ በቅርስ እንክብካቤና ጥገና፣ በሙዚየም ግንባታ፣ በቱሪዝም ልማት ዘርፍ የማህበረሰብ አቀፍ እና ኢኮቱሪዝም ማህበራት በማቋቋም፣ በባህል ተቋማት ግንባታዎች፣ በዕደ-ጥበብ ሙያዎች፣ በኪነ-ጥበብ ኢንተርፕራይዞች ቋሚ 500,000 እና ጊዜያዊ 600,000 በድምሩ ለ1,100,000 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚሉ ግቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ። የዘርፉን የተቋማት ግንባታ እና የሰው ሀብት ልማት እንዲሁም የዘርፉን የህግ እና የአሠራር ማዕቀፎች ማሳደግ፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች የማጎልበት እንዲሁም የዘርፉን የሀብት ምንጮች ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የአሥር ዓመቱን የዘርፍ ዕቅድ ለማሳካት ፖሊሲዎችን ወቅታዊ ማድረግ፣ የፖሊሲ ማስፈፀሚያ የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ ማድረግ፣ የባህልና የቋንቋ ጥናት ማዕከላትን በማቋቋም የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃና ልማት፣ የባህል ልማት፣ የመዳረሻና የቱሪዝም ምርት ልማትና አስተዳደር ስትራቴጂ ማውጣት፣ የቱሪዝም የሰው ኃብት ልማት፣ የገበያና ፕሮሞሽን፣ የቱሪዝም አገልግሎቶች ልህቀት፣ የቱሪስት መረጃ ሥርጭት፣ የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ በቱሪዝም ልማት የመንግስትና የግል ዘርፍ አጋርነትን እና ፍትሐዊ የቱሪዝም ንግድን ማረጋገጥ እንዲሁም የቱሪስት ደህንነትና ጥበቃ ማቋቋም የዕቅዱ መተግበሪያ መንገዶች ይሆናሉ።

በዘርፉ የሚታዩ የመረጃ ክፍተቶች እና በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ለባህልና ቱሪዝም መስህቦች የሚሰጥ ትኩረት ማነስን ለማሻሻል ተከታታይነት እና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሥራት በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመገናኛ ብዙሃን፣ የትምህርት እና የምርምር ተቋማትን በመጠቀም ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በመጠን እና በጥራት እንዲያቀርቡ የድጋፍና የክትትል ሥራዎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ በክልሉ ያለውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን መሠረተ ልማቶችን በመጠቀም የዘርፉ መረጃዎች በዘመናዊ መንገድ እንዲደራጁ በማድረግ ለጥናት እና ምርምር ሥራዎች ማዋል፣ በስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራር መፍጠር፣ በየደረጃው በተቋም ደረጃ የስትራቴጂክ ትኩረት መስኮችን አፈጻጸም የሥራ አመራር ካውንስሉ በባለቤትነት እንዲመራው መሰየም እና በየደረጃው ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚሰሩ ሥራዎችን የሚመራ ዓብይ ኮሚቴ ማቋቋም ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

## 12.2. መሠረተ ልማት ዘርፍ

እንደ መንገድ፣ ቤቶች ልማት፣ የውኃና ኢነርጂ መሰል መሠረተ ልማቶችን ጥራት ባለው መልኩ በመገንባት ተደራሽነትን ማሳደግ በክፍላተ ኢኮኖሚዎች እና በገጠርና በከተማ መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር እንዲሁም የቢዝነስ እንቅስቃሴ ወጪን በመቀነስ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ኢንቨስትመንት እንዲሳለጥ በማድረግ ለሚጠበቀው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽዖ ቁልፍ እና የማይተካ ነው፡፡ የኢነርጂው ዘርፍ ከግብርና መር ኢኮኖሚ ከተማን መሠረት ወደ አደረገ የኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገውን መዋቅራዊ ለውጥ በማቀጣጠል ረገድ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በተለይ እንደ ክልል ከውኃ ኃይል እንዲሁም ከፀሐይ ኃይል ትልቅ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ያለ በመሆኑ ይህን ዕምቅ አቅም መጠቀም ቢቻል የክልሉን የኃይል ፍላጎት ክፍተት መሸፈን የሚችል እንደሆነ ይታወቃል፡፡

### 12.2.1. መንገድ

### የትኩረት አቅጣጫዎች

**የማስፈፀም አቅምን ማሳደግ**:- የመንገድና ትራንስፖርት መሠረተ ልማት አቅርቦት እና ሌሎች በርካታ አገልግሎቶች በተሟላ ሁኔታ ማቅረብ እና የህብረተሰቡን እርካታ ማረጋገጥ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አደረጃጀት እና አሠራር በመዘርጋት ሥራዎችን በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችል የሰው ኃይል አቅም መፍጠር፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎችን በመጠቀም እና የግሉን ዘርፍ የመሠረተ ልማት ግንባታና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ በንቃት ማሳተፍ፣ በየደረጃው የሚገኘው የተቋሙ አመራር እና ፈፃሚ በዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡ የተለጠጡ ዓላማዎች እና ግቦችን ማሳካት የሚያስችል ቁመናን እንዲይዝ በክፍተት ላይ የተመሠረተ እና ተከታታይ የሆነ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠና በመስጠት ለማስፈጸም አቅም ግንባታ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን የቢሮውን አሠራር ለማሳለጥ እንዲሁም አገልግሎቱን ለማቀላጠፍ እና ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ዝርጋታ እና ትግበራ ሥራዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ በተቋሙ አደረጃጀት ሁለት ትላልቅ የሥራ ዘርፎች አንድ ላይ የተደራጁ በመሆኑ ሥራውን በተገቢው ሁኔታ ለመምራት እንዲቻል ሁለቱም ዘርፎች ለየብቻቸው እንዲደራጁ ትኩረት ይሰጣል፡፡

**የመንገድ እና የትራንስፖርት የመሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሻሻል**:- በአጠቃላይ የመንገድና ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ማለትም መንገዶች፣ የመንገደኛ ማስተናገጃ ተርሚናሎች፣ ዴፖዎች እንዲሁም የአውቶቡስ ማቆሚያዎች (Bus Stops) ስታንዳርዳቸውን ጠብቀው እንዲገነቡ በማድረግ የመንገድና ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ሀብቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ሕጻናት እና ነፍሰ ጡሮች ወ.ዘ.ተ) ምቹ እና እኩል ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን መሠረተ ልማቶች በአግባቡ በማስተዳደር እና ደህንነታቸው በተከታታይ ጥገና በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የመንገድ እና ሌሎች የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ድርሻ እንዲያድግ ልዩ ትኩረት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ በተለይም በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ለብዙሃን ትራንስፖርት እና ለሞተር አልባ ትራንስፖርት (Active Mobility) ልዩ ትኩረት የሚሰጡ

መንገዶች በመስቀለኛ እና ዋና ዋና መንገዶች ላይ እንዲኖሩ በማድረግ የተሽከርካሪ ፍሰቱ በማይዋዥቅ ሁኔታ እንዲቀጥል እና ደህንነቱ በዘላቂነት የተጠበቀ የተሽከርካሪ እና የእግረኛ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማድረግ፣

**ደህንነቱ የተጠበቀ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፡-** የሚሠጡት አገልግሎቶች በዋነኛነት ደህንነትን፣ ፍትሐዊ ተደራሽነትን፣ ጥራትን እና ቅልጥፍናን፣ የሥራ ውጤታማነትን ያረጋገጡ እንዲሆኑና ከሌብነት በጸዳ መልኩ እንዲፈፀሙ ማድረግ። የመንገድ ልማት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት በማረጋገጥ እና ሁሉን አቀፍ የመንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም (URRAP) አጠናክሮ በማስቀጠል የብዙሃን ትራንስፖርት አገልግሎቱ የግል ባለሀብቱን ባሳተፈ መልኩ እንዲስፋፋ እና ተደራሽ ማደረግ፣

**የግል ባለሀብቱን እና የህብረተሰቡ ተሳትፎንና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፡-** የህዝቡ፣ የባለሀብቱና የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በመሆኑም የቢሮውን የልማት አቅሞች ተቀናጅቶ መሥራትና በየደረጃው የሚገጥሙ ችግሮችን የጋራ መፍትሄ እያስቀመጡ መሄድ፣ አገልግሎት አሰጣጥ የአንድ ተቋም ኃላፊነት ብቻ ባለመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የጋራ ሥምምነት ላይ በመድረስ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ባለድርሻ አካላት በለውጥ ሂደቱ ላይ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማድረግና በእኔነት ስሜት እንዲሰሩ ለማስቻል ትስስሩን በመፍጠር ሁሉንም የልማት አቅሞች አቀናጅቶና አስተባብሮ መጠቀም፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ እና ያለውን ሰፊ የሰው ጉልበት የሚጠቀሙ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በማድረግ በርካታ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል። በተጨማሪም የህብረተሰቡን ተሳትፎ በተለይም ሴቶችና ወጣቶች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ብቃታቸውን በማሳደግ በተቋሙ የሚኖራቸውን ሚና በተገቢው መጠን እንዲጫወቱና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት የሚሰጣቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዓላማ የመንገድ መሠረተ ልማት ፍትሐዊነትንና ተደራሽነትን ማሳደግ እና የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን መገንባት ሲሆን ይህንን ለማሳካት የተቀመጡ ግቦችም የክልሉን አጠቃላይ የመንገድ ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው 27,962.46 ኪ.ሜ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 51,665.06 ኪ.ሜ ማሳደግ፣ እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ 1,471 ኪሎ ሜትር የነባር መንገዶች ደረጃን ማሻሻል፣ በመንገድ ተደራሽነት ቀበሌን ከቀበሌ እንዲሁም ከወረዳና ከዋና መንገድ በማገናኘት የቀበሌ ሽፋንን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 2,479 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 3,383 ቀበሌ ማድረስ፣ የመደበኛና የወቅታዊ ጥገና ሽፋን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,544.52 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 6,303 ኪሎ ሜትር ማሳደግ፣ በዩራፕ መደበኛ እና ወቅታዊ የመንገድ ጥገና ሽፋንን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 5,520 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 70,000 ኪሎ ሜትር ማሳደግ፣ የክልል ጠጠር መንገድ ግንባታን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 5,084 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 7,690.19 ኪሎ ሜትር ማድረስ፣ እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ 4,095 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ መገንባት እና 1,894 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ መጠገን፣ የወረዳ ገጠር መንገድ ግንባታን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 12,055.96 ኪሎ ሜትር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 19,705.96 ኪሎ ሜትር ማድረስ፣ እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ 10 ከፍተኛ ድልድዮችን መገንባት፣ በዩራፕ ከ2004 እስከ 2009 በጀት ዓመት የታለፉትን 370 ድልድዮችን ሠርቶ ማጠናቀቅና አዲስ 300 ድልድዮችን መገንባት፣እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ በ5 መስመሮች 873 ኪሎ ሜትር የክፍያ የፍጥነት መንገድ እንዲገነባ ማድረግ፣ በዘርፉ ከሚሰጡ አገልግሎቶች በዓመት ይሰበሰብ ከነበረው ገቢ ብር 13 ሚሊየን በ2022 በጀት ዓመት ወደ ብር 143,705,730 ማሳደግ፣ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ እንዲሁም ውጤታማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ አሠራሩን በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ የሚሉት ናቸው።

### የማስፈፀሚያ ሥልቶች

ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና ከአቅም ማጎልበቻ ማሠልጠኛ ተቋማት ጋር በትብብር መሥራት፣ የመንግስት እና የግል ባለሀብት አጋርነትን ማሳደግ፣ የፖሊሲ እና የህግ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ማፈላለግ፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ተዋናዮች (ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ ኦፕሬተሮች ወዘተ) አቅምና ተሳትፎ ማሳደግ፣ የትራንስፖርት ዘርፉን በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ፣ የተቋሙን ተልዕኮ ለማስፈጸም የሚያስችል መዋቅራዊ አደረጃጀት እና አሠራር መዘርጋት እና መተግበር፣ የሴቶችን የአመራርነት ድርሻ አሁን ካለበት 20 በመቶ ወደ 35 በመቶ ማሳደግ፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ ተጋላጭነትን መቀነስ እና ድጋፍ ማድረግ፣ በቢሮው የሚዘጋጁ መመሪያዎች፣ ዕቅዶች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች የሴቶችን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን ጉዳይ ያካተቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ልዩ ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከለ የመንገድ አገልግሎት አሰጣጥን ማሳደግ የሚሉት ናቸው።

## 12.2.2. ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሠራር በመዘርጋት የሚሰጠውን አገልግሎት ማሻሻል፣ ችግር ፈች የሆነ የክትትልና ድጋፍ ሥራ መሥራት፣ በሴክተሩ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት፣ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለው አሠራር መዘርጋት፣ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነትን መፍታት እና የቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### ዓላማዎችና ግቦች

የትራንስፖርት መሠረተ ልማትን የተቀናጀ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የህዝብ ትራንስፖርት መናኻሪያዎችን ከተደረሰበት 231 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 312 ማሳደግ፣ እስከ 2022 በጀት ዓመት ድረስ 24 የጭነት ትራንስፖርት ተርሚናሎች እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ ደረቅ ወደቦች እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የከተማ ትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች በመገንባት በ2022 በጀት ዓመት 40 ማድረስ፣ በክልሉ የሚገኙትን የትራፊክ ኮምፕሌክስ በ2014 በጀት ዓመት ካለበት 3 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 13 ማሳደግ፣ እስከ 2022 በጀት ዓመት 5 አዳዲስ የአውሮፕላን ማረፊያዎችና የመንገደኞች ማስተናኛ ተርሚናሎች እንዲገነቡ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ 2 የውኃ ትራንስፖርት ወደብ መሠረተ-ልማቶችን መገንባት የሚሉት ግቦች ተጥለዋል።

የትራንስፖርት አገልግሎትን የተቀናጀ፣ ፍትሐዊና ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የትራንስፖርት አገልግሎቱ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ የህዝብ፣ የከተማ፣ የጭነትና የውኃ ትራንስፖርት አገልግሎት ማስፋፋትና ተደራሽነትን ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተቀምጠዋል። በሌላ በኩል ብቃቱ የተረጋገጠ ተሽከርካሪ እና አሽከርካሪ በማፍራት በክልሉ እየደረሰ ያለውን የትራፊክ አደጋ በ30 በመቶ ከመቀነስ አንፃር የአሽከርካሪዎችን ብቃት ማረጋገጥ፣ በተሽከርካሪ የብቃት ማነስ የሚደርሰውን ትራፊክ አደጋ በ10 ሺህ ተሽከርካሪ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 106 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10 ዝቅ ማድረግ፣ በትራፊክ አደጋ ምክንያት የሚደርሰውን የሰው ሞት በ10 ሺህ ተሽከርካሪ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 106 በ2022 በጀት ዓመት ወደ 10 ዝቅ ለማድረግ እንዲሁም የውስጥ እና የውጭ ኢንስፔክሽን በማካሄድ ህገወጥ አሠራርን ለመቀነስ ታቅዷል። የሎጅስቲክስ አገልግሎቱን ቀልጣፋና አስተማማኝ ከማድረግ አንፃር ደግሞ የበለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን አካቶ በማቀድ ማጎልበት፣ የበለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ትኩረትና ግንዛቤ ማሳደግ፣ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መፍጠር፣ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣ በአገልግሎት መስጫ

ተቋማት የስነ ሕዝብ ጉዳዮችን በአካቶነት መፈጸም፣ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነውን Covid-19 መከላከል እንዲሁም ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ይሠራል።

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

በሴክተሩ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ፣በቴክኖሎጂ የተደገፈ አሠራር በመዘርጋት ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ ለሴክተሩ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እና መርሃ ግብሮች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ በመንግስት እና የግል ባለሀብቱን በማሳተፍ የትራንስፖርት መሠረተ ልማት እና የሎጂስቲክስ ማዕከላት እንዲገነቡ ማድረግ፣ የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የትራንስፖርት ዘርፍ ስትራቴጂን መተግበር እንዲሁም የሞተር አልባ ትራንስፖርት ስትራቴጂ መተግበር ናቸው።

### 12.2.3. ውኃ እና ኢነርጅ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የንጹህ መጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ማዳረስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማስፋፋት፣ የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማትን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማስቻል፣ የታዳሽ ኃይል የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አማራጭን ለገጠር መጠጥ ውኃ ተቋማት እንደ አንድ የኃይል ምንጭ መጠቀም፣ በተጨማሪም በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት ለሚደርስባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ንጹህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ድጋፍ ሥራን በትኩረት ማከናወን እንዲሁም ልዩ ድጋፍ በሚሹ አካባቢዎች ወጥነትና ዘላቂነት ያለውን ድጋፍ ማድረግ በቀጣይ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ።

## ዓላማዎችና ግቦች

የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን በማስፋፋት የአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ፣ የንፁህ፣ አስተማማኝና በቂ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋኑን በ2022 በጀት ዓመት 90 በመቶ በማድረስ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የውኃ ጥራት ደረጃ ማስጠበቂያ መንገዶችን ተግባራዊ በማድረግ የመጠጥ ውኃ ጥራትን ማረጋገጥ፣ የዋሽ (WASH) ዘመናዊ መረጃ አያያዝና አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት፣ በዘርፉ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ አለመኖሩን ማረጋገጥና የውኃ ሀብት አስተዳደርን ማስፋፋትና ማጠናከር ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው። የክልሉን የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በዕተዕ-2 መጨረሻ ከተደረሰበት 66.82 በመቶ ላይ 23.18 በመቶ በመጨመር ወደ 90 በመቶ ማድረስ፣ በዚህም በገጠር የሚኖሩ ዜጎች በ1 ኪሎ ሜትር ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው ለአነስተኛ ተቋማትና በ0.5 ኪሎ ሜትር ርቀት 25 ሊትር በቀን በሰው በባለመስመር ተቋም በማቅረብ በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ ከተደረሰበት 67.57 በመቶ የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን ላይ 22.43 በመቶ በመጨመር በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 90 በመቶ ሽፋን ማድረስ፣ የከተማ ነዋሪዎች በ0.25 ኪ.ሜ ርቀት ከ40-80 ሊትር በቀን በሰው እንደየከተማ ምድባቸው በማቅረብ የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋንን በዕተዕ-2 መጨረሻ ከተደረሰበት 63.7 በመቶ በመነሳትና የ26.3 በመቶ ዕድገት በመጨመር 90 በመቶ ሽፋን ማድረስ፣ እንዲሁም በከተሞች የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድና ንጽህና አጠባበቅ (liquid west management and sanitation) ሥርዓት በመዘርጋት 20.69 በመቶ የክልሉን ከተሞች ወይም 60.4 በመቶ የከተማ ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ ይሠራል ።

የተገልጋይን ፍላጎት ያማከለ ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የውኃ ሀብት መረጃ መሰብሰብ ማደራጀትና መተንተን፣ የክልሉን የውኃ ሀብት ባግባቡ ማስተዳደር እንዲሁም የተገነቡ የመጠጥ ውኃ ተቋማት የሚያስተዳደሩ አካላትን

በማቋቋም እና በአሠራር በመደገፍ የክልሉ ህዝብ በውኃ ሀብቱ የላቀ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ የውኃ ተቋማትን የብልሽት መጠን ከ12.89 በመቶ ወደ 7 በመቶ መቀነስ፣ በ450 ባለመስመር የገጠር ውኃ ተቋማት (RPS) የገጠር ንፁህ መጠጥ ውኃ ተጠቃሚዎችን ማህበር በማቋቋም 650 የገጠር መጠጥ ውኃ አገልግሎት ማደራጀት፣ በከተማ ያለውን የውኃ ብክነትን ከ22.85 በመቶ ወደ 15 በመቶ በመቀነስ ንጽህናውን የጠበቀ የመጠጥ ውኃ ለህብረተሰቡ ማዳረስ፣ በውኃ ተቋማት ጥገና በጥሬ ገንዘብ፣ በቁሳቁስና በጉልበት በድምሩ 196.69 ሚሊየን ብር በማህበረሰቡ ተሳትፎ እንዲሸፈን ማድረግ፣ የከተማ ውኃ አገልግሎቶች ተገቢውን የውኃ ታሪፍ እንዲያወጡ ድጋፍ በማድረግ 162 ሚሊየን ብር የኢንቨስትመንት ወጪ እንዲመልሱ ማድረግ፣ የክልሉን 50 በመቶ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃ ሀብት ክምችት በማጥናትና በማስጠናት ለክልሉ ህዝብ ልማት አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፣ በውኃው ዘርፍ ለሚሰሩ ለ8,631 አካላት አዲስ የሙያ ፈቃድ መስጠትና 11,989 የሙያ ፈቃዶችን ማደስ እንዲሁም የክልሉን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውኃ ሀብት መረጃ ለተጠቃሚው ማቅረብ በአሥር በዓመቱ ዕቅድ ተፈጻሚ የሚሆኑ ግቦች ናቸው፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የውኃ ጥራት ማረጋገጫ ፕሮቶኮሎችንና ደንቦችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ግንባታ ማካሄድ፣ የውኃ ጥራት መመርመሪያ ቁሳቁሶችንና ኬሚካሎችን ማቅረብ፣ የውኃ መገኛ አካባቢዎችን ከጎርፍ መከላከልና ከንክኪ ነፃ ማድረግ፣ የዋሽ ኮሚቴዎችን ማደራጀት፣ የከተሞች ውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ቦርድ ማደራጀት፣ ለፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ምህንድስና ጥናትና ዲዛይን መሥራትና የገጠርና የከተማ ማህበረሰብ ስለሳኒቴሽን ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፣ ከህብረተሰቡ እና ከፈጻሚዎች ጋር በየዓመቱ በዕቅዶች ላይ መግባባት ላይ መድረስ፣ በየዓመቱ የሚታቀዱ ዕቅዶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ሴቶችንና ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ ሥራዎች የመልካም አስተዳደር ጥያቄን የሚመልሱ እና ፍትሐዊነትን መሠረት እንዲያደርጉ ማድረግ፣ መንግስታዊ ከሆኑና መንግስታዊ ካልሆኑ የልማት ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ተግባራትን በጋራ ተናቦና ድግግሞሽን አስወግዶ በቅንጅት እንዲከናወኑ ማድረግ፣

በመጠጥ ውኃ ዘርፍ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መንስኤዎችን ከወዲሁ መለየትና በውኃ ተቋማት ግንባታ ጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዲጠናቀቁ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መከተል፣ እንደ ውኃ መገኛው ሁኔታ በማየት አነስተኛ ቴክኖሎጂ /በቀላሉ ውኃ በሰው ተቆፍሮ የሚገኝበት/ ለመጠቀም በሚያስችሉ ቦታዎች ህብረተሰቡ ሙሉ ኃላፊነት ወስዶ ጉልበቱን በመጠቀም እንዲሠራ ማስቻል፣

በሁሉም የግንባታ ሥራዎች ላይ ህብረተሰቡ የጉልበትና የማቴሪያል አስተዋጽፆ እንዲኖረው በማድረግ አቅም በፈቀደው ሁሉ የገንዘብ አስተዋጽፆ እንዲያደርግ ማስቻል፣ ከዕርዳታና ብድር በመጠጥ ውኃ ግንባታ በዋሽ (WASH) ኘሮግራም የተገኘን ሀብት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በጐላ መንገድ ማስገኘት በሚያስችል ሥልት በባለመስመር የቀበሌ አገናኝ የውኃ ተቋማት ቴክኖሎጂ በተመጣጣኝ እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ ወጪ እንዲሠራበት ማድረግ፣ ሁሉም የመጠጥ ውኃ ግንባታዎች ከመገንባታቸው በፊት ሊኖር በሚችለው የኦፐሬሽንና ጥገና ወጪ ላይ ውይይት በማድረግ በተጠቃሚው ህብረተሰብ እንደሚሸፈን መተማመን ደረጃ ላይ መድረስ፣ በረሀማ የገጠር አካባቢዎች የንጹህ መጠጥ ውኃ አቅርቦታቸው አነስተኛ በሆነባቸውና የንፁህ መጠጥ ውኃ ያልደረሳቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ አማራጭ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ የከተማ መጠጥ ውኃ ማስፋፊያ ሥራዎችን በከተማ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽህፈት ቤቶች እንዲሰራ ማድረግ፣ በተጨማሪም የውኃ መገኛ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ በክልል ደረጃ በጀት ተይዞላቸው የጥናትና ዲዛይን ሥራ መሥራት ዋና ዋና የዕቅዱ የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

## ኢነርጂ ልማት

### የትኩረት አቅጣጫዎች

**ፍትሐዊ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን ተደራሽነት ማረጋገጥ፡-** በልማት ዕቅዱ ዘመን አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች ሽፋን ባልተዳረሰባቸው የገጠርና ከተማ አካባቢዎች ለማዳረስ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል። ለዚህም በዘርፉ የሚስተዋሉ ማነቆዎችን በአግባቡ በመለየት እና በመፍታት ያሉ ዕምቅ አቅሞች በሙሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል። በተጨማሪም በየደረጃው ያሉ አደረጃጀቶችን የበለጠ በማጠናከር እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ በሰፊው በማረጋገጥ ፍትሐዊና ጥራት ያለው አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን ተደራሽነት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ለማረጋገጥ በትኩረት ይሠራል።

**የንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትንና አማራጭ የፋይናንስ ምንጭን ማሳደግ፡-** ወጪ ሊቀንሱና ሊቆጥቡ የሚችሉ ንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል። በተጨማሪም የኢነርጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ትልቅ የፋይናንስ ፍላጎት የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋምና ጠንካራ የኢነርጂ ዘርፍ ኢንቨስትመንት እንዲፈጠር ማድረግ የግድ ነው። በመሆኑም በቀጣይ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን በመጠቀም ዘርፉ የሚፈልገውን ኢንቨስትመንት ለመሳብ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በኢነርጂ ዘርፍ የግሉ ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ የፖሊሲ እና የአሠራር ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የመንግስትና የግል አጋርነት በሰፊው ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል።

**ተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሀብት ልማት ማሳደግ፡-** ውጤታማ የሆነ የኢነርጂ ዘርፍ ልማትን በልማት ዕቅዱ ዘመን ዕውን ለማድረግ ዘርፉ የሚፈለገውን ክህሎትና ዕውቀት ያሟላ የሰው ኃይልና ተቋማዊ አቅም መገንባት ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

### ዓላማዎችና ግቦች

በክልሉ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን እና ቴክኖሎጂዎችን በማልማት፣ በማላመድ እንዲሁም በማሠራጨት በደን ሀብት ላይ የሚደርሰውን ሚዛናዊ ያልሆነ ተፅዕኖ መቀነስና በካይ የሆነ የኢነርጂ አጠቃቀም መቅረፍ እና የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ጥራትንና ደህንነትን በመቆጣጠር አቅምን ያገናዘበ ፍትሐዊ የኢነርጂ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ ንፁህ የኢነርጂ ቴክኖሎጂ ለገጠሩ ህብረተሰብ ማዳረስ፣ ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋም እንዲኖር ማድረግ፣ ባለሀብቶች በዘርፉ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ ማበረታታት እንዲሁም ብቃትና ሥነምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል በመፍጠር ለክልሉ ህዝብ ዘላቂ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

የተሻሻሉ ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችን የሥርጭት ሽፋን ከ54.39 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ 26,034 የቤተሰብ እና 40 የተቋማት ባዮጋዝ ቴክኖሎጂ ግንባታ በማካሄድ 130,170 ቤተሰቦችንና 40 ተቋማትን የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ፣ ከአማራጭ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች 26.23 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ በማመንጨት በገጠር መንደሮችና ከተሞች የሚኖረውን 1,446,830 ህዝብ ከአማራጭ ኢነርጂ ምንጮች እና ቴክኖሎጂዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ እና 590,332 የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ቴክኒሻኖች እንዲሁም በኤሌክትሪክና ኤሌክትሪክ ነክ ንግድ ለሚሠማሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣ ማደስና መከታተል በአሥር ዓመቱ ዕቅድ ተፈጻሚ የሚሆኑ ግቦች ናቸው።

### የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የፍትሐዊ አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣ በዘርፉ ዘለቄታዊ ኢንቨስትመንትን ማረጋገጥ፣ ተቋማዊ ገቢን ማሳደግና የንፁህና ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማስፋፋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው።

## 12.2.4. መስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ልማት

### የትኩረት አቅጣጫዎች

**የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሳደግ የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፡-** የመስኖ ልማት የግብርና ዝመናን በማረጋገጥ በዘርፉ ምርትና ምታማነትን ለማሳደግ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንፃር በአለፉት ዓመታት በመስኖ ልማት ግብርናን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ከማሳደግ አኳያ ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። በመሆኑም በልማት ዕቅዱ ዘመን የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ ዋነኛ የዘርፉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ የሚተገበር ይሆናል።

**የልማት ኮሪደሮችን ዕምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ የመስኖ መሠረተ ልማት አቅርቦትን ማረጋገጥ፡-** የመሠረተ ልማት አቅርቦት እና ዝርጋታ በራሱ የሚኖረው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት በአካባቢዎች ላይ ያለውን ዕምቅ የመልማት አቅም በአግባቡና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ በማዋል ለአካባቢውና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የሚኖረውን ፋይዳ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም የመሠረተ ልማት አቅርቦት እና ዝርጋታው በቀጣይ የሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማት ኮሪደሮችን ዕምቅ አቅም ማዕከል ያደረገ እንዲሆን በትኩረት የሚሠራ ይሆናል።

**የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማጎልበት፡-** የመንግስት ወጪ ሊቀንሱና ሊቆጥቡ የሚችሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ በዘርፉ የሚሠራ ይሆናል። በተጨማሪም የመስኖ መሠረተ ልማት ዝርጋታ የሚፈልገው ፋይናንስ ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር በመንግስት ወጪ ብቻ ለማከናወን አዳጋች በመሆኑ በቀጣይ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን በመከተል ዘርፉ የሚፈልገውን ኢንቨስትመንት ለመሳብ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል። ከዚህ አንፃር በዘርፉ የግሉ ዘርፍ ያለውን ተሳትፎ ለማጎልበት የተለያዩ የፖሊሲና አስተዳደራዊ ርምጃዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። በተጨማሪም የመንግስትና የግል አጋርነት በዘርፉ በሰፊው ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል።

**ቅንጅታዊ አሠራርን ማጎልበት የሚያስችል ሥርዓትን መከተል፡-** የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር አስተሳስሮ ማካሄድ ዘርፉ ከመሠረተ ልማት ዝርጋታ ባሻገር በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ የሚኖረውን አዎንታዊ ተጽዕኖ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም በቀጣይ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት በመዘርጋት ቅንጅታዊ አሠራርን ዕውን ለማድረግ በትኩረት ይሠራል።

**ተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሀብት ልማት ማሳደግ፡-** በመስኖ ልማት ዘርፍ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት በዘርፉ የሚፈለገውን ክህሎትና ዕውቀት ያሟላ የሰው ኃይል እና ተቋማዊ አቅም መገንባት ወሳኝ ሚና የሚጫወት ይሆናል። ይህም የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የበለጠ በማጎልበት በዘርፉ የተቀመጡ የመስኖ ልማት ግቦችን ለማሳካት ያስችላል። በመሆኑም በቀጣይ ጠንካራ ተቋማዊ አቅምና የመስኖ ዘርፍ የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማልማት ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ይሆናል። በሚቀጥለው አሥር ዓመት በአገር ደረጃ የተጀመሩና ያልተጠናቀቁ ዘመናዊ የመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታዎች (መገጭ፣ ርብ እና መገጭ ሰራባ እና ሊሎች) ተጠናቀው ወደ ልማት የማስገባት ሥራ እንዲሁም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን ጥናትና ዲዛይን ተሠርቶላቸው ወደ ግንባታ ያልገቡ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ የማስገባት ሥራዎች የትኩረት አቅጣጫ ይሆናሉ።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዓላማዎች የመካከለኛ እና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን ማስፋፋት፣ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ ለተማሩና መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች በዘመናዊ መስኖ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በተፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማስቻል፣ ተቋማዊ አቅምና የሰው ሀብት ልማትን ማሳደግ፣ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማደራጀት የጥገና ወጪን እንዲሸፍኑ ማስቻል፣ የሥርዓተ ፆታና አካል ጉዳተኞች አካታችነትን ማረጋገጥና የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው።

ዓላማዎቹን ለማሳካት የተጣሉ ግቦችም የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ አውታሮችን ጥናትና ዲዛይን በ2014 በጀት ዓመት ከደረሰበት 427 ፕሮጅክቶች በ2022 በጀት ዓመት ወደ 1,419 ፕሮጀክቶች በማድረስ ማልማት የሚችለውን መሬት ከነበረበት ከ97,356 ሄክታር ወደ 408,806 ሄክታር ማድረስ፣ የአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ አውታሮችን ግንባታ በ2014 በጀት ዓመት ከደረሰበት 5,721 ፕሮጀክት በ2022 በጀት ዓመት ወደ 8,281 ፕሮጀክት በማድረስ የሚለማውን መሬት ከነበረበት 221,959 ሄክታር ወደ 478,114 ሄክታር ማድረስ፣ ለ453 የመስኖ ተቋማት ቀላል፣ መካከለኛና ከበድ የጥገና ሥራ በማካሄድ የውኃ አጠቃቀምና ውጤታማነታቸውን በማሻሻል የሚለማውን መሬት ወደ 17,739.7 ሄክታር ማሳደግ፣ አዲስ እና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትን እና አጠቃቀምን በመፈተሽ የሥርጭት መጠኑን ከነበረበት 2 በመቶ በ2022 በጀት ዓመት ወደ 22 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም በዘመናዊ መስኖ ተቋም ማስፋፋት ጥናት፣ ግንባታ፣ ጥገና፣ መስኖ ቴክኖሎጂ ግብዓት አቅርቦትና ተዛማጅ ሥራዎች ላይ በማሳተፍ ለ465,680 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

በመስኖ ልማት ዙሪያ የመንግስት ወጪ ቅነሳና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋት፣ የመስኖ ፕሮጀክቶች በተመደበላቸው ጊዜና በጀት እንዲሁም በተፈለገው የጥራት ደረጃ ተጠናቅቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ፣ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በማደራጀት የጥገና ወጭን እንዲሸፍኑ እንዲሁም ለመስኖ ልማት አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን በማጎልበት የበጀት ፍላጎት እንዲሟላ ማድረግ፣ በመስኖ ልማት ዘርፍ የተቋማዊ አቅምና የዘርፉን የሰው ሀብት ልማት ለማሳደግ አስቻይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ መመሪያዎች እና ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣ ተቋማዊ አሠራርን በማጠናከር ፋሲሊቲዎችን ማሟላት፣ በመስኖ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችን እና የመስኖ ተጠቃሚዎችን አቅም መገንባት፣ የመስኖ ልማትን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር ሥርዓት መዘርጋት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው።

የመስኖ ሥራዎች ባልተስፋፉባቸው እና ህብረተሰቡ የመስኖ ልምድ ሳይኖረው ቀርቶ ጥያቄ በማያቀርብባቸው አካባቢዎች የዘመናዊ መስኖን አስፈላጊነት ህብረተሰቡ እንዲገነዘበው ማድረግ፣ የዘመናዊ መስኖ ፕሮጀክቶች ከመገንባታቸው በፊት የመስኖ ኦፕሬሽን እና ጥገና ሙሉ ወጪ በተጠቃሚው ህብረተሰብ እንደሚሸፈን ከህብረተሰቡ ጋር ሥምምነት ላይ መድረስ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

### 12.2.5. ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የአሥር ዓመቱ የከተማ ልማት ዕቅድ ከአለፉት ዓመታት አፈጻጸሞች ስኬት እና ክፍተቶች የሚመነጩ የዘርፉን የወደፊት ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ያስገባ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል። ከተሞችን እንደ ሀብት

መሠረታቸው የልማት ማዕከላት ማድረግ የተሳካ የከተሞች መዋቅራዊ ሽግግር ግብዓትም ውጤትም ነው። ከተሞች በዘላቂነት ሊያድጉ የሚችሉት ከአካባቢያቸው ካሉ ፀጋዎች ጋር ተሳስረው መልማት ሲችሉ ነው። በመሆኑም ከተሞችን እንደ ሀብት መሠረታቸው ከከባቢያቸው ጋር በማስተሳሰር ለመዋቅራዊ ሽግግር የሚኖራቸውን ፋይዳ በማጉላት በተለይም ከተሞችን የግብርና ዝመና፣ የአምራች ኢንዱስትሪ፣ የዘመናዊ አገልግሎት እና የቱሪዝም ልማት ማዕከላት ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

በዜጎች ተሳትፎ የሚገነቡ ዘላቂ የመኖሪያ ቤቶችን በማስፋፋት የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ አሳታፊ፣ ዘላቂ እና ለኑሮ ተስማሚ መሆን ይኖርበታል። በመንግሥት፣ በግሉ ዘርፍና በማህበራት ቅንጅት በከተሞች የመኖሪያ ቤት ፍላጎትን በማሟላት ከተሞችን ለኑሮ ተስማሚ ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ከመገንባት ግብ ጋር የሚጣጣም የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ በከተሞች መተግበር፣ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን ማዘመን እና ቀልጣፋ ማድረግ፣ በከተሞች ዕድገትና ልማት የሚታዩ ነባራዊ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል የዘመኑን ቴክኖሎጂና የረጅም ዘመን የወደፊት ፍላጎቶችን ግምት ውስጥ ባስገባ የከተማ ፕላን መምራት፡ የሥርዓታት ሽግግር (Institutional transformation) በከተሞች ማስፈን፣ ዘመናዊና ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በክልሉ በማረጋገጥ በዘርፉ የቴክኖሎጂና የሥርዓታት ሽግግር እንዲመጣ በመሥራት ጥራት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ እንዲኖረው ማስቻል።

## ዓላማዎችና ግቦች

የክልሉ ክትመት የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን፣ መሬትንና ሌላ ሀብትን በቁጠባ የሚጠቀም፣ እንቅስቃሴን የሚያፋጥን፣ ለአካባቢ ተጽዕኖ የማይበገር፣ አካታች፣ አሳታፊ እና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ ተዋረድ ባለው የተሟላ ፕላን እንዲመራ ከማድረግ አንፃር ሁሉም የክልሉ ከተሞች በአገር አቀፍ የከተሞች አመሰራረት እና ቅንጅት ፕላን (National Spatial Development Plan)፣ የከተማ ልማትን በሚያቀናጅ የክልል ልማት ፕላን (Regional Spatial Development Plan) እና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ልማት ቅንጅትን መሠረተ ባደረገ የትስስር ፕላን (City Cluster Development Plan) እንዲመሩ የማድረግ፣ ለ996 ከተሞች ካርታና ፕላን (ለ660 ከተሞች የክለሳ ካርታና ፕላን እና ለ336 አዲስ ከተሞች መሠረዊ ካርታና ፕላን) እንዲዘጋጅላቸው የማድረግ እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ሁሉም ከተሞች 100 በመቶ በተዘጋጀላቸው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢዊ ልማትና አገልግሎቶች ቅንጅትና ትግበራ ፕላን እንዲመሩ የማድረግ ግቦች ተጥለዋል።

ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ልማትን የሚያፋጥን፣ ወጪን የሚያስመልስ፣ ፍትሐዊነትን የሚያሰፍን የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር የከተሞችን የመልማት አቅም/ዕድል ታሳቢ ባደረገ መልኩ የመሬት ፍላጎትን ቢያንስ 75 በመቶ እንዲዘጋጅና እንዲቀርብ የማድረግ፣ የከተማ መሬት 40 በመቶ በጨረታ፣ 60 በመቶ በምደባ እንዲተላለፍ የማስቻል እንዲሁም በከተሞች የደቀቁና የተጎሳቆሉ የከተማ ክፍሎችን በመልሶ ማልማትና በከተማ ማሻሻል እንዲለሙ በማድረግ አሁን ካለበት 74 በመቶ ወደ 30 በመቶ በታች እንዲደርስ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ። በሁሉም ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የተቀናጀ መሠረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ከማሳደግ አንፃር የመንገድ መሠረተ ልማት፣ የመጠጥ ውኃ እና የኃይል አቅርቦት ሽፋንን ወደ 90 በመቶ እንዲደርስ የማድረግ፣ ከ20 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች የእሳትና ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት ሽፋን 100 በመቶ እንዲደርስ የማድረግ፣ ከ20 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች የዘመናዊ ቄራ አገልግሎት ሽፋን የፍላጎቱን 100 በመቶ እንዲደርስ የማድረግ፣ ከ20 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች ተደራሽና ደረጃውን የጠበቀ የከተሞች የገበያ አገልግሎት ሽፋን 100 በመቶ እንዲደርስ የማድረግ እንዲሁም ከ20 ሺህ በላይ ነዋሪ ያላቸው ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የጭነትና የህዝብ ማመላለሻ መናኸሪያ አገልግሎት ሽፋን 100 በመቶ እንዲደርስ ይሠራል።

በከተሞች የአገልግሎት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓትን በማጠናከር መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር በማዘጋጃ ቤቶች አገልግሎት አቅርቦት የተገልጋዮችን የዕርካታ መጠን ከ45 በመቶ ወደ 85 በመቶ ለማሳደግ እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ባለባቸው የክልሉ ከተሞች የከተማ አገልግሎቶች ስታንዳርድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይሠራል፡፡

በከተሞች ያልተማከለ አስተዳደርን ማጠናከር እና የተመጣጠነ የክትመት ልማትን በማስፋፋት በማጠናከ ምጣኔውን አሁን ካለበት 19.42 በመቶ ወደ 26.28 ለማሳደግ ይሠራል፡፡ የከተማነት መሥፈርቱን የሚያሟሉ 336 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ዕውቅና እንዲያገኙ በማድረግ የከተሞችን ቁጥር አሁን ካለበት 660 በየዓመቱ 5 በመቶ በማሳደግ ወደ 996 ማድረስ እንዲሁም ከተሞችን በፈርጅ የማደራጀት ሥርዓቱን በማጠናከር በየዓመቱ 5.5 በመቶ ከተሞች የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ ማስቻል የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

የከተሞችን የጽዳት አገልግሎት እና የአረንጓዴ መሠረተ-ልማት ሽፋንና ተደራሽነት በማሳደግ በከተሞች ለሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮሎጅያዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ፣ ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ ከማድረግ አኳያ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና በአረንጓዴ ልማት 10 የህግ ማዕቀፎች፣ የአሠራር ማንዋሎች እና የጥናት ሠነዶች በማዘጋጀትና 10 የንቅናቄ መድረኮችን በማዘጋጀት ለ10 ሚሊየን የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት ዙሪያ በቀጥታ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በሁሉም ከተሞች ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ 15 በመቶ ከምንጩ በመቀነስ 35 በመቶ መልሶ በመጠቀም እና በመጨረሻም 30 በመቶ በተገቢው እንዲወገድ በማድረግ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋን 80 በመቶ እንዲደርስ ማስቻል፣ በ150 አዲስ ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ገቢና የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋት፣ በሁሉም ከተሞች የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ሽፋን በፕላን ላይ ከተቀመጠው የመሬት ድርሻ 30 ከመቶ ሆኖ እንዲለማ ማስቻል እንዲሁም በ200 ከተሞች በፕላን ላይ ከተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙና ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ማስቻል የሚሉ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡ በተለያዩ አማራጮች በዕቅድ ዘመኑ 774,893 ቤቶች ለነዋሪዎች የመገንባት ሥራ ይሠራል፡፡

በከተሞች የምግብ ዋስትና ሥርዓትን በማስፋት የከተማ ድህነትን ከመቀነስ አንፃር በ972 ከተሞች የሚገኙ ነዋሪዎች በምግብ ዋስትና ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ፣ አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 3,618,276 ዜጎች የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች እንዲሳተፉ የማድረግ፣ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ሥራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 1,206,092 የቤተሰብ ኃላፊዎች በዘላቂነት ኑሮአቸውን በሚያሻሽሉ የሥራ አማራጮች እንዲሸጋገሩ የማድረግ፣ በከተሞች የሚገኙ የመሥራት አቅም የሌላቸውና ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ 689,195 የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማን እና ህጻናት እና 44,000 የጎዳና ተዳዳሪዎች የማህበራዊ ሴፍቲኔት ድጋፍና የመሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ የማስቻል እንዲሁም በሴፍቲኔት ከታቀፉት ውስጥ የሥራ ባህላቸው ላልዳበረ ሥራ ፈላጊ ለሆኑ 200,000 ወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ከመገንባት አኳያ በክልሉ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በክልሉ በሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተወዳድረው በማሸነፍ የገበያ ድርሻቸው አሁን ካለበት ወደ 80 በመቶ እንዲያድግ ማደረግ፣ የክልሉ ተቋራጮችና አማካሪዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በዘርፉ የሚኖራቸው ድርሻ አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ ወደ 30 በመቶ እንዲያድግ ማስቻል እንዲሁም የጊዜ ብክነትን /Time over run/ በመቀነስ 90 በመቶ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የውል ጊዜ እንዲጠናቀቁ ማስቻል የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

በከተማ ልማት ዘርፍ (በፕላን ዝግጅት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም በአረንጓዴ ልማትና በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል በ2012 ከነበረበት 624,265 በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (በ2022) ወደ 1,500,000 ከፍ እንዲል የማስቻል ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ በከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን በማካተት 50 በሙቶ ሴቶችን እና 70 በሙቶ ወጣቶችን የልማቱ ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ በመሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሥርዓት የሴቶች እኩል ተጠቃሚነትን ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ማስቻል፣ በአካባቢ ልማት ሥራዎች፣ በቤቶች፣ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንዲሁም በሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ድርሻ 50 በሙቶ የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ድርሻ 70 በሙቶ እንዲደርስ ማስቻል፣ በከተሞች የአመራር ግንባታና ሥምሪት 50 በሙቶ ሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በትምህርትና ሥልጠና 50 በሙቶ ሴቶች ድርሻ እንዲኖራቸው ማስቻል፣ እንዲሁም በየደረጃው የሚዘጋጁ ፕላኖች፣ የግንባታና መሠረተ ልማት ዲዛይኖች የሴቶችን እና የወጣቶችን ልዩ ፍላጎት ያሟሉ እንዲሆኑ ማስቻል የሚሉ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የአገራዊ እና ክልላዊ የከተማ ስፓሻል ፕላን ጥናትን እና ዝርዝር ሶሽዮ ኢኮኖሚ ጥናትን መሠረት ያደረገ፣ የተናበበና የተሳሰረ፣ ክልላዊና አገር አቀፍ የልማት ዕድገትን የሚያረጋግጥ የከተማ ትስስር ፕላን እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ የከተሞች ፕላን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና በአካባቢያዊ ጉዳዮችን በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመሥርቶ በመተንተን ዘላቂና ቀጣይነት ያለው የከተማ ልማትን በሚያረጋግጥ አግባብ ዘመናዊና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ የከተሞችን መዋቅራዊ ፕላን ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላን (NDP) በማዘጋጀት እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ የከተማ ፕላንን በጥራት ለማዘጋጀትና ለመተግበር ሁሉን አቀፍ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ ሥልጠና በመስጠት የፈፃሚውን አቅም የማሳደግ እና በየደረጃው የክትትልና ድጋፍ ሥራ ይከናወናል፡፡ 40፣ 30፣ 30 የቦታ ምጣኔ ስታንዳርድን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊና ዘላቂ ልማትን ያረጋገጠ የከተማ መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖች በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ፀድቀው በከተማው ህዝብ ባለቤትነት 100 በሙቶ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ የከተማ ፕላን ጥሰትን እና ተገቢ ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም ምደባ ለውጥን የመከላከል ሥራ ይሠራል ፡፡የከተሞች ፕላን በዘመናዊ የቅየሳ መሣሪያ (GPS) ዓለም አቀፍ ኮርድኔት በመጠቀም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 12.2.6. ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

የቴክኖሎጂ ልማት እና ሽግግር አቅም ማጎልበት፣ የተቀናጀ እና ተናባቢ አሠራርን ማጎልበት፣ ዲጂታል ኢኮኖሚን በዕድገት ምንጭነት መጠቀም፣ ቴክኖሎጂን ለምርታማነት ማሻሻያ ማዋል፣ ኢኖቬሽንና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነትን የመወሰን አቅም ማሳደግ የሚሉት ናቸው፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እና የቀጣይ ዘመን ኢንዱስትሪ ውስጥ በብቃት የሚሳተፍ የሰው ኃይል የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ሽፋንና ደህንነትን ማሳደግ፣ በምርምርና ጥናት ላይ የተመሰረቱ ቴክኖሎጂዎችን ማልማትና ማሸጋገር፣ የተቋማት ትስስርና ትብብርን በማጠናከር ክልላዊና አገራዊ አጋርነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ ዋና ዋናዎቹ የመሪ ዕቅዱ ዓላማዎች ናቸው፡፡ ይህን ከማሳካት አንፃር የሚቋቋሙ የማህበረሰብ የመረጃ ማዕከላትን ብዛት ከነበረበት 86 ወደ 163 ማሳደግ፣ የለሙ አፕሊኬሽኖችን ብዛት

ከ26 ወደ 118 ከፍ ማድረግ፣ የለሙ ዌብሳይቶችን ብዛት ከ20 ወደ 180 ከፍ ማድረግ፣ የቴክኖሎጂ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ተደራሽነቱን ማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ምርምር፣ ልማት፣ ሽግግርና አጠቃቀም አቅምን ማጎልበት፣ ለሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አመራር የሰው ኃይል ማልማት፣ ዘመኑ ያፈራቸውን የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ሽፋንን ማሳደግ፣ የመሠረተ ልማትና የመረጃ ደህንነትን ማረጋገጥ፡ በየደረጃው የሚገኙትን የቴክኖሎጂ ማዕከላትን ማደራጀትና ማጠናከር፣ የቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከላትን አተገባበር ሥርዓት ማሳደግና ደህንነታቸውን መጠበቅ፣ የክልሉን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያግዙ ቴክኖሎጂ ነክ የሆኑ የምርምር ሥራዎችን ማከናወን የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የዕቅዱ ግቦች ናቸው፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማጣመር በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማስቻል የዕቅዱን ዓላማዎች በቀላሉ እንዲተገበሩ ማድረግ፣ ተቋማዊ አቅምን ከመጀመሪያውና 2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ትንተናና ግምገማ የተገኙትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ በአደረጃጀት ለሥራ ምቹ የሆኑ በየደረጃው ያሉ ተቋማትን መፍጠርና ማጠናከር፣ በአሠራር ሥራን ማሳለጥ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች፣ ስታንዳርዶች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች፣ የአሠራር ልምዶችና የመሳሰሉት መደራጀትና እነዚህ በተሟሉበት ሁኔታ ሥራን መሥራት የሚችል በዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የሠለጠነና የበቃ፣ የሥራ ልምድ ያለው፣ በታታሪነትና በሥራ ወዳድነት፣ በመልካም የሥራ ሥነምግባር መሰማራት የሚያስችለው አቅምና ባህል ያዳበረ ይህን ዕውቀት በመጠቀም አንድን ሥራ በውጤት መደምደም የሚያስችል የሰው ኃይልና ተቋም መፍጠር እንደ ዋና ሥልት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 12.3. ማህበራዊ ልማት ዘርፍ

### 12.3.1. ትምህርትና ሥልጠና

ዕውቀቱ የዳበረ፣ ክህሎትና የተስተካከለ አመለካከት ያለው የሰው ኃይል ልማት ወይም ሰብዓዊ ሀብት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ብሎም ልማትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ ቁልፍና የማይተካ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አንፃር እንደ አማራ ክልል ወደሚፈለገው ብልፅግና ለመሸጋገርና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት የሰብዓዊ ሀብት ልማት ስትራቴጂ ዋና ዕሳቤ ያለውን ሰፊ የአምራች ኃይል የማምረት አቅም በማሳደግ የሥነ ህዝብ ትሩፋት ዕምቅ አቅምን /መልካም አጋጣሚ/ Demographic Dividend/ በአግባቡ መጠቀምን መሠረት የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

**የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ሥርዓት፡-** የትምህርት ዋና ግብ ዜጐችን በዕውቀት፣ በክህሎት እና በመልካም ሥነ ምግባር በማነጽ ለራሳቸውም ሆነ ለአገር ግንባታ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የመማር ውጤት እና በመልካም ሥነ ምግባር መታነጽ በየደረጃው ማለትም በትምህርት ምዘና፣ በፈተና ሥርዓት፣ በተቋማት ኢንስፔክሽን እንዲሁም በመምህራንና በትምህርት አመራር የሙያ ብቃት ምዘናዎች ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በላይ ትምህርት ለሥራ ዓለም እና ማህበራዊ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም ሥርዓተ ትምህርቱ፣ የማስተማር ሥነዘዴው፣ የማስተማሪያ እና የመማሪያ ቁሳቁሶች እና ግምገማ ሥርዓቶቹ ከገበያው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡ የትምህርት ውጤትን ለማሻሻል በሁሉም ደረጃዎች የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ አፈፃፀም ካላቸው ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች ጋር

የሚነፃፀሩ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ውጤቶችን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር እና የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የማስፈጸም አቅም በማጎልበት ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓትን በማጠናከር በተለይም ትምህርት ቤቶች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዲኖራቸው ማጠናከር እንዲሁም ህብረተሰቡን፣ ወላጆችን፣ ተማሪዎችን እና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አሳታፊነቱን በማጎልበት በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ላይ ሙሉ ኃላፊነትን ከተጠያቂነት ጋር መስጠት ወሳኝ በመሆኑ በክልሉ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። የትምህርት ሥርዓቱ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣቱን በተወሰኑ የዕቅድ ዘመናት እንዲረጋገጥ ማድረግ ይገባል፡፡

**ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡-** ትምህርት የሰው ልጆች የመማር መብት ነው፡፡ በአዲሱ ረቂቅ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ድረስ ነፃ እና ግዴታ እንዲሁም ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ነፃ እና ጥራት ያለው ትምህርት በማቅረብ የዜጐችን መብት ማክበር ይገባል፡፡ ትምህርቱን የአካቶ ትምህርት ሥርዓት ተከትሎ በመልከዓ ምድር (ገጠርን እና ከተማ)፣ በፆታ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በስጦታ እና ተሰጥዖ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይፈጠር ሕፃናት እና ወጣቶች ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም በክልላችን በርካታ ዕቅዶች የተዘጋጁ ሲሆን ለስኬቱ ርብርብ ይደረጋል፡፡

**ከሥራ ጋር የተሳሰረ የጐልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፡-** ጐልማሳው የሀገሪቱን ወቅታዊ ዕድገት በመገንባት በኩል ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም ጐልማሳውን የመፃፍ፣ የማንበብ እና የማስላት ክህሎት እንዲኖረው ከማሠልጠን ባሻገር የሕይወት ክህሎትን በማበልፀግ ኑሮውን እንዲያሻሽል ማድረግ እና ለአገር የኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማስቻል ከፍተኛ ሥራ ማከናወን ይጠበቃል፡፡

**የትምህርት ሥርዓቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍ፡-** ጥራት ያለው ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ ዲጂታል ቴክኖሎጂን መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ-ትምህርት ቀረፃ፣ የመምህራን ትምህርት፣ የትምህርት አመራሩን አቅም ግንባታ፣ የመማር ማስተማር ሂደት፣ ፈተና እና ምዘናዎች እንዲሁም የትምህርት መረጃ አስተዳደር በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመደገፍ እና በማዘመን የትምህርት ጥራት ለሁሉም እንዲዳረስ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም በክልላችን ይህን የትኩረት አቅጣጫ ለማስፈጸም ርብርብ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

**በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁ ዜጐች ማፍራት፡-** የትምህርት አንዱ ዓላማ ብዝሀነትን የሚቀበሉ፣ ለሀገራቸው አንድነት ዘብ የሚቆሙ፣ በግብረገብ፣ በሥነ ምግባርና በዴሞክራሲ ባህል የታነጹ ዜጐችን ማፍራት ነው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ተቋማት እና ሌሎች የመማሪያ ማዕከላት ከተለያዩ አስተዳደሮች፣ ሃይማኖቶች እና ጎሳዎች የመጡ ተማሪዎችን የእርስ በእርስ ተግባቦትን ለመፍጠር፣ ሌሎችን ለመረዳት፣ ልዩነቶችን ለመቀበል እና ለመቅረጽ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህም የጋራ ልምዶችን እና ዕሴቶችን በማጠናከር አገራዊ አንድነት ለመገንባት ስለሚረዳ በክልላችን በትኩረት የሚሠራ ይሆናል፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

የትምህርት ዘርፉ ዋና ዓላማ ጥራት ያለው ትምህርት እና ሥልጠና በተለይም ከቅድመ አንደኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የግዴታ ትምህርት ለሁሉም በፍትሐዊነት ማዳረስ እና የሁለተኛ ደረጃ የነፃ ትምህርት በሳይንስና ተስማሚ ቴክኖሎጂ የተደገፈና በብቁ አመራር የሚመራ ትምህርት ለሁሉም በፍትሐዊነት ማዳረስ ነው፡፡ በመሆኑም በግለሰብ ደረጃ አዕምሮአዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና መልካም ዕሴቶችን በማጐልበት ለሀገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች

ምላሽ የሚሰጡ እንዲሁም ግብርናውን ወደ ላቀ ደረጃ በማሻገር ኢኮኖሚውን የሚያሳድጉ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጐችን ማፍራት ነው።

ዓላማውን ለማሳካት የተጣሉ ዋና ዋና ግቦችን በሚመለከት የትምህርት ተደራሽነትና ውስጣዊ ብቃትን ከማሳደግ አኳያ ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ቅበላ ምጣኔን በ2012 ከተደረሰበት 37.2 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ የ1ኛ ክፍል ጥቅል እና ንጥር ቅበላ ምጣኔን በ2012 ከተደረሰበት 86.9 በመቶ እና 74.14 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ጥቅል እና ንጥር ተሳትፎን በ2012 ከተደረሰበት 85.13 በመቶ እና 71.3 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 98.16 በመቶ እና 100 በመቶ ማድረስ፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ጥቅል እና ንጥር ተሳትፎን በ2012 ከተደረሰበት 77.15 በመቶ እና 47.17 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 98.16 በመቶ እና 100 በመቶ ማድረስ፣ ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ጥቅል እና ንጥር ተሳትፎን በ2012 ከተደረሰበት 36.38 በመቶ እና 27.84 በመቶ ወደ 75 በመቶ ማድረስ፣ የ1ኛ ክፍልን መጠነ መድገም በ2007 ከተደረሰበት 7 በመቶ ወደ 5 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣ የ6ኛ እና የ8ኛ ክፍል የማለፍ ምጣኔን በ2007 ከተደረሰበት 71.7 በመቶ እና 71 በመቶ እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 100 በመቶ እና 90 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ የ7ኛ ክፍል የመዝለቅ ምጣኔን በ2007 ከተደረሰበት 73.4 በመቶ ወደ 75.6 በመቶ ማድረስ፣ የእጩ መምህራን የማጠናቀቅ ምጣኔን በ2022 ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

የትምህርት ፍትሐዊነት እና አካታችነት ከማሻሻል አንፃር የሥርዓተ ፆታ ምጥጥን በተመለከተ የቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል እና ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትምህርት በ2012 ከተደረሰበት 1.0፣ 0.94፣ 1.10 እና 1.08 ምጥጥን በ2022 እንደ ቅደምተከተላቸው በሁሉም የትምህርት ክፍሎች ወደ 1፡1 ለማድረስ ግብ ተይዟል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጥቅል ተሳትፎን በተመለከተ የቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል፣ ከ7ኛ-8ኛ እና ከ9ኛ-12ኛ ክፍል በ2012 ከተደረሰበት 0.03 በመቶ፣ 2.4 በመቶ፣ 1.19 በመቶ፣ 0.34 በመቶ በ2022 ወደ 0.2 በመቶ 8.87 በመቶ፣ 5.81 በመቶ እና 2.74 በመቶ እንደ ቅድምተከተላቸው ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

**የሴት መምህራን ድርሻ ከማሳደግ አኳያ** የቅድመ 1ኛ ደረጃ፣ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል እና ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትምህርት፣ የሴት አሠልጣኝ መምህራን ድርሻ በ2012 ከተደረሰበት 94.3 በመቶ፣ 45.94 በመቶ፣ 25.89 በመቶ እና 15 በመቶ፣ እንደ ቅድምተከተላቸው 95 በመቶ፣ 50 በመቶ፣ 30 በመቶ እና 25 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል። በተጨማሪም **የሴት አመራርን ድርሻ ከማሳደግ አኳያ** የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሴት አካዳሚክ አመራሮች፣ የመጀመሪያ ደረጃ የሴት ርዕሰ መምህራን፣ የሁለተኛ ደረጃ የሴት ርዕሰ መምህራን፣ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የሴት ሱፐርቫዘሮች እንዲሁም የሴት ባለሙያዎች ድርሻ በ2012 ከተደረሰበት 20.77 በመቶ፣ 6.52 በመቶ፣ 1.38 በመቶ 2.51 በመቶ፣ 0.91 በመቶ እና 32.15 በመቶ እንደ ቅድምተከተላቸው 30 በመቶ፣ 25 በመቶ፣ 15 በመቶ 45 በመቶ፣ 25 በመቶ እና 40 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል።

የመምህራን እና የትምህርት አመራሩን ሙያዊ ብቃት ከማሳደግ አኳያ ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ የሚያሟሉ በየደረጃው የሚገኙ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች ቁጥር ለማሳደግ ግብ ተይዟል። በመሆኑም የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ መምህራንን ቁጥር በ2012 ከተደረሰበት 3,117፣ 5,619 እና 3,454 በ2022 ወደ 66,134፣ 150,000 እና 72,462 እንደ ቅደምተከተላቸው ከፍ ለማድረግ ታቅዷል።

ለደረጃው የተቀመጠውን የትምህርት ደረጃ በሚያሟሉ ርዕሰ መምህራን የሚመሩ የቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 0፣ 66 በመቶ፣ 53.5 በመቶ በ2022 በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ወደ 100 በመቶ ለማድረስ እንዲሁም የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች እና

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 92.8 በመቶ እና 83.6 በመቶ በ2022 ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል። ከዚህም ባሻገር በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሙያ ፈቃድ ምዘና ያለፉ እና ዕውቅና ያላቸው መምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 27.5 በመቶ፣ 1.63 በመቶ በ2022 ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት በመተግበርና በመገምገም የቅድመ አንደኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ 1:1 በዘላቂነት ማስጠበቅ፣ የዕጩ መምህራን ሞጁል ጥምርታን በ2012 ከተደረሰበት 1:2 በ2022 ወደ 1:1 ለማድረስ ታቅዷል። በተጨማሪም የ2ኛ እና የመካከለኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት በዲጅታል ቴክኖሎጂ ተደግፎ ለተማሪዎች ተደራሽ ከማድርግ አንፃር በ2012 ከነበረበት 0 በ2022 ወደ 100 በመቶ ከፍ ለማድረግ ግብ ተይዟል።

የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 71 በመቶ በ2022 ወደ 90 በመቶ ማድረስ እንዲሁም የ6ኛ ክፍልን ከ71.7 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ የ12ኛ ክፍል አገራዊ ፈተና ተመዝነው 50 በመቶና በላይ አምጥተው ያለፉ ተማሪዎች ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 26.6 በመቶ በ2022 ወደ 75 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

በ2ኛ እና በ3ኛ ክፍል የንባብና ክህሎት ምዘና ተፈላጊ ዝቅተኛ የብቃት ደረጃ የደረሱ ተማሪዎች በ2012 ከተደረሰበት 4.2/8.1 በመቶ በ2022 ወደ 72/96 በመቶ ማድረስ እንዲሁም በ2ኛ እና በ3ኛ ክፍል የሂሳብ ክህሎት ምዘና ተፈላጊ ዝቅተኛ የብቃት ደረጃ የደረሱ ተማሪዎች በ2022 ወደ 72/96 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

የሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን የመማር ማስተማር ሂደትን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ በዕቅድ ዘመኑ በትኩረት ይከናወናል። በመሆኑም ለSTEM (Science,Technology, Egineering & Mathematics) ፕሮግራም የሳይንስ ላብራቶሪ የተሟላላቸው በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማትን በ2012 ከተደረሰበት 302 (50.9 በመቶ) በ2022 ወደ 1,064 (100 በመቶ) ለማድረስ፣ አንድ (1) በአግባቡ የተደራጀ ክልላዊ የSTEM የልህቀት ማዕከል መመስረት እንዲሁም በክልል ደረጃ በፈጠራ ሥራዎች ዕውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች እና መምህራን ብዛት በ2012 ከተደረሰበት 9 እና 3 በ2022 እንደ ቅደምተከተላቸው ወደ 60 እና 30 ለማሳደግ ግብ ተይዟል።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በቀጣይነት በማሻሻል ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ሁኔታ መፍጠር በትኩረት የሚከናወን ይሆናል። ከዚህ አንፃር ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 4 በመቶ፣ 14 በመቶ፣ 17.1 በመቶ እና 60 በመቶ በ2022 እንደ ቅደምተከተላቸው 70 በመቶ፣ 70 በመቶ፣ 70 በመቶ እና 100 በመቶ ለማድረስ እንዲሁም ደረጃ 4 የደረሱ የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛና መካከለኛ፣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሽፋን በ2022 እንደ ቅደምተከተላቸው 30 በመቶ፣ 30 በመቶ፣ 30 በመቶ እና 50 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የትምህርት ተቋማት ግንባታ፣ ዕድሳትና የማስፋፋት ሥራዎች ይከናወናሉ። በመሆኑም 990 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም 471 የሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤቶች ግንባታ ይካሄዳል። 11,063 የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ፣ 839 የሁለተኛ ደረጃ (9-12) ትም/ቤቶች ዕድሳት ይደረጋል። በ10 ኮሌጆች የእድሳትና የማስፋፋት ሥራ ይከናወናል። 85 በመቶ የሚሆኑት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት ወደ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ የማሳደግ እና 340 የሚሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስፋፋት (9-12) ወደ "ኮምፕረሄንሲቭ" ትምህርት ቤቶች ለማሳደግ ታቅዷል።

የንፁህ መጠጥ ውኃ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2012 ከተደረሰበት 44.25 በመቶ እና 73.86 በመቶ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ፣ የመፀዳጃ ቤትና ንፅህና መጠበቂያ ያላቸው የአንደኛና መካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2012 ከተደረሰበት 83.98 በመቶ እና 97.64 በመቶ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ እንዲሁም የሴቶች ንፅህና መስጫ ያላቸው የትምህርት ተቋማትን ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 18.1 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡ የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ ግብር ተጠቃሚ የሆኑ የቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሽፋን በ2012 ከተደረሰበት 0.8 በመቶ በ2022 ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የትምህርት ሥርዓቱን ከማሻሻል አኳያ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በብሮድባንድ ኔትዎርክ መሠረተ ልማት ተሳስረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ የብሮድባንድ ተጠቃሚ የነበሩ 3 በመቶ ኮሌጆች ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ ይደረጋሉ፡፡ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዲጂታላይዝድ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ሁሉም የቅድመ አንደኛ፣ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተዳዳኝነት የዲጂታል ቴክኖሎጂ ግብዓቶች ተደራሽ ይሆናሉ፡፡ ሁሉም መምህራንና ተማሪዎች የዲጂታል ልዩ የመለያ ኮድ ያገኛሉ፣ ሁሉም ከ9-12 ደረጃ የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ያሏቸው ትምህርት ቤቶች የዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም መድረስ፣ በአግባቡ የተደራጀ 1 የልህቀት ማዕከል መመስረት የሚሉ ግቦች ተይዘዋል፡፡

የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ የትምህርት መርሀ ግብሮችን ከገበያ ፍላጎት ጋር በማስተሳሰር ተደራሽነትን እና ፍትሐዊነትን ከማሳደግ አንፃር የጎልማሶች የህይዎት ክህሎት ትምህርት ፕሮግራሞች ያጠናቀቁ ጎልማሶችን ብዛት በ2012 ከነበረበት 111,082 (ወንድ 65,639፣ ሴት 45,443) በ2022 ወደ 8,137,363 (ወንድ 3,296,078፣ ሴት 4,841,285) በማድረስ ሽፋኑን 100በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ ይህን ግብ ለማሳካትም የመማማሪያ ጣቢያዎችን ቁጥር ከ14,407 ወደ 122,098 ከፍ ለማድረግ፣ የአመቻቾች ብዛትን ከ7,830 ወደ 239,804 ከፍ ለማድረግ እና በስታንዳርዱ መሠረት የተቋቋሙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት (CLC) ብዛት ከ6 ወደ 166 ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም የመማር ዕድል ያላገኙ ዜጎች በተከታታይ (የማታና የርቀት) ትምህርት ተደራሽነት በ2012 ከተደረሰበት 47.9 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማድረስ ግብ ተይዟል፡፡ የጎልማሶች የህይዎት ክህሎት ትምህርት መርሀ ግብር ተሳታፊዎች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርትና ሥልጠናዎች የተሳተፉ ወጣቶችና ጎልማሶች የፆታ ምጥጥን በተመለከተ ታቅዷል፡፡

የትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓቱ ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ወሳኝ ሚና እንዲጫወት የጥራት፣ የተገቢነት እና የተጠያቂነት ለውጥ የሚያስፈልገው እንደሆነ ስለታመነበት የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ማጠናከር ላይ ትኩረት የተደረገ ሲሆን የትምህርት ሥርዓቱ በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራቱን በጥናት የማረጋገጥ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

የሥርዓተ ትምህርት አተገባበር ማሻሻያ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ ሥርዓተ ትምህርቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍና ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ፣ የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ሥልጠና እና ሥምሪት መመሪያዎችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ ተቋማት በቴክኖሎጂ የተደገፈ የትምህርት አገልግሎትና ተደራሽነት እንዲያሻሽሉ ቴክኖሎጂ ተኮር የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ዲጅታል ቴክኖሎጂን ከትምህርት ጋራ ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ፣ ደንብና ስታንዳርድ ክልላዊ ማስማማት መፍጠር እና መተግበር፣ በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ሊተገበሩ የሚችሉ አግባብነት ያላቸው የትምህርት ቴክኖሎጂ መረጣ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና መተግበር፣ ለመምህራን፣ ለትምህርት ባለሙያዎች እና አመራሮች በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሥራ ላይ

የሥልጠና ማዕከል ማቋቋም እና አሠራራቸውን ማሻሻል፣ የSTEM ትምህርቶችን ለመተግበር የሚያስችል አደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓት በጥናት ላይ በመመርኮዝ ተግባራዊ ማድረግ፣ የተማሪዎችና መምህራን የፈጠራ ሥራን ማበረታታትና ዕውቅና የሚያገኙበትን የአሠራር ሥርዓት መፍጠር፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን በማሳተፍ የትምህርት ተቋማትን መገንባትና ትምህርት ቤቶች በስታንዳርዱ መሠረት በግብዓት እንዲሟሉ ማድረግ፣ በየደረጃው ተልዕኮውን በብቃት መፈጸም የሚችል የትምህርት ተቋም ማቋቋም፣ የትምህርት ቤቶችን ሥርጭት ፍትሐዊ እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ School mapping ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የተማሪዎችን የምዘና እና የፈተና ውጤት ግምገማ እና ትንተና ሪፖርቶች በመጠቀም የተማሪዎች ውጤት የሚሻሻልበትን ሥልት መቀየስ እና መተግበር፣

የትምህርት ዘርፉን ያልተማከለ ሥርዓት ለማዘመን የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የጥናት እና ምርምር ሥራዎች ለማካሄድ የአሠራርና የአደረጃጀት ሠነዶችን በማዘጋጀት በየጊዜው እየፈተሹ ተግባራዊ ማድረግ፣ በጥናት እና ምርምር ሥራዎች የተለዩ ክፍተቶችን ለመድፈን የሚያስችሉ ሥልጠናዎችን የመስጠት፣ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎች የመተግበር እንዲሁም የመሠረተ ልማት እና የግብዓት ችግር ያለባቸውን ተቋማት በመለየት ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ፣ የተመዘገበውን ለውጥ መገምገም እና የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ፣ የትምህርት አመራርና ባለሙያውን የአቅም ክፍተት በጥናት በመለየት የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥልጠናዎች የሚሰጡበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ የትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን ማሳደግ የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እና በክልሉ የትምህርት እና ሥልጠና ፈንድ /Education Development Trust Fund/ እንዲቋቋም ማድረግ፣ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች በፍትሐዊነት ለማድረስ የሚያስችሉ ሥልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፣ የሴቶች፣ ልዩ ድጋፍ የሚሹና ስደተኞች (ተፈናቃዮች) ትምህርት ተደራሽነት፣ ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ የአዎንታዊ ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፣

ወጣቶችን እና ጎልማሶችን መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለማድረግ የሚዘረጋውን ፖሊሲና ስትራቴጂ መጠቀም፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞችን ተደራሽ ለማድረግ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን ማስፋፋት፣ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞች ተቋማዊ አደረጃጀት ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣ የተከታታይ (የማታ እና የርቀት) ትምህርት ፕሮግራም ተደራሽነት የሚያሳድግ ሥርዓት መዘርጋት፣ በሁሉም የቅድመ መደበኛ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ እና ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ የማበረታቻና የመደገፊያ ሥልት መዘርጋት እና መተግበር፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጥ ራሱን የቻለ የተጠናከረ አመራርና አደረጃጀት መፍጠር፣ በዞኖች መካከል፣ በወረዳዎች መካከል እና በገጠርና በከተማ አካባቢዎች የተመጣጠነ እና ጥራት ያለው ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የትምህርት ጥራት አመልካቾችን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ መሰብሰቢያ፣ ማጠናቀሪያና የትንተና ሥርዓት መዘርጋት፣ የመምህራን፣ የትምህርት ቤቶችንና የተማሪዎችን መለያ ኮዶችን (Unique ID) በተቀናጀ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 12.3.2. ጤና ልማት እና ጥበቃ

ጤናው የተጠበቀ የሰው ኃይል ልማት ወይም ሰብዓዊ ሀብት የጉልበት ምርታማነትን በማሳደግ ፈጣን ኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ብሎም ልማትና ብልፅግናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

**ሁሉን አቀፍ የጤና አግልግሎት ጥራት እና ፍትሐዊ ተደራሽነት ማረጋገጥ፡-** ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ ጉልህ ድርሻ አለው። ጥራት ያለው ጤናን ማበልጸግና በሽታን መከላከል ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ከመከላከልና ከመቆጣጠር ባለፈ በአሁኑ ወቅት በፍጥነት እየጨመረ የመጣውን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችንና ድንገተኛ የጤና አደጋዎችን/ጉዳቶችንም ለመቆጣጠር ያስችላል። ይህም እያደገ የመጣውን የክልሉን ማህበረሰብ የጤና አገልግሎት ፍላጎት ለማሟላት እና ጤናማና አምራች ዜጋን ለማፍራት የሚያስችል ነው። ከዚህም በላይ የመሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች ፓኬጅን ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም ተጋላጭ ለሆኑት ተደራሽ ማድረግ እና አገልግሎቱን በጥራትና በፍትሐዊነት እንዲጠቀሙ በማዳረስ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን Universal Health Coverage (UHC) ማረጋገጥ ያስችላል።

**የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎችና የአደጋ ስጋት አስተዳደር ማጠናከር፡-** የህብረተሰቡ የጤና ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሻሻለ እንዲሆንና ህዝብን ከድንገተኛ የጤና አደጋ እና ከአደጋ ስጋት ተጋላጭነት ለመጠበቅ ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሆነ የትንበያ፣ የመከላከያ እና የጤና አደጋን ለይቶ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ሂደት ያካትታል። የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች ስጋት አስተዳደር ርምጃዎችን በስፋት ለመተግበር በየደረጃው ያለው የጤናው ዘርፍ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ትብብር፣ ግንኙነት እና አቅም እንዲኖር ማድረግ አስገዳጅ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ ለሁሉም የጤና ድንገተኛ አደጋዎች እና ከባድ የአደጋ ክስተቶች (health emergencies and disasters) ቅድመ ዝግጅት፣ ልየታ፣ መከላከል፣ ምላሽ ሰጪነት ላይ ትኩረት ይሰጣል። እነኚህ አደጋዎች የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ለመቀነስ የህብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች አስተዳደር እና የክሊኒካል ድንገተኛ አደጋ ክብካቤ ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል። ከዚህ ስትራቴጂክ አቅጣጫ የሚጠበቀው የህዝቡን ድንገተኛ የጤና አደጋዎች እና ከባድ የአደጋ ክስተቶች (health emergencies and disasters) ተጽዕኖ መቀነስ ነው።

**የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ አካታችነት እና ባለቤትነት፡-** በጤና እና ጤና ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በሚዘጋጁ ዕቅዶች፣ የዕቅድ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ ሂደቶች የማህበረሰቡን ንቁ ተሳትፎ ማረጋገጥ እና የባለቤትነት ስሜት ማሳደግ፣ የማህበረሰቡን ንቃተ-ጤና እና የመወሰን አቅም ማዳበር፣ ሌሎች ችግር ፈቺ የሆኑ የአማራጭ ሀሳቦችን እና ዘዴዎችን በመንደፍ እና በመተግበር ሁሉን-አቀፍ የጤና ሽፋንን (UHC) ለማፋጠን ይሠራል ። በአጠቃላይ የተሻለ ተጠያቂነት፣ የተሻለ የጤና ባህሪ እና የተሻለ የጤና ስኬት ያስመዘገበ ማህበረሰብ መፍጠር ላይ ያተኩራል።

**የመድኃኒትና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች የአቅርቦት ሥርዓትን ማጠናከር፡-** በዚህ በኩል የመድኃኒት፣ የፋርማሲ አገልግሎት እና የህክምና መሣሪያዎች አስተዳደር ሥርዓት በማጠናከር ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ውጤታማ የሆኑ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች ለህብረተሰቡ ወይም ለተጠቃሚው ሳይቆራረጡ መቅረባቸውን እና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል። በተጨማሪም የመድኃኒት ብክነትን መቀነስ እና አገልግሎት የማይሰጡ መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አካባቢውን ሳይበክሉ እንዲወገዱ ማድረግ ላይ ትኩረት ያደርጋል። የአገር ውስጥ የመድኃኒት እና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አምራቾችን ለማሳደግ ስትራቴጂ ተነድፎ ወደ ሥራ ይገባል። እንዲሁም የግዢ እና የህክምና አገልግሎት አስተዳደር ሥርዓት ወጥነት እንዲኖረው ለማድረግ በትኩረት የሚሠራ ይሆናል።

**የጤናውን ዘርፍ የቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር፡-** ይህ የትኩረት አቅጣጫ በዋናነት የሚያነጣጥረው ህብረተሰቡን ደረጃውን ካልጠበቀ የምርት አቅርቦትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ማነስ ጋር ተያይዞ ከሚፈጠር የጤና ስጋት ለመጠበቅ እንዲያስችል የጤና እና ጤና ነክ ምርቶች እና አገልግሎቶች ደህንነትና ጥራት የማረጋገጥ ሥራ ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በመሆኑም የመድኃኒት (ደህንነት፣ ጥራት፣ ፈዋሽነት፣ እና አግባብነት ያለው

አጠቃቀም)፣ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች የአፈጻጸም ብቃት፣ የምግብ ደህንነት፣ የጤና እና ጤና ነክ አገልግሎቶች በመሥፈርቱ መሠረት ያላቸው ጥራት፣ የጤና ባለሙያዎች ብቃት እና የትንባሆ እና አልኮል ቁጥጥር ላይ የሚያተኩር ነው። በሁሉም የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የአገሪቱን የጤና ቁጥጥር መሥፈርት እና የህግ ማዕቀፎች ተፈፃሚነትን በማረጋገጥ ውጤታማ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለው የቁጥጥር ሥርዓት መፍጠርን ያካትታል።

**የጤና ዘርፍ ሰው ኃብት ልማት እና አስተዳደር፡-** የሰው ኃብት አስተዳደሩ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ቅጥር፣ ሥምሪት እና የሰው ሀብት ልማት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ሴቶችን ወደ አመራር እርከኖች እንዲመጡ ማድረግ እና ማሳተፍ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ በቂ የሰው ኃይልና የሙያ ስብጥር እንዲኖር፣ የሥራ የተነሳሽነት እና ብቃት ያለው፣ ሩህሩህ እና ክብካቤ ሊያደርግ የሚችል ባለሙያ በጤናው ዘርፍ እንዲኖር ያረጋግጣል። ባለሙያዎች ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት የቅድመ አገልግሎት ሥልጠና እንዲያገኙ እና ቀጣይነት ያለው የሙያ ዕድገት ላይ ትኩረት ያደርጋል። በአጠቃላይ በዚህ የትኩረት አቅጣጫ የጤና ባለሙያ ለመሆን ፅኑ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ያለውን ባለሙያ ከመመልመል ጀምሮ የጤና ሳይንስ ተማሪዎችን በተከታታይነት ስለሙያቸው ኃሳባቸውን የሚያጋሩበት ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም በሥራ ላይ ያሉትን ደግሞ ለህዝባቸው እና ለሚንከባከቡት ህመምተኛ በቁርጠኝነት እንዲሰሩ ማነቃቃት ላይ ትኩረት ተሰጥቶት መሥራት ይጠይቃል።

**በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥና ፈጠራ /Innovation/ ማሻሻል፡-** ይህ የትኩረት አቅጣጫ በመረጃ ቴክኖሎጂ (ICT) የተደገፉ የተቋማትን፣ የሥነ-ህዝብን እና የጤና መረጃ ሥርዓት ማዕቀፎችን በመጠቀም መረጃን የማመንጨት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትንና አጠቃቀምን ማሻሻል ላይ ያተኩራል። በመሆኑም ከህዝብ እና ቤት ቆጠራ፣ ከወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ፣ ከዳሰሳ ጥናቶች፣ ቅኝቶች፣ ከምርምሮች እና ከመደበኛ የክትትል እና ግምገማ ሥራዎች የሚገኝ መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ላይ ትኩረት ያደርጋል። ከዚህም በላይ የማህበረሰቡን ጤንነትና ደህንነት ለማሻሻል የሚያግዙ አዳዲስ ሀሳቦችና የጤና ግኝቶች፣ የጤና ፖሊሲዎች፣ የአሠራር ሥርዓቶች፣ የምርት ውጤቶች፣ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም አገልግሎቶችና የአገልግሎት አሰጣጥ መንገዶች በመከተል ጥቅም ላይ ማዋልን ያካትታል። በሌላ በኩል የምርምር ግኝቶች በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥ እና አዳዲስ ሀሳቦች ለማመንጨት እንዲቻል የአሠራር ሥርዓት ማመቻቸት ያካትታል።

**የጤናውን ዘርፍ የፋይናንስ አቅም ማሳደግ፡-** ይህ የትኩረት አቅጣጫ የጤና ፍትሐዊነትን ከማስፈን አንፃር ድሀ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል የጤና አገልግት ክፍያ ወጪ መሸፈን እንዲቻል ውጤታማ አሠራሮችን መዋቅራዊ ማድረግ፣ በፈጠራ የታገዘና ቀጣይነት ያለው፣ ፍትሐዊነትንና እኩልነትን ያረጋገጠ፣ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን ማዕከል ያደረገ የፋይናንስ አቅርቦት እና የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት እንዲሁም የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ ትብብርን በማጠናከር እና ጠንካራ የጤና መድህን ኢንሹራንስ እንዲኖር በትኩረት የሚከናወን ይሆናል። ከዚህ ባሻገር በክልልና በሃገር ደረጃ የተያዘውን የጤና ግቦች ስኬት ለማረጋገጥ በቂና ቀጣይነት ያለው የፋይናንስ አቅም መፍጠር ያስፈልጋል። ይህን በማድረግ የዜጎችን የጤና ወጪ ጫና ከመቀነስ አኳያ፣ የተጠናከረ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ እንዲኖር ከማድረግ አንፃር እና ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ዕውን ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽፆ ያለው በመሆኑ በትኩረት ይከናወናል።

**የጤናው ዘርፍ መሠረተ ልማት፡-** በጤና መሠረተ ልማት ግንባታ ዙሪያ ለሚታዩ ችግሮች በቂ ምላሽ የሚሰጥ እና የህብረተሰቡን ወቅታዊ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የጤና ተቋማትን በግብዓት እና በቁሳቁስ የተሟሉ በማድረግ ተደራሽነትን ማሻሻል እንዲሁም ነባር እና አዳዲስ የጤና ተቋማት አነስተኛውን ስታንዳርድ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቁልፍ ሥራ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ ደረጃውን የጠበቀ የግንባታ ዲዛይኖችን ማዘጋጀት፣ የጤና ተቋማት መገንባት፣ ማስፋፋት፣ ዕድሳት ማካሄድ፣ ጤናና ጤና ነክ ተቋማት ማሻሻያ (Renovation) እና ጥገና ማካሄድን ያጠቃልላል። ከዚህ በተጓዳኝ የጤና ተቋማትን በመሠረተ ልማት (እንደ ውኃ እና

መብራት ያሉ) እና የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) መሠረተ ልማት በበቂ ሁኔታ እንዲኖር ማስቻል እና የግንባታ ጥራት ማረጋገጥ የዚህ አቅጣጫ ዋና ዋና አካል ናቸው፡፡

**ዲጂታል የጤና ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻል፡-** የጤናው ዘርፍ የመረጃ አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ማለትም የተገልጋዮችን መረጃ በግለሰብ ደረጃ ከማዘመን አኳያ፣ በጤናው ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች የዕለት ከዕለት ሥራቸውን ዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በዘመናዊ መንገድ ከመሥራት ጋር በተያያዘ፣ ለሥራ አመራር አካላቶች እና አጠቃላይ የጤና መረጃ ሥርዓቱን ከማዘመን እና ዲጂታይዝ ማድረግ በትኩረት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ዲጂታል ቴክኖሎጂ መጠቀም የጤና ሥርዓት ላይ የሚታዩ የአሠራር ችግሮችን ለመፍታትና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት እና የጤና ሽፋን ተደራሽነት ከማሳደግ አኳያ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ዲጂታይዜይሽን በዋናነት ለደንበኞች ወይም ለአገልግሎት ፈላጊዎች፣ ለጤና ባለሙያዎች፣ ለጤና ሥራ አመራር አካላት እና ለጤና መረጃ አያያዝ ሠራተኞች በቀላሉ አገልግሎቶችን ለማድረስ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ዲጂታል የጤና ሥርዓቶችን ለተጠቃሚዎች አመች በሆነ ዘዴ መተግበር እና በየጊዜው ማዳበር ይኖርበታል፡፡

**ባህላዊ የሕክምና አገልግሎት፡-** በአገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የባህል ህክምና ከዘመናዊው ህክምና ጋር ሲነፃ ጻር ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ከዘመናዊው መድኃኒት ጎን ለጎን እንዲሰራበት ከባህል ህክምና አዋቂዎች ጋር በትስስር መሥራት እና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ በኩል የባህላዊ ሕክምና ምዝገባ ማካሄድ፣ ፈቃድ መስጠት፣ በባህል መድኃኒት ላይ ምርምር ማድረግ፣ የባህል መድኃኒት ማምረት፣ ከባህላዊ መድኃኒት አጠቃቀም እና ልምድ ጋር በማቀናጀት ይሠራል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአገር ውስጥ ባህላዊ መድኃኒቶችን ደህንነት፣ ውጤታማነት እና ጥራት በማረጋገጥ እንዲሁም የባህላዊ መድኃኒቶች ፈዋሽዎችን ደረጃቸው የተጠበቀ እንዲሆን እና የማህበረሰቡን ጤና በማስጠበቅ ዙሪያ በትኩረት እንዲተገበር ጥረት ይደረጋል፡፡

**የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፡-** የግሉ ዘርፍ በጤናው ላይ ያለውን ተሳተፎ በተለይም ደግሞ ጥራት ያለው የህክምና አገልግሎት በመስጠት እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ በትኩረት ይከናወናል፡፡ በዚህ በኩል ተሳትፎ እንዲያደረግባቸው ከሚጠበቁት ተግባራት መካከል የአገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር፣ የመድኃኒት እና የህክምና መሣሪያዎችን ማምረት፣ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉ የግብዓት አያያዝ እና ሥርጭትን ማሻሻል፣ ለጤናው ዘርፍ ፋይናንስ ማድረግ፣ የጤና መረጃ አያያዝ ሥርዓትን ማጠናከር፣ የሰው ሀብት ልማትን ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የጤና አገልግሎት አስተዳደር እና የአመራር አቅም ግንባታን ማጠናከር እና በሌሎችም ተግባራት የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሻሻልን ዓላማ በማድረግ የሚሠራ ይሆናል፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

የጤናው ዘርፍ የአሥር ዓመት ዕቅድ ዋና ዓላማ የህብረተሰቡን የጤና ሁኔታ በማሻሻል፣ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን በማሳደግ፣ ከድንገተኛ የጤና አደጋዎች እና ችግሮች ማህበረሰቡን በመጠበቅ፣ በወረዳ ትራንስፎርሜሽን ትግበራ አስተዋጽዖ በማድረግ እና የጤና ሥርዓት ምላሽ ሰጪነትን በማሳደግ ፍትሐዊ፣ ተደራሽነትና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ማቅረብ፣ የህብረተሰቡን የጤና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና የህበረተሰቡን ንቃተ ጤና ከፍ በማድረግ ራሱን ከተለያዩ ጤና ጠንቆች እንዲጠብቅ ማስቻል ነው፡፡

የዘርፉን ዓላማ ከማሳካት አንፃር የተጣሉ ዋና ዋና ግቦችን አስመልክቶ የሚቀጥለው አሥር ዓመት የጤናው ዘርፍ የዕቅድ ዘመኑን የአፈጻጸም ደረጃ የሚያሳዩ መለኪያዎች በዋናነት Strategic pillars እና የትኩረት መስኮችን እንዲለኩ ሆነው የተዘጋጁ ሲሆን ዒላማዎቹ የተቀመጡት ዘርፉ አሁን ያለበትን መነሻ አፈጻጸም፣ በጤናው ዘርፍ ሊሳኩ የሚችሉ ጤና ነክ እና ተዛማጅ የሆኑ ዘላቂ የልማት ግቦች መዳረሻ፣ የዓለም የጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን ደረጃዎች ታሳቢ በማድረግ One Health የተባለ የስትራቴጂክ ዕቀድ ማቀጃ ሶፍትዌር በመጠቀም እና ከዘርፉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ባለሙያዎች ጋር ሰፊ ምክክር ተደርጎ የተቀመጡ ኢላማዎች ናቸው፡፡

አማካይ በህይዎት የመኖር ዕድሜ ጣሪያን ከማሻሻል አኳያ በ2012 በጀት ዓመት ከተደረሰበት ከ67.5 በመቶ ወደ 70 በመቶ ከፍ ማድረግ እንዲሁም የማህበረሰብ ጤና ተደራሽነትን በማስፋት ሁሉን አቀፍ የጤና ሽፋን ኢንዴክስ (UHC index) አሁን ካለበት ከ0.43 ወደ 0.79 ማድረስ፣ የወጣቶች ጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች ሽፋን ከ60 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣ የአፍላ ወጣቶችን እርግዝና አሁን ካለበት ከ15 በመቶ ወደ 5 በመቶ ዝቅ ማድረግ እንዲሁም የብልህ ጀምር (RICE ) ፕሮግራምን አሁን ካለበት ከ18 ወረዳዎች ሽፋን ወደ ሁሉም ወረዳዎች ለማሳደግ ግብ ተይዟል።

የእናቶችን ጤና ከማሻሻል አንፃር የእናቶች ሞት ምጣኔን ከ401/100,000 በህይዎት ከሚወልዱ እናቶች ወደ 140 መቀነስ፣ የቤተሰብ ዕቅድ ምጣኔ (CPR) ከ50 በመቶ ወደ 55 በመቶ ማሳደግ፣ 4 ጊዜ የቅድመ ወሊድ ክትትል ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን ከ50 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በሠለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ47 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በቀዶ ጥገና የሚወልዱ እናቶች ሽፋን ከ4 በመቶ ወደ 12 በመቶ ማሳደግ፣ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ከ42 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ እና የማህፀን በር ካንሰር ቅድመ ምርመራ ያደረጉ ዕድሜያቸው ከ30-49 ዓመት የሆናቸው ሴቶች ሽፋን ከ16.4 በመቶ ወደ 70 በመቶ ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል።

የህፃናትን ጤና ከማሻሻል አኳያ ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ሕፃናት የሞት ምጣኔ ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ69 ወደ 33 መቀነስ፣ ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች ሕፃናት የሞት ምጣኔ ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ58 ወደ 20 መቀነስ፣ የጨቅላ ህፃናት የሞት ምጣኔ ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ46 ወደ 15 መቀነስ፣ ሞተው የሚወለዱ ጨቅላ ሕጻናት ምጣኔ ከ1,000 በህይዎት ከሚወለዱ ህጻናት መካከል ከ17 ወደ 10 ለመቀነስ የሚሉ ግቦች ተጥለዋል።

የክትባት አገልግሎትን በተመለከተ የሶስተኛ ዙር የፔንታቫለንት ክትባት ያገኙ ሕፃናት ሽፋን ከ76 በመቶ ወደ 99 በመቶ ማሳደግ፣ ሙሉ በሙሉ ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን ከ73 በመቶ ወደ 96 በመቶ ማሳደግ፣ የሁለተኛውን ዙር የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት (MCV2) ያገኙ ሕፃናት ሽፋን ከ60 በመቶ ወደ 98 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

ከዚህም በላይ የአተነፋፈስ ችግር ለሚያጋጥማቸው ጨቅላ ህጻናት resuscitation ድጋፍ ተደርጎላቸው የሚድኑ የህጻናት ሽፋን ከ73 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በጨቅላ ሕጻናት ኢንፌክሽን በሽታ (VSD) ተይዘው የታከሙ ህጻናት ሽፋን ከ38 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ የታቀዱ ሲሆን በሣንባ ምች ታመው በፀረ ተዋህሲያን የታከሙ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሽፋን ከ47 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በተቅማጥ በሽታ ይጠቃሉ ተብሎ ከሚታሰቡት ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ ሕፃናት መካከል የህይዎት አድን ህክምና (ORS & Zinc or ORS) አገልግሎት ያገኙ ሽፋን ከ15 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

ከሥርዓተ ምግብ አንፃር ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ህፃናት የመቀንጨር መጠን (stunting prevalence) ሁኔታ ከ42 በመቶ ወደ 13 በመቶ መቀነስ፣ ከአምስት ዓመት ዕድሜ በታች ያሉ ህፃናት የመቀጨጭ ምጣኔ (wasting prevalence) ከ8 በመቶ ወደ 3 በመቶ መቀነስ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል።

የተላላፊ በሽታዎች የቁጥጥር እና የመከላከል ሥራዎችን በተመለከተ የኤች.አይ.ቪ ምርመራ ውጤታቸውን ያወቁ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸውን ሰዎች ምጣኔ ከ71 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማድረስ፣ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት ህክምና ሽፋን ከ74 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒት ከሚወስዱ ውስጥ በደማቸው ያለው የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ መጠን በሚሊ ሊትር ከ1,000 ኮፒ በታች የሆኑት (viral suppression) ከ46 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የሁሉም ዓይነት የቲቢ በሽታ ልየታ መጠን ከ54 በመቶ ወደ 92 በመቶ ማሳደግ፣ የቲቢ ህክምና ሙሉ ለሙሉ ያጠናቀቁ የቲቢ ህሙማን ሽፋን ከ61.8 በመቶ ወደ 97 በመቶ ማሳደግ፣ መድኃኒት የተላመደ ቲቢ

ልየታ ከ59 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ መድኃኒት የተላመደ ቲቢ ህሙማን ከበሽታው የመዳን መጠን ከ82 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማድረስ፣ በወባ በሽታ የመያዝ ምጣኔ ከ1,000 ሰዎች መካከል ከ18 ወደ ዜሮ (0) ማውረድ፣ በወባ በሽታ ምክንያት የሚደርስ ሞት ምጣኔ ከ100,000 ሰዎች መካከል ከ0.02 ወደ ዜሮ (0) ማውረድ የሚሉ ግቦች ተጥለዋል፡፡

ትኩረት የሚሹ የቆላ በሽታዎች ህክምናን በተመለከተ የአይን ሞራ ግርዶሽ (ካታራክት) ቀዶ ህክምና ያገኙ ሰዎች ቁጥር ከ1 ሚሊየን ህዝብ መካከል አሁን ካለበት 539 ወደ 2,000 ማሳደግ፣ ዕድሜያቸው ከ1-9 ዓመት የሚሆናቸውን ህጻናት የትራኮማ ኢንፍላሜሽን Follicular (T.F) ሥርጭት ከ5 በመቶ በታች ያወረዱ ወረዳዎች ብዛት ከ51 ወደ 166 (100 በመቶ) ማሳደግ፣ ዕድሜያቸው ከ1-9 በታች በሆኑ ህጻናት ላይ የTrachomatous Inflammation Follicular (T.F) ሥርጭት ከ26.3 በመቶ ወደ  ከ5 በመቶ በታች መቀነስ፣ ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች በሆኑ ተጋላጭ ህጻናት ላይ የዋራ /Onchocerciasis/ በሽታ ሥርጭትን ከ0.1 በመቶ በታች ማድረስ፣ በ5-14 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ ሕፃናት መካከል ከባድ እና መካከለኛ በአፈር ንክኪ የሚተላለፉ ጥገኛ ትላትሎች ብክለት /soil transmitted helmentiasis/ ሥርጭት መጠንን  ከ20 በመቶ በታች መቀነስ፣ ዕድሜያቸው ከ6 እስከ 7 ዓመት በሆኑ ሕፃናት የሊምፋቲክ ፊላርያሲስ ማይክሮፊላሪሚያ (lymphatic filariasis microfilaraemia) ሥርጭትን ከ1 በመቶ በታች ማድረስ፣ የቪዘራል ሊሽማንያሲስ በሽታ የመግደል ምጣኔ (case fatality rate) ከ3.4 ወደ 3 በመቶ በታች ዝቅ ማድረግ፣ ዕድሜያቸው ከ5-14 ዓመት ለሆኑ ሕፃናት የሺስቶሶሚያሲስ /Schistosomiasis/ መካከለኛ እና ከፍተኛ ተጽዕኖ /infection intensity/ ከ10 በመቶ በታች ለማድረስ ታቅዷል፡፡

ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ያለ ዕድሜ የሚከሰት የሞት ምጣኔ ከ20 በመቶ ወደ 10 በመቶ መቀነስ፣ የደም ግፊት ልየታ ከተሰራላቸው ውስጥ ከፍተኛ ደም ግፊት ያለባቸው ህክምና አገልግሎት የሚያገኙ አዳዲስ ታካሚዎችን ከ45 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማድረስ፣ በልየታ ወቅት የተገኙ አዲስ የሰኳር መጠናቸው ከፍተኛ የሆነባቸው ሰዎችን ህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሽፋንን ከ46 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣ ዕድሜያቸው ከ30- 49 ዓመት ለሚገኙ ሴቶች የማህፀን በር ጫፍ ካንሰር ቅድመ ምርመራ አገልግሎትን ከ2 በመቶ ወደ 70 በመቶ ማድረስ፣ የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ቅድመ ምርመራ አድርገው በሽታው የተገኘባቸውና ህክምና ያገኙ ሽፋንን ከ70 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማድረስ፣ በአዋቂዎች የዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍል መካከል የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን ከ26 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ በአዋቂዎች የዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍል መካከል የሚከሰት የስኳር በሽታን የመቆጣጠር ሽፋን ከ24 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ የድባቴ የአዕምሮ ህመም ህክምና አገልግሎት ሽፋን ከ5 በመቶ ወደ 60 በመቶ ማሳደግ፡፡

የጤና አገልግሎት አቅርቦት ጥራት ከማሻሻል አንፃር በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አዎንታዊ ምላሽ ያላቸው ታካሚዎች ሽፋን ከ33 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማሳደግ፣ በጤና ተቋም የሚከሰት የሞት ምጣኔ ከ2.1 በመቶ ወደ ከ1 በመቶ በታች ማድረስ፣ የተመላላሽ ህክምና አገልግሎት ምጣኔ ከ1.3 ወደ 3.5 ማሳደግ፣ የአልጋ መያዝ ምጣኔ ከ48 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ የድንገተኛና መሠረታዊ ቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ጣቢያዎች እና የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ሽፋን ከ8 በመቶ ወደ 33 በመቶ ማሳደግ፣ ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማትን (PHCUs) ሽፋን ከ8 በመቶ ወደ 80 በመቶ ማድረስ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ መመሪያን (EPHCG) ተግባራዊ የሚያደርጉ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና እንክብካቤ አሃዶችን ከ85 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ አጠቃላይ የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ኬላዎች ሽፋን ከ0 ወደ 25 በመቶ ማሳደግ እና ከሚሰበሰብ ደም ውስጥ የደም ተዋጽኦን (blood component production) ከ2.4 በመቶ ወደ 65 በመቶ ማሳደግ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል፡፡

የህክምና ግብዓቶች አቅርቦት ማሻሻልን በተመለከተ የመሠረታዊ መድኃኒቶች አቅርቦት በጤና ተቋማት በየደረጃቸው ከ20 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በህክምና ግብዓት በአቅራቢ ድርጅቶች የአቅርቦት ምጣኔ ከ45

በመቶ ወደ 95 ማድረስ፣ በክልሉ የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጡ ጤና ተቋማት መመሪያ ባስቀመጠው መሠረት የምርመራ ዓይነት (Test menu) ሙሉ በሙሉ በሁሉም ጤና ተቋማት (100 በመቶ) እንዲሰጡ ማድረግ የሚሉ ግቦች ተካተዋል፡፡

የጤና ቁጥጥር ሥርዓትን ከማሻሻል አኳያ ጥራታቸው ያልተጠበቀና ህገወጥ መድኃኒት በገበያ ላይ ሥርጭት ሽፋን ከ8.6 በመቶ ወደ 5 በመቶ መቀነስ፣ ደህንነታቸው ያልተጠበቀና ህገወጥ ምግብ በገበያ ላይ ያለውን ሥርጭት ሽፋን ከ40 በመቶ ወደ 0 መቀነስ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል፡፡

የጤና መሠረተ ልማት ጥራትን ከማሳደግ አኳያ የተሻሻለ የውኃ አቅርቦት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ከ20 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የኤሌትሪክ አቅርቦት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ሽፋን ከ25 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ መሠረታዊ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ሽፋን ከ47 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ የጤና ተቋማትን ደረጃ ስታንዳርድ ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን ወደ 100 በመቶ ማሳደግ እና የተሻሻለ መጸደጃ ያላቸው ጤና ተቋማት (ጤና ኬላን ጨምሮ) ሽፋን ከ46 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፡፡ የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ማሻሻልን በተመለከተ ሁሉም ዓይነት መፀዳጃ ቤት ያላቸው አባዎራዎች/እማዎራዎች ሽፋን ከ58 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ ዘወትር በወሳኝ ጊዜያት እጃቸውን በአግባቡ የሚታጠቡ ቤተሰቦች ሽፋን ከ34 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ ሜዳ ላይ ከመጸዳዳት ነፃ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋን ከ19 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሳደግ፣ የሞዴል ቤተሰቦች ሽፋን ከ45 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ የሞዴል ቀበሌዎችን ብዛት ከ687 ወደ 4000 ማሰደግ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል፡፡

የጤና መረጃ ሥርዓትን ከማሻሻል አንፃር የሪፖርት ሙሉነትን ከ97 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ የሪፖርት በጊዜ መድረስን ከ 65 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማድረስ፣ የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ መሥፈርትን ያሟሉ ጤና ተቋማት ሽፋን (data verification factor within 10 በመቶ range for selected indicators) ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የውልደት ማሳወቅ (በተቋም ከተወለዱ ህጻናት) ሽፋን ከ92 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ የሞት ማሳወቅ (በተቋም ውስጥ ሞት) ሽፋን ከ47 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ የጤና አደጋዎች ደህንነት ኢንዴክስ ከ0.63 ወደ 0.9 ማሳደግ፣ በስታንዳርዱ መሠረት በቁጥጥር ሥር የዋለ የጤና ወረርሽኝ ከ56 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣

የጤና አገልግሎትን በፋይናንስ ከመደገፍ አኳያ ከተያዙት ግቦች መካከል ከአቅም በላይ የሆነ የጤና ወጪ ክስተት ከ2.1 በመቶ ወደ 1.5 በመቶ መቀነስ፣ ለጤና አገልግሎት ከኪስ የሚወጣ ወጪ (out of Pocket Expenditure) ከ31 በመቶ ወደ 20 በመቶ መቀነስ፣ የማህበረሰብ አቀፍ የጤና መድን ሥርዓት ሽፋን (ቤተሰቦች) ከ80 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ በማህበራዊ የጤና መድን (SHI) የታቀፉ ሠራተኞች ሽፋን ከ0 ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ መንግሥት ለጤና ዘርፍ የሚመድበውን በጀት ድርሻ (GGHE) ከጠቅላላው የመንግስት ወጪ (GGE) አንፃር ከ15 በመቶ ወደ 20 በመቶ ከፍ ማድረግ፣ ከስድስት ወር በላይ የሆነ የተራድኦ በጀት ማወራረድ ዓቅምን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ የፋይናንስ ሥርዓቱን በማዘመን የኦዲት ግኝቶችን ወደ 0 ማድረስ፣ የጤና ኬላ ለህዝብ ጥምርታን ከ6,232 ወደ 4,000 ማድረስ (ከ3,565 ወደ 7,500 የጤና ኬላዎችን ብዛት በማድረስ) ማድረስ፣ የጤና ጣቢያ ለህዝብ ጥምርታን ከ25,745 ወደ 20,000 ማድረስ (ከ874 ወደ 1,500 የጤና ጣቢያዎች ብዛት በማድረስ፣ የማህበረሰብ ስኮር ካርድ የተገበሩ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋማት ሽፋን ከ79 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ፣ የጤና ባለሙያ ህዝብ ጥምርታ በ1000 ህዝብ ከ0.96 ወደ 4 ማድረስ የሚሉ ግቦች ተይዘዋል፡፡

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

የጤና ዘርፍ መሪ ዕቅድ እና የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ሥልቶችተዘጋጅተው የቀረቡ ሲሆን እነሱም እንደሚከተለው ተመላክተዋል፡-

የጤናውን ዘርፍ የመሪ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የዘርፉን አመራሮች እና ፈጻሚዎች በማቀናጀት የጤናውን ዘርፍ ርዕይና ተልዕኮ እንዲያሳኩ በተለዩት አምስት አጀንዳዎች መሠረት በማድረግ የተለያዩ የግምገማ መድረኮችን በመፍጠር በመደበኛነት የክትትል እና ድጋፍ ሥራዎችን በማጠናከር እና የተቀናጁ ጥረቶች በማድረግ በዕቅድ አተገባበር ዙሪያ ተጠያቂነትን በሚያሰፍን መልኩ በመተግበር፣ ወረዳን መሠረት ያደረገ የጤናው ዘርፍ ዕቅድ ሂደት ላለፉት አሥርት ዓመታት በየደረጃው እንዲታቀድ በማድረግ ሲተገበር ቆይቷል። በዚህ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመውሰድ የመሪ ዕቅዱን እና የወረዳ ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን ወደ ተግባር መቀየር፣ በጤናው ዘርፍ በየደረጃው ያለው ተቋማዊ የመዋቅር ችግርን ለመመለስ ዝግጅት ማድረግን የሚመለከት ሲሆን ጥራት እና ፍትሐዊነት ያለው የጤና ሥርዓት ለመዘርጋት ተቋማዊ የመዋቅር ለውጦችን ታሳቢ በማድረግ፣ በመረጃ ላይ ተመሥርቶ የዘርፉን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ከማጠናከር በተጨማሪም ከክትትልና ምዘና የሚገኙ መልካም ሥራዎች አጠናክሮ መቀጠል፣ አዳዲስ አሠራሮችን እና ፈጠራዎችን ወደ ዘርፉ በማስገባት ተግባራዊ ማድረግ፣ መፍትሔ አምጪ የሆኑ ፈጠራዎች ተግባራዊ ማድረግ፣ ዘርፈ ብዙ ትብብርን በማጠናከር እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎን በማጎልበት የትብብር ማዕቀፎችን መተግበር፣ የሁለተኛውን ምዕራፍ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በማድረግ የዘርፉ የሰው ኃይል ብዛት፣ ክህሎትና የሙያ ስብጥር እንዲሻሻል በማድረግ በተለይም በጤና ባለሙያው ፍልሰት ሳቢያ የሚፈጠረውን የባለሙያዎች እጥረት ለመቅረፍ በጥናት ላይ የተመሠረተ የባለሙያዎች ሥልጠና ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር ተቀናጅቶ መሥራትና የግሉ ዘርፍ በመዳኃኒትና በህክምና መገልገያ ቁሳቁስ ማምረት፣ የመረጃ አያያዝ፣ የሰው ኃይል ልማትና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ እና በሌሎች ክፍተት በሚታይባቸው የጤና ዘርፍ አገልግሎትና መሠረተ ልማቶች ዙሪያ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር የሚሉት ናቸው።

### 12.3.3. ስፖርት ልማት

ህዝባዊ መሠረት ያለው ስፖርት በክልሉ እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ የህበረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እንዲሁም የነቃ ማህበረሰብ እና አሸናፊ ክልልን በመገንባት ስፖርት የልማት መሣሪያ ሆኖ የክልሉን ብልፅግና እንዲያረጋግጥ መሥራት የዘርፉ ሚና ይሆናል፡፡

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

**የስፖርት መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት፡-** የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችና የማሠልጠኛ ማዕከላት ተደራሽነት፣ ህጋዊነት እና የጥራት ደረጃ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱን ተከትሎ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እና የማሠልጠኛ ማዕከላት ከሕብረተሰቡ ቁጥር አንፃር ቁጥራቸውን በማሳደግ እና በአዋጅ ቁጥር 729/2004 መሠረት አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግላቸው በማድረግ የአገር አቀፍ እና የክልል አቀፍ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የሚገነቡበት እና የሚስፋፉበት ሥልት ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

**የህብረተሰብ ስፖርት ተሳትፎን ማጎልበት፡-** በክልላችን በርካታ የህብረተሰብ ክፍል ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የመጠቃት ዕድሉ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ ጤናማ፣ ንቁ እና አምራች ዜጎችን ለመፍጠር በቀጣይ አሥር ዓመታት ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ስፖርት እንቅስቃሴ ፕሮግራሞች እና ኩነቶችን ሥራ ላይ በማዋል የነቃ ማህበረሰብ መፍጠር ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል፡፡

**የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን ማጠናከር፡-** በአገር አቀፍ እና ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድር መድረኮች ክልላችንን የሚወክሉ ተተኪ ስፖርተኞችን በተፈጥሮ ብቃት ላይ በተመሠረተ ሳይንሳዊ የስፖርት ሥልጠናዎች ማፍራት እና የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎችን ወጥ በሆነ የሥልጠና ሥርዓት በማብቃት በቀጣይ ዓመታት በስፖርቱ ዘርፍ አሸናፊ ክልል መፍጠር ትኩረት የሚሠጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

**የግል ዘርፉን ተሳትፎ ማጎልበት፡-** ስፖርትን ቀስ በቀስ ከመንግስት ድጎማ ለማላቀቅ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና ሊጫወት የሚችለውን የግሉን ዘርፍ በስፋት ለማሳተፍ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡

**ስፖርትን ለማህበራዊ ልማትና ለአገር ብልፅግና ማዋል፡-** ስፖርትን ለልማት ለማዋል የሚያስችል አደረጃጀትና ሥርዓት በመፍጠር፣ በዘላቂነት ችግሮችን በመፍታት ስፖርት ለማህበራዊ ልማትና ለአገር ብልፅግና፣ ህዝቦችን ለማቀራረብ፣ ለገጽታ ግንባታ እና ለቱሪዝም ዕድገት እንዲሁም ከአጎራባች ክልሎችና እና ሀገሮች ህዝቦች ጋር አንድነትን ለማምጣት መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ይሆናል፡፡

**ሀብት (Resource)፡-** በዚህ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ የስፖርቱን ልማት መሠረት ያደረገ የሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት ልማት ግንባታን ማሳደግ፣ ለሴክተሩ የአሥር ዓመት ዕቅድ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊና የፋይናንስ ሀብቶች ማሳደግ እና አጋርነትን ማጠናከር ላይ ማዕከል ያደረገ ነው፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዓላማ የስፖርት ልማትን በማስፋፋት በአገር አቀፍ መድረኮች ተፎካካሪና አሸናፊ በመሆን ኤሊት ስፖርተኞችን ማፍራት ሲሆን ለተግባራዊነቱም የስፖርት ማህበራትን ማደራጀትና ማጠናከር፣ ህዝባዊ እና መንግስታዊ የስፖርት ተቋማት ሰብዓዊ ሀብትን በማልማት የአሠራር ሥርዓቶችን በማሻሻልና አደረጃጀቶችን በማጠናከር ክልል አቀፍ እና አገር አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ተቋማትን ከ6,334 ወደ 9,459 ለማሳደግ እንዲሁም በየደረጃው በሁሉም የሀብት ማግኛ መንገዶች በመጠቀም ገቢን ከ17.42 ሚሊየን ወደ 2.43 ቢሊየን በማድረስ ተቋማዊ የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ የሚሠራ ይሆናል፡፡ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እና የሥልጠና ማዕከላት ማስፋፋትና ማሳደግን በተመለከተ ቁጥራቸውን ከ6,501 ወደ 8,440 በማሳደግ ህጋዊነታቸውን ለማረጋገጥ እና ተደራሽ ለማደረግ የሚሠራ ይሆናል፡፡

ተደራሽ እና ፍትሐዊ የሆነ የማህበረሰብ ስፖርትን በማስፋፋት ስፖርቱን ባህሉ ያደረገ ንቁ፣ ጤናማና አምራች ዜጋን ለመፍጠር በየደረጃው የሚሳተፈውን ህብረተሰብ ቁጥር ከ757,483 ወደ 6,000,000 በማሳደግ የተሳትፎ ሽፋኑን ከ9 በመቶ ወደ 20 በመቶ የማድረስ እንዲሁም በስፖርት ለሁሉም መዝናኛና ባህል ስፖርቶች ህብረተሰቡን በማሳተፍ ስፖርት ለሁለንተናዊ የአገር ዕድገት ያለውን ሚና የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ በሌላ በኩል የታዳጊና የባለሙያ ሥልጠና በመስጠት ውጤታማ ስፖርተኞችን የማፍራት እንዲሁም የባለሙያዎችን አቅም በማጎልበት በክልል አቀፍ፣ አገር አቀፍ፣ አህጉርና ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ውጤት የሚያስመዘግቡ አትሌቶችን ለማፍራት ይቻል ዘንድ በትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የባለሙያዎችን ቁጥር ከ4,578 ወደ 13,857 የማሳደግ እንዲሁም የታዳጊ ሥልጠና ፕሮግራምን ከነበረበት 6,579 ሠልጣኞች ወደ 10,000 የማሳደግ ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የስፖርታዊ ውድድር መድረኮችን በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የተዘጋጁ ክልል አቀፍ የውድድር መድረኮችን ከ28 ወደ 30 ከፍ በማድረግ የኤሊት ስፖርተኞችን ቁጥር ለማሳደግ እንዲሁም በስፖርት አበረታች ቅመሞችና በሰፖርት ሳይንስ ህክምና ዙሪያ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር የምርመራ እና የቁጥጥር ሥራዎች በማከሄድ ዶፒንን የመከላከልና ሁለንተናዊ ስዕብናቸው የተገነባ ስፖርተኞችን የመፍጠር ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡ በሌላ በኩልም የስፖርት ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት በዘርፉ የሚሰማራውን የባለሀብት ቁጥር ከ409 ወደ 700 ለማሳደግ የሚሠራ ይሆናል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

ስፖርቱን ለማጠናከር የስፖርት ሀብቶችን ማፈላለጊያ ፈንድ ጽ/ቤት ማደራጀት፣ የህብረተሰቡን የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበትና ህዝባዊ ንቅናቄ ለመፍጠር ፌስቲቫሎችንና ሁነቶችን ማዘጋጀት፣ የስፖርት ፋሲሊቲዎችንና የስብዕና

ማዕከላትን ለማስፋፋትና ለማደራጀት አዋጅ የወጣላቸውን ሥራ ላይ ለማዋል ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር የጋራ ሥምምነት በመፍጠር አዋጅ ያልወጣላቸውን እንዲወጣላቸው የማድረግ ሥራዎች መሥራት፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የቅንጅትና ትብብር ሥርዓትን ማሳደግ፣ ተቋማዊ የመዋቅር አደረጃጀትን መፍጠር፣ የተለያዩ ህዝባዊ አደረጃጀቶችን እንዲቋቋሙ መደገፍና ማጠናከር፣ የአሠራር ማዕቀፎች ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም የተጠያቂነትና ውጤታማ የተግባቦት ሥርዓትን መዘርጋት በዕቅድ ዘመኑ በሴክተሩ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶችናቸው።

## 12.4 ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 12.4.1 የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ

የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በትኩረት መሥራት፣ የሥርዓተ ፆታ እኩልነት የሰፈነበት፣ የህፃናት መብት የተከበረበትና ደህንነታቸው የተጠበቀበት ህብረተሰብ እንዲፈጠር አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ እንዲሁም ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለአረጋውያንና ለአካል ጉዳተኞች የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት መሥራት፣ የማህበራዊ ጥበቃ እና የማህበራዊ ደህንነት ሥርዓትን በመዘርጋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እና የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን ጉዳይ እያንዳንዱ ተቋም አካቶ እንዲሰራ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ የዘርፉ ዋና ዋና ሚናዎች ናቸው። በመሆኑም በዕቅዱ ዓመታት ዘርፉ ሚናውን በሚገባ እንዲወጣ የሚጠበቅ ይሆናል።

### የትኩረት አቅጣጫዎች

የዘርፉ የአሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ በዋናነት መብት (Right)፣ ውክልና (Representation) እንዲሁም ሀብት (Resource) ላይ ያተኮረ ይሆናል። ስለሆነም፡-

**ከመብት አኳያ** የሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ተፈጥሮአዊ፣ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩላቸው የማድረግ፣ አገራችን ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዙሪያ የፈረመቻቸውን አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥምምነቶችና ቃልኪዳኖችን ተግባራዊነት የማረጋገጥ፣ በሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ከባህልና ወግ ተቃራኒ የሆኑ መጤ ባህሎችን፣ ሱሰኝነትን፣ ብዝበዛና አድሎዎችን፣ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ማስቀረት ላይ በትኩረት መሥራት፣ የሴቶችን፣ ህጻናትን የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን በነፃ ፍላጎት የመደራጀት መብት የማረጋገጥ እንዲሁም ለሴቶች፣ ለህፃናትና አረጋውያን የተሰጡ ሁለንተናዊ መብቶች በህበረተሰቡ ተቀባይነት እንዲኖራቸውና እንዲከበሩ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

**ከውክልና አኳያ** ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በየደረጃው በሚካሄዱ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መስኮች ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ፣ መንግስታዊና ሲቪል የማህበረሰብ ድርጅቶች የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋውያንን ጉዳይ የማካተትና ተቋማዊነትን የማረጋገጥ፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች በመረጧቸው አደረጃጀቶች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማሳደግ፣ በቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማጎልበት እንዲሁም በህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚና ህግ ተርጓሚ አካላት በየደረጃው የሚኖራቸውን ውክልና ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ይደረጋል።

ከሀብት አኳያም  በሴቶች፣ በህፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋውያን እና በሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ መሠረት ያደረገ የሰብዓዊ ልማት ግንባታን ማሳደግ፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ሌሎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ከክልሉ አጠቃላይ ልማት የሚኖራቸውን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና

የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጥ፣ ለተቋሙ የአሥር ዓመት ዕቅድ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊና የፋይናንስ ሀብቶችን ማሳደግና አጋርነትን ማጠናከር የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዓላማ የሴቶችን እና የህጻናትን መብት፣ ውክልና እና ተጠቃሚነት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ መስኮች ማረጋገጥ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና አገልግሎቶችን በማስፋፋት ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፍትሐዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት፡-

**የሴቶችና ህፃናትን መብትና ሁለንተናዊ ደህንነት ማስጠበቅ፡-** በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርሱባቸውን ጥቃቶች እና የሚፈጸሙባቸውን ጎጂ ልማዳዊ ድርቶች በማስወገድ የሴቶች አካላዊ ጥቃት ምጣኔን ከ24 በመቶ፣ የሴቶች ወሲባዊ ጥቃት ምጣኔን ከ10 በመቶ እንዲሁም የሴቶች ስነ-ልቦናዊ ጥቃት ምጣኔን ከ24 በመቶ ወደ 5 በመቶ የመቀነስ ግብ ተቀምጧል፡፡ የህፃናት ያለዕድሜ ጋብቻ ምጣኔን ከ43 በመቶ ወደ 0 ለመቀነስ የሚሠራ ሲሆን የሴት ልጅ ግርዛት ምጣኔን ከነበረበት 62 በመቶ እና ያለዕድሜ ጋብቻ ምጣኔን ከነበረበት 43 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ግብ ተጥሏል፡፡

በሴቶችና ህጻናት ላይ ከሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ነፃ የሆኑ ቀበሌዎችን ድርሻ ከ11 በመቶ ወደ 100በመቶ ማሳደግ፣ የጥቃት ሰለባዎች ድጋፍ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ድርሻ 90 በመቶ ማድረስ፣ በአደጋ ጊዜ ነፃ የስልክ ጥሪ አገልግሎት ተደራሽ የሆኑ ሴቶችን ድርሻ 90 በመቶ ማድረስ፣ የሴቶችን፣ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋዊያንን ጉዳይ ተቋማዊ ያደረጉ ተቋማትን ቁጥር ከ0 ወደ 7 ማሳደግ፣ የተቋቋሙ የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላትን/one stop service/ ከነበሩበት 2 ወደ 16 ማሳደግ፣ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ማረፊያዎችን (Safe house) ከነበረበት 0 ወደ 6 ማዕከላት ማሳደግ፣ የተጠናከሩ የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት/one stop service/ ብዛትን ወደ 16 ማሳደግ፣ እንዲሁም የተቋቋሙ የሴቶች የተሃድሶ መስጫ ማዕከላትን ቁጥር ከ0 ወደ 1 ማሳደግ የሚሉት ግቦች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

በመደራጀት መብትና ጥቅማቸውን ያስጠበቁ ሴቶችን ድርሻ 70 በመቶ ማድረስ፣ ለሴቶች ተሳትፎ አዎንታዊ አመለካከት ያለውን ህብረተሰብ ወደ 80 በመቶ ማድረስ፣ በበጎ ፈቃድ የአገልግሎት መስኮች ላይ የተሰማሩ ሴቶችን ከ1.3 ሚሊየን ወደ 2.66 ሚሊየን ማድረስ፣ የልደት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ልጆችን ድርሻ ከ17 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ በተቋማት የተቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችን ቁጥር ከ29 ወደ 120 ማሳደግ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የተቋቋሙ የህጻናት ማቆያዎችን ቁጥር ከ0 ወደ 23 ማሳደግ፣ በአገር ውስጥ አማራጭ ፕሮግራሞች የተደገፉ ህፃናትን ቁጥር 2,256,319 ማድረስ፣ በተሀድሶ ማዕከላት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት ድርሻን ከ0 ወደ 50 በመቶ ማድረስ፣ ወደ ጎዳና የሚወጡ ህፃናትን 100 በመቶ መቀነስ፣ የኢኮኖሚ ድጋፍ ያገኙ ቤተሰቦችን በቁጥር 5,000 ማድረስ፣ በልጆች ላይ የተፈጸመ ወንጀልን 20 በመቶ ማድረስ፣ የህፃናት ህገወጥ ዝውውር ምጣኔን 2 በመቶ ማድረስ፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ምጣኔን ከ55 በመቶ ወደ 20 በመቶ ማድረስ፣ ጥቃት ደርሶባቸው የተሀድሶ አገልግሎት ያገኙ ህፃናትን ምጣኔን 50 በመቶ ማድረስ እንዲሁም ጥቃት ደርሶባቸው የተቀናጀ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን ድርሻ 90 በመቶ ማድረስ በትኩረት ለመተግበር የተቀመጡ ግቦች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአደጋ ጊዜ የስልክ ጥሪ መስመር /hot line/ አገልግሎቱን ለማግኘት ተደራሽ የሆኑ ህፃናትን ድርሻ 80 በመቶ ማድረስ፣ በህጻናት የሚፈጸም ወንጀል ምጣኔን 10 በመቶ ማድረስ፣ ተስማሚ የህፃናት ችሎቶችን ቁጥር ከ30 ወደ 115 ማድረስ፣ ህግ ተላልፈው የተሀድሶ አገልግሎት ያገኙ ህፃናት ድርሻን 70 በመቶ ማድረስ፣ በድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ድርሻን 50 በመቶ ማድረስ፣ በተሻለ የህፃናት አያያዝና አስተዳደግ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት ድርሻን 50 በመቶ ማድረስ፣ በምቹና ተስማሚ የህፃናት የቀን ማቆያ ተጠቃሚ

የሆኑ ህፃናት ድርሻ 70 በመቶ ማድረስ፣ ህፃናትን ያሳተፉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ቁጥር 40 በመቶ ማድረስ፣ ለትምህርታቸው አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ህፃናት ድርሻን 80 በመቶ ማድረስ፣ ለብዝህነት በጎ አመለካከት ያላቸው ሕጻናት ድርሻን 75 በመቶ ማድረስ የሚሉት ግቦች የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

**የሴቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን ተሳትፎንና ውክልናን ከማረጋገጥ አኳያ** ለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ህፃናትን ድርሻ 75 በመቶ የማድረስ፣ በውይይት ውስጥ በንቃት መሳተፍ የሚችሉ ሕጻናትን ድርሻ 50 በመቶ የማድረስ፣ ከቤተሰቦቻቸው /ከማህበረሰቦቻቸው ጋር ጤናማ ግንኙነት ያላቸው ህፃናትን ድርሻ 80 በመቶ የማድረስ፣ ትምህርት ቤታቸው ከጥቃትና መድልዎ ነፃ ነው ብለው የሚያምኑ ህፃናትን ድርሻ 100በመቶ የማድረስ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው ህፃናትን ድርሻ 90 በመቶ የማድረስ እንዲሁም የህፃናት ጥቃት ምጣኔን ወደ 10 በመቶ ዝቅ የማድረግ ግቦች በከፍተኛ ትኩረት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የተቋቋሙ የህፃናት የተሃድሶ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በቁጥር ከ0 ወደ 1 ማሳደግ፣ ለህፃናት ተሳትፎ አዎንታዊ አመለካከት ያለው ህብረተሰብ ድርሻን 80 በመቶ ማድረስ፣ የተደራጁ የህፃናት ፓርላማዎችን ቁጥር ከ3,592 ወደ 3,939 ማሳደግ፣ በህፃናት ፓርላማዎች ንቁ ተሳትፎ ያደረጉ የህፃናት ድርሻን 100 በመቶ ማድረስ፣ የህፃናት ተወካዮችን ያሳተፉ የህዝብ ምክር ቤቶችን ድርሻ 95 በመቶ ማድረስ፣ የማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ድጋፍ ያገኙ የህፃናት ቤተሰቦችን ቁጥር 100,000 ማድረስ፣ በስብዕና ማዕከላት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን ድርሻ 50 በመቶ ማድረስ፣ በአስፈፃሚ አካላት የሴቶች ውሳኔ ሰጪነትን ድርሻ ከ20 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣ በአመራር ሰጭነት የሴቶች ድርሻን በክልል በከፍተኛ አመራር የሚኖራቸውን ድርሻ ከ20 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በመካከለኛ አመራር ከ19 በመቶ ወደ 50 በመቶ በዞን በከፍተኛ አመራር ከ26 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በመካከለኛ አመራር ከ20 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በወረዳ በመካከለኛ አመራር ከ24 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማድረስ፣ በህዝብ ምክር ቤቶች በሴቶች የሚያዙ መቀመጫዎች ድርሻን በክልል ከ47.7 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በብሔረሰብ ዞን ከ40.63 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በወረዳ ምክር ቤት ከ47.5 በመቶ ወደ 50 በመቶ፣ በቀበሌ ምክር ቤት ከ41.34 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማድረስ እንዲሁም የተቋቋሙ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን የክትትልና ድጋፍ ኮሚቴዎችን ብዛት ወደ 215 ማድረስ የሚሉት ግቦች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

**የሴቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞችና የአረጋዊያን ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አኳያ** ከጠቅላላ ሴት የመንግስት ሠራተኞች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ የሆኑ ሴት የመንግስት ሠራተኞችን ድርሻ ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፣ ድጋፍ የተደረገላቸው የአዳሪ ትምህርት ቤት ሴት ተማሪዎችን ከ55 ወደ 2,000 ማድረስ፣ ብድር አግኝተው በገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሳተፉ ሴቶችን ከ73 በመቶ ወደ 83 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ከ967,000 ወደ 2,681,568 ማሳደግ የሚሉት ግቦች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በቁጠባ የሚሳተፉ ሴቶችን ቁጥር ከ1.5 ሚሊየን ወደ 3,189,464 የማድረስ፣ የሴቶች የቁጠባ መጠንን ከብር 11,200,000 ወደ 2,124,886,000 የማሳደግ፣ የሴቶች የሥራ አጥነት ምጣኔን ከ28.1 በመቶ ወደ 12.4 በመቶ የመቀነስ፣ በጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የሴቶች የባለቤትነት ድርሻን ከ32 በመቶ ወደ 50 በመቶ የማሳደግ፣ በህብረት ሥራ ማህበራት በአባልነት የታቀፉ ሴቶችን ቁጥር ከ1,000,173 ወደ 2,599,070 የማሳደግ፣ የገጠር መሬት ባለቤትነት የተረጋገጠላቸው ሴቶችን ቁጥር ከ43.5 በመቶ ወደ 100 በመቶ የማሳደግ፣ በማይከፈላቸው የቤት ውስጥ ሥራዎች የሴቶችን የሥራ ሠዓት ከ15 ሠዓት ወደ 2 ሠዓት ዝቅ የማድረግ፣ በጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶችን ቁጥር ከ1,132,063 ወደ 2,318,632 የማሳደግ፣ የሴቶች የገበያ ማዕከላትን ቁጥር 1 የማድረስ እንዲሁም የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ምጣኔን ከ49.5 በመቶ ወደ 100 በመቶ የማድረስ ሥራዎች በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

**የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት የዜጎችን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንፃር**

የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች ተጠቃሚዎችን መረጃዎች ወጥነትና ተመጋጋቢነት ባለው መንገድ ከክልል እስከ ወረዳ አደራጅቶ ለመያዝ የሚያስችል የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት በመዘርጋት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ፍትሐዊ ተደራሽነትን ማሳደግ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አስተማማኝና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በክልል 1 የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ ጽ/ቤት በማቋቋም የዜጎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አቀናጅቶ እና አስተባብሮ ለመምራት የሚያስችል በክልል 1 የማህበራዊ ጥበቃ ምክር ቤት በማቋቋም የማህበራዊ ጥበቃ ተደራሽነትንና ሽፋንን ማሳደግ እንዲሁም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ 728,000 የቤተሰብ ተቋም ተገቢ ሚናውን የሚወጣበት አደረጃጀትንና አሠራርን ተግባራዊ በማድረግ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መቀነስ የሚሉት ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

**የአካል ጉዳተኞች፣ የአረጋዊያን እና የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ተካታችነት፣ ተሳታፊነት፣ ተደራሽነት እና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አኳያ** በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ድሀና ተጋላጭ የሆኑ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እንዲሁም ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ የሀረተሰብ ክፍሎችን (Urban Destitute) የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እና የሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚነታቸውን ሽፋን አሁን ካለበት 246,953 ወደ 320,039 የማሳደግ፣ ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙት አረጋዊያን መካከል 253,944 እና በክልሉ ትላልቅ ከተሞች የሚገኙ ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ ከሆኑ የሀረተሰብ ክፍሎች መካከል 11,503 የሥነ ልቦና እና የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በተለያዩ የሥራ መስኮች መሳተፍ ከሚችሉ ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙ አረጋዊያን መካከል 159,037፣ ከአጠቃላይ አካል ጉዳተኞች መካከል 71,277 እና በክልሉ ትልልቅ ከተሞች የሚገኙ ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ የሀረተሰብ ክፍሎች (Urban Destitute) መካከል 33,078 የትምህርት፣ የሥልጠና እና የሥራ ሥምሪት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውን እና ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ እንዲሁም ማህረሰብን መሠረት አድርገው የተዋቀሩ አደረጃጀቶች፣ የሲቪክ ማህበራት እና የንግዱ ማህረሰብ ለ6,624 አካል ጉዳተኞች፣ ለ14,125 አረጋዊያን እና ለ7,441 ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ላደረጉ ዜጎች የድጋፍ እና የእንክብካቤ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ ሥራ በትኩረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ተከታታይነት ያላቸው በየዓመቱ 3,962 ቀበሌዎች ላይ የሥልጠናና የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመፍጠር ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው አካላት ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን እና ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያድርጉትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍና እንክብካቤ ሽፋን ማሳደግ፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበርና በማቀናጀት ለአረጋዊያን እና በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን አሁን ካለበት 1 ወደ 9 ማሳደግ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከአጠቃላይ አካል ጉዳተኞች መካከል የአካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎትን አሁን ካለበት 28,322 ወደ 401,676 ለሚሆኑት እንዲሁም ከድህነት ወለል በታች ከሚገኙት ዕድሜያቸው ከ70 ዓመት በላይ የሆኑ አረጋዊያን መካከል 289,148 የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶች እንዲያገኙ በማድረግ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር እና በመምራት ከአጠቃላይ አካል ጉዳተኞች መከካል 9,000 ለሚሆኑት የኪነጥበብና የስፖርት ተሳትፏቸውን ማሳደግ፣ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር እና በመምራት ሥራ ላይ በዋሉ ህጎች ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች የሚጋፉ ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ በማድረግ አድልዎና መገለልን መቀነስ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች ኮንቬሽን ማስፈፀሚያ ዝርዝር የህግ ማዕቀፍ (Disability Act)) ህግ በማውጣት የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማሳደግ እንዲሁም የአደገኛ ዕጾችና መድሃኒቶች ተጠቃሚ ከሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች

መካከል 1 ሚሊየን ለሚሆኑት የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠት እና በማቋቋም ችግሩን መቀነስ የሚሉት ግቦች በዕቅዱ ተካተዋል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የተቀመጠውን የዘርፉን የልማት ዕቅድ ማሳካት ይቻል ዘንድ በርካታ የማስፈጸሚያ ሥልቶችበዕቅድ ዘመኑ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱና እንዲቀንሱ ለማድረግ ብሄራዊ የጥቃት አድራሾች መረጃ ሥርዓት መዘርጋት፣ ሥርዓተ ፆታ ላይ መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የመንግስትን ዜሮ የመታገስ አቋም ተግባራዊ ለማድረግ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶችንና ህፃናትን በልዩ ሁኔታ የሚመረምሩ እና ጥቃትን ለመከላከል የሠለጠኑ የፖሊስ አባላት ያሉት ግብረ ኃይል ማቋቋም፣ ፍኖተ ካርታውን መተግበርና የግንዛቤና ንቅናቄ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣ የህፃናት ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ የማቋቋም እና የኬዝ ማኔጅመንት ሥርዓቱን ተግባራዊ ማድረግ፣ የወጣቶችን የእርስ በርስ ትብብር ማሳደግ፣ የሴቶች እና ህፃናት ተሳትፎ እና ውክልናን ለማረጋገጥ የሴቶች አመራር ማዕከል፣ በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች እርስ በእርስ የሚማማሩባቸው፣ ውይይቶች የሚያካሂዱባቸው እና ልምድ የሚለዋወጡባቸው ምቹ ማዕከላት ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም ነፃና ጠንካራ የህፃናት፣ የሴት፣ የአካል ጉዳተኞች እና የአረጋዊያን አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡

በተመሳሳይ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል የልማት ፈንድ በማቋቋም ሥራ ፈጣሪ ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የህፃናት መጫወቻና መዝናኛ ሥፍራዎች ለማስፋፋት የሚያስችሉ አገራዊ ስትራቴጂያዊ ርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የቅንጅትና ትብብር ሥርዓትን ማሳደግ፣ ተቋማዊ መዋቅር ወይም አደረጃጀት መፍጠር፣ የተለያዩ የሴቶች፣ የአሠራር ማዕቀፎች ማዘጋጀትና ተፈፃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ የተጠያቂነትና ውጤታማ የተግባቦት ሥርዓት መዘርጋት በዕቅድ ዘመኑ በሴክተሩ ተግባራዊ የሚደረጉ የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

ሁሉም ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ የማካተት አገልግሎቱን ተደራሽ እንዲያደርጉ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ የቅንጅትና ትብብር ሥርዓት በመዘርጋት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣ የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን ተግባራዊነት ለማሳለጥ የተቋቋሙ ፕላት ፎርሞች፣ የማህበረሰብ ድጋፍና እንክብካቤ በማቋቋም፣ አቅማቸውን በመገንባት ከህብረተሰቡ ሀብት በማሰባሰብ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል እንዲስፋፋ ማድረግ እንዲሁም በህብረተሰቡ የመረዳዳት ባህል እንዲጎለብት ቤተሰብ ተኮር ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የሚሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶችይሆናሉ፡፡

## 12.4.2 የወጣቶች ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት

ከወጣቶች አኳያ የዘርፉ ሚና የወጣቶችን መብትና ደህንነት፣ ተሳታፊነትና ውክልና እንዲሁም ተጠቃሚነት በትኩረት ይዞ መተግበር ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዕቅድ ዘመኑ በዘርፉ የወጣቶችን በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ልማት የማሳደግ፣ ፖሊሲዎችን የማስረጽ፣ ፖለቲካዊ ተሳትፏቸውን እንዲሁም መብትና ጥቅሞቻቸውን የማስከበር፣ ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ የማድረግ፣ ከአሉታዊ መጤ ባህሎች ደህንነታቸውን የመጠበቅ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን የመዘርጋት ሥራዎች በትኩረት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

## የትኩረት አቅጣጫዎች

**መብት (Right)፡-** ይህ ስትራቴጂ የሆነ የትኩረት አቅጣጫ የወጣቶችን ተፈጥሯዊ፣ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩላቸው የማድረግ፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዙሪያ የተፈረሙ

አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሥምምነቶችን እና ቃልኪዳኖችን ተግባራዊነት የማረጋገጥ፣ በወጣቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ከባህል እና ወግ ተቃራኒ የሆኑ መጤ ባህሎች፣ ሱሰኝነት፣ ብዝበዛ እና አድሎዎች የማስወገድ፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን የማስቀረት፣ የወጣቶችን በነፃ ፍላጎት የመደራጀት መብት የማረጋገጥ እንዲሁም የተሰጡ ሁለንተናዊ መብቶችን በህበረተሰቡ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና እንዲከበሩ የሚያስችሉ ሥራዎችን ያቀፈ ነው።

**ውክልና (Representation)፡-** ይህ የትኩረት አቅጣጫ ወጣቶች በየደረጃው በሚካሄዱ እና ወጣቶች በመረጧቸው አደረጃጀቶች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማሳደግ፣ በቀጣናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች የሚኖራቸውን ተሳትፎ የማጎልበት እንዲሁም በህግ አውጪ፣ በህግ አስፈፃሚ እና በህግ ተርጓሚ አካላት በየደረጃው የሚኖራቸውን ውክልና ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደረገ አቅጣጫ ነው።

**ተጠቃሚነት፡-** የክልሉ ወጣቶች በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መስኮች ትርጉም ባለው መልኩ እንዲሳተፉ እና እንዲጠቀሙ፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የወጣቶችን ጉዳይ ማካተት እና ተቋማዊነትን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያስችል የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል።

**ሀብት፡-** ይህ የትኩረት አቅጣጫ የወጣቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማጎልበት ወጣቶች ከአገሪቱ አጠቃላይ ልማት የሚኖራቸውን ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እና የንብረት ባለቤትነት የማረጋገጥ አቅጣጫ ይሆናል።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዓላማ የወጣቶችን መብት፣ ውክልና እና ተጠቃሚነት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እና በፖለቲካ መስኮች ማረጋገጥ ሲሆን ለተግባራዊነቱም የወጣቶችን የመደራጀት መብት ለማስጠበቅ ወጣቶች በፍላጎታቸው እና በመረጧቸው መስኮች የመደራጀት እና ነፃ ሆነው የመንቀሳቀስ መብታቸውን ለማረጋገጥ ለ10.7 ሚሊየን ያልተደራጁ ወጣቶች በመደራጀት ጥቅም እና አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር፣ 5.6 ሚሊየን ወጣቶች በአዲስ አደረጃጀቶች እንዲደራጁ የማደረግ፣ ለ787,563 የወጣት አደረጃጀት አመራሮች እና ለ3.9 ሚሊየን የወጣት አደረጃጀት አባላት የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የወጣት አደረጃጀቶችን ውጤታማ ለማድረግ አደረጃጀቶችን በሙያ፣ በቁሳቁስ እና በገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ግብ ተጥሏል።

የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ከማረጋገጥ አኳያም ወጣቶች በተለያዩ እርከኖች ውክልና እዲኖራቸው በማድረግ በየደረጃው ባለው ምክር ቤት የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን ለማረጋገጥ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በህግ አውጪ ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችን በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት ወደ 36 በመቶ፣ በህግ ተርጓሚ ወደ 36 በመቶ እንዲሁም በህግ አስፈፃሚ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ይሠራል። በተመሳሳይ ወጣቶች በአገራችንና በክልላችን በሚካሄዱ ሁሉን አቀፍ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት 785,862 ወጣቶች በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ያለ ድምጽ እንዲሳተፉ ግንዛቤ የሚፈጠር ሲሆን በሌላ መልኩ ለ10.8 ሚሊየን ወጣቶች የንቅናቄ ተሳትፎ መድረኮች ማካሄድ፣ በዓለም አቀፍ የወጣቶች ቀን 7.1 ሚሊየን ወጣቶች እና በአፍሪካ ወጣቶች ቀን 7.1 ሚሊየን ወጣቶችን በማሳተፍ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል ።

የወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አኳያም 8.8 ሚሊየን ሥራ አጥ ወጣቶችን የመለየትና በሥራ ፈጠራ ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር እንዲሁም የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣ ለ10.4 ሚሊየን ወጣቶችና ለ14.2 ሚሊየን ወላጆች ወጣቶች በቤተሰቦቻቸው መሬት ላይ የግብርና ግብዓት እና ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለ7.1 ሚሊየን ወጣቶች በግብርና ፓኬጅ ጠቀሜታ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ሥራዎች ዙሪያ ለ6.1 ሚሊየን ወጣቶች ንቅናቄ በመፍጠር ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ለ7.1 ሚሊየን

ወጣቶች በህብረት ሥራ ማህበራት ጠቀሜታና ፋይዳ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለ49,950 ከስደት ተመላሽ ለሆኑ ወጣቶች ግንዛቤ በመፍጠር ተደራጅተው እንዲሰሩ ማድረግ፣ 5.7 ሚሊየን ወጣቶችን በ1.1 ሚሊየን ኢንተርፕራይዝ በማደራጀትና ሁሉን አቀፍ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ተጠቃሚ አንዲሁኑ ማስቻል፣ በተመሳሳይ ለ10.4 ሚሊየን ወጣቶች በቁጠባ አገልግሎት ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር የወጣቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነት አሁን ካለበት 15 በመቶ ወደ 80 በመቶ፣ የቁጠባ ምጣኔያቸው ደግሞ አሁን ካለበት 7 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ ግብ ተጥሏል፡፡

ከወጣቶች ማህበራዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት አኳያ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስታንዳርድ /መመሪያ/ ዙሪያ ለ10.7 ሚሊየን ወጣቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት በበጎ ፈቃድ የአገልግሎት መስኮች ላይ የተሰማሩ ወጣቶችን የክረምት በጎ ፈቃድ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 3,646,082 ወደ 6,652,498 እንዲሁም በበጋ በጎ ፈቃድ በ2012 ከነበረበት 1,972,259 ወደ 5,088,204 ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡ በየደረጃው 4,167 የወጣቶች በጎ ፈቃድ ስትሪንግ እና የቴክኒክ ኮሚቴ ከዚህ በተጨማሪም የወጣቶችን የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭነት ከመቀነስ አኳያ በማህበራዊ ጠንቅ ተጋላጭነት ዙሪያ ለ8.9 ሚሊየን ወጣቶችና ለ5.3 ሚሊየን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ዙሪያ ለ8.9 ሚሊየን ወጣቶችና ለ5.3 ሚሊየን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በአሉታዊ መጤ ባህሎችና አደንዛዥ ዕፆች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ይሠራል፡፡ በሌላ በኩልም ለማህበራዊ ጠንቆች ተጋላጭ ለሆኑ ወጣቶች 5 ከሱስ ማገገሚያ ማዕከላት እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል ለ10.7 ሚሊየን ወጣቶች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል እና በሥነተዋልዶ ጤና አገልግሎት ላይ ግንዛቤ በመስጠት 176 የወጣት ማዕከላትን ለወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና እና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ፡፡

የወጣቶችን የጠባቂነት አመለካከት ለመለወጥ ለ5.3 ሚሊየን ወጣቶች በአዕምሮ ውቅር እና በባህላዊ ዕሴቶች ዙሪያ እንዲሁም ለ3.5 ሚሊየን ወጣቶች በህይዎት ክህሎት እና በአቻ ለአቻ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር በትኩረት የሚሠራ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 450 አዳዲስ የስብዕና ልማት ማዕከላትን በመንግስትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በመገንባት 9 በወጣት ማዕከላት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ካፌዎችን የማስፋፋት ሥራ በመሥራት እንዲሁም 3,105 ማዕከላት በሙያ፣ በቁሳቁስና በገንዝብ በማጠናከር እና በወጣቶች ማዕከላት ጠቀሜታ እና አስተዳደር መመሪያ ዙሪያ ለማዕከል ሥራ አስኪያጆች እና ለቦርድ አመራሮች ሥልጠና በመሰጠት 31,035,128 ወጣቶች በወጣት ማዕከላት ተጠቃሚ ለማድረግ ይሠራል ፡፡

የወጣቶች ጉዳይን በማካተት ረገድ ከክልል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ 100 በመቶ ተቋማዊ ያደረጉ ተቋማት ቁጥር 5 በማድረስ እና የሁሉንም ተቋማት የመፈፀም አቅም በ2013 ከነበረበት 42 በመቶ ወደ 75 በመቶ ለማድረስ ግብ ተቀምጧል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የወጣቶችን የእርስ በእርስ ትብብር ለማሳደግ እንዲሁም የወጣቶችን ጉዳይ በየደረጃው በሁሉም ሴክተሮች እንዲካተት ለማድረግ እና የወጣቶች ድምፅ ተሰሚ እንዲሆን የወጣቶችን ካውንስል ማቋቋም፣ የወጣቶችን ተሳትፎና ውክልና ለማረጋገጥ የወጣቶች ማዕከል፣ የወጣቶች የግንኙነት እና የመረጃ ማዕከል፣ ወጣቶች ከአህጉራዊ አቻዎቻቸው ጋር ትስስር የሚፈጥሩበት የዩዝ ኮኔክት ፕሮግራምን በማካሄድ ነፃና ጠንካራ የወጣት አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ እና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ የወጣቶችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ለማሳደግ የሚያስችል የልማት ፈንድ በማቋቋም ሥራ ፈጣሪ ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ እንዲሁም ወጣቶች ከሱስ የሚያገግሙበት የወጣቶች የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን ማቋቋም የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ናቸው፡፡

### 12.4.3 የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች

አማራ ክልል በህዝብ ብዛት ከኦሮሚያ ክልል ቀጥሎ በ2ኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ ክልሉ በህዝብ ቁጥር በርካታ የዓለም ሀገሮችን የሚበልጥ እንደሆነም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለሆነም ክልሉ ብዙ ሕዝብ ያለው እና ይህም ለልማት ትልቅ አቅም እንደሆነ መረዳት አያዳግትም፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ 70 በመቶ ያህሉ የክልሉ ህዝብ ከ30 ዓመት ዕድሜ በታች ያለ ነው፡፡ ይህም ማለት ክልሉ በቀጣይ የዕቅዱ ዓመታት የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገት ማፋጠን እና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ሰፊና ርካሽ የሰው ኃይል ዕምቅ አቅም የታደለ ነው ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ውልደቱ ከአብዛኛዎቹ ያደጉና በፍጠነት በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ጋር ሲነፃፀር ከፍ ያለ በመሆኑና አምራች ያልሆኑ ህጻናት በብዛት የሚገኙበት በመሆኑ የጥገኝነት ጥምርታው እንዲሁ ከፍ ያለ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ወደ ዝቅተኛ ውልደት እና ሞት የሚደረገውን ሽግግር /Demographic Transition/ እንዲዘገይ አድርጓል፡ ፡ የዚህ ሁኔታ ጥሩ ጎኑ የሚባለው በሚሠሩ የተለያዩ ፕሮግራሞች የውልደት ምጣኔ በፍጥነት እየቀነሰ እንዲሄድ የሚያስችለው በመሆኑ በዚህ ምክንያትም ቁጥራቸው ያነሰ ህጻናት ወደ ህዝቡ እንዲጨመሩ እና በተነፃፃሪ ብዙ ቁጥር ያለው ክፍል ወደ አምራች ኃይሉ እንዲቀላቀል ስለሚያደርግ በአምራች ኃይል የዕድሜ ክልልን በመጨመር የዕድሜ ስብጥሩ እንዲቀየር ያደርጋል፡፡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በአምራች ኃይል /ከ15-64 ዓመት / ክልል ያለ ህዝብ ብዛት በ1999 ከነበረበት 50 በመቶ በ2012 ወደ 56 በመቶ ከፍ ብሏል፡፡ ይህ ሁኔታ የሥነ-ህዝብ ትሩፋት /መልካም አጋጣሚ እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ የሥነ-ህዝብ ትሩፋት /መልካም አጋጣሚ /Demographic Dividend/ ከአጠቃላይ ህዝቡ የአምራች ህዝቡ ድርሻ በመመጨመሩ ምክንያት የሚገኝ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማለት ነው፡፡ የሥነ-ህዝብ ትሩፋት በኢኮኖሚ ዕድገት ተዓምር ለፈጠሩ /Economic Miracles/ የእሰያ አገሮች ለፈጣን ዕድገታቸው ከሚጠቀሱ ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ ዕድል ለክልሉ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚታይ በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም እና ሰብዓዊ ሀብትን በማልማት ለልማቱ አለኝታ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በየደረጃው የተቋቋሙ የሥነ ህዝብ ምክር ቤቶችን ማጠናከር፣ የክልሉ ልማት በሚፈለገው ፍጥነት ይራመድ ዘንድ የህዝብ ቁጥር ዕድገቱን ከልማት ዕድገት ጋር ማጣጣም፣ ክልሉ ከሥነ-ህዝብ መልካም አጋጣሚዎች /Demographic Dividend/ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አቅጣጫ መከተል፣ በሥነ-ህዝብ እና ልማት ጉዳዮች ዙሪያ የህብረተሰቡንና የውሳኔ ሰጭ አካላትን ግንዛቤ ለማሳደግ የትምህርትና ቅስቀሳ ተግባራትን አጠናክሮ መቀጠል፣ በክልሉ የተሟላ፣ ወቅታዊ እና ተአማኒነት ያለው የሥነ-ህዝብ መረጃ እንዲኖር በመረጃ አሰባሰብና ትንተና እንዲሁም የጥናትና ምርምር አቅም ከማጎልበት አንፃር ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### ዓላማዎችና ግቦች

ከሥነ-ህዝብ አንፃር ዋናው ዓላማ በሥነ-ህዝብ ባህሪያት /Demographic variables/ የዕድገት ምጣኔ እና በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የተፈጥሮ አካባቢ የልማት ዕድገት ምጣኔ መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ በህዝብ እና በልማት ዕድገት መካከል ያለውን ልዩነት ማመጣጠን ሲሆን ግቦቹም የክልሉ ህብረተሰብ በሥነ-ህዝብ እና ልማት ትስስር ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ፣ የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች በፈጻሚ ሴክተሮች የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው እንዲታቀዱ ማስቻል እና ትግበራቸውን መከታተል፣ ወቅታዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ህዝብ መረጃ አያያዝ፣ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ እንዲሁም በክልሉ በሥነ-ህዝብ እና ልማት ዙሪያ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ለማከናዎን የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ማከናዎን የሚሉት ናቸው፡፡

ከወሳኝ ኩነቶች አንፃር በክልላችን የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ የጀመሩ 3,971 የምዝገባ ጣቢያዎችን ወደ 3,973 ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በየዓመቱ በክልሉ ይከሰታል ተብሎ ከሚጠበቀው የክልሉ ህዝብ ውስጥ 3.11 በመቶ የውልደት

ኩነት፣ እንዲሁም 5,065 ህዝብ ውስጥ ይከሰታል ተብሎ በወር ከሚጠበቀው 5.8 ሞት፣ 8.2 ጋብቻ እና 0.9 ፍች ኩነቶች ምዝገባ በማከናወን ልደት በ2012 ከተደረሰበት 259,081 (37.5 በመቶ) በ2022 ወደ 633,992 (80 በመቶ) ዓመታዊ ምዝገባ ለማድረስ፣ ሞት በ2012 ከተደረሰበት 32,683 (9.3 በመቶ) በ2022 ወደ 280,286 (80 በመቶ) ማድረስ፣ ጋብቻ 10,780 (ከሚጠበቀው 2.6 በመቶ) ወደ 396,040 (80 በመቶ) ለማድረስ፣ ፍች በ2012 ከተደረሰበት 2,186 (ከሚጠበቀው 4.8 በመቶ) በ2022 ወደ 43,468 (80 በመቶ) ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በ3,973 የምዝገባ ጣቢያዎች ሁሉንም የተከሰቱ ኩነቶች (100 በመቶ) መዝግቦ መረጃውን መያዝ፣ የውዝፍ ምዝገባ አገልግሎትን ፈልገው የሚመጡትን 100 በመቶ ለመመዝገብ፣ በክልሉ የምዝገባ ጣቢያዎች ማቋረጥ ምጣኔ አሁን ካለው 7 በመቶ ወደ 0 ዝቅ ለማድረግ፣ በ3ቱ ሪጅዮፖሊታንት ከተሞች ከ5 ዓመት በታች ልደት በየዓመቱ ምዝገባ ለማካሄድ ታቅዷል፡፡ የምዝገባ ሽፋንና ጥራቱን እና አጠቃላይ የምዝገባ ሥርዓቱን በተመለከተ ልዩ ልዩ ጥናቶችን ማጥናት አሁን ካለበት 2 ወደ 6 ጥናቶች ለማሳደግ ታቅዷል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የሥነ-ህዝብ ጉዳይ በባህሪው ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ ከመሆኑ አንፃር ሁሉንም የሥነ-ሕዝብ ባለድርሻ አካላት (መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን) ባሳተፈ መልኩ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር፣ በየደረጃው የሥነ-ህዝብ ጉዳይ ምክር ቤቶች ማቋቋምና ማጠናከር፣ የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች በልማት ዕቅድ ዝግጅት ተካተው እንዲታቀዱ የሚያስችል ሥርዓትን ማጠናከር፣ ተዓማኒነት ያለው የሥነ-ህዝብ መረጃ እንዲኖር ለማስቻል በመረጃ አሰባሰብ፣ ዝግጅትና ትንተና የባለሙያዎችን አቅም ማጎልበት፣ አራተኛውን አገር አቀፍ የህዝብ እና ቤቶች ቆጠራ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ማድረግ፣ አጋር አካላትን ማስተባበርና የማስፈጸሚያ ሀብት ማሰባሰብ፣ በሥነ-ህዝብ እና ልማት ዙሪያ ፖሊሲ ተኮር የምርምር ፍላጎትን በመለየት ጥናትና ምርምር ማካሄድ እንዲሁም የተቀናጀ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ናቸው፡፡

### 12.4.4 የአካባቢ እና ደን ጥበቃ

## የትኩረት አቅጣጫዎች

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ በክልሉ የልማት ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት እና እንዲተገበር ማድረግ፣ ከዘርፍ መሥሪያ ቤቶች የሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነሱን ማረጋገጥ፣ በዘርፉ በክልሉ ውስጥ እየተተገበሩ ያሉ ፕሮጀክቶች /ፕሮግራሞች የታለመላቸውን ዓላማ ማሳካታቸውን ማረጋገጥ፣ ችግር ፈቺ ጥናቶች እና ምርምሮችን እንዲሁም መረጃና ቴክኖሎጂ በመለየት፣ የማስተዋወቅ እና የማሠራጨት ሥራዎችን በትኩረት መሥራት፣ በህብረተሰቡ ላይ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ የመቋቋም አቅም እንዲጎለብት በትኩረት መሥራት፣ የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት እና እንዲከበሩ የሚያስችሉ ተግባራትን በትኩረት መሥራት፣ የመጤ ወራሪ ዝርያዎችን መለየትና እያደረሱ ያሉትን ጉዳት በጥናትና ምርምር በመታገዝ ለመፍታት ህብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ ህይዎት ሀብቶች የአደጋ ስጋት የመለየት፣ የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራን በትኩረት መሥራት፣ የተራቆቱ በታዎች እንዲያገግሙ ማድረግ፣ አዳዲስ ጥብቅ በታዎችን ማቋቋም፣ ነባር ጥብቅ በታዎችን እንዲሁም የተፈጥሮ ደኖችን የማልማት፣ የመጠበቅና የመንከባከብ ሥራን በትኩረት መሥራት፣ የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ ህይዎት ሀብቶች የአጠቃቀም ዓይነት እና ስብጥር ማስፋት፣ የግል ባለሀብቱን እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ የሚያሳድጉ ሥልቶችን መንደፍ እና የፕሮሞሽን ሥራዎችን በትኩረት መሥራት፣ በአካባቢ፣ ደን፣ ዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ-ሕይወት ሀብቶች ህብረተሰቡን በማሳተፍ የጥቅም ተጋሪነት ሥርዓት በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ በትኩረት መሥራት፣ በአካባቢ፣ ደን፣ ዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ-ህይወት ሀብቶች

ጥበቃና ልማት ምክንያት በሰውና በብዝሀ-ሕይወት ሀብቶች መካከል በሚከሰት ግጭት ምክንያት የሚደርሰውን ውድመት ለማካካስ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋትና ለመተግበር በትኩረት መሥራት የሚሉት ናቸው።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዓላማ በክልሉ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ዕውን ለማድረግ የአካባቢ፣ የደን፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የብዝሀ ሕይወት ሀብቶችን በማልማት፣ በመጠበቅ እና የአጠቃቀም ሥርዓት በማስፈን ከኢኮኖሚ ልማት ዕቅዱ ጋር በማጣጣም፣ ጤናማ የሥርዓተ ምህዳር መስተጋብር በማሳደግ ዘላቂ ልማት እና ዕድገት እንዲረጋገጥ ማድረግ ሲሆን ዋና ዋና ግቦችም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል፣ የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ሥርዓት ማጎልበት፣ የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ሥፍራዎችን ሽፋን ማሳደግ፣ በአካባቢና ብዝሀ ህይዎት ሀብት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት መቀነስ የሚሉት ናቸው። ከጣና ኃይቅና ሌሎች የውኃ አካላት ጥበቃ እና ልማት ሥራዎች አንፃር በጣና ኃይቅ ላይ በመስፋፋት ከፍተኛ ችግር እያደረሰ ያለውን የእንቦጭ አረምና በሌሎች የውኃ አካላት እና ውኃ አዘል መሬቶች የተከሰቱትን መጤ አረሞች ችግር ወደማይሆኑበት ደረጃ መቀነስ፣ 6ቱን የልማት ቀጣና ወይም ተፋሰስን መሠረት ባደረገ በክልሉ ያሉ የተፈጥሮ እና የሰው ሠራሽ ሀይቆችን እና ውኃ አዘል መሬቶችን በጥናት የመለየት ተግባር ከነበረበት 10,500 ሄክታር በ2022 በጀት ዓመት ወደ 400,000 ሄክታር በማሳደግ የራሳቸው የሆነ የአያያዝና አጠቃቀም ዕቅድ በካርታ በማዘጋጀት እና የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎታቸውን በማጎልበት የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ህብረተሰብ እና አካባቢን መፍጠር እንዲሁም በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የሚያቋርጡ 400 ወንዞችን ከውኃ ብክለት መከላከል እና የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ሥፍራ እንዲሆኑ ማድረግ በ10 ዓመቱ የተጣሉ ግቦች ናቸው።

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም ተቋማዊ አቅም በማጠናከር ዕቅዶችን በተደራጀ እና በተቀናጀ አግባብ መተግበር፣ በፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በማከናወን በየደረጃው የሚገኙ አካላትን ግንዛቤ ማሳደግ እና ተሳትፏቸውን ማጎልበት፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት፣ ከህዝብ ክንፍ፣ ከህብረተሰቡና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በአሠራር የተደገፈ ቅንጅታዊ ትስስር መፍጠር እና ተግባራዊ ማድረግ፣ በአካባቢ፣ ደንና ዱር እንስሳት የልማት ዕቅድ ትግበራ ሂደት የሚለዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ማስፋፋት፣ ከልማት ድርጅቶች ጋር በሚደረግ ትብብር የተገኙ ፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞች እና ድጋፎች የተቋሙን ስትራቴጂክ ግቦች ማሳካት በሚያስችል አግባብ እንዲተገበሩ፣ የሀብት ብክነትና የሥራ ድግግሞሽ እንዳይኖር በጥንቃቄ መፈፀም፣ በዘርፉ የዕቅድ ትግበራ ሂደት የወጣቶችን እና የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚያስችሉ ተጨባጭ ሥራዎች መከናወናቸውን በልዩ ትኩረት ማረጋገጥ፣ የተቀናጀና የተናበበ አሳታፊ የዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ የአሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ፣ የመሥሪያ ቤቱን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ በሚዲያ እና ኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች በማስደገፍ ሰፊ የህብረተሰብ ንቅናቄ እና ተሳትፎን በማጠናከር ዕቅዱን ለማሳካት እንደ አጋዥ መሣሪያ መጠቀም እንደ ዋነኛ ሥልቶች በሥራ ላይ ይውላሉ።

## 12.5 የፍትህና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ

### 12.5.1 ሲቪል ሠርቪስና የሰው ኃይል ልማት

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

ተቋማት ውጤታማ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የተቋማትን የአሠራር ሥርዓት ማጠናከር፣የሰው ሀብት ልማት ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የለውጥ መሣሪያዎችን የዕቅድ ማሳለጫ አድርጎ መጠቀም፣ ተቋማዊ አገልግሎት አሰጣጡን ፍትሐዊ፣ ፈጣንና ውጤታማ ማድረግ፣ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓት መዘርጋት እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት ናቸው፡፡

#### ዓላማና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዓላማ ተቋማትን ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ በአደረጃጀት እና በአሠራር እንዲሁም በሰው ሀብት አስተዳደር እንዲጠናከሩ ማድረግ ሲሆን ይህን ከማሳካት አንፃር የመንግስት ተቋማትን ውጤታማነት በአደረጃጀትና በአሠራር ማጎልበት፣ የሰው ሀብት ልማት ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የሰው ሀብት ሥምሪት ሥራዎችን አፈፃፀም ማሻሻል፣ የለውጥ መሣሪያዎችን ውጤታማነት ማሳደግ፣ የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓቱን ማሻሻል፣ የመንግስት አገልግሎት ፍትሐዊነትን ማሻሻል፣ የዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች አካታችነትን ማጎልበት እንዲሁም የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል የሚሉት ግቦች ተጥለዋል፡፡

#### የማስፈፀሚያ ሥልቶች

በአደረጃጀት ዙሪያ የባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ፣ ለቀረቡ የአደረጃጀት ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ምላሽ መስጠት፣ ክልላዊ የሰው ሀብት ልማት ሥራው በዕቅድና በአንድ ማዕከል እንዲመራ ማድረግ፣ በጥናት ላይ የተመሠረቱ፣ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡና ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ማዋል፣ የክትትል፣ የድጋፍ እና የቁጥጥር ሥራዎች ወቅታዊ እና ችግር ፈቺ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የለውጥ ሥራዎችን መተግበር፣ ደንበኞች የሚሰጡትን አስተያየትና የሥራ አፈጻጸም ግምገማ መነሻ በማድረግ ክፍተትን መሙላት፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ያለን የክህሎት ችግር በሥልጠና ማብቃት፣ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርዓቱን መተግበር፣ ወጥ የሆነ የሥራ አፈጻጸም ምዘና መመሪያን ወደ ሥራ ማስገባትና አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የማሻሻል ሥራ ማከናወን ናቸው፡፡

### 12.5.2 የፍትህ ዘርፍ

ህገ መንግስቱን፣ ሰብዓዊ መብትን እና ህግን ማክበር እና ማስከበር፣ ወንጀልን በመከላከል እና የወንጀል ህግን በማስከበር የህዝብ፣ የመንግስት እና የግለሰቦችን ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ፣ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ማስወገድ፣ የመንግስትን እና የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ፣ የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ ማሳደግ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ፍትሐዊና ውጤታማ የፍትህ አገልግሎት መስጠት የሚሉት ዋና ዋና የዘርፉ ሚናዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም መሠረታዊ የህግ እና የፍትህ ችግሮችን በመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ችግሮቹን ለመቅረፍ እና ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት አደረጃጀት እና አሠራር በመዘርጋት እየተሰራ ያለውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ይሆናል፡፡

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

አስተዳደራዊ ፍትህን ማስፈን፣ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት፣ የዳኝነት ተደራሽነትን ማስፋፋት፣ የፍርድ ቤት ነፃነትና ተጠያቂነትን ማጎልበት፣ የወንጀል ህግን አፈጻጸም ውጤታማነት ማረጋገጥ፣ የማስፈፀም አቅምን በማሳደግ የመንግስት እና የህዝብን ጥቅም ማስከበር፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የልማት ጉዞን በማፋጠን የተጀመረውን የልማት፣ የሰብዓዊ መብት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማሳደግ፣ የህግ

የበላይነትን በማስከበር ህብረተሰቡ ሠላምና ደህንነቱ እንዲሁም ህገ መንግስታዊ መብቱ የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ፣ የፍትህ ሥርዓቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሐዊ፣ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ እንዲሆን መሥራት በዘርፉ ትኩረት የሚሠጣቸው አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በየደረጃው ያለውን ባለሙያና ሠራተኛ ጠንካራ የፍትሕ ሠራዊት ኃይል አድርጎ ማብቃት፣ ቅንጅታዊ አሠራርን በጥብቅ መከተል፣ ዓቃብያነ ህግና የአስተዳደር ሠራተኞችን ተሳትፎ ማጎለብት እንዲሁም ሥራዎችን ከተደራሽ ግብ እና ውጤት ተኮር አንፃር መለካት የሚሉት የዘርፉ ዋና ዋናዎቹ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዋና ዋና ዓላማዎች ተልዕኮውን ማሳካት የሚችል ጠንካራና ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ ኃይል በመገንባትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ህብረተሰቡ በፍትህ አስተዳደሩ ላይ ያለውን አመኔታ ማሣደግ፣ የሙስና፣ የኢኮኖሚ ነክና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ወንጀል ፈፃሚዎችን በማስቀጣት የህብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ፣ በፍትሐብሄር ፍትህ አስተዳደር ጉዳዮች የመንግስትና የህዝብን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ እንዲሁም የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን፣ የህጻናት ጉዳይን፣ የአካል ጉዳተኞች ጉዳይን፣ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን፣ በአጠቃላይ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጉዳይ አካቶ በመሥራት የክልሉ ህብረትሰብ መብትና ጥቅም ሙሉ በሙሉ መከበሩን ማረጋገጥ የሚሉ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የተቀመጡትን ዋና ዋና ዓላማዎች ለማሳካት የአመራሩንና የፈጻሚውን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ፣ የለውጥ ኘሮግራሞች አጠቃቀም ውጤታማነትን ማጠናከር፣ የሰው ኃይል አቅርቦትንና አያያዝን ማሻሻል፣ ከጠቅላይ ዓቃቤ ህግ መሥሪያ ቤቶችና ከልማት ተባባሪ ድርጅቶች ጋር ያለውን ትብብር ማጠናከር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ማሣደግ፣ የሙስናና የብልሹ አሠራር አመለካከትና ተግባራትን ለመታገል ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማሳደግ፣ በፍትህ አስተዳደሩ ውስጥ የህብረተሰቡን የተደራጀ ተሣትፎና ባለቤትነት ማሣደግ፣ 30 በመቶ ለሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፣ እንዲሁም የህግ ማሻሻያ ጥናት፣ ምክር ማርቀቅ እና ማጠቃለል ሥራዎችን በማከናወን የተቋሙን ውጤታማነት ማሻሻል፣ የቅድመ ሥራ ላይ ሥልጠና ጥራት 100 በመቶ መሆኑን ማረጋገጥ፣ 2,500 የሚሆኑ የቅድመ ሥራ ሠልጣኞችን በመመልመል እንዲሁም ለ16,500 የፍትህ አካላት እና የህግ ባለሙያዎች በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በሥነምግባርና በአመለካከት የበቁ ሊያደርጋቸው የሚችል ውጤታማ ሥልጠና መስጠት፣ 20 ርዕሶችን በመምረጥ ችግር ፈችና አዳጊ የህግ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን እንዲሁም የህግ ጥናትና ምርምር ሥራዎች ያመጧቸውን ውጤቶች ለመለካት የሚያስችል 1 የዳሰሳ ጥናት ማከናወን የሚሉት ዋና ዋና ግቦች ተቀምጠዋል፡፡

የወንጀል ምርመራ መዛግብት ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦችን መርምሮ የመወሰን /መዝገብ የማጥራት/ አቅምን ከ98.95 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሣደግ፣ በወንጀል የቀጥታ ክስ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ ተከራክሮ የማስቀጣት አቅምን ከ94.46 በመቶ ወደ 97 በመቶ ማሣደግ፣ የፍርድ ውሳኔዎችን የማስፈጸም አቅምን ወደ 98 በመቶ ማሳደግ፣ በወንጀል ጉዳይ የዓቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን ከ79.34 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማሣደግ፣ በሴቶች በህጻናት በወጣቶች በአረጋውያንና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዓቃቤ ህግ ይግባኝና ሰበር የጠየቀባቸው መዝገቦች አፈጻጸም ውጤታማነትን ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የፍርደኛ ይግባኝና ሰበር አቤቱታ መዝገቦች የክርክር ውጤታማነትን ከ84.3 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሣደግ፣ በቀዳሚ ምርመራ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች 100 በመቶ ማስረጃ እንዲጠበቅ በማድረግ አጥፊዎችን በህግ ፊት ተጠያቂ ማድረግ፣ የተከሣሽ፣ የምስክር፣ የመልስ ሰጭ እና የተጠሪ አቀራረብን በማጠናከር የመዛግብት መቋረጥ ምጣኔን ከ5.56 በመቶ ወደ 1 በመቶ ዝቅ ማድረግ፣ በሚቀርቡ የዋስትና ጉዳዮች ላይ ቀልጣፋና ህጋዊ አስተያየት 100 በመቶ በመስጠት እንዲከበር ማድረግ፣ የወንጀል አቤቱታ አቀባበል ውሣኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነትን ከ94 በመቶ ወደ 98 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም የይቅርታ አሰጣጥ ጥራትና ውጤታማነትን ከ93 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ የሚሉት ግቦች ስኬታማ እንዲሆኑ ይሠራል፡፡

በፍትሐብሄር ጉዳዮች የቅድመ መከላከል ሥራን በማጠናከር የመንግስትና የህዝብን ሀብትና ንብረት ከብክነት ከመከላከል አኳያ በመዝገብም ሆነ በገንዘብ 99 በመቶ የነበረውን አፈጻጸም ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ የታቀደ

ሲሆን በፍትሐብሄር ከሚያዙ ጉዳዮች ውስጥ በድርድር መጨረስ በመዝገብ 15.02 በመቶ እንዲሁም በገንዘብ 3.67 በመቶ የነበረውን ወደ 30 በመቶ የማሳደግ ግብ ተቀምጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የክስ አመሠራረት እና መልስ አቀራረብ ቅልጥፍና /መዝገብ የማጥራት አቅምን/ በመዛግብት 92.91 በመቶ እንዲሁም በገንዘብ 98.81 በመቶ የነበረውን ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ በፍትሐብሄር ጉዳዮች በቀጥታ ክስና መልስ የዓቃቤ ህግ ተከራክሮ የማሸነፍ አቅምን በመዝገብ ከ86.43 በመቶ በገንዘብ ከ83.96 በመቶ ወደ 92 በመቶ ማሣደግ፣ በፍትሐብሔር ጉዳዮች በይግባኝ ባይና ሰበር አቅራቢ አቤቱታ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነትን በመዝገብ ከ54.48 በመቶ እንዲሁም በገንዘብ ከ60.74 በመቶ ወደ 70 በመቶ ማሣደግ፣ በፍትሐብሔር በይግባኝ መልስ እና ሰበር ተጠሪ አቤቱታ መልስ መዝገቦች የዓቃቤ ህግ የክርክር ውጤታማነትን በመዝገብ ከ77.47 በመቶ በገንዘብ 72.09 በመቶ ወደ 85 በመቶ ማድረስ፣ ክስ በቀረበባቸው ጉዳዮች አስቀድሞ ንብረት ፈልጎ ማሳገድን ከ32.33 በመቶ ወደ 50 በመቶ ማድረስ፣ የመሪ ትዕዛዝ፣ የክስ እና የይግባኝ አይቀርብም ውሳኔዎችን ውጤታማነት 100 በመቶ ማድረስ፣ የአፈጻጸም ክስ ከቀረበባቸው ጉዳዮች ውስጥ የማስፈፀም አቅም አሁን ካለበት በመዝገብ 50 በመቶ እንዲሁም በገንዘብ 50 በመቶ ወደ 70 በመቶ ማሣደግ፣ የአቤቱታ አቀባበል ውሣኔ አሰጣጥ እና የአቤቱታ ተፈፃሚነትን ከ92 በመቶ ወደ 98 በመቶ ማሳደግ፣ የሠነዶች፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የማህበራት እና ጠበቆች ምዝገባ ሥራን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ተገልጋዮችን 100 በመቶ ማርካት እንዲሁም ጠበቆች በአመለካከት በክህሎትና ሥነምግባር ዳብረው ለፍትህ ሥርዓት አጋዥ እንዲሆኑ ማድረግ የሚሉት ግቦች ታቅደዋል፡፡

በሁሉም የክልሉ ተቋማት እና በሚመለከታቸው አካላት የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር በአግባቡ መተግበሩን 100 በመቶ ማረጋገጥ፣ ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችንና የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በዘርፉ ውስጥ እየታቀደና ትኩረት እየተሰጠው መሆኑን መደገፍና ማረጋገጥ፣ በህገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ምላሽ መስጠት ላይ የሚሰሩ አደረጃቶችን ማጠናከር፣ በፍርድም ሆነ በጊዜ ቀጠሮ በማረሚያ ቤቶች የሚገኙና በፖሊስ ጣቢያዎች በህግ ቁጥጥር ሥር ውለው የሚገኙ ሰዎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው በአግባቡ መከበሩን ማረጋገጥ፣ የሥነ-ህዝብ ጉዳይን በፍትህ ሥርዓቱም ውስጥ ትኩረት በመስጠት አፈጻጸሙን ማሳደግ እንዲሁም በአካባቢ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ ችግር መፍትሄ ላይ የፍትህ ሴክተሩን ተሳትፎ ማሳደግ የሚሉትን ግቦች ለማሳካት የሚሠራ ይሆናል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

ለተገልጋዮች መረጃ የሚደርስባቸውን አሠራሮች ማዘመን፣ ግልጽ የሆነ የዳኞች ምልመላና ሹመት ሥርዓት መዘርጋት፣ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ፣ ፕሮግራምና መርሃ ግብሮችን መንደፍና መተግበር፣ ወንጀልና የወንጀል ስጋት አካባቢዎችን፣ የወንጀል ዓይነትና ወንጀል ፈፃሚዎችን መለየት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ በወንጀል መከላከል ስትራቴጂ ህብረተሰቡን በተደራጀ መልኩ ማሳተፍ፣ የማስፈፀም አቅምን በመገንባት ተቋማዊ ለውጥ በማምጣት የለውጥ ሰራዊት ግንባታን ማጠናከር፣ በየሩብ ዓመቱ የግምገማ መድረኮችን በማዘጋጀት የግምገማ ሥርዓቱን ማጠናከር፣ ቅንጅታዊ አሠራርን በጥብቅ መከተል፣ የባለሙያውንና የሠራተኛውን ተሳትፎ የማጐልበት አቅጣጫን መከተል፣ በየደረጃው ያለውን ባለሙያ ጠንካራ የፍትሕ ኃይል አድርጐ መጠቀም፣ ውጤት ተኮር አሠራርን አጠናክሮ በመሥራት ጠንካራ ባለሙያን ማበረታታት እና ደካማውን ማብቃት፣ ሥራዎችን ከተደራሽ ግብ አኳያ መለካት፣ የክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ አሠራር ሥርዓትን ማጠናከር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ ማስፋት፣ የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን፣ ውጤታማነትን፣ ፍትሐዊነትን፣ ቀልጣፋነትን፣ አሳታፊነትንና ተጠያቂነትን ይበልጥ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የባለድርሻ አካላትና የህዝብ ክንፍ በሰብዓዊ መብትና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡ ማድረግ፣ የህብረተሰቡን የንቃተ-ህግ ደረጃ በማሻሻል ህግ እና ሥርዓት የሚያከብርና የህግ ማስከበር ሥራውን በንቃት የሚደግፍ አቅምና አደረጃጀት በመፍጠር ሕጎች ለህብረተሰቡ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲታወቁና እንዲሠራጩ ማድረግ፣ ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ የሚሆኑበትን ሥርዓት ማጠናከር፣ የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የህፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ ለኤች.አይ.ቪ ቫይረስ

የተጋለጡ ዜጎችና የአረጋዊያን መብትና ጥቅሞች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉት ለዘርፉ የ10 ዓመት ዕቅድ ዋና ዋና የማስፈጸሚያ ሥልቶች ይሆናሉ፡፡

### 12.5.3 የሠላም ግንባታ ዘርፍ

የፀጥታ ተቋማቱ ሚና ህብረተሰቡን ባለቤት ያደረገ ሠላም እና የህግ ልዕልና የበላይነት እንዲይዝ ማስቻል፣ የማህበረሰባዊ ሀብቶችን እና ባህላዊ እሴቶችን ተጠቅሞ አለመግባባቶችን በውይይት እና በመቻቻል የሚፈታ ማህበረሰብ እና አገሩን የሚወድ ዜጋ እንዲፈጠር ማስቻል፣ የህግ ማስከበር እና የሰብዓዊ ደህንነት አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ በዜጋው እና በመንግስት መካከል መተማመን መፍጠር እንዲሁም በክልሉና ከክልሉ ተጎራባች ክልሎች እና ህዝቦች መካከል ግንኙነቶችን እና ትብብሮችን ተቋማዊ በማድረግ ዘላቂ ሠላም ማስፈን ይሆናል፡፡

### የትኩረት አቅጣጫዎች

የተቀመጠውን ዓላማ እና ግቦች ለማሳካት ሁለንተናዊ ሠላምና የዳበረ ዴሞክራሲን ማስፈን፣ማህበራዊ ሀብቶችን፣ ዕሴቶችንና አካባቢያዊ ዕውቀቶችን በማሳደግ ህግ በማስከበር፣ የሰብዓዊ ደህንንት አቅምንና ተዓማኒነትን ማሳደግ፣ በክልሉ ህግን በማስከበር የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ በአጎራባች ክልሎች መካከል ያሉ ትብብሮችንና ግንኙነቶችን ማጠናከር፣ ተቋማዊ አቅምን በዘላቂነት መገንባት፣ የአመራር እና የአባላት ሥነምግባርን እና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትን ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት በተዋረድ ያሉትን ተቋማት መልካም ገጽታ ሊያበላሹ የሚችሉ አሠራሮችን እና የሥነምግባር ችግሮችን ወጥነት ባለው እና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አስፈላጊውን ርምጃ በመውሰድ ችግሩን ማቃለል እንዲሁም የቅድመ መከላከልና ፈጣን ምላሺ ሥርዓትን ማሳደግ የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ይሆናሉ፡፡

### ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዓላማ በክልሉ አስተማማኝ ሠላም እና የህግ የበለይነትን በማረጋገጥ በ2022 ዜጎች ያለምንም የፀጥታ ስጋት በልማትና በዴሞክራሲ ግንባታ ሥራዎች ላይ ተሳትፏቸው እንዲያድግና ክልሉ ፍጹም ሠላማዊ ክልል እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦች የፀጥታ ተቋማቱን በሰው ኃይል፣ በአሠራር እና በአደረጃጀት በማጠናከር ተቋማዊ ብቃትን ማሳደግ፣ ለ12,824 ነባር ብሄራዊ ተጠባባቂ ኃይልና ለ3,119 አዲስ የሚሊሻ ባለሙያዎች የአመለካከት እና የሥነምግባርሥልጠና መስጠት፣ በፖሊስ ኮሚሽን በሥራ ላይ ሥልጠና እና በልዩ ልዩ የአጭር ጊዜ ሥልጠና በሁሉም የሥራ ዘርፎች ለ60,000 ባለሙያዎች፣ በሰርተፊኬት ለ800 አባላት በመኮንንነት እና ለ1,500 አባላት የመከከለኛ አመራር ሥልጠና፣ ለ468 የማረሚያ ቤት ፖሊሶች በድምሩ 2,768 አባላትን በሠርተፊኬት ማሠልጠን፣ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች 222,000 ፖሊስ በማሠልጠን የፖሊስና ህዝብ ጥምርታን አሁን ካለበት በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በገጠር 1:1,000 እንዲሁም በከተማ 1:500 ማድረስ፣ ለ40,000 ነባር የማረሚያ ቤት ፖሊስ የአጭር ጊዜ ሥልጠና እንዲሁም 6,100 አዲስ አባላትን በማሠልጠን አሁን ካለው 3,654 አባላት ወደ 9,754 አባላት ማድረስ፣ 200,000 አዲስ ሚሊሻ በማሠልጠን ወደ ሥራ ማስገባት፣ የፀጥታ ተቋማትን ቁሳዊ ግብዓት በማሟላት የአፈፃጸም ብቃትን ማሳደግና ተደራሽ ማድረግ፣ የቢሮ ግንባታ ፕሮጀክትን ተግባራዊ ማድረግ እና ችግሩን በዘላቂነት መፍታት፣ በክልሉ በተመረጡ 5 ቦታዎች ጋራዥ እና ነዳጅ ማደያ በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣ ለልዩ ኃይል እና ለአዲስ ምልምል ፖሊስ 3 የማሠልጠኛ ማዕከል መገንባት፣ 2 ሪፈራል የፖሊስ ሆስፒታል እና በዞን ደረጃ ጤና ጣቢያ መገንባት እና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ ለሚዲያ ኮምኒኬሽን አገልግሎት የሚውል 1 ስቱዲዮ መገንባትና የመገልገያ ቁሳቁሶችን ማሟላት፣ አሁን ያለውን የፖሊስ ጋራዥ 95 በመቶ የውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ ማሟላትና ተጨማሪ 3 የፖሊስ ጋራዥ ማቋቋም፣ በክልሉ በተመረጡ ማዕከላት የፎረንሲክ ላብራቶሪ መሣሪያዎችን ማቋቋምና 100 በመቶ ሥራ ማስጀመር፣ 10,000 የተሽከርካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ ዘመናዊ ራዳሮችን እና 200 የእጀባ ሞተሮችን ማሟላት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ2 ማረሚያ ቤቶች የተጀመሩ አዲስ የማረሚያ ቤቶች ግንባታ ማጠናቀቅ እና የ4 አዲስ ማረሚያ ቤቶች ግንባታ ማካሄድ፣ ለማረሚያ ቤቶች የፖሊስ አባላት አገልግሎት የሚሰጥ ራሱን የቻለ አንድ የሥልጠና ተቋም መገንባት እና ማደራጀት፣ ለህግ ታራሚዎች አገልግሎት የሚውል 12 የቴክኒክና የሙያ ማሠልጠኛ ተቋም መገንባት እና ማደራጀት፣ ወጣት ጥፋተኛ ታረሚዎች ራሳቸውን ችለው የሚታረሙበት 2 ተቋም እንዲገነባ ማድረግ፣ ለማረሚያ ቤቱ አመራሮች አገልገሎት የሚሰጥ 12 መኖሪያ ቤት መገንባት፣ 27 የነባር ማረሚያ ቤቶች ጥግና ማካሄድ እና ለአገልግሎት ምቹ ማድረግ፣ ተሽካርካሪ ለሁሉም ማረሚያ ቤቶች ማሟላት፣ ለማረሚያ ቤቶች አገልገሎት የሚሰጡ 2 ጋራዥና 1 መለስተኛ የነዳጅ ማደያ መገንባት፣ በየደረጃው ለሚገኘው ለወረዳ፣ ለዞን እና ለክልሉ ሚሊሻ ተቋማት 100 በመቶ ተሽከርካሪ ማሟላት፣ የሚሊሻ ማሠልጠኛ ማዕከል ግንባታን 100 በመቶ እንዲጠናቀቅ ማድረግና ለሥልጠና ምቹ ማድረግ እንዲሁም ለሠላም አስከባሪ ኃይል ወታደራዊ አልባሳት እና የጥይት ግዥ 100 በመቶ በመፈጸም አገልገሎቱን ተደራሽ ማድረግ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ለፀጥታ ሥራዎች የህዝቡን ተሳትፎ እና ድጋፍ ከማጐልበት አኳያ በህብረተሰብ አቀፍ የወንጀል መከላከል የህዝብ ተሳትፎን ብር 82.5 ሚሊየን ማድረስ፣ በክልሉ ከሚገኘው የሚሊሻ አደረጃጀት 719 የሻለቃ 3,073 የሻምበል፣ 7,999 የመቶና 18,298 የጓድ አደረጃጀቶችን ክፍተት በመለየት የማጠናከር ሥራ መሥራት፣ 413,246 የጥበቃ ቡድኖችን አደረጃጀት ክፍተት በመለየት እና 100 በመቶ በማጠናከር በሠላም ማስፈን ሥራው ተሳታፊ ማድረግ እንዲሁም በሚሊሻ ምልመላና መረጣ ላይ 2,301,208 ህዝብ እንዲሳተፍ በማድረግ በሥነምግባር የተሻሉ እጩ የሚሊሻ አባላትን መመልመል የሚሉትን ለማሳካት ከፍተኛ ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የፀጥታ ስጋት የሆኑ ፀረ-ሠላም ኃይሎች ጉዳት ሳያደርሱ በቅድመ መረጃ ላይ ተመሥርቶ 100 በመቶ መከላከል እና መቆጣጠር በሚመለከት የአመፅ እና የሽብር ኃይሎች እንቅስቃሴን 100 በመቶ መከታተልና መቆጣጠር፣ ማንነትን እና ኃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ግጭት ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞችን በመለየት 100 በመቶ መከታተል እና መቆጣጠር፣ የተደራጀ ህገወጥ መሣሪያ ዝውውርን 100 በመቶ መከላከል እና መቆጣጠር፣ በትምህርት ተቋማት የሚታዩ የአመፅ እና የሁከት እንቅስቃሴዎችን 100 በመቶ መከታተልና መቆጣጠር፣ በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተሳታፊ ኃይሎችን በመለየት 100 በመቶ መከላከል እና መቆጣጠር፣ በማህበራዊ ድህረ ገጽ የሚሠራጩ አሉባልታዎችን እየተከታተሉ የዕርምት ርምጃ 100 በመቶ እንዲወሰድ ማድረግ እንዲሁም የተደራጁ የዘረፋ እና ቅሚያ ቡድኖችን በመለየት 100 በመቶ መከታተል እና መቆጣጠር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የሠላም ባህል በመገንባት በክልሉ ውስጥ እና በአጎራባች ክልሎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን የግጭት ክስተት የመፍታት አቅምን አሁን ካለበት 96.6 በመቶ ወደ100 በመቶ ለማሳደግ የሚሠራ ሲሆን 4,133 የሠላም ምክር ቤቶችን በማጠናከር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መከታተል፣ በክልሉ ባሉ 9,666 ትምህርት ቤቶች የሠላም ክበባት አደረጃጀቶችን በማጠናከር ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መከታተል፣ በክልሉ በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የሠላም ፎረሞችን ማጠናከርና መከታታል፣ በክልሉ ውስጥ እና ከአጎራባች ክልሎች ሊከሰቱ የሚችሉ የግጭት አመላካቾችን ለመከላከል የቅድመ የ24 ሠዓት የመረጃ ልውውጥን ማሻሻል እንዲሁም ከሱዳን ጋር ለ20 ጊዜ የአመራር ለአመራር ግንኙነት በማድረግ የሁለቱን ህዝቦች ግንኙነት ማጠናከርና ችግሮችን መፍታት በትኩረት ይሠራል ፡፡

በክልሉ በኃይማኖቶች መካከል በሠላም አብሮ የመኖር ዕሴትን በመገንባት የኃይማኖት ጽንፈኝነትን 95 በመቶ መቀነስ፣ የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎትን ተደራሽ በማድረግ የወንጀል ክስተቶችን መቀነስ፣ የቀበሌ ኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሽፋንን አሁን ካለበት 67.99 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማድረስ፣ በክልሉ በሁሉም ቀበሌዎች የህዝብ ቁጥርን ታሳቢ በማድረግ በቀበሌ ደረጃ ከ3-5 የፖሊስ ኦፊሰር መመደብ እና 100 በመቶ ወደ ሥራ ማስገባት፣ የኮሚኒዩቲ ፖሊሲንግ አፈፃፀም የጥራት ደረጃ አሁን ካለበት ከፍተኛ 38.6 በመቶ፣ መካከለኛ 60.1 በመቶ፣ ዝቅተኛ 1.3 በመቶ ወደ ከፍተኛ 90 በመቶ እና መካከለኛ 10 በመቶ ማድረስ፣ ለህብረተሰብ አቀፍ ወንጀል የመከላከል ሥራ የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን 100 በመቶ ማጠናከር፣ በድግግሞሽ ለ199 ሚሊየን በላይ ህዝብ በኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ፅንሰ ሀሳብ ዙሪያ ግንዛቤውን ማሳደግ፣ ለድረሱልኝ ጥሪዎች በገጠር በ5 ሠዓት እና በከተማ በ15 ደቂቃ

ውስጥ ምላሽ መስጠት፣ አጠቃላይ ወንጀልን በ1,000 ሰዎች መካከል በገጠር ከ1.6 ወደ 1፣ በከተማ ከ5.45 ወደ 3.0 ዝቅ ማድረግ፣ ዋና ዋና ወንጀልን በገጠር ከ0.6 ወደ 0.5፣ በከተማ ከ1.95 ወደ 1.0 መቀነስ፣ በክልላችን የሚፈፀሙ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን፣ የመሠረተ ልማት አውታሮች ስርቆትና ዘረፋን፣ የመኪና አስቁሞ ዘረፋን 100 በመቶ ማስቆም፣ በወንጀል ተጠርጥረው ከህግ የራቁ ሰዎችን የመቆጣጠር አቅምን 100 በመቶ ማሳደግ፣ የአደገኛ ዕፅ ዝውውርን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር፣ ህገወጥ ኮንትሮባንድን እና የጦር መሣሪያ ዝውውርን 90 በመቶ መቆጣጠር የሚሉት በዕቅድ ዘመኑ ይከናወናሉ፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ምርመራ አቅም እና ጥራትን በማሳደግ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ማሻሻል፣ የግል አቤቱታ እና የመንግስት ክስ የማጣራት አቅምን ከ85 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የመንግስት ክስ የማጣራት አቅምን ከ80 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የወንጀል ምርመራ አቅም ከ85 በመቶ ወደ 95 በመቶ እና የሙስና ወንጀል ምርመራ አቅም ከ75 በመቶ ወደ 99 በመቶ ማድረስ፣ የተከሳሽ አቀራረብን ከ95.66 በመቶ ወደ 97 በመቶ የምስክር አቀራረብን ከ96.46 ወደ 97 በመቶ ማሳደግ፣ የፎረንሲክ የወንጀል ምርመራ አገልግሎትን ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ የትራፊክ አደጋ የምርመራ አቅም አሁን ካለበት 77.61 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ እንዲሁም የእጅ ከፍንጅ /RTD/ ወንጀል ምርመራ አቅምን ከ87.31 በመቶ ወደ 100 በመቶ ማሳደግ የሚሉት በተገቢው ሁኔታ የሚተገበሩ ይሆናል፡፡

የእግረኞችን የመንገድ አጠቃቀም በማሻሻል እና የደንብ መተላለፍን በመቆጣጠር የመንገድ ትራፊክ አደጋዎችን መቀነስ፣ በድግግሞሽ ለ82.5 ሚሊየን ማህበረሰብ፣ ለተማሪዎች እና ለአሽከርካሪዎች የትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፣ በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ የትራፊክ ደህንነት ክበባትን 100 በመቶ ማጠናከር እና መደገፍ፣ የተማሪዎችን የእግረኛ መንገድ አጠቃቀም በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት በገጠር 72 በመቶ እና በከተማ 78 በመቶ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በከተማና በገጠር ወደ 95 በመቶ ማሳደግ፣ በገጠርና በከተማ የህብረተሰቡን የግራ መስመር አጠቃቀም ከ75 በመቶ ወደ 95 በመቶ ማድረስ፣ የሞት አደጋ የሚያስከትለውን የትራፊክ አደጋ አሁን ካለበት በ40 በመቶ መቀነስ፣ በትራፊክ አደጋ የሚደርስን የሰው ሞት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 1,080 በ50 በመቶ መቀነስ፣ የደንብ ተላላፊዎችን ተከታትሎ የማስቀጣት አቅምን 100 በመቶ ማድረስ፣ ደንብ ተላልፈው ወይም አደጋ አድርሰው ያመለጡ አሽከርካሪዎችን እና ተሽከርካሪዎችን ተከታትሎ የመያዝ አቅምን ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ በ2012 በጀት ዓመት የነበረውን 2,295 አጠቃላይ የትራፊክ አደጋ ብዛት በ92 በመቶ መቀነስ፣ በ2012 በጀት ዓመት የነበረውን 1,646 በቁጥጥር ማነስ የደረሰውን የትራፊክ አደጋ በ50 በመቶ መቀነስ፣ በ2012 በጀት ዓመት የነበረውን በግንዛቤ እጥረት የደረሰውን 25 በመቶ አደጋ በ75 በመቶ መቀነስ የሚሉት ይከናወናሉ፡፡

የመንግስት እና የግል ጦር መሣሪያ አስተዳደር ሥርዓቱን በማጠናከር ለሠላም እና ፀጥታ ማስከበር የሚሰጠውን አገልግሎት ከማሳደግ አኳያ 100 በመቶ የመንግስትና የግል ጦር መሣሪያዎች የፈቃድ ዕድሳት ማድረግ፣ 100 በመቶ የመንግስት እና የግል ጦር መሣሪያዎችን በመለየት የአካል ቆጠራ ማድረግ፣ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የመንግስት የጦር መሳያዎች በመለየት 100 በመቶ ጥገና ማድረግ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ 164 የጦር መሣሪያ መጋዝኖችን አዲት ማድረግ፣ አገልግሎት የማይሰጡ የጦር መሣሪያዎችንና ተተኳሾችን በመለየት 100 በመቶ እንዲወገዱ ማድረግ፣ የመንግስትና የግል ትጥቅ የሸጡ እና ያጠፉ አካላት ሁሉም በህግ እንዲጠየቁ ማድረግ፣ በክልሉ ያለውን ህጋዊ የጦር መሣሪያ በሙሉ በዓይነት እና በንምራ ቁጥር ለይቶ 100 በመቶ በዳታ ቤዝ (በሶፍት እና ሀርድ ኮፒ) እንዲያዝ ማድረግ እንዲሁም ጥናትን መሠረት በማድረግ 100 በመቶ ህገወጥ ትጥቅን ማስወረድ የሚሉት ሥራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የታራሚዎችን የሰብዓዊ መብት በማክበር በማረሚያ ቤት ቆይታቸው የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ በማድረግ የዕውቀት እና የክህሎት ባለቤት ለማድረግ፣ ለ56,121 ታራሚዎች በተለያዩ የግብርና ሙያዎች በተግባር የተደገፈ ሥልጠና ለመስጠት፣ ለ41,166 የህግ ታራሚዎች በባህላዊ እና በዘመናዊ የዕደ ጥበባት ሙያዎች እንዲሁም ለ37,905 የህግ ታራሚዎች በልዩ ልዩ ሙያዎች ሥልጠና ለመስጠት፣ 34,897 የህግ ታራሚዎች በመደበኛ እና ለ12,285 ደግሞ መደበኛ ባልሆነ ትምህርት እንዲከታተሉ ለማድረግ፣ ለ45,537 ታራሚዎች የግልና ለ95,450

ታራሚዎች የቡድን  የምክር አገልግሎት ለመስጠት፣ ለ93,992 የህግ ታራሚዎች የጋይዳንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እና ለ8,121 ደጋጋሚ ታራሚዎች የግል ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲሁም ልዩ ልዩ የምክር አገልግሎት ከተሰጣቸው ታራሚዎች መካከል 155,012 ታራሚዎች የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ለማድረግ ታቅዷል፡፡

## የማስፈጸሚያ ሥልቶች

የአሥር ዓመቱን ዕቅድ ለመተግበር የሚከተሉት የማስፈጸሚያ ሥልቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡እነሱም የጦር መሣሪያዎች አያያዝና አተቃቀም ሥርዓት መተግበርና ህገውጥነትን በመከላከል የህዝቡን ሠላምና ደህንነት በማረጋገጥ እንዲሁም የወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥርዓት በመተግበር የተደራጁ ወንጀሎችና ሽብርተኝነትን መከላከል፣ በአጎራባች ክልሎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት በመተማመንና በአብሮነት እንዲያድግ ማድረግ፣ ጠንካራ መንግስታዊ እና ሕዝባዊ አደረጃጀቶችን መፍጠርና ማብቃት፣ አስተማማኝ የሆነ የክልሉን ሠላም ማረጋገጥ፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን የኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊትን በትግል የመምራት አቅምን የሚያጠናክር የአሠራር ሥርዓት በመፍጠር ተፈፃሚነቱን በህዝቡ ተሳትፎ ማረጋገጥ፣ የአመራሩንና የአባላትን የአመለካከትና የሥነምግባር ችግሮችን በመፍታት በየደረጃው ተጠያቂነትን እና ግልጸኝነትን የሚያሰፍን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ መመሪያና ደንብ ማሻሻልና ተግባራዊነቱን መከታታል፣ እንዲሁም በየደረጃው በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የአመራር እና የባለሙያ ምደባ ማካሄድና ውጤቱን መገምገም ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህም ባሻገር ዕቅዱ ተከታታይነት ባለው የሕዝብ ግንኙነት እና የህዝብ ንቅናቄ ታጅቦ እንዲፈፀም ማድረግና ውጤቱንም የጋራ ማደረግ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በአጋርነትና በትብብር የመፈፀም የአሠራር ባህልን ማዳበር፣ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚከሰቱ ግጭቶችን በመግባባትና በመተባበር መንገድ መፍታት፣ መረጃ ሀብት መሆኑን በማሰብ የመረጃ ሥርዓቶችን የሚያዘምኑ የአሠራር ሥልቶችን መከተል እና ውጤታማነቱን የመገምገም አሠራር መፍጠር፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመር እና ማስፋት፣ በሁሉም ዘርፍ ሠላምን ለማስፈን እና ህገወጥ ድርጊቶችን ለመቆጣጠር የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ፣ ሠላምን በትምህርት ቤቶች፣ በሚዲያ፣ በጥበብ ወዘተ እንዲዘከር እና የትውልድን የሥነልቦና ውቅር እንዲገነባ ማድረግ፣ የዜጎች እና የወጣቶችን በጎ ፈቃደኝነት እና የመስጠት ዜግነታዊ ኃላፊነት የህይዎት ዘመን ባህል እንዲሆን ማድረግ እንዲሁም የህግ ማስከበርና የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ሥራዎች የዜጋውን መብት ያከበረና ያስከበረ እንዲሆን ማድረግ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 12.5.4 ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና

### የትኩረት አቅጣጫዎች

**የተቋም አቅም ግንባታ፡-** የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስናን መከላከል ተልዕኮ ለመወጣት የአሠራር ሥርዓት፣ ስትራቴጂ እና አደረጃጀት በተከታታይ ማሻሻልና በብቃት ማረጋገጥ፣

**የሥነምግባር ግንባታ፡-** በሥነምግባር የታነጹ፣ ሙስናን የሚጠየፉና በጽናት የሚታገሉ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና ዜጎች እንዲበራከቱ በትብብር መሥራት፣

**የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት**፡- በመንግሥት ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራር በዘላቂነት እንዲቀንስ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣

**የሙስና መረጃ አስተዳደር እና አገልግሎት፡-** የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮች መረጃ እና ማስረጃ በማደራጀት፣ የሕዝብ እና የመንግሥት ሀብት ከብክነት ለማዳን ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት መሥራት የሚሉት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

### ዓላማዎችና ግቦች

የትውልድ ሥነምግባር እና የሞራል ዕሴቶችን በብቃት በመግንባት የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፣ ተቋማዊ አቅምና ብቃትን በማሳደግ የተገልጋዮችን እርካታና አመኔታ ማሣደግ፣ የተቋም የሥነምግባር ሞራል ዕሴቶች ግንባታ አቅም እና ብቃትን ማሳደግ፣ የተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ስጋትን መቀነስ እንዲሁም የሙስና መረጃ አስተዳደር እና አገልግሎትን ማሳደግ የሚሉት ናቸው።

### የማስፈፀሚያ ሥልቶች

የሥልጠና ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፣ የሥልጠና ማቴሪያል በትኩረት መስክ ማዘጋጀት፣የሥልጠና በጀት እና የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት፣ ሥልጠናው ያመጣውን ለውጥ መገምገም፣ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ በተለይም የአሠራር ጥናት በተካሄደባቸው ተቋማት ላይ የጋራ ውይይት ማድረግ፣ ወደ ትግበራ በማስገባት ጥናቱ ያመጣውን ውጤት መገምገም፣ ማህበራዊ ሚዲያን እና መገናኛ ብዙሀንን በአግባቡ መጠቀም፣ የፀረ-ሙስና ትግሉን ተደራሽ ለማድረግ ካሉት ቅርንጫፎች በተጨማሪ ደብረ ማርቆስ እና ወልደያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች መፈቀዳቸውን ተከትሎ በጀት በማስመደብ ወደ ሥራ በማስገባት በህብረተሰቡ የሚነሱ ተደጋጋሚ ቅሬታዎችን በመቅረፍ የፀረ-ሙስና ትግሉን በተደራጀ ሁኔታ መምራት የሚሉት ናቸው።

## 12.5.5 የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች

### የትኩረት አቅጣጫዎች

በአገሪቱ የልማት፣ የሠላምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ በንቃትና በባለቤትነት መንፈስ መሳተፍ የሚችል እና በዋና ዋና ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ የክልሉን ህዝብ ማግባባት የሚያስችል አቅም ያለው የኮሚዩኒኬሽን ሠራዊት በሚፈለገው ደረጃ መገንባት፣ ክልላዊም ሆነ አገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚሰነዘሩም ሆኑ የሚከሰቱ አፍራሽ አዝማሚያዎች ዕቅድ ላይ በመመስረት በፈጣን ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት ለመመከት የሚያስችል አደረጃጀት እና አሠራር መፍጠር።

የተደራጀ የመንግስት ኮሚየኒኬሽን፣ ኢንፎርሜሽን እና የሚዲያ የልማት ሠራዊት በመገንባት እና የተጠናከረ የቃል አቀባይነት ሚናን በመወጣት ዘርፉ በ10 ዓመቱ የዕቅድ ዘመን የተነደፉ ፕሮግራሞች እና የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ የለውጥ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ሲሆን በዚህ ውስጥ ዋነኛ የትኩረት አጀንዳዎች መላ የክልሉ ህብረተሰብ በፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች፣ በህግ ማዕቀፎች እንዲሁም በለውጥ ፕሮግራሞች ግልፅነት እንዲኖረው እና የጠራ አመለካከት ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ ነው።

በሌላ በኩል የክልሉ ታሪክ፣ ባህል እና ዕሴቶች በማሳወቅ ለህዳሴ ጉዞ መሠረት ሆነው እንዲያገለግሉ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር፣ በገፅታ ግንበታ እና በተነደፉ የልማት፣ የሠላም፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ግንባታ ሥርዓት ውስጥ አጠቃላይ መግባባት ተፈጥሮ እንቅስቃሴ እንዲደረግ ማድረግ፣ በየደረጃው የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያነሷቸውን መሠረታዊ የህዝብ ጥያቄዎች በመለየት ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ ማስቻል የሚሉ የዕቅዱ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው።

### ዓላማዎችና ግቦች

የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዋነኛ ዓላማ ዘላቂነት ባለው የኮሚዩኒኬሽን ሥራ በዋና ዋና አገራዊ እና ክልላዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት ፈጥሮ በሠላም፣ በልማት እና በመልካም አስተዳዳር ፕሮግራሞች ውስጥ የራሱ ሚና የሚጫወት በአገሩና በብሄራዊ ጥቅሞቹ ላይ በምክንያታዊነት ብያኔ የሚሰጥ እና በመረጃ የረካ ማህበረሰብ መፍጠር የሚችል አቅም መገንባት ነው። ይህንን ዓላማ ለማስፈጸም የተለያዩ ግቦች ተቀምጠዋል። እነዚህም

የተገልጋዮችን የመረጃ ተጠቃሚነት አመኔታ ማጎልበት፣ በመረጃ አቅርቦት የህብረተሰቡን እርካታ በአማካይ ወደ 80 በመቶ ማድረስ፡፡

በዋና ዋና ክልላዊ እና አገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት በመፍጠር የክልሉን ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ለማጎልበት በወሳኝ ጉዳዮች ላይ በየወሩ አንድ ጊዜ የመንግስትን አቋም የሚያንጸባርቁ መግለጫዎችን በሚዲያዎች ማሠራጨት፣ የህብረተሰቡን ግንዘቤ ለማሳደግ በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ በወሳኝ እና ወቅታዊ ክልላዊ ጉዳች ላይ የፓናል ውይይት እና ፕሬስ ኮንፍረንስ ማካሄድ፣ በክልሉ ሁለንተናዊ የገጽታ ግንባታና የጋራ መግባባቶች ዙሪያ የመረጃ አቅርቦት ጥራትን ማሻሻል፣ ህብረተሰቡን ለልማት የሚያነሳሱ የሚዲያ ውጤቶችን ተደራሽነት ለማሳደግ በተመረጡ ልዩ ልዩ ይዘቶች ላይ ያተኮሩ ዘጋቢ ፊልሞችን በየሩብ ዓመቱ እያዘጋጁ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የዚህ መሪ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች ናቸው፡፡

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

መሪ ዕቅዱ የታለመለትን ዓላማ እና ግብ ይመታ ዘንድ የሚፈፀሙትን ተግባራት በተያዘላቸው ጊዜ፣ የጥራት ደረጃ እና መጠን ለማከናወን ከዚህ በታች ወሳኝና መሠረታዊ የሆኑ የማስፈጸሚያ ሥልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ ማስፈጸሚያ ሥልቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**የለውጥ እና የማስፈፀም አቅም ግንባታን ማሳደግ፡-** ከክልል እስከ ታችኛው የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን መዋቅር ድረስ ተናባቢ አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት እና ምቹ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የዘርፉን ዘለቄታዊ ልማት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው፡፡ በመዋቅሩ ውስጥ የሠራተኛውን የአቅም ክፍተት በአጫጭር እና በረዥም ጊዜ የሥልጠና መርሃ ግብሮች በማሟላት ብቁ ፈፃሚ ኃይል ማፍራት የልማት ሰራዊት ግንባታ ሥራዎች የተግባራት ሁሉ ማጠንጠኛ ሥልት ተደርጐ ተወስዷል፡፡

**ጠንካራ የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት**፡- የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ከዝግጅት እስከ ማጠቃለያ ምዕራፍ ባሉት ሂደቶች ከላይ እስከ ታች ያለው ፈፃሚ ኃይል የሚንቀሳቀስበት አሠራር ሊኖር ይገባል፡፡ ስለሆነም በዘርፉ ያለውን የሰው ኃይል አደረጃጀት በመፍጠር በክህሎት፣ በአመለካከት፣ በአሠራር እና አደረጃጀት የተሟላ በማድረግ በዕቅድ የተያዙ ግቦች ውጤታማ መሆናቸውን በየሩብ ዓመቱ የክትትል እና ግምገማ ቡድኖች ተደራጅተው ከክልል ወደ ዞን፣ የሜትሮ ፖሊታን ከተሞች እና የብሄረሰብ አስተዳደር ዞኖች እንዲሁም ወደ ወረዳዎች በመውረድ አፈፃፀሙን ይከታተላል ይገመግማል፡፡

**ቅንጅታዊ አሠራርን መከተል/ተግባራትን አቀናጅቶ መፈፀም**፡- ይህ መሪ ዕቅድ ባለድርሻ አካላትን ቀድሞ በመለየት፣ ወጥ አሠራር በመዘርጋት፣ በተቀመጠው የአሠራር ሥርዓት መሠረት ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር እና በየጊዜው እያደገ በሚሄድ የቅንጅት አሠራር ግቦቹን የማሳካት ሥልት ይከተላል፡፡

**ውጤታማና ቀልጣፋ የሀብት አጠቃቀም፡-** ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም ሥርዓት መከተል የዕቅዱ ስኬት ላይ የሚኖረው ፋይዳ ግምት ውስጥ ገብቶ ተግባራት ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲመሩ ይደረጋል፡፡

## 12.6. የልማት ፋይናንስ

### 12.6.1 ገቢዎች

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

**ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን ማሳደግ፡-** ታክስ ከፋዩን በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማር፣ በመደገፍ እና ዕውቅና በመስጠት አብዛኛው ግብር ከፋይ በፈቃደኝነት የታክስ ግዴታውን እንዲወጣ ማስቻል አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የታክስ ህግ ተገዢነት ባህሪ ለውጥ ማምጣት ባልቻሉ አካላት ላይ ተመጣጣኝ የህግ ማስከበር ተግባር ተፈፃሚ የማድረግ ሥራ ትኩረት ይሰጠዋል።

**ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓትን መገንባት፡-** ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓት የመገንባት አቅጣጫ ታሳቢ የሚያደርገው አጠቃላይ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱን ዓለም በደረሰበት የመረጃ ቴክኖሎጂ ሥርዓት እንዲደገፍ ማድረግን ነው። ይህ የዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓት ለአገልግሎት ተቀባዩ ግልጽ፣ ቀላል እና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት፣ የህግ ተገዥነትና አስተዳደራዊ ወጪ በመቀነስ እና የተገልጋዩን ዕርካታ በላቀ ደረጃ በማረጋገጥ የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት ነው።

**ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ፡-** የአገራችንን የታክስ አስተዳደር ሥርዓት በኢመደበኛ ኢኮኖሚ፣ በህገወጥ ንግድ፣ በታክስ ማጭበርበር እና በኮንትሮባንድ ምክንያት የመወዳደሪያ ሜዳውን እኩል ማድረግ አልተቻለም። ከዚህ አኳያ ወደ ታክስ መረቡ ያልገቡትን እንዲታቀፉ በማድረግ እና የታክስ ህጎችን በሁሉም ታክስ ከፋዮች በእኩል ደረጃ ተፈፃሚ በማድረግ የታክስ ፍትሐዊነትን የማረጋገጥ ጉዳይ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

**ስትራቴጂክ አጋርነትን ማጠናከር፡-** የታክስ አስተዳደር ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከአጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ለአንድ ዓላማ በጋራ መንቀሳቀስን ይጠይቃል። በመሆኑም ይህ አቅጣጫ የመረጃ ልውውጥን፣ ህገወጥነትን የመከላከል አሠራር መዘርጋትን ታሳቢ ያደረገ ነው። በዚህ መሠረት አጋር አካላትን መለየት፣ ግንኙነት እና ሥምምነት መፍጠር እና በሥምምነቱ መሠረት ለመፈፀም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችንና ማነቆዎችን በጋራ ለይቶ በመፍታት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል።

**የዳበረ የሥራ ባህል ማምጣት፡-** የታክስ ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶችን የተላበሰ እና ሁለንተናዊ አቅሙን በመገንባት የዳበረ የሥራ ባህል ያለው የሰው ኃይል ማፍራትን ታሳቢ ያደረገ ነው። ይህ አቅጣጫ የሰው ኃይል ሥራ አመራር ልማት ስትራቴጂ ከመቅረፅ ጀምሮ፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መሳብና ማቆየት፣ የምዘና፣ የማትጊያ እና የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፣ ምቹ የሥራ ከባቢ መፍጠር፣ ታማኝና ለሥራ ተነሳሽ የሆነ አመራር እና ፈፃሚ ማፍራትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶት ይሠራል።

#### ዓላማዎችና ግቦች

የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀምን ማሻሻል፣ የመረጃ አስተዳደር አፈፃፀም ማሻሻል፣ የአሠራር ሥርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል፣ የአጋር አካላት አጋርነትና ትብብርን ማሻሻል፣ የታክስ ማጭበርበርን መከላከል አፈፃፀምን ማሻሻል፣ የታክስ ህግ ተገዥነት አፈፃፀምን ማሻሻል እንዲሁም የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል የሚሉት ይገኙበታል።

### 12.6.2 ገንዘብ

#### የትኩረት አቅጣጫዎች

የመፈጸምና የማስፈፀም አቅምን ማጎልበት፣ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደርን ማጠናከር፣ የውጭ ሀብት ግኝትና አስተዳደርን ማሳደግ፣ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር፣ ከፍያና የሂሳብ አያያዝን ማዘመን፣የመንግስት ግዥ እና ንብረት

አስተዳደርን ማጎልበት፣ የውስጥ ኦዲት ተደራሽነትና ግኝት አመላለስን ማጠናከርና ድጋፍና ክትትልን ማጎልበት የሚሉት ናቸው።

## ዓላማዎችና ግቦች

የዘርፉ ዓላማዎች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ግንባታን ማሳደግ፣ የልማት ሀብት አቅርቦትን ማሳደግ፣ የሀብት አመዳደብ ውጤታማነትን ማሻሻል እንዲሁም የመንግስት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደርን ማሻሻል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በግብ ደረጃም የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ያደረገ የአደረጃጀት ማሻሻያ ማድረግ፣የፋይናንስ፣ የግዥና ንብረት የህግ ማዕቀፎችን ማሻሻል፣ የአመራሩንና የባለሙያዎችን አቅም መገንባት፣ የክልሉን መንግስት ገቢ ማሳደግ፣ የመንግስት፣ የበየነ መንግስታት እና የሲቪክ ማህበራት ግንኙነትን ማጠናከር፣ የቻናል አንድ፣ የቻናል 2፣ የቻናል 3 እና ሌሎች የውጭ ሀብት ግኝቶችን ውጤታማ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል፣ የበጀት ማከፋፈያ ቀመርን ማሻሻል፣ የበየነ መንግስታትና ሲቪክ ማህበራትን ሀብት አጠቃቀም የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጠናከር፣ የበጀት አስተዳደርን ወደ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል፣ የክፍያ የጥሬ ገንዘብና የሂሳብ አያያዝን ወደ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓትን ማሻሻል እንዲሁም የውስጥ ኦዲት አሠራርን ወደ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ማሻሻል የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

## የማስፈፀሚያ ሥልቶች

ቁጠባን መሠረት ያደረገ የሀብት አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ለበለጠ ልማት መነሳሳት፣ ከአለፉት ዓመታት አፈፃፀም ግምገማ ትምህርት መቅሰም፣ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ተቋማትን በአግባቡ የመጠቀም አሠራርን መከተል፣ በተግባር እንቅስቃሴ የሚገኙ መልካም ልምዶችን እየቀመሩ በሌሎች አካባቢዎች ማስፋፋት እንዲሁም ከክልል እስከ ወረዳ ያለው የሴክተሩ አመራር እና ባለሙያ ሥራውን በተደራጀ አግባብ በባለቤትነት እንዲመራ ማድረግ የሚሉት ናቸው።

# 13. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

በቀጣይ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ አፈጻጸም ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በመፍታት ዕቅዱ ውጤታማ እንዲሆን ከማድረግ እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር የተጠናከረ የክትትልና ግምገማ ሥራ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን አሠራር መዘርጋትና የዕቅዱ አካል ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ የመሪ ዕቅዱ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## የክትትል ሥርዓት

በ10 ዓመት መሪ ዕቅዱ የተቀመጡ የማክሮ ኢኮኖሚ አመልካቾችና እያንዳንዱ ዘርፍ እንዲያሳካቸው የሚጠበቁ ቁልፍ የልማት አመልካቾችን /Key Performance Indicators/ የያዘ ሠነድ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በሚመለከታቸው የክልል መሥሪያ ቤቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ምሁራን እና ሌሎች አካላት ዳብሮ ከጸደቀ በኋላ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል። በመሆኑም እነዚህን ቁልፍ አመልካቾች መሠረት ባደረገ መልኩ ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን፣ ከክልል መሥሪያ ቤቶች፣ ወዘተ እንዲሁም በፕላንና ልማት ቢሮ በሚሰበሰቡ መረጃዎችና በሚካሄዱ ጥናቶች አማካይነት የመጀመሪያ ደረጃ /Primary Data/ እና ሁለተኛ ደረጃ /Secondary Data/ መረጃ እየተሰበሰበ እና እየተተነተነ ለክትትል ሥራ ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል።

በፕላንና ልማት ቢሮ የክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት የክትትልና ግምገማ ሥራውን በባለቤትነት የሚመራው ሲሆን የክልሉን አኪኖሚ አካውንት በሚመለከት የአኪኖሚ አካውንት ዳይሬክቶሬት የሚከታተለው ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ከፌደራል ጋር ተናባቢ የሆነና ተጠያቂነት ያለበት የክትትልና ግምገማ መመሪያ የተዘጋጀ ቢሆንም እስከ አሁን ጸድቆ ወደ ተግባር ያልተገባ በመሆኑ በቀጣይ ጊዜ በክልሉ የበላይ አካላት ጸድቆ ወደ ተግባር ይገባል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተጨማሪም በፕላንና ልማት ቢሮ ሥር ያለው የመልክዓ ምድራዊና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የሚሰበሰብ፣ የሚያደራጅና ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ ዳይሬክቶሬትም የመረጃ አያያዝ ሥርዓት /Data Base/ እንዲኖረውና በመረጃ አያያዝ ረገድ በክልሉ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ሥራ ይሠራል፡፡

## የግምገማ ሥርዓት

ውጤቶች ማለትም የመጀመሪያ ደረጃ ውጤት /Output/፣ የግብ ስኬት /Outcome/ እና ፋይዳ /Impact/ እንዴት እንደሚተሳሰሩና እንደሚመጋገቡ የሚያሳይ ፖሊሲ ማትሪክስ ይዘጋጃል፡፡ ይህም እስከ አሁን ከነበረው በሂደት /process/ ላይ የማተኮር ልምድ በመውጣት ከፍ ወደአሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የግምገማ ሥራው ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም የአጋማሽ ዘመን /Mid-term/ እና የማጠናቀቂያ /Terminal/ ግምገማ በተጠናከረና አሳታፊ በሆነ መልኩ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ምን ያህል በታቀደው መሠረት ውጤት መጣ፣ ህዝቡ በምን ደረጃ ተጠቃሚ ሆነ እና የመሰሰሉትን ጉዳዮች ሊመልስ በሚያስችል አግባብ ፕላንና ልማት ቢሮ ወይም በኮንሰልታንት የተለያዩ የግምገማ ጥናቶች ያካሂዳል፡፡ በአጠቃላይ ዕቅዱ እንዲሳካ ከማድረግና ተጠያቂነትን ከማስፈን አንፃር በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት፣ ፕላንና ልማት ቢሮ፣ የህዝብ ወኪል የሆኑት ምክር ቤቶች እና ሌሎች አካላት ሚናቸው ጉልህ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡